


t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ

በወንጀል ምርመራ ድርሰቶቿ የዘመኑ ቁንጮ የሆነችው እንግሊዛዊቷ አጋታ ክርስቲ ከ80 መጻሕፍት በላይ ለአንባቢዎች አበርክታለች ። ሥራዎቿም እጅግ ተወዳጅ በመሆናቸው ከ400,000,000 የሚበልጡ ቅጂዎች ተሸጠዋል። የተለያዩ መጻሕፍቶቿ ከያዟቸው ረቂቅ ፖሊሳዊ ትምህርቶችና ምርምሮች ጐን ከፍተኛ ሥነ ልቦናዊ ትንታኔዎችንም የሚያስተላልፉ ናቸው ።

እኔም ከሃያ ጊዜያት በላይ በተደጋጋሚ ታትሞ ዓለም አቀፍ አድናቆትን ያተረፈውንና ታላቅ ፊልም ሆኖ የተቀረጸውን “ ዴዝ ኦን ዘ ናይል ” ( Death on The Nile ) ወደ አማርኛ ሲመለስ “ ሞት በዓባይ ወንዝ ላይ ” የሚለውን የክርስቲ መጽሐፍ “ ጃክሊን ” በሚል ስያሜ ተርጉሜ በቀላሉ ለመከታተል በሚቻልበት መንገድ አቀርቤአለሁ ። ምንም እንኳን ሁለቱም ርእሶች የመጽሐፉን ይዘት በትክክል የሚያንጸባርቁ ቢሆንም “ ጃክሊን ” ለሚለው ስያሜ ምርጫ የሰጠሁበትን ምክንያት አንባቢያን በጽሑፉ መደምደሚያ ላይ እንደሚረዱት አልጠራጠርም ።

“ ጃክሊን ” ከተወሳሰበና ከረቀቀ የወንጀል ታሪክ ጋር በማዳበል ሥነ ልቦናዊ ምርምሮችንም ይዛለች ። የመጀመሪያ ፍቅርን ፣ የሚያገረሽ ፍቅርን ፣ ቅናትና ቂም በቀልን ፣ ጭፍን ጥላቻንና መሠሪነትን ፤ የመሳሰሉትን በዓይት ነጥቦች በጉጉት በሚነበቡት ልብ ሰቃይ ምእራፎቿ



t.me/OLDBOOKSPDF

እካታለች ። ገንዘብ ሲኑር አስፈላጊ ቢሆንም ግለሰቦች ገደብ የሌሽ በሆነ ፍቅረ ንዋይ ተነድፈው ሲራሯሯጡም ሆነ ለሌሎች ሕይወት ዝቀትና ጥፋት ምክንያት እንደሚሆኑም “ ጃኪሊን ” በግልጽ ታሣያለች ።

ዓቢይ ደምሴ

አዲስ አበባ

1980 ዓ.ም.



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

ደብዛዛ ያለ ብርሃን የሚበረብሩ የአስዋን ከተማ "ካታራክት" ሆቴል በረንዳ ቀስ በቀስ ባዶ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው ። የዓባይን ወንዝ ዳርቻ በእጥብቀልቀው ጠርቃማ አሸዋ ውስጥ እልፍ አእላፍ ጉብ ባሉት ጥቁር ድንጋዮች ላይ የጨረቃዋ ብርሃን ሲያርፍባቸው ከውሃው ውስጥ የወጡ የተለያዩ ግዙፍ አውሬዎች አስመስሎአቸዋል ። በንብረው ወበቅና ሙቀት ምክንያት በመጠኑም ቢሆን ቀዝቀዝ ያለ አየር እየነፈሰ ስለነበረ ከዚህ የተፈጥሮ ጸጋ ላለመለየት የፈለገ ይመስል ፣ በበረንዳው በስተምግ በኩል ካለ መዝናኛ ወንበር ላይ ብቻውን የተቀመጠ ሰው ይታያል ። ልብ ብሎ ላየው ግን ዓይኖቹ ከፊት ለፊቱ በተንጣለለው የዓባይ ወንዝ ውሀ ላይ ተተክለው መንፈሱ በሆነ ሐሳብ ተጠምዶ ፈዞ የቀረ ሰው እንጂ ፣ በዙሪያው ለነበረው ሁኔታ ደንታ ያለው አይመስልም ነበር ።

ድንገትም "ሙሴ ፒዮሮ !" የሚለውን የጥሪ ድምጽ ሲሰማ ከእንቅልፉ እንደ ቀሰቀሱት ሰው ብርግግ ብሎ ተነሣ ። የዚያ የተራቀቀ ቃና ፣ ጸጋን የተላበሰና ማራኪ ድምጽ ባለቤት ልትሆን የምትችል አንዲት ልጅ ብቻ ነበረች ። ያቺ ልጅ በሺህ ላይ ሺህ የሆኑ ወጣቶች ብርሃን በሚያንጸባርቁት ዓይኖቿ ተጠምደው የሚያለቅሱላት ፣ ሕይወታቸውን ለመሰዋት ወደ ኋላ የማይሉላት ፣ ሲተክዙ ሲያንጐራጉሩ ስሟን ከአፋቸው የማይለዩት ቆንጆና ለግላጋ ፍጥረት ነበረች ። ያቺ ልጅ እልፍ አእ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላፍ ወንዶች ልባቸው በምኞት የተቃጠለላት ፡ የቋሰጠላት ፡ እንደ ፍቅር ጣኦት በየመኝታቸው የሚያመልኳት የሚሰግዱላት ውብ ልጅ ነበረች ። ያቺ ልጅ ስፍር ቍጥር የሌላቸው ጉረምሶች በቁመናዋ ተማርከው ፡ በፈገግታዋ ተነድፈው በሕልም በውናቸው የሚኳለሉላት አስደሳችና ፍልቅልቅ ወጣት ሲሬት ዶዮሌ የምትባል ነበረች ።

ከላይ እስከታች የለበሰችው አንድ ወጥ የሆነውን ንጭ የሐር ቀሚስ ከወርቅ ዘቦ በተሠራ ጉንጉን ከወገቧ ላይ ሸብ አድርጋችዋለ ። በሱፉና በአልማዝ እሸብርቆ ውቶት በሚመስለው ደረቷ ላይ ድንቅግትማ የነበረው የአንገቷ ድሪ ውበቷን ተጨማሪ ድምቀት አጎናጽፎለታል ፡ ለዝንኛው ጥዋርም ቢሆን ውጋመት እስከሚያዳግተው ድረ ፡ ብልፅ ግርማና ጸዳል ተክባ እንደፀሐይ ስታብራቃየው ።

"ሙሴ ሄርኩል ጥዋሮ ! " ስትል ድምጿን እንደ ሙዚቃ አጣፍጣ በድንገት ስትጣራ ፡ ጥዋሮ ፈዞ በመቆም፡

" ኖኝ እመቤቴ ! ምን እንድታዘዝሽ ትፈልጊያለሽ ? " ሲል በትህትና መለሰላት ።

" ማን እንደሆንኩ ሳያውቁኝ የሚጠሩ እይመስለኝም ? " አለችው ምናልባት እራሷን ማስተዋወቅ ማስፈለግ አለማስፈለጉን እየተጠራጠረች ።

" አውቅሻለሁ እመቤቴ ! ስምሽን ሌሎች ሰዎች ሲጠሩት ስለሰማሁ በትክክል አውቅሻለሁ ለማለት እችላለሁ " ሲል ጥዋሮ ፡ ሲሬት የምትጠቀምው መልስ ይህንኑ ስለነበረ " እባክዎን ይቀመጡ " ብላ እርሷም እጠገቡ ከነበረው ሶፋ ላይ አረፍ አለች ። ለጥቂት ደቂ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሎዎችም ያህል እንግዷን አቀርቅራ በትክክዜ ስሜት ተው
ጣ ከቆየች በኋላ ፡ ቀና በማለት ጆዋሮን በብሩህ ዓይኖቿ
እየቃኘች ፡

" እኔም ብሆን እርስዎን በቅድሚያ አውቅዎት
ነበረ ። ስለእርስዎ ብዙ አስደናቂ ታሪኮች ሰምቻለሁ ።
በጣም ብሩህ ሰው መሆንዎንም ተረድቻለሁ ። ስለዚህም
ብቻዎን ላነጋግርዎት የምችልበትን አመቺ ጊዜና ቦታ
ስፈልግ ነበርኩ ። ስጠባበቀው የነበረው ዕድል አሁን
እንዲገጣጠመኝ በማመን የደረሰብኝን ከፍተኛ ችግር ፊታ
ድዎ ቢሆን ላዋይዎት እፈልጋለሁ ። ከላእርሲም በስተ
ቀር ማንም ሰው ሊረዳኝ የሚችል እንደማይኖር አው
ቀዋለሁ " ብላ ልታነጋግረው የፈለገችበትን ምክንያት
በዜማ ልብን በሚሰረስር ድምጿ ልትገልጽለት
ሞከረች ።

ጆዋሮም በዚህ ባልታሰበ ንግግር ኤሌክትሪክ እንደ
ነዘረው ሰው መላ አካሉ ለጊዜውም ቢሆን ኩምትርትር
ካለ በኋላ አእምሮውን በተቻለ ፍጥነት በመቆጣጠር፣

" እንቺን ለመሰለሽ ተወዳጅ ፍጥረት ማድረግ
የሚገባውን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ ማለት እንደማይ
ኖርብኝ ይሰማኛል፡" እሷና ጥቂት አሳብ በማድረግ ፣
"ሆኖም እንደምታይው አሁን ያለሁት በዕረፍት ላይ ነው።
ስለዚህም ደግሞ በዕረፍት ጊዜዬ ማናቸውንም የስለላና
የወንጀል ምርመራ ጉዳዮች ለመከታተል አልፈልግም።
ከዚህ ውጭ የሆነ ችግር ካለብሽ ግን ያለአንዳች ገደብ
ልተባበርሽ ፈቃደኛ ነኝ " ሲል እረጋ አለና መለሰላት ።
ሆኖም ለሊኖት ሕሊና ጉልቶ የታየው የእራሷ ችግር እንጂ
ጆዋሮ ለመስጠት የሞከረው ምክንያት ባለመሆኑ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“በእኔ የተነሣ ለሚያጋጥሙት የዕረፍት ጊዜዎ ማካ ካሻ የሚሆን በቂ ገንዘብ እከፍላለሁ ” አለችና ሴላ ተቃ ውሞ በማቅረብ ሳያቋርጣት በፊት በጣል ኮሮጆ ላይ ለጭቋጨው ያልቻልኩት ቢሰት ተንሰቀሰቀችና ። የደረሰ ብኝን በደል በመዘርዘር በዝኩሉ ለፖሊስ ለማሳወቅ ፈልጌ ነበረ ፣ ሆኖም ጉዳዩ ፖሊስን አይመለከትም በማ ለት ባሌ ሳይስማማ በመቅረቱ ያለኝ አማራጭ ዕድል እርስዎን ብቻ ማስቸገር ስለሆነ እባክዎን ይርዱኝ ” ስትል እንባዋ በዓይኗ ግጥም እያለ ትለማመጠው ጀመር።

ፑዋሮ በቀጥታ ለመቃወምም ሆነ ለመስማማት አቅማ አጣነው ፣ የሊኔትም ሁኔታ አሳዘነው ። ሊኔትን የመሰለች ሐብታም ፣ ሊኔትን የመሰለች ቆንጆ እራሷን በዚህ ደረጃ ዝቅ በማድረግ ልትማፀድ የፈለገችው ልዩ ችግር ቢደርስባት እንደሆነ ተረዳ ፣ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ በገንዘቧ ኃይል እዛ ለማስደረግ ፣ በ... ብቻም አጥምዶ ለማስፈጸም የሚያስችላት ዓይነት ልጅ አልነበ ረችም ። በተለይ የእርሱን እርዳታ የጠየቀችበትን ምክ ንያት ለማወቅ በመፈለግ ፣

“በቅድሚያ ምንም ዓይነት የገንዘብ ክፍያ እንደ ማልፈልግ እንድታውቂው ሆኖ ፣ እስቲ ስለደረሰብሽ በደል ታሪኩን በመጠኑ አጫውቺኝ!” አላት ፑዋሮ፣ ዓይኖቹን ከሥሩ በሚታየው የዓባይ ወንዝ ውሃ ላይ እንደተከለ ። በሊኔት ፊት ላይ ይነበብ የነበረው የሥጋት መንፈስ ከመ ቀጽበት ጠፋ ፣

“ እሺ ! በቀላሉ ለእስረዳዎት እሞክራለሁ ” ብላ ታሪኳን እየተቻኮለች ማውራት ጀመረች ።

“ እኔና ሳይመን ከተጋባን ሁለት ወር አልሞላንም ። ባሌም እኔን ከማግባቱ በፊት ጃክሊን የምትባል እጮኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበረችው ። ጆሲ ልጅ ለእኔም ቢሆን የቅርብ ጓደኛዬ ብትሆንም ፡ ሳይመንና እርሷ ተጣጥመው ጥሩ ትዳር ሊመሠርቱ እንደማይችሉ የታወቀ ነበረ ። ስለዚህም እርሷን ትቶ እኔን ለማግባት ይወስናል ። ተጋባንም ። ጃኪሊን ግን ይህንን ሐቅ ለመረዳት አልፈለገችም ። በእኔና በሳይመን መካከል የተፈጸመውን ጋብቻ በእርሷ ላይ ሆን ተብሎ እንደተፈጸመ ግፍና በደል አድርጋ ቆጠረችው ። ስለዚህም በመጀመሪያ ላይ በየጊዜው ልትዝትብኝና ልታስፈራራኝ ጀመረች ። እኔ ግን አደጋ እንዳትጥልብኝ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳደርግ ቆየሁኝ ። ከዛስ ምን አደረገች መሰለህ ? ዛቻና ስድቧን ትታ ሌላ ቁጭቷን የመበቀያ ዘዴ ፈጠረች ። እኛ በምንሄድበት ሥፍራና አገር ሁሉ ዝም ብላ ትከታተለን ጀመረ ።” ብላ ትንፋሽ ለማግኘት ንግግሯን ቆም ስታደርግ ፑዋሮ ወደ እርሷ ዞር ብሎ በሐዘኔታ እየተመለከታት ፡

“ ይህ ድርጊትዋ ተሰምቶም የማያውቅ ያልተለመደ ነገር ነው ። ተበድያለሁ ያለ ሰው ቁጭቱን በዚህ ዓይነት ዘዴ ሊወጣት ይሞክራል ሲባል ስሰማ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ” አለ ። ሊኔት ግን ከንፈሯን እየነከሰች ፡

“ ያልተለመደ ብቻ አይደለም ፡ ሙሴ ፑዋሮ ! በጣም አርካሽ የሆነ ዘዴም ነው እንጂ ። ሆኖም አድራጎቷ ሁሉ ደም የሚያፈላ ነው ” ስትል ፑዋሮ በአባባሏ ሊስማማ ባይናገርም ፡ እራሱን በማወዛወዝ አሳየ ። ሊኔትም ንግግሯን በቁጭት በመቀጠል ፡

“ ሳይመንና እኔ ያለነው በእፍላ ፍቅር ላይ ነው ። እንደ አዲስ ሙሽሮች ድንብ ልዩ ልዩ አገሮችን እየተዘዋወርን በመጎብኘት ላይ ነን ” አለችና የተረሳትን ነገር ለማስታወስ ያህል ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ ብላ ከቆየች በኋላ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

" አዎን ! ከእንግሊዝ አገር ተነስተን ፡ ከኢጣልያዋ ከተማ ቬኒስ እንደደረስን ነበረ ክትትሏን የጀመረችው ። እኛ አርፈንበት ከነበረው ሆቴል ውስጥ ሳያት ለጊዜው ግር ቢለኝም ፡ የአጋጣሚ ጉዳይ ሊሆን ይችላል ስል ወዲያውኑ እረሳሁት ። ከቬኒስ ወደ ደቡብ ጣልያን ቀጥ ዞን ከብሪንዲሲ ከተማ ስንደርስ አሁንም አየኋት ። እኛ ወደ ግብጽ ምድር የሚያደርሰንን መርከብ በመጠባበቅ ላይ ነበርን ። 'ጃኪሊንስ ምን ታደርጋለች ?' ብዬ እራሴን ስጠይቅ በአእምሮዬ ውስጥ አንድ ሐሳብ መጣ ። ወደ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ልትሄድ መሆን አለበትም ስል ገመትኩ ። ግን ጃኪሊን ከእኛ በፊት ግብጽ ደርሳ ካይሮ ከተማ ውስጥ ቀደም ሲል ለማረፊያ ከተመዘገብንበት ሆቴል ውስጥ ጠበቀችን ። ጥርጣሬዬ ከበድ እያለ ቢሄድም ፡ ማን ያውቃል ? አሁንም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ስል እራሴን ለማጽናናት ሞከርኩ " ብላ በአረጀው ትንፋሿን ተንፍሳ አረፍ አለች ።

" አሁንስ ? " አለና ፑዋሮ በማበረታታት ጠየቃት ።

" ከካይሮ ወደ አስዋን ከተማ የመጣነው በአንስተኛ ጀልባ ነው ። ጃኪሊን ግን በዚያች ጀልባ ላይ አልተሳፈረችም ነበር ። በበኩሉም የነበረኝ ግምት አድራሻቿ ሁሉ የሕጻን ሥራ መሆኑን ተረድታ የድብብቆሽ ጨዋታዋን አቋርጣለች የሚል ነበረ። ሆኖም እዚህም ቢሆን እኛ ከምናርፍበት ሆቴል ቀድማ መጥታ ይዛ አገኘናት" ብላ ንግግሯን ስታቆም መልኳ በመጠኑም ቢሆን በንዴት ተለዋውጦ ነበረ ። ፑዋሮም ቀስ ብሎ ሊያበርዳት እየሞከረ ፡

" እንደመሰለኝ ሥጋትሽ ሁሉ ሁኔታው በዚህ ይቀጥል ይሆን ወይ በማለት ነው ? " አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እርሷም " አዎን " ስትል መልሳ " ሥራዋ ሁሉ የዕብድ ሥራ መስሎ ታየኝ ። የሴትነት ክብርና ልዕልናዋን ሽጣ በሌቦች ፊት ማለት ይቻላል " ስትል ጥዋር በእጇ ጭምር ለማውራት እየሞከረ ፤

" ከእንጋገርሽ ለመረዳት እንደቻልኩት ማንኛውንም ነገር ቢሆን ጊዜ እንደሚለዋወጠው ነው ። እራስን መቆጣጠር፣ ክብርን መጠበቅ ፤ ትዕግሥትና የዋሕነትን የመሳሰሉት ሠናይ ባህሪያት ፤ ተቀራኒ በሆነ ሌላ የስሜት ኃይል በቀላሉ ሊደመሰሱና ሊተኩ እንደሚችሉ ያሳየናል " ሲል ሊኔት ቀበል አደርጋ ፤

" ታዲያ ይህ ለእርሷስ ቢሆን ምን ጥቅም ያስገኝላታል ? ያለችግርስ በስተቀር ምን ታተርፋለች ? " ስትል ጠየቀች ። ጥዋር አሁንም ወደ ወንዙ ውሀ አቅጣጫ እየተመለከተና የሚናገራቸውን ቃላት እየመረጠ ፤

" እንደገባኝ ከሆነ የጃኪሊን ዓላማ በማግኘትም ሆነ በማትረፍ ላይ ያተኮረ አይመስለኝም ። ለማንኛውም ለእሚወትሽኝ ችግር ቀላል መፍትሔ ያለው ይመስለኛል ። ከዚህ ሁሉ ብስጭት ወደ አገራችሁ ብትመለሱ አይሻልም ? " ሲል ጥያቄም አስተያየትም አቀረበላት።

" እዚያም ቢሆን ልትከታተለን ትችላለች !"
" ሊሆን ይችላል ።" አለ ጥዋር ፤
" ሥራዋ ሁሉ የዕብድ ሥራ ነው!"አለች ሊኔት።
" እውነትም የዕብድ ሥራ ።" ሲል ድጋፉን ሰጠ።

" ግን ከእርሷ እስከመቼ ስንሸሽ ልንኖር ነው ? ልክ እንደ . . . . " ብላ ቆም ስትል ጥዋር ይጠባበቀው ከነበረው ነጥብ ላይ ደርሳለት ኖሮ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

« እንዳልኸው ልክ እንደ . . . » አለና አየት እያደረጉትና : «መልሱ ያለው እዚህ ላይ ነው» ብሎ አቆመ።

« ምን ማለትዎ ነው አባክዎን ? » ስትል በመገረም ጠየቀችው ።

ጥሞር ወደ እርሷ ጠጋ በማለት ድምጹን ዝቅ አድርጎ « የጃኩሊን መከታተል እስከዚህ ሊያናድድሽ የሚገባ ነገር አልነበረም ። ግን ልክ እንደ . . . ብለሽ ጀምረሽ ልትናገሪው ያልፈለግሽው ምሥጢር አለ ። የምታደምጭኝም ከሆነ ታሪኩን እኔ እጨርሰዋለሁ » ብሎ ንግግሩን በዝግታ ቀጠለ ።

« ከሁለት ወራት በፊት እኔም በእንግሊዝ አገር ነበርኩኝ ። ለንደን ከተማ ውስጥ በሚገኘው በሼ ማ ታንት ምግብ ቤት ውስጥ እራት በመብላት ላይ እንዳለሁ ፤ ሁለት ወጣቶች መጥተው አጠገቤ የነበረውን ጠረጴዛ ይዘው ተቀመጡ ። በጣም ደስተኞች እንደነበሩ ከዓይኖቻቸው ማንበብ ይቻላል ። እጅግም የሚፋቀሩ እንደነበረ በቀላሉ ለመገመት ችያለሁ ። ወደፊት ስለሚመሰርቱት ትዳርና ስለኑሮአቸው ከብሩህ ተስፋ ጋር ይወያያሉ ። የሚነጋገሩትን ለመከታተል ፍላጎት ባይኖረኝም ፤ ወጣቶቹ የተዘፈቁበት በሆነ ልዩ የደስታ ዓለም ውስጥ ስለነበሩ፤ የእኔ በአጠገባቸው መገኘት አለመገኘት፤ ጨዋታቸውን ማዳመጥ አለማዳመጥ ምንም መስሎ አልታያቸውም ነበረ ። የወንድየውን መልክ በትክክል ለመለየት ባልችልም ልጅቱ ግን የተቀመጠችው ከፊት ለፊቴ ስለነበረ የምትናገረው ሁሉ ከንጹሕ ፍቅር በመነጨ ስሜት፤ ከልቧ እንደነበረ ለመገንዘብ ችያለሁ ። ከፊቷም ላይ እንዳነበብኩት በቀላሉ በፍቅር የምትጠመድ ዓይነት ልጅ ባትመስልም፤ ከወደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶች ግን በሙሉ ልቧ ነፍሷና አካሏ ጭምር የምታፈ ቅር ነበረች ። ለእርሷ ከዚህ የተለየ ሕይወት ፡ ከዚህ የበለጠ ደስታ አልነበራትም ። ወጣቶቹ ወደ መጨረሻው ላይ ይወያዩ የነበረው ጋብቻቸውን በቶሎ ፈጽመው ፡ ለሽርሽር ወደ ግብጽ አገር ለመሔድ ስለነበራቸው ዕቅድ ነበር ” ብሎ በትካዜ ይመለከት ጀመረ ። ሉሲት ግን ፡

“ በቃ ! ታሪኩን ይቀጥሉልኝ ! ” ስትል ተቆጣቻቸው ። ፒዋሮም እንደ ቀድሞው በእርጋታ አነጋገሩ እንደዚህ ሲል ቀጠለ ።

“ በታሪኩ መጀመሪያ ላይ እንደ ገለጽኩልሽ ፡ ይህ የሆነው ከሁለት ወራት በፊት ቢሆንም ፡ በተለይ የልጂቱ መልክ የሚረሳኝ አይደለም ። የልጅየውንም ድምጽ ቢሆን በቀላሉ የምለየው ነው ። የሚደንቀው ነገር ያንን መልክ እዚህ በግብጽ ምድር አየሁት ፤ ያንንም ድምጽ በዚሁ በግብጽ አገር ሰማሁት ። ሆኖም ያ ወጣት ጋብቻ ፈጽሞ ከሚስቱ ጋር በሽርሽር ላይ ነበረ ። ያገባት ልጅ ግን ቀድሞ ሲል ቃል ኪዳን የገባላት ሴትዮ ሳትሆን ሌላ ነበረች” አለና አቆመ ።

ሉሴት ፡ የፒዋሮ አባባል በግልጽ ስለገባት ውስጥዋ ውስጡን እየተናደደች “ ታዲያ ልጅየው ቀድሞ ቃል ከገባላት ልጅ በይበልጥ የሚወዳት እንደኔ ቢያ ገባ ምን አለበት ። ስለእኔና ሳይመን ጋብቻም ቢሆን ቀደም ሲል አጫውቼዎታለሁ ” አለቻቸው ።

“ ማጫወትስ አጫውተኸኛል ። ግን ይህን ሁሉ ለማውራት የፈለግከው በዚያን ምሽት ወቅት ፡ ያቺ ልጅ አለችኝ የምትለው ጓደኛዋ አንቺ ብቻ እንደ ነበርሽና ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምንም ነገር እንደማትሰውሪት እርግጠኛ ሆና በቴሌፎንሽ ስትናገር በመስማቴ ነው ” ሲል ፑዋሮ ፡

“ ካልረቡት በስተቀር ስለእኔና ጃክሊን ጓደኝነትም ቢሆን ነግሬዎት ነበረ ” አለችው ሊኔት ፈጠን ብላ ።

“ እና በእንቺ ላይ ፍጹም የሆነ እምነት እንደነበራት ታውቂ ነበሩ ? ” ሲል ፑዋሮ አሁንም ጠየቃት ።

“ አዎን ! ” አለች ሊኔት ሳታመነታ ። ሆኖም ይህንን መልስ በመስጠቷ የተጸጸተች ይመስል ከንፈሯን በመጂጋግም እየነከሰች አባባሏን ለማስተካከል ሞከረች።

“ እንደነዚህ ያሉ አጋጣሚዎች አንዳንድ ጊዜ ሊከሰቱ ይችላሉ ” ስትልም ምክንያት ሰጠች ። ፑዋሮ በመልሷ አልረካም ነበረ ። ስለዚህም “ እንዳልሺውም ሊሆን ይችላል ” አለና “ ግን ከሁኔታሽ እንደምገምተው የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ተከታይ ትመስይኛለሽ ? ” ሲል ያስታሰበ ጥያቄ አቀረበላት ። ሊኔት በአጠያየቁ ግራ ብትጋባም “ አዎን ” ስትል መለሰችለት ።

“ ይህ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ታሪኮች አልፎ አልፎም ቢሆን በሰንበት ዕለት ሲነበቡ ስትሰሚ አትቀሪም ። እኔም በመጽሐፈ ሳሙኤል ውስጥ ከተጻፈው በመጠኑ ልጠቅስልሽ እፈልጋለሁ ። ‘ እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ ፡ ወደ እርሱም መጥቶ አለው ። በአንድ ከተማ ውስጥ አንዱ ባለጠጋ አንዱም ደሀ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ ። ባለጠጋውም እጅግ ብዙ በግና ላም ነበረው ፤ ለድሃው ግን ከአንዲት ታናሽ በግ በስተቀር አንዳች አልነበረውም ። አሳደጋትም በብብቱም ትተኛ ነበረ ፡ እንደ ልጁም ነበረች ። ወደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዘለዓለማዊውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለማረድ ሳሳ ። የዚያንም የድሀውን ሰው በግ ቀምቶ አረደበት ። ዳዊትም በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቆጥቶ ናታንን ሕያው እግዚአብሔርን ! ይህን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው ! አለ" " አለኝ ጥቁር ሊሬትን ትኩር ብሎ እያየ ፤ " ይህ እንግዳህ ተፈጽሟል ! " ሲላት የሊሬት ሰውነት ፍጹም ተቀያየረ ። ዓይኖቿ እንባቸ ፈጠው ቀሩ ። ከዚያም ቁርጥ ቁርጥ በሚለው ትንፋሿ ፤

" ምሳሌዎ ወደ ማን እንዲያመለክት ገብቶኛል ። እንደእርስዎ አስተሳሰብ የጓደኛዬን ዕጮኛ በማፍ የቀማኋት ለማስመሰል ሞክረዋል ። እንደርስዎም በዕድሜ ከገፉ ሰዎች ከዚህ የተለየ የዋሕ አመለካከት አልጠብቅም ነበረ ። ለእርስዎ ባይዋጥልዎትም መራራው ሐቅ ግን ከዚህ የተለየ ነው ። ጃክሊን ሳይመንን ነፍሷ እስኪወጣ ድረስ ታፍቅረው እንበል ። ግን ሳይመን በሕጋዊው ክልሉ ይወዳት እንደነበረ እርግጠኛ ሆነው መናገር ይችላሉ ? " አለችና ከንዴቷ በመጠኑም ቢሆን በረድ እያለች፤

" አዎን ! እንደ ጥሩ እህት ወዷት ሊሆን ይችላል ። ለዚህ ደግሞ ዋናው ማረጋገጫ የሳይመን ዓይኖች በዓይኖቼ ላይ ገና ከማረፋቸው ልቡን ወዲያውኑ ከፍቶ የፍቅሩን ስሜት ጥልቀት ለእኔ በግልጽ ማሳየቱ ነው ። ታዲያ ይህ ወጣት የወደፊት በደስታ የተሞላ ሕይወቱን ለይሉኝታ ሲል መስዋዕት አድርጎ ከልቡ የማያፈቅራትን ሴት እንዲያገባ እርስዎስ ቢሆን ይደግፋሉ ? አስተሳሰብዎ ይህ ከሆነ ለምን በአንዲት ሴት ሐዘን ምትክ ሶስት ሰዎች አልተሰቃዩም ? ወይንም በአንድ ሰው ዕድል መጨለም ምትክ ለምን የሶስት ሰዎች ሕይወት አልተጨለመላቸውም ! ብለው እንደሚከራከሩ ከሚያስመ



t.me/OLDBOOKSPDF

ዎት በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም ። ሳይ
ወግ እኔን ከማግኘቱ በፊት ጃክሊንን አግብቷት እንኳን
ቢሆን ኖሮ ከእርሷው ጋር እንዲፈረደበት ለመኖር የሕ
ሊና ግዴታ ባደረበት ነበረ ። ግን ከዕለታት አንድ ቀን
ቃል ገብቶላት ነበር በማለት ብቻ ሰብሮ ለመውጣት
በማይሞክር የእግር ብረት እንደታሠረ አድርገን ልንቆ
ጥረው አይገባም ። እንዲያውም ስሕተት ላይ መውደቁን
ተረድቶ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ የሚወስድ ሰው ሊመ
ሰገን እንጂ ሊወቀስ አይገባውም ። ስለዚህ እኔ ጃክሊንን
ብሆን ኖሮ እራሴን በእራሴ አጽናናዋለሁ እንጂ ‘ የፈ
ሰሰን ወተት በለቅሶ አይመልሱትም’ እንደሚባለው
አነጋገር አንዴ ላመለጠ ነገር አትል ባልተንገታገትኩም
ነበረ ” ስትል ሐሳቧን አጠቃለለች ።

ለጥዋር አእምሮ የሊኔት ንግግር አርኪ ሆኖ አልተ
ገኘም ። ስለዚህም “ በክርክር ነጥቦችሽ አደራደር ልታ
ሳምኝኝ ብትሞክሪም ፤ ሸፋፍነሽ ለማለፍ የምትፈልጊው
የተደበቀ ነገር አለ ” ሲል አሁንም መልሶ ከጥርጣሬ
መንፈስ ላይ ጣላት ።

ሊኔትም እየተጨነቀች “ ጥያቄዎን ግልጽ ቢያደር
ጉልኝ ? ” አለችው ።

“ በመሸፋፈን ለማለፍ የምትሞክሪው የእራስሽን
ስሜትና አስተያየት ነው ” አለና “ ጓደኛሽ መሆኗን
ያልካደችው ጃክሊን በደረሰባት የመንፈስ ጭንቀት የተ
ነሣ አንዳንድ ያልተለመደ አድራጎት በመፈጸሟ የሚያ
ስገርምሽ ቢሆንም ሲበዛ ደግሞ ሊያሳዝንሽ በተገባ ነበረ።
አንቺ ግን ልታዝኚላት ቀርቶ በንዴት ተብገንገንሽ ።
ለምን ? ለዚህ ሊኖር የሚችለው አንድ መልስ ብቻ
ነው ። ግፍና በደል መፈጸምሽን ሕሊናሽ ስለተረዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውና ዕረፍት ስለነሳሽ ነው!" ሲላት ሊዜት ከተቀመጠችበት በንዴት ብድግ ብላ ያንን እንደ ፀሐይ የሚያበራ ፊቷን በማጥቆር ፡

"ይህማ ብልግና ነው ፡ ሙሴ ጥዋሮ! እንዴት እቃ ልሰው ቢመስክቱኝ ነው ይህን ድፍረት የተሞላበት አስተያየት የሚሰጡት!" ስትል እምርሯ ተናገረች ። ሆኖም ጥዋሮ ከተቀመጠበት ቦታ ቅስቅስ ሳይልና የረጋ እንደበቱን ሳይለውጥ ፡

"አሁንም ቢሆን ድፍረት የተሞላበትን አነጋገሬን የምትደፍር አይደለሁም ። አንቺ ለመሸፋፈን የምትፈልጊውን እኔ ደግሞ ግልፅ ለማድረግ አእምሮዬ ያስገድደኛል ። በጃኩሊን እጮኛ ስለተማረክሽ የእራስሽ ልታደርጊው ፈለግሽ ። ምርጫውም ያንቺ ብቻ ነበረ ። ቆንጆ ነሽ ፡ ሐብታም ነሽ ፡ ብልህ ነሽ ፡ በማራኪው ውበትሽ በመሳብ የፈለግሽውን ሰው በቀላሉ እንዲያፈቅርሽ ማድረግ ትችያለሽ ። በፍቅርሽ ለማጥመድም ሆነ ላለማጥመድ ሁሉም ምርጫ በእጅሽ ውስጥ ያለ ዕድል ነበረ ። ስለሆነም አንቺ እንደመጽሐፍ ቅዱሱ ሐብታም እጅሽ የድሃዋን የጃክሊንን እጮኛ ለመውሰድ መረጠ ። የጓደኛሽን ተስፋ አጨለምሽበት ። ስለዚህም የሕሊና ዕረፍት የነሳሽ የፈጸምሽው በደል ትዝታ ብቻ ነው" ብሎ ሐቁን እንደቦንብ እፊቷ ላይ ሲያፈነዳባት ሊዜት ይሉኝታ ባይዛት እሪ! ብላ በጩኸትና መሬት ላይ ተንደፋደፋ ባለቀሰች ምርጫዋ ነበረ ። ግን አሁንም ላለመረታት እየተግደረደረች ፡

"ልክ አይደለም! ፍጹም ተሳስተዋል!" ብላ መቃወሙን መረጠች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፒዋር በዛው የተለመደ አንደበቱ ፡ አሁንም መላልሶ ሊያስረዳት ሞከረ ።

“ ስሚኝ እመቤት ሊኔት ! ቀደም ሲል ጤናማና ደስተኛ ኑሮ የምትኖሪ ፡ ቸርና አሩኅሩህ ልጅ ነበርሽ ። ሰው እንዲቀየም ፡ በሰው ላይ ግፍ እንዲፈጸምም የማትፈልጊ የዋህ ፍጥረት ነበርሽ ። ስለዚህ ጃክሊንን መበደልሽ በታወሰሽ ቁጥር ያስጨንቅሻል ። ቢሆንም ለወደፊቱ እራስሽን በራስሽ ማጽናናት ይኖርብሻል ። መበረታታትና የሚገጥምሽን ሁሉ በድፍረት ለመቋቋም መሞከር አለብሽ ” ሲላት ሊኔት አድሮባት በነበረው ንዴት ምትክ የፍርሃት ስሜት እየወረራት ሄደ ፡

“ ጃክሊን እኮ ለየት ያለች ፍጥረት ናት ። ከመስላት ከባድ አደጋ ለማድረስ ወደ ኋላ አትልም ” አለች ፒዋሮን ዓይን ዓይኑን በመለማመጥ እያየች ።

“ አዎን ! እንደዛተችብሽም አጫውተሽኝ ነበረ ። ግን የዛቻውን ቃል በትክክል ብትነግሪኝ ? ”

“እኔንም ሳይመንንም እንደምትገድለን ፎክራለች ” አለችው ሊቃ እየተናነቃት ። ፒዋሮ ከተቀመጠበት ተነስቶ ሊኔትን ሊያጽናናት ሞከሮ ፡

“ ጃክሊንን እንደምንም ብዬ አነጋግራታለሁ ። እንዳ ተበደለች ባውቅም ይቅርታ እንድታደርግ እለምናታለሁ ” ሲል ቃል ገባላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሁለት

ሄርኩል ፑዋሮ፡ጃክሊንን ያገኛት በወንዙ ዳር ካለ አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ ነበረ ። ጉንጮቿን በመዳፎቿ መሐል ይዛ በጭንቷን ጨብጣ በከባድ ሰመመን ተውጣለች ። ፑዋሮ አጠገቧ ደርሶ እስኪያነጋግራት ድረስ ዘወር ብላም አላየችውም ። እርሱም በሁኔታዋ እጅግ ቢያዝንላትና ሀዘኑም ቢረብሸበት፡በይበልጥ እንዲያጽናናትና እንዲያወያያት ስሜቱ ስለገፋፋው፡ለብቻዋ የተያያዘችውን ትካዜ አቋረጠ ፡

“ ይቅርታ አድርጊልኝ ጃክሊን ! ለጥቂት ደቂቃዎች እንዳነጋግርሽ ብትፈቅጂልኝ ? ” ሲል ለመናት ። ጃክሊን እራሷን ቀና በማድረግ የደረቁ ከንፈሮቿን በግድ እያላቀቀች ፡ “ ባልሳሳት ሙሴ ፑዋሮ መሆን አለብዎት ፤ ሆኖም ሊያነጋግሩኝ የፈለጉት ሊኔት ልካዎ ከሆነ ብዙም ባይጥሩ” አለችው።ፑዋሮ ከምሯ እንደምትናገር ቢረዳም ተስፋውን በቀላሉ አልቆረጠም ነበረ ። በተቻለ መጠን ግልጽ ለመሆን ፈልጎ ፡

“ የመጣሁት እንደምትጠረጥሪው ለአማላጅነት ፤ ወይንም ገንዘብ ተከፍሎኝ አንቺን ለመሸንገል አይደለም ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንዳወያይሽ መንፈሴ ስላስገደደኝ ነው ” ብሎ ከጎኗ ካለው ድንጋይ ላይ ቀስ ብሎ ተቀመጠ ። ጃክሊን ዳግመኛ ለመናገር ስላልፈለገች እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

በፊቱ ተኮፈትሞታ በመቀመጥ አንገቷን አቀርቅራ ዝም አለች ። ጸጥታም ሰፈነ ። ጥዋሮም በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም የጃክሊንን ገጽ ባህርያት ለማጥናትና ለመረዳት ሞከረ ።

ጃክሊን እንደ ሊኔት ዕድሜዋ ከሃያ ዓመት አይበልጥም ። ቁመናዋም ከሊኔት ጋር ተመሳሳይነት ነበረው ። ግን እንደሊኔት የሚያንጸባርቅ ጸዳል ፡ እንደሊኔት የሚያበራ ገጽታ አልነበራትም ። ሆኖም የግሏ የሆነ አንዳንድ ማራኪ ባህርያት እንዳሏት ተገነዘበ ። ውብና ትላልቅ ዓይኖቿ ጥቁር ዘንፋላ ጸጉሯ ፡ ከሰፊው ግንባሯ ሥር ስልክክ ብሎ የወጣው አፍንጫዋ፡እምቡጥ የሚመስለው ከንፈሯ ሲብ ብሎ ላየው የመንፈሷን ንጽሕና እንደሚመሰክሩላት አመነ ። ሊኔት በፍቅሯ የምታቃጥል ፡ በቅናት የምታሳብድ ፡ የምታነንፍና ሕሊናን የምታስት የሆነችውን ያህል ፡ ጃክሊን ካፈቀሯት የምታበርድ፡በራስ መተማመንን የምታገለምስ ፡ የምታበረታታና የምታጸናናር ልጅ መሆኗን በይበልጥ ተረዳ ።

ጥዋሮ የሰፈነውን ጸጥታ አቋርጦ ጃክሊንን ሊያነጋግር የሚችልበትን ዘዴ ፈለገ ፡

“ ከአሁን በፊት አይተሽኝ የምታውቂ አይመስለኝም ? ” ሲል ጠየቃት ። እርሷ ግን መልስ ከመስጠት ተቆጥባ ያላየችው መሆኗን ለመግለጽ አራሷን በማወዛወዝ ብቻ አሳየች ።

“ እኔ ግን አይቼሻለሁ ! አንድ ምሽት በለንደን ከተማ በሺ ማ ታንት ሆቴል ውስጥ ከሳይመን ጋር ሆናችሁ የተቃመጣችሁት አጠገቤ ነበረ” ሲላት የጃክሊን ትዝታ በመጠኑም ቢሆን በመቀስቀሱና ሙሴ ጥዋሮንም ላለማስቀየም ስትል ፡

“ አዎን ፡ ያ ምሽት ትዝ ይለኛል ” አለችው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ከዚያን ወዲህ ብዙ ነገሮች ተፈጥረዋል " አለ ፑዋሮ ውይይቱን የሚቀጥልበትን ሁኔታ እያመቻቸ ፤

ጃክሊን ግን ተከፋ በቆረጠና በምሬት አነጋገር " አዎን እንዳሉትም ሆኗል " ብላ ጸጥ አለች ።

" ስሚኝ ጃክሊን፤ የማነጋግርሽና የምመክርሽ ሲሆን እንደ አባትሽ አለበለዚያም እንደ ጥሩ ዘመድሽ ሆኜ ነው። ስለዚህም የሞተውን ነገር ቅበሪው ፤ እርሺውም !" ሲላት ከአፍላ እንቅልፍ ላይ እንደቀሰቀሱት ሰው ብርግግ ብላ ፤

" ምን ማለትዎ ነው ? " ስትል በመደናገር ጠየቀችው ።

" ያለፈውን እርሺው ! ስለወደፊት ዕድልሽ አስቢ። ግፍ በፈጸምሽበትም የእንቢ ምሬትና ሐዘን አንድ ጊዜ የሆነውን ነገር ሊፍቀው እንደማይችል ተረጂ ! " ሲል ፤

" ምክርዎ ለእኔ ሳይሆን ለሊኔት የሚረዳ ነው ። እውነትም ጥሩ አማላጅ ነዎት " ስትል አሾፈችበት ። ፑዋሮ ግን አሁንም በሐዘን መልክ እያያት ፤

" ምናልባትም የተጨነቅኩት ለሊኔት መስሎሽ ይሆናል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ያዘንኩት ለአንቺ ነበረ ። ስትሰቃዪ ቆይተሻል ፤ ከእንግዲህ ወዲያም ሐዘንሽ የሚቀጥልበት ምክንያት የለም ! " ከማለቱ ሐሳቡን ያልተቀበለችው ለመሆኗ እራሷን ጭምር በማወዛወዝ እያሳየች ፤

" ተሳስተዋል ! አሁን በቀድሞው ስቃይና ሐዘን ምትክ ደስታ እየተሰማኝ ነው ! " አለችው ።

" ይህንን ደስታ አልፈውም ጃክሊን ። የምመክርሽ ጤናማ ደስታ እንድታገኚ ነው ። ወደ አገርሽ ተመለሺ



t.me/OLDBOOKSPDF

መጣት ነሽ ! መልከ መልካም ነሽ ! ጥሩ አእምሮ አለሽ !
በዓለም ውስጥ እውነተኛውን ደስታ አግኝተሽ ለመኖር
ተስፋሽ ብሩህ ነው” አላት ። እርሷ ግን መለስ አደረገ

“ ያልገባዎት ነገር አለ ። ለእኔ ደስታዬ ዓለማዊ
ሳይመን ጠቢባንን ሰውን ሊረዱልኝ አልሞከሩም ። ሳይ
መን ይወደኛል እወደዋለሁ ። ሊጌት ግን በሀብቷና በው
በቷ አዘናግታ ሳይመንን ቀማችኝ ” አለች በማማረር።

“ የዋሕ አትሁኝ ጃክሊን ፤ እንዳልሽው ሳይመን
የሚያፈቅርሽ ከሆነ ሊጌትን እንዲያገባ ማን አስገ
ደደው ። መቃወም አይችልም ነበር ማለት ነው ?” አለ ።

“ እንደዚያ አይደለም ሙሴ ፐዋሮ ! ሳይመን ሊጌ
ትን አፍቅሯት ማግባቱን ባምንበት ኖሮ እነርሱን ተከ
ታትዬ እዚህ ድረስ ባልመጣሁም ነበረ ። ሊጌት እንደ ኳር
ቃኛ ንግሥታት የፈለገችውን ለማድረግ የምትችል ናት ።
እርሷን ለማግባት ያልለመነ መስፍን ያልተማጠነ ከበ
ርቴ የለም ። እነኝህን ሁሉ ንቃ የእኔን ሳይመንን መረ
ጠች ። እርሱም ባላሰበበት ጊዜ ባልጠረጠረው ቦታ ወጥ
መድ ውስጥ ወደቀ ። ” አለችና ወደ ሰማይ በመመል
ከት ቀኝ እጅዋን አንስታ ወደ ጨረቃዋ እያመለከተች ፡
“ እስኪ ያቺን ጨረቃ ይመልከቱ ! በግልጽ ትታያለች ።
በምሽቱ የመጣች ድንገተኛ ክስተት ሳትሆን ምንጊዜም
የነበረች ናት ። ግን የፀሐይ ደማቅ ብርሃን ሲወጣበት ለዓ
ይን ትሰወራለች ፡ አትታየንምም ። በጨረቃዋ የምመ
ሰለው እኔ ነኝ ። በሊጌት ደማቅ ብርሃን ስለተጋረድኩ
ሳይመን ሊያየኝ አልቻለም ። ስለዚህም አለችና” በጭኗ
ላይ የነበረውን ቦርሳ አንስታ ከከፈተች በኋላ አንዲት
እጀታዋ ነጭ የሆነ ትንሽ ሽጉጥ አውጥታ እያሳየችው ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

« ጨረቃዋ እንደትታይ ፀሐይ መጥፋት ይኖርባታል ። ካስፈለገም ለእርሱም ቢሆን የምመለስበት አይደለሁም ! ። ለጊዜውም ቢሆን አረስቶኛል ! ንቆኛል ! ጠልቶኛልና ! » ስትል ተናገረች ። ጥዋሮ ምንም መልስ ሆኖ አስተያየት ለመስጠት አልፈለገም ። በሐሳቡ ወደ ሌላ አቅጣጫ ከብልሎ ሄዷል ። እርሷ ግን ያቺን ሽቱዋ በእጅዋ እያገላበጠች ፤

“ አባቱም እናቱም ደህና ተኳሾች ነበሩ ። የሚደንቀው ግን ሁለቱም በፍቅር ጦስ የተነሣ እንዳንድ ሰው ገድለዋል ። ስለዚህ ለፍቅር ሲባል ደም ማፍሰስን በዘር የወረስነው ጠባይ ሊሆን እንደሚችል ወደማመኑ ደርሼ አለሁ ። ከፈለግከኝ ሁለቱንም ቢሆን በቀላሉ መግደል እችላለሁ ። በተለይም እርሷን ከጆሮ ግንዷ ላይ ብዬ መድፋት አለብኝ ። ከዚያ በፊት ግን በቁም እንዲሰቃዩ እፈልጋለሁ ! ። የትም ይሂዱ የትም እንደምፈልግ እከተላቸዋለሁ !። ሞቴ በየሰከንዱና በየደቂቃው የሚያገኙባቸው መሆኑን አስታውሳቸዋለሁ ! ። ደስታን ሲያውቋት ወደመቃብራቸው ይወርዳሉ ። በጭንቀት የተጨማለቀ በመርዝ የተበከለ ኑሮ ይኖራሉ ! » እያለች እንደ አበደ ሰው ጆሮ በሚሰነጥቅ ሣቅ ትንከትከት ጀመረ ። ጥዋሮ እንደምንም ታግሶም ሆነ ተለማምጦ ዝም ካሰኛትና ካስታገሳት በኋላ ፤

“ እባክሽን ጃክሊን ፤ እጅግ አድርጌ እጥብቄ እለምንሻለሁ ። የልብሽን በር ወለል አድርገሽ ከፍተሽ ክፋትና ኃጢዓት እንዲገቡበት አትጋብዢያቸው ። እርኩስ መንፈስ ድንኳኑን በልብሽ ውስጥ ከዘረጋ በኋላ ማስወጣቱ በጣም የከበደ ይሆናል » አላት አሁንም እንደአባት በርኅራኄ እያየት ፤ “ ለሌሎችም ቢሆን ሳይመንን



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳለማማበት ዕድል ነበራት ። ግን እራስ ወዳድ ሆነችና በዚያ ዕድል ሳትጠቀምበት አመለጣት ። አንቺም በክፋት ምትክ ደግነት ለመሥራት በጭካኔ ምትክ ርኅራኄ ለማ· ስትችይ ፤ እራስሽን ለኃጢዓት ተገዢ አድርገሽ በጸጸት ሰንሰለት እንዳትተበተቢ !” ብላት አንገቷን እንዳቀረቀረ ወደ ሆቴሉ አመራ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሦስት

ሳይመን የመኝታ ቤቱን መስኮት መጋረጃ ገለጥ እያደረገ ሲመለከት ጁዋሮን ከሆቴሉ ግቢ ውስጥ ሊወጣ ሲል አየው ። እየተቻኮለ በመራመድ ከደረሰበት በኋላ ለንጋቱ ሰዓት ተገቢ የሆነውን ሰላምታ ተለዋወጡ ። በመንገዱም ግራና ቀኝ በተተከሉት ዛፎች ጥላ ተከልለው ጥቂት እንደተጓዙ ሳይመን በአፉ ጎርሶት የነበረውን ፒፓ ካወጣ በኋላ ፤

« የምትሄዱት ወደ ከተማ ከሆነ አንዳንድ ጉዳዮችን እያጫወትኩዎት አብሬዎት ብሄድስ ? » ሲል የጁዋሮን ስምምነት ጠየቀ ።

ጁዋሮም « በደስታ ! ብቸኛ ከመሆን ገላገልከኝም እንጂ » አለው። ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ሁለቱም ዝም ዝም ተባባሉ ። ሳይመን የንግግር ተሰጥኦ ስላልነበረው በአእምሮው ውስጥ ይብላላ የነበረውን ጥያቄ የሚያቀርብበት ዘዴ ጨንቆት ነበረ ። እንደምንም ብሎ ሲፈራ ሲቸር « ሲኔት ትናንትና ማታ አነጋግራዎት ነበረ መሰለኝ ? » ሲል የዝምታውን መጋረጃ ቀደደ ።

ሆኖም ጁዋሮ « አዎን » የምትለዋን ቃል ብቻ በመናገሩ ፤ ሳይመን በዚች ቁርጥ ባለች መልስ ሰውነቱ ስቅጥጥ አለ ። ሊሰማት ፈልጎ የነበረው እረዘም ያለ ታሪክ ነበረ ። ስለዚህም ይሻላል ብሎ ባውጠነጠነው ዘዴ ጭውውቱን ለመቀጠል ሞከረ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

" ሊኔት የፈጸመችው ምንም በደል የለም ። ባል ሠራችው ሥራ መሰቃየቷ ግን ያሳዝነኛል። እኔን ማንም ሰው እንደፈለገ ቢናገረኝና ቢዘልፈኝ ምክንያት ስለ አለው ሊገባኝና ልታገሥ እችላለሁ ። ግን ኃጢዓቱ ሁሉ በሊኔት ላይ በጭፍን መደፍደፉ የሚያሳዝን ነው" ። አለና ደማቅና ወርቃማ ጸጉሩን በጣቶቹ እንደሚያበጥር ሰው እየነካካ " ለመሆኑ ጃኩሊንንስ አነጋግረዋት ነበረ ? " ሲል አረጋ አለና ጠየቀ ።

" አዎን አነጋግሬአት ነበረ " አለ ፑዋሮ አሁንም መልሱን አሳጥሮ ።

" ስህተቷን ተረድታ እንድታርም አሳመናት ? "

" አዝናለሁ አልቻልኩም ። "

ብሩሁ የሳይመን ፊት በንዴት ልውጥ ውጥ አለና ፡ " እራሷን የሰው መሳቂያ ማድረጓ እንዴት አይገባትም ? ምንስ ዓይነት አዕምሮ ብትሆን ነው ይሉኝታ ያጣችው ? ጨዋ ልጅ ብትሆን ኖሮ ክብሯን የመጠበቅ ከፍተኛ ስሜት ሊኖራት በተገባ ነበረ " አለ እየተበሳጨ ።

"ጃኩሊን በሊኔት የስሜት ኃይል ቁጥጥር ሥር ናት ፣ የተበደለችና ግፍ የተዋለባት ስለሆነ የተረፋት የጥላቻ ስሜት ብቻ ነው " አለው ፑዋሮ ለሳይመን ንግግር እም ብዛም ክብደት ሳይሰጥ ።

" ግን እኮ ይህ ልክ አይደለም ሙሴ ፑዋሮ ! እኔ በደልኳት ፡ እኔ አሰቀየምኳት ፡ እኔ ግፍ ዋልኩባት ፡ ለጥ ፋቱ ተጠያቂ እኔ ነኝ አልኩ ! ስለዚህ በእኔ ላይ በፈለገ ችው መንገድ ቂሟን ለመወጣት ትችላለች ። ግን ሰውን ውሻ ይመስል እየተከታተሉ መዞር ፣ የሰው መሳቂያና



t.me/OLDBOOKSPDF

መሳለቂያ ከሚያደርጋት በስተቀር ፣ ምን ጥቅም ያስገኝላታል ? ” አለ ሳይመን በመረረ ድምፅ ።

“ የእራሷ የሆነ ቁጭቷን የመወጫ ዘዴ ሊሆን ይችላል ”

“ አብዷለች ማለት ነው ። ከዚህ ይልቅ ለሚያይ ለሚሰማውም ቢሆን ነሸጥ የሚያደርግ እርምጃ ብትወስድ አይሻልም ነበረ ? ከፈለገች ለምሳሌ እኔን በቀላሉ ለመግደል ትችላለች ” አለ በንዴት የተከሰታተረውን ፊቱን በማዝናናት ፈገግታ እየሳየ ።

“ጨክና ይህን ማድረግ ትችላለች ብለህ ታምናለህ?” አለው ጥዋሮ ።

“ ግልፁን ለመናገር ከተፈለገ ፣ ጃክሊን ይህንን ለማድረግ እንደምትችል አልጠራጠርም ። ግልፍተኛ ናት፡ ደመ ፍሉ ናት ፡ እራሷን የመቆጣጠር ችግር አለባት ።ንዴቷ ቱግ ባለበት ወቅት የማይታሰብ እርምጃ ለመውሰድ ትችላለች።ግን ሰላይ ይመስል ሰውን እየተከታተሉ መዞርን ከርሷ በሕልሜም በውኔም የማልጠብቀው ድርጊት ነው ” ሲል፣

ጥዋሮ “ ማን ያውቃል ? ምናልባት ክትትሉ ረቂቅ የሆነ ጡሳትን የማጥፊያ ዘዴስ ከሆነ ? የብልህ አእምሮ ውጤት ሊሆን ይችላል ” አለው ፈገግ እያለ ። ሳይመን ጥዋሮን ፍዝዝ ብሎ እየተመለከተ ፣

“ ይቅሬታ መስለኝ ሙሴ ጥዋሮ ! እኔ የምናገረው የምሬን ነው፡ ሊኔትን ከመንፈስ ጭንቀት ላይ እንደጣላት አልተረዱም ? ” አለው በምሬት ፣

“ አንተንስ ?” አለው ጥዋሮ አሁንም ፈገግ እያለ ። ሳይመንም በድጋሚ ጥዋሮን በመገረም እያየ ።

“ እኔ እንኳን አላመች ብሎኝ ነው እንጂ ፣ ንንያ ቮኪካ አንገቷን እንደ ዶሮ ጠምዝዤ ላስርፋት ነበር የምፈልገው ” አለ በንዴት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ያ ሁሉ የጋለ ፍቅር በረዶ ተጫኖው ማለት ነዋ!” አለ ፑዋሮ እራሱን እየነቀነቀ ። የሳይምን ንደት እየጋለ መሄድ ጀመረ ።

“ ቢገባዎት ፡ የሊኔትን ፍቅር እውነተኛነት እንጂ፡ የጃኩሊንን መኖር እስመኖር ለማስታወስ አልፈልግም። ምናልባት ሊኔትን ለሐብቷ ስል እንደወደድኳት በማስ መሰል ሰሜን ለማጥፋት ስትል ጃኩሊን አውርታልዎት ሊሆን ይችላል ። ግን ውሸት መሆኑን ይመኑኝ ። ለገ ንዘብ ስል የወደድኩትን የምጠላ ፡ ለገንዘብ ስል የምታ ለል ሰው አይደለሁም ። በተጨማሪም ጃኩሊን ያልገባት አንድ ነገር አለ ። እኔ ማንንም ሴት ብትሆን ከመጠን በላይ እንድታስብልኝ ፡ እንድትጨነቅልኝ የምፈልግ ሰው አይደለሁም ! ” አለና በረጅሙ ተነፈሰ ።

“ እሃ ! ” አለና ፑዋሮ ሳቅ በማለት “ ፍቅር በአንደኛው ወገን ላይ ግደብ የለሽ ስሜት ሲያሳድር፡ ሌላውን ደግሞ ግን ሚዛን ጠብቆ በመጠኑ እንዲኖር የሚያደርግ ኃይል ነዋ ! ” አለ እየሸፈ ። ሳይመንማን እርር ትክን ብሎ ፡

“ እውነት መሰሉ ፑዋሮ ! እኔ ለምወዳት ልጅ እንዳለ ብላት እንድትጨነቅላት እፈልጋለሁ እንጂ ፡ እርሷ ወላጅ እናት ይመስል እንድትንተረበረብልኝ ከቶ አልሻም ! ጃኩሊን፣ መንፈሷንም አካሏንም የግሏ፣ የብቻዋ ለማድረግ የምትፈልግ ናት ። እኔ ደግሞ የቀፍድድ ታሥሬ፣ የርሷ ተራኛ ሆኜ ልመኖር የምፈልግ አልነበርኩም ። ጃኩ ሊን ከፈለገች የሳይመን ተገዢ ልትሆን ትችላለች ! ሳይ መን ግን የጃኩሊን ንብረት ሊሆን አይችልም ! ወንድ ነኝ ያሉ ሁሉ ይህንን ነጻነት ስለሚፈልግ ፡ የእኔን አባ ባር እንደማያደግፉት እርግጠኛ ነኝ ። ” ሲል ፑዋሮ ሳይ መንን ለመጀመሪያ ጊዜ ትክ ብሎ ሊያየው ጀመረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይመን ቁመናው ያማረ አጆቹም ሲበዛ መልከ መልካም ወጣት ይሁን እንጂ ፡ በአእምሮው ብስለት ፡ በአስተሳሰቡ አድማስ ስፋትና ጥልቀት ፡ ከጃኩሊንም ከሲኔትም በታች መሆኑን ጆዋሮ ተገንዝበ ። ስለዚህም የእውነት ጠባዩ ካልተገራው ሳይመን ጋር አለመናገ ሩንም ሆነ አለመከራከሩን መርጦ ዝም አለ ። ግን ዝም ታው ለሳይመን የመግባቢት ምልክት መስሎ ስለታየው በፈገግታ እየተፍንከነከ ፡

" ጃኩሊን ይህንን ባሕርዩን ለመረዳት ባለመቻሏ ለእኔ የሐሲና ዕረፍት ነስቶኝ በጣም አቅበጥብጦኝ ነበረ። ላስረዳትም ብሞክር የሚገባት ዓይነት ባለመሆኗ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን አብሬአት የቆንኩት ጊዜ አሳለፍሁ ። በሊታገሥኩም ሲኔትን አገኘሁ ። ዓለም የሰገደላትም ውብ ልጅ እኔን ደሃውን ሳይመንን መርጣ ከገባሁበት ሲኦል ውስጥ መንጥቃ አወጣችኝ ። " አለና ንግግሩ በጆዋሮ ላይ ያሳደረውን ስሜት ለመረዳት በመከጀል አየት አደ ረገው ። ጆዋር ግን አሁንም እራሱን ከማወዛወዝ በስተቀር ለመናገር ፈቃደኛ አልነበረም ። ለሳይመንም ቢሆን አሳመርኩ ብሎ ያነበነበው ዝባዝንኪ በድንጋይ ላይ የፈሰሰ ውሀ መሆኑ ቀስ በቀስ እየገባው ሄደ ። ስለዚህም የጭውውቱን አቅጣጫ ለወጥ አደረገና " ጃኩሊን ለምን እንደኔ ተጨባጩን ሁኔታ ለመረዳት እንደማትሞክር ይገርመኛል ? " አለ ። ጆዋሮ ትዕግሥት ቢያልቅም፡" እንደ አንተ ወንድ ባለመሆኗ ይሆናል ! " ሲል ፈገግ በማለት መለሰለት ።

ሳይመን ግን ቶሎ አለና " ይህንን ማለቴ እንኳን ሳይሆን ፡ ለምን ነገሮችን ቀለል አድርጋ አታያቸውም ለማለት ነበረ ። ለነገሩማ አንድ ሕመምተኛ ወደደም፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠላም የተሰጠውን መድኃኒት መውሰድ አለበት እያለ ? ፍቅር በእልህና በችኩሎነት ፣ በንትርክና በግድ የሚያሸንፉት ቀላል ስሜት አይደለም ። የጃኪሊንና የእኔ ግንኙነት ብዙም ሳይንዛዛ በአጭሩ በመቋጨቱ ዕድለኛ ነኝ ለማለት እችላለሁ !" አለ ።

ፑዋሮ እኔ ጋገሩን በዝምታ ለማለፍ ባለመፈለጉ፡“ግን ኋኔታችሁ ለመቁረጡ መቶ በመቶ እርግጠኛ ልትሆን አትችልም !" አለና የሆነ ነገር እያሰላሰለ ፡ “ ምናልባትም ለእንተ ቢመስልህ፡ለጃኪሊን ግን ያ የነበራችሁ ግንኙነት እንዲህ በቀላሉ የሚያከትምለት መስሎ እንደማይታያት ላረጋግጥልህ እወዳለሁ " አለው ።

“ ለምን ? . . . . ይማምስ ምን ማለትዎ ነው ? "አለ ሳይመን እንደ መደናገጥ ብሎ ።

“ከእጅዋ በማይለየው ቦርሳዋ ውስጥ የተቀባበለ ሽጉጥ እንዳለ አታውቅም ? " አለው ፑዋሮ ። የሳይመን ፊት ከመቅጽበት ተለዋወጠ ። እንገቱንም አቀርቅሮ ጥቂት ሲያስብ ከቆየ በኋላ የሆነ ስሜት ተሰምቶት ቀና አለና፡ “ አሁን እንኳን በዚያ ሽጉጥ ደፍራ የምትጠቀምበትእይመስለኝም ። የነበራት ወኔ እንደጉንዴቷ እየበረደ የሄደ ይመስለኛል ። አሁን አፋፍጣ የተያያዘችው ምቀኝነትን ነው ። ከእባብ የባሰች ተንኮለኛ ወጥቷታል ። ሊኔትን እያበሳጨች እያናደደች ልታጣብዳት ምንም አልቀራትም። ስለዚህም ሙሴ ፑዋሮ!ቢፈቅዱልኝና ዛሬ ላነጋግርዎት ወደ ፈለግኩበት ቀና ጓዳማ ተመልሼ ባስረዳዎት ብሞክር " ሲል በማስተዛዘን ጠየቀ ።

“ ለሌላም ጉዳይ ፈልገኸኝ ኖሯል ? በል እስቲ አጫውተኝ! ልስማህ ! " አለው ፑዋሮ ። ሳይመን ለመጀመሪያ ጊዜ እራሱን ተቆጣጥሮ ዝግ ብሎ ማውራት ጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ከጃኪሊን የምንገላገልበትን ዕቅድ ንድፌ ነበረ ። በበኩልዎም የሚኖርዎትን አስተያየት እንደሚለግሱኝ አልጠራጠርም ። እንደሚያውቁት " ካርናክ ' የምትባለዋ መረከብ አገር ለመጎብኘት የመጣነውን ሰዎች ወደ አቡሲምበል ለመውሰድ በነገው ቀን ትነሳለች ። እኔና ሊኔት ግን ሐሳባችንን በመቀየር ወደ ካይሮ ለመመለስ የወሰንን በማስመሰል እናስወራለን ። ዜናውም በዛሬዶቱ ቀን ከጃኪሊን ጆሮ የደረሰ ለመሆኑ እረጋግጣለሁ ። በተጨማሪም ሠራተኞቻችን ሻንጣችንን በማስጫን ወደ ካይሮ ለመሔድ እንዲንቀሳቀሱ አደርጋለሁ ። ጃኪሊን እንደልማዱ ልትከታተለን ስትከትናፍ ፡ እኛ ግን መንገድ በማሳበር በመርከቧ ተሳፈርን ልናመልጣት እንችላለን ። የሚያዋጣ ዕቅድ አይመስልዎትም ? " ሲል ሳይመንን መልሱን በጉጉት በመጠባበቅ ጠየቀ ።

ፑዋሮ አሰብ አደረገና " ዕቅዱ ደህና ነው ፡ መሸሻችሁም ባልከፋ ነበረ ። ግን ጃኪሊን እንዲህ በቀላሉ የምትታለል ልጅ አይመስለኝም " አለው ። ሳይመን ተስፋ በመቁረጥ እጆቹን ያወናጭፍ ጀመረ ። " ከእቡ ሲም በሏ ቀጥለን ካርቱም ፡ ከካርቱም ኬኒያ ፡ ከኬኒያ ወደ አገራችን በአውሮፕላን ብንበርስ ?" አለ ሌላ አማራጭ እየፈለገ ።

ፑዋሮ ሳቅ ብሎ " እናንተን የሚወስደው መርከብ እናንተን የሚጭነው አውሮፕላን ጃኪሊንን ለይቶ አላሳፍር ይል ይሆን ? " ሲለው ሳይመን እያጉረመረመ " እንግዲህ ምን ተሻለን ? ወይንም እኮ ያበጠው ፈንድቶ በለየለት መልካም ነበረ ። ይቺን የሚያመዛዝን መዘዘኛ ፍጥረት በምን ቀን አጋጠመችኝ ይሆን ? " ሲል ፑዋሮ እረጋ በማለት " ማመዛዘን እስክትጀምር ድረስ በትዕግሥት መጠበቁ ሳይሻል ይቀራል ብለህ ነው ፡ይል



t.me/OLDBOOKSPDF

ቂት እጠይቅሃለሁ ስለ የነበረውን ጉዳይ አንተም አስታ ወስኸኝ ። ያ ከአንተና ከሲኔት ጋር የማይለየው ረጅም ሸ በጉ ሰውዬ . . . . . . . . . . .”

“ ፔኒንግተንን ነው ? ” አለ ሳይመን ፈጠን አለና፣

“ መሰለኝ ፤ ግን የሚገነው ከእናንተ ጋር ነው ?” አለና አሁንም ጭዋር ጠየቀው ።

“ አዎን ! ሰውየው አሜሪካዊ ቢሆንም ለሲኔት ሞግዚት ሆኖ እንዲያሳድጋት ፤ ለአቅመ ሔዋን እስክት ደርስም በሚሊዮን የሚቆጠር ሐብቷን በበላይነት እን ዲያስተዳድር አባቷ በጽሑፍ ኑዛዜው የወከለው ነው። ግን እንደአጋጣሚ ካይሮ ላይ ከተገናኘን ወዲህ ከእኛ ሊመለየት አልፈለገም ” አለ ሳይመን ።

“ ለምን ? ድንገት ሲኔት ስለጃኩሊን አደገኛነት አሜውቃው ይሆን ? ” አለ ጭዋሮ አሁንም ምሥጢሩን ለማወቅ ያለው ጉጉት እየጨመረ ።

ሳይመን ግን “ በፍጹም አልነገረችውም ! እርግ ጠኛ ነኝ ” ሲል እራሱን ጭምር በኃይል በማወዛወዝ መለሰ። “ በእኔና በሲኔት ግምት የጃኩሊን ክትትል ካይሮ ላይ የሚያቆም መስሎን ነበረ ።” አለ ።

“ ማቆም አልከ ? ” ሲል ጭዋሮ ተገረመ “ ገና ምኑ ተጀመረና ፤ ገና ምኑ ተነካና !” ሲለው ሳይመን በን ደዱ በመጋየቱ ጭዋሮን ብቻውን በአስዋን ከተማ መሀል ጥሎት ሄደ ።

ጭዋሮ ግን በቅድሚያ ከሲኔት ፤ ከዚያም ከጃኩሊ ንና ዛሬም ከሳይመን የሰማቸውን ታሪኮች በአእምሮው እያብላላ ፤ ወደ ሆቴሉ በማዝገም ተመለሰ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ 4

በ"ካታራክት" ሆቴል ሰፍረው ለነበሩት አገር ጎብኝዎች የሚቀጥለው የጉዞ ምዕራፍ የአቡ ሲምበል ጥንታዊ የታሪክ ሥፍራ ነበረ ። እነፖዋሮም 'ካርናክ' በምትባለዋ መለስተኛ መርከብ ተሳፍረው ለሁለት ቀናት ያህል እንደተጓዙ አንዲት የሞተር ጀልባ በታላቅ ፍጥነት እየከነፈች ስትከታተላቸው ታየ ። ፖዋሮም የሆነ መንገደኛ ይዛ መምጣቷን ገመተ ። ጀልባዋም መርከቧን በመታከል ካለቀመች በኋላ አንድ ሰው ወደ መርከቧ ተሻግሮ ተሳፈረ ። መንገደኛውም ኮሎኔል ሬስ መሆኑን ፖዋሮ እንዳረጋገጠ ለጊዜው ግራ ቢጋባም ውስጥ ውስጡን ተደስቶ ነበረ ።

" ካርናክ " በእንፋሎት ኃይል የምትንቀሳቀስ ፣ በሶስት እርከኖች የተከፋፈለች መርከብ ናት ፤ የታችኛው እርከን ወይንም የምድር ቤቱ የተራ መንገደኞችና የመርከቧ ሠራተኞች መኝታ ክፍል የሚገኝበት ሲሆን ፤ የመሀሉ ወይንም ሁለተኛው እርከን ሀብት ላላቸው የተከለለ ክፍል ነበረ ። የመርከቧ ሳሎንና ምግብ ቤት እንደዚሁም በብረት የታጠረው የመናፈሻው ሥፍራ ደግሞ የሚገኙት በላይኛው ወለል ወይንም በሶስተኛው እርከን ላይ ነበረ ።

ኮሎኔል ሬስና ሙሴ ፖዋሮ ተመሳሳይ በሆኑ የስለላና የምርመራ ሥራዎቹ ላይ ተደጋግሞ በመሠማራታቸው ለአረጅም ጊዜ የቆየ ጓደኝነት አትርፎላቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበረ ። ሆኖም የአሁኑ ያልታሰበ ግጥምጥሞሽ ሁለቱንም ሰዎች አስገርሟቸዋል ። ሬስና ፑዋሮ ከመርከቢ ላሉን ውስጥ ጥግ ቦታ መርጠው ከተቀመጡ በኋላ የቀረበላቸውን የብርቱካን ጭማቂ እየጠጡ ጭውውት ጀመሩ ።

" ጥንታዊውን የአቡ ሲምበልን መቅደስ እንደአኛው ለመጎብኘት የመጣህ ይመስለኛል ? " ሲል ፑዋሮ አስቀድሞ ተናገረ ።

"አመጣጤ እንኳን እንደታደሉት ሰዎች የታሪክ ሥፍራዎችን ለመጎብኘት ሳይሆን በዚች መርከብ ላይ ያተኮረ ምርመራ ለማካሄድ ነው " ሲል ሬስ ፈገግ እያለ መለሰ ።

" በመርከቢ ላይ ስትል በተጓዦቹ ላይ ማለትህ ይመስለኛል ?" አለ ፑዋሮ ።

" በአንድ ተጓዥ ላይ ብቻ ነው " ሲል ሬስ መለሰ።

" የትኛው ሊሆን ይችላል ? " አለ ፑዋሮ ራሱን ወደ ላይ እንጋጦ እያሰላሰለ ።

" ባይገርምህ እኔም አላውቀውም " ብሎ ሬስ ሲናገር ፑዋሮ በመደናገርና በመጠራጠር ዓይኖቹን በሬስ ላይ አሳረፈ ። ሬስም ነገሩ ስለገባው " ከአንተ የምደብቀው ምሥጢር እንደማይኖር ታውቃለህ ። በዓለም ውስጥ ተሠራጭተው በሚገኙት የከበርቴ ይዞታዎች ላይ ያልታሰቡ አደጋዎች በመደጋገም እየደረሱ ነው ። በየፋብሪካው ለተፈጠሩት የሥራ ማቆም አድማዎች ከበስተ ጀርባ ሆነው የሚገፋፉትን ሰዎች ለጊዜው አንፈልጋቸውም ። አማጺፈው ተልዕኮአችን ግን በአንዳንድ የኢኮኖሚ አውታሮች ላይ ፈንጂዎች እየቀበሩ አያሌ ንብረቶችን የሚያጋዩትን አደኖ ለመያዝ ነው ። ቀንደኞቹ አደጋ ጣዮች ስድት መሆናቸውን ደርሰንበታል ። አንደኛው እጁን ለመስጠት ባለመፈለጉ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ ወቅት ገድለነዋል ። ሁለተኛውም ወደ እሥር ቤት ተልኳል ። ልናገኘው ያልቻልነው ሶስተኛውን ወንጀለኛ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

ያ ሰው ከሌሎች ሌሎች ከባድ ጥፋቶች ጐን የስድስት ንጹሐ
ን ሰዎችን ደም በግፍ አፍስሷል። ከተደበቀበት ከግብጽ
አገር ሆኖ ከአንዳንድ ግብረ አበሮቹ ጋር ያደርገው የነ
በረው የጽሑፍ ግንኙነት ከመረጃ ክፍላችን እጅ ወድቋል።
በምሥጢር የተጻፈውም ደብዳቤ በባለሙያዎች ሲነበብ
ምን የሚል መልእክት አዝሎ ተገኘ መሰለህ ? ” አለና
ፑዋሮን ለጥቂት ጊዜ አየት ካደረገው በኋላ ፡ 'እራሴን ለጥ
ቂት ጊዜ መደበቅ ስለሚኖርብኝ ፡ 'ካርናክ' በምትባ
ለዋ መርከብ ላይ ከሚጓዙት አገር ጎብኝዎች ውስጥ
አንዱን በመምሰል ለሚቀጥሉት ሰባት ቀናት እጓዛለሁ'
የሚል መልዕክት ደብዳቤው እንዳዘለ ታውቋል ። ስለዚ
ህም ከለንደን በአውሮፕላን ካይሮ ከደረስኩ በኋላ ፡ ካር
ናክን ለመታከል በሞተር ጀልባ ስከንፍ መጣሁ።” በማ
ለት ሬስ ከመናገሩ ፡
“ ስለ መልኩ ቅርጽና ስለቁመናው የምታውቀው
ነገር አለ ? ” ሲል ፑዋሮ ፡ ጠየቀው ።
“ የለም ፡ ግን የዘር ሐረጉ ከአሜሪካ ፣ ከአየር ላንድ
ና ከጀርመን የተቀየጠ ነው ። የእንደዚህ ዓይነት ሰው
መልክና ቁመና ምን እንደሚመስል መገመት ያስቸግ
ራል ። ወጥፎ ዓይነት አከላለስ ነው።” ብሎ ሬስ ሳቅ
አለና “ ለመሆኑ በአንተ አመለካከት ምናልባት በመር
ከቧ ላይ የምትጠረጥረው ሰው አጋጥሞህ ይሆን ? ”
አለና ሬስ በተራው ጠየቀ ።
የሚሰጠው መልስ ትክክለኛ መሆኑን እርግጠኛ
እስካልሆነ ድረስ ፡ የግምት አስተያየት መሠንዘር የማይ
ወደው ፑዋሮ ፡ “ካልተጣደፍን የምንጠረጥረው እናገኛለን ፡ ”
ሲል በደፈናው መልሶለት ፡ “ ለጊዜው ግን በዚች መር
ከብ ውስጥ ሌላም አደጋ እያንዣበበ ነው ። እኔም ወን
ጀሉ እንዳይፈፀም በተቻለኝ አቅም እየተከታተልኩን
ኝ ” አለና ወደ ሬስ ጠጋ በማለት “ ምሥጢሩን እራ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስህ ልትደርስበት ትችላለህ ። ታሪኩን ግን በምሳሌ አደርጌ በአጭሩ አጫውትሃለሁ ።" ብሎ ንግግሩን ቀጠለ።

" ሀ ብዬ የምጠራው ሰው ለ ብዬ በሰየምኩት ሰው ላይ ከፍተኛ በደል ፈጽሞበታል ። ለ ቁጭቱን ለመወጣት ቆርጦ ተነስቷል ። የበቀል ዛቻም አሰምቷል።" ሲል ሬስ አቋረጠውና " ሀ እና ለ በዚች መርከብ ላይ አብረው እየተጓዙ ነው ማለት ነው ? " አለው ።

" አዎን !" አለና ፑዋሮ ሲመልስለት :

" በእኔ ግምት ለ ብለህ የሰየምካት ሴት ሊኔትን አትቀርም !" አለና ሬስ ሲጋራውን አያያዘ ።

" ትክክል ነህ ! ታዲያ በቅድሚያ የሚገቡቱ ሰዎች እንዲህ በሥራ እንደማይተረጎሙት አንተም እኔም ብዙ ጊዜ ከሥራ ልምዳችን ያየነው ነው ። በተለይም ደግሞ ሴቶች" አለና ፊቱን ኮስተር አድርጎ ለጥቂት ጊዜ ዝም ካለ በኋላ " ግን እጅግ ያሳሰበኝ ነገር ቢኖር በትናንትናው ዕለት ሀ ያልኳት ሴት ከሞት አደጋ ለጥቂት አመለጠች " አለው ።

" እንዴት ? እንደፎከረች ልትገላት ! " ሲል ሬስ ጣልቃ ገባና ጠየቀ ።

"ይህማ በሆን ኖሮ ነገሩ ሁሉ ቀለለ ማለት ነበረኖት ውስብስብ ጉዳይ የሆነብኝ ግን ፎካሪዋ በአካባቢው አለመኖሯ ነው። እጅዋም እንዳልገባበት ግልጽ ነው" አለፑዋሮ ።

" እንግዲያውስ ማንንም እየተኑማ ሊገድላት የሚፈልግ ከሆነ፤ ይቺ ሀ ያልካት ሴት የከፋች ፍጥረት መሆን አለባት ማለት ነው ።" ሲል ሬስ አስተያየቱን ሰጠ ።

" በተቃራኒው፤ ውብና የደስ ደስ ያላት፤ ሀብታምና ወጣት ሴት ወይዘሮ ናት" አለና ፑዋሮ "ይህ ሳያንስ ደግሞ አንተም በበኩልህ ሌላ ተጨማሪ ችግር ይዘህ መጣህ፤ በመርከቧ ላይ ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ እንዳለ ነገርከኝ" ሲለው፤



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮዛሊ በተራቸው ወደ ምግብ ቤቱ ውስጥ ገቡ ። ሚስስ ሁተርቡርን አጭር ቁመትና ዕድሜዋ ወደ ሃምሳ ዓመት የተጠጋ ፤ ፊቷ የተጨማደደ ፤ ሁለንተናዋ የማይማርክ ቢሆንም ሴትዮዋ ፤ ልጅዋ ሮዛሊ ግን በገጿ ላይ ከሚነበበው የሐዘንና የትካዜ መልክ በስተቀር ፤ መልክ መልካምና ሰግላጋ ወጣት ነበረች ።

በምግብ ቤቱ ውስጥ ቀድመው የገቡት ሁሉ ዓይናቸው በበሩ ላይ ተሰክቶ ለጥቂት ጊዜ ቆረ ። ውቢቷ ሊኔት እንደ ፀሐይ እያበራች በሳይመንና በሞግዚቷ በፔኒንግተን ታጅባ ገባች ። እርሷም ለሁሉም እጅ እየነሳች አልፋ አንድ ጠረጴዛ ስትመርጥ ፤ ሳይመን ተሽቀዳድሞ ወንበር ከሳበላት በኋላ ተቀመጠች ። ሳይመንና ፔኒንግተንም ቦታ ቦታቸውን ያዙ። እንግሊዛዊው ፋንትሮፕም ፤ ከነርሱ ተከታትሎ በመግባት አጠገባቸው ካለው ጠረጴዛ ተቀመጠ ። ፋንትሮፕ ፤ በአለባበሱም በአድራጎቱም ንፅሕናና እርጋታ የሚታይበት ወጣት ሲሆን ብዙውንም ጊዜውን የሚያሳልፈው መጽሐፍ በማንበብ ነበረ ።

በመጨረሻም የደረሰችው ጃክሊን ናት ። ስታለቅስ የዋለች ይመስል አይኗ ሁሉ ቀልቷል ። አንገቷንም እንዳቀረቀረች ለብቻዋ አንድ ጠረጴዛ መርጣ ተቀመጠች ። ቀስ በቀስም ቀና ብላ ዙሪያዋን ማየት ስትጀምር የእርሷና የሙሴ ፑዋሮ ዓይኖች ተገናኙ ። በቃል ባይገልጽላትም ፑዋሮ ለእርሷ የሚሰማውን ሐዘንና ቁጭት በዓይኖቹ አስተላለፈላት ። እርሷም ገብቷት ስለነበረ አንገቷን ከአንድም ሁለት ጊዜ ጉንበስ በማድረግና ፈገግ በማለት ምስጋናዋን ለመግለጽ ሞከረች ። ኮሎኔል ሬስም በፑዋሮና በጃክሊን መካከል ጥልቅና ስሜት የሚነካ የምልክት ልውውጥ ሲደረግ እየተመለከተ ፤ ፑዋሮ ቀደም ብሎ ባጫወተው ታሪክ ውስጥ ለ ብሎ የሰየማት ልጅ ማን እንደሆነች ለመገመት ቻለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

ከመርከቧ ተሳፋሪዎች ብዙዎቹ በጊዜ እራታቸውን እየበሉ ወደ መኝታቸው እምርተዋል ። ሰሌቱ ከሌሎች ቀናት ይልቅ በጣም ሞቃት ሆኖ ከመዋሉም ሌላ የአቡ ሲምበልን መቅደስ ለሁለተኛ ጊዜ ተዘዋውረው በመጐብኘት በዚያ ኃይለኛ የፀሐይ ሐሩር ተቀቅለው ስለነበረ ፥ ተደካክመዋል ። በመርከቢቱ ሳሎን ውስጥ ፈንጠር ብሎ ተቀምጦ የነበረው ወጣት ፋንትሮፕ ግን መጽሐፍ ያነብ ነበረ ፤ እንደዚሁም ሲኔት፥ሳይመን፥አሜሪካዊ ፔኒንግተንና ኮሎኔል ሬስ በአንዲት ጠረጴዛ ዙሪያ ካርታ ሲጫወቱ ፥ ሄር ኩሊ ፑዋሮ ግን ከአንድ ሶፋ ላይ ጋደም ብሎ በመደጋገም ያዛጋ ነበረ።የንሲኔት ካርታ ጨዋታ አሳልቆ ስላለው ፑዋሮ ቀስ ብሎ ተነስቶ ወደ መኝታ ክፍሉ ማዝገም ጀመረ ። የሳሎኑን በር ወጣ እንዳለም ጃኪሊንን ብቻዋን አጠገቡ ቆማ አግኝቷት ሰላምታ እንደተለዋወጡ ፤

"እንቅልፍዎ መጣብዎት መሰለኝ ፥ ሙሴ ፑዋሮ?" ስትል ጠየቀችው ።

"አዎን ፤ እንደዛሬ ከብዶኝና እንቅልፍ ተጫጭኖኝ አያውቅም ። ምናልባትም የአየሩ ሁኔታ ይሆናል ።" ብሎ አለፏት ሊሄድ ሲል ፤

" እውነትም የቀፈፈና የተረገመ ቀን ! መኖርን የሚያስጠላ ፤ ሕይወትን ለማጥፋት የሚገፋፋ . . . ." እያለች በሐዘኔታ ስትናገር ፑዋሮ ዞር ብሎ ተመለከታት።



t.me/OLDBOOKSPDF

የጃኩሊን ዓይኖች በዓይኑ ላይ ሲያርፉ፣ከሆን አደጋ እን
ዲያስጥላት የሚለማመጡ፣የሚለምኑ ይመስሉ ነበረ ።
ዮም አመለካከት በጭዋር ሕሊና ውስጥ ተቀርጾ የማይ
ረሳው ሆነ ።

በሳሎኑ ውስጥ የቀሩት አራቱ ካርታ ተጫዋቾች
አሁንም በከፍተኛ ፉክክር ላይ ነበሩ ። እንደዚሁም በሚ
ያነበው መጽሐፍ ተመስጦ የነበረው ፋንትሮን ከተቀ
መጠበት መቀመጫ ንቅንቅ አላለም ። እንቅልፍ በዓ
ይና አልዞር ያላት ኰርኔሊያ ከአክስቷ ጋር ከምትተ
ኛበት መኝታ ክፍል ተሰርቃ ወጥታ ወደ ሳሎኑ በመግ
ባቷ የሆኑ መጽሔቶችን ማገላበበጥ ጀምራለች ።

ከጥቂት ጊዜም በኋላ የሳሎኑ በር ቀስ ሲል ተከ
ፍቶ ጃኩሊን ራቷን እንዳከላተረች ገባች ። ከዚያም
ማራፍ ቀሚን ማትራ ከኰርኔሊያ አጠገብ ከነበረው ወን
በር ላይ ተቀመጠች ። ደወልም በመደወል የመርከቧን
አስተናባሪ ጠርታ አጥፍ ጂን እንዲያመጣላት ከአዘዘች
በኋላ፣ዓይኖቿን ካርታ ወደሚጫወቱት ሰዎች አቅጣጫ
አተኮረች ።

የመጣላትንም ጂን በአንድ ትንፋሽ ጨልጣ ሌላ
አጥፍ ጂን እንዲመጣላት ስታዝዝ ሳይመን ሁኔታዋ ስላላ
ማረው አፍጦ ሊያያት ጀመረ ። በተራውም የጀመረ
ውን የካርታ ጨዋታ መጫወቱን ስለረሳ፣ሊኔት ጉሸም
አድርጋ "የማትፈልገውን ካርታ ጣል እንጂ፣እየጠበ
ቅንህ ነው" አለችው ። ጃክሊን ሁለተኛው ዙር ጂን
እስኪመጣላት ድረስ የሆነ የሙዚቃ ዜማ እያንጎራ
ጎረች ቆይታ ብርጭቆውን በማንሳት "ሞት ለግፈኞች!"
ብላ አሁንም በአንድ ትንፋሽ ጨልጣ ለሶስተኛ ጊዜ አዘ
ዘች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

የሳይመን ዓይን አሁንም ከርቧ ላይ አልተነቀለም ነበረ ። የካርታውንም ጨዋታ የቀጠለው በግማሽ ልቡ ነው ። ጃኩሊን በማከታተል የጠጣችው ጂን ሞቅ እያደረጋት ሲሄድ ታዜመው የነበረው ዘፈን በሳሎኑ ውስጥ መሰማት ጀመረ ።

“ አረዳት ! ገደላት ! በቁሟ ቀበራት !

“ የእኔ ነህ ስትለው በሌላ ለወጣት . . . ”

ሲኔት ይህንን ጊዜ “ ይቅርታ አድርጉልኝ ፤ እንቅልፍ እየተጫጫነኝ ነው ” ብላ በእጅዋ የያዘቻቸውን ካርታ በጠረጴዛው ላይ አስቀምጣ ተነሣች ። ኮሎኔል ሬስና ፔኒንግተን እንደርሷው ወዲያውኑ ብድግ ብለው ተከታትለዋት ሲወጡ ፤ ሳይመን ተለይቷት ለሆነ ነገር ወደ ኋላ ቀረ ። እርሱም መጠጥ እንዲመጣለት አዞ እስከ ዚያው አንድ መጽሔት በማንሳት አቀርቅሮ መመልከት ጀመረ ።

ኮርኔሊያም በበኩሏ ለመሔድ ስትነሣ ፤ ሞቅ ብሏት የነበረችው ጃኩሊን እጅና እጅዋን ይዛ “ እባክሽ ጥለሽኝ አትሂጂ ! ይህ ምሽት የመጨረሻዬ ሊሆን ስለሚችል ብቻዬን አትተይኝ ! ” እያለች ተለማመጠቻት ። ኮርኔሊያም ተመልሳ ተቀመጠች ።

ጃኩሊን ግን አሁንም ስስተኛውን ዙር ጂን እያጋባች ፤ ያለፈውን ታሪኳን በመዘክዘክ ትተርክ ጀመረ ። ታሪኩ ማለቂያ የሌለው ስለነበረ ኮርኔሊያ እየተቁነጠነጠች ደግማ ለመሔድ ስትነሣ ጉትታ አስቀምጣት ፤ በተሳሰረ አፍና በተገመደ ዓረፍተ ነገር እንደምንም የጀመረችውን ወሬ ጨርሳ ወደ ሳይመን ዞር አለችና ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

" ሌላ ጂን ስለምፈልግ አዘዝልኝ!" ስትል ከእሱህ ጋር ተናገረችው ። ሳይመንም ይመለከክት የነበረውን መጽሔት ወደ ጐን አድርጎ ፡

"አስተናባሪዎቹ ተኝተዋል ። እኩለ ሌሊት ሆኗል" አላት ዝግ ብሎ ።

" ነግሬሃለሁ ! ሌላ መጠጥ እፈልጋለሁ ነው የምለው !" ስትል ጮኸችበት ።

" ጃኩሊን ! የጠጣሽው ይበቃሻል " አለ ቁጾ ቷን ለማብረድ እየሞከረ ። እርሷ ግን " ስሜን እንድ ትጠራው አልፈልግም ! ደግሞስ አንተ ነህ የእኔን ፍላ ጎት የምትወስነው ?" ስትል አምባረቀችበት ።

" አይደለሁም " አለ ሳይመን በተለመደ የረጋ አነ ጋገሩ ። ከዚያም ለአንድ ሁለት ደቂቃ ያህል ዝምታ ሰፈነ ። እርሷም ትኩር ብላ ስትመለከተው ከቆየች በኋላ ፡

" ትንቀጠቀጣለህ መሰለኝ ፡ ፈራህ እንዴ ? " አለ ችው በንቀት ዓይን እያየች ።

ሳይመን ግን ምንም ሳይመልስላት ያስቀመጠውን መጽሔት አንስቶ መመልከት ጀመረ ። እርሷም ተንደ ርድራ ሄዳ መጽሔቱን ከእጁ ላይ መንጭቃ ከወረወ ረች በኋላ ፡

" ውድ ሳይመን ! ከፈራህ መከለል ያለብህ በብ ጣሽ መጽሔት አይደለም ! ከሊኔት ብብት ሥር ብት ደበቅ ይሻልሃል !" እያለች ታሾፍበት ጀመረ ።

" ለምን የሰው መሳቂያ ትሆኛለሽ ጃኩሊን ? ይልቁ ኑስ ሄደሽ ብትተኚ አይሻልም ? " አላት ሳይመን ሲ.ዶግ ባባት የቻለውን ያህል እየሞከረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እንድትለማመጠኝ አልፈልግም !። ከፈለግህ ሂድና ሚስትህ ቁም ሣጥን ውስጥ አስገብታ ትቆልፍብህ !” ስትለው ፡ እስከአሁን ከመጽሐፉ ጋር ተጣብቆ የነበረው ፋንትሮፕ የሚሰማው ሁሉ ስለቀፈፈው ሰዓቱን አየት አድርጎ እንቅልፍ እንደተጫጫነው ሰው በማስመሰል አፉን እያዛጋ ወጣ ። ኰርኒሊያ ግን ምንም ዓይነት ጭቅጭቅ ስትሰማ የመጀመሪያዋ ጊዜ ስለነበረ የሚሆነውን ሁሉ ፈዛ ትመለከት ነበረ ።

ጃክሊን አሁንም በሳይመን ላይ እንዳፈጠጠች “ አንተ ደደብ አህያ ! በእኔ ሕይወት ተጫውተህ የመኖር ዕድል ያለህ ይመስልሃል ! ” አለችው እልህ እየተናነቃት ። “ እንደምገድልህ አስጠንቅቄሃለሁ ! አንተ ግን አሁንም ቢሆን ደፍሬ የማደርገው አልመሰለህም ። ከየጋባህ የሰው ንቀትህ !” ብላ እጅዋን ወደ ቦርሣዋ ውስጥ በማስገባት ያቺን የማትለያትን ትንሽ ሽጉጥ አውጥታ “ እንደ ውሻ እገልሃለሁ ! ከውሻ የባሰክ ልክስክስና ከሐዲ ነበርክና ! ” ብላ ወደርሱ አቅጣጫ ስትደግንበት ሳይመን በቅጽበት ከተቀመጠበት ተነስቶ እጅዋን ለመያዝ ሞከረ ። በመሐሉ ምላጩን ስባው ስለነበረ ሳይመን ተሽከርክሮ ከተነሳበት ወንበር ላይ ተመልሶ ወደቀ ። ኰርኔሊያ እየጮኸች ከሳሎኑ እሮጣ ስትወጣ ከበረንዳው ላይ ቆሞ የነበረውን ፋንትሮፕን አግኝታ ኖሮ ፡

“ ገደለችው ! ገደለችው ! ” እያለች ታለቅስ ጀመረ። ሁለቱም ተሯሩጠው ወደ ሳሎኑ ተመልሰው ሲገቡ ፡ ሳይመን በወንበሩ ላይ እንደተጋደመ ፡ ሱሪው ቀስ በቀስ በደም እየተጥለቀለቀ ሲሄድ አዩ ። ጃክሊን ግን በቆመችበት ድርቅ ቅርቅ ብላ ነበረ ። ዓይኖቿም በእንባ እንደተሸፈኑ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ልገድለው አልነበረም አምላኬ ! የፈለግኩት ላስ ፈራራው ብቻ እንደነበረ አንተ ታውቀዋለህ !” ስትል በሚንቀጠቀጠው እጅዋ ይዛት የነበረችው ያቺ ሽጉጥ ወደ መሬት ወደቀች ። ጃክሊንም ሽጉጡን በንዴት በሚገማዋ መታ ወደ ሶፋ ሥር አሽቀንጠረቻት ።

ሳይመን ከተጋደመበት ወንበር ላይ ሆኖ በተዳከ መና በጐረነነ ድምጽ ፡ “ ፋንትሮፕ ! እባክህን ሰው እየ መጣ ነው መሰለኝ ። በሩፋን ዝጋውና ምንም እንዳል ተፈጸመ አስመስልልኝ ። ይህንን ጉድ ማንም ቢሆን እን ዲያውቀው አልፈልግም ፡” እያለ ይለምን ጀመረ ።

ፋንትሮፕም “ አይዞህ አትፍራ ! ሁሉም ተደኅክ መው ተኝተዋል ። የተኩሱም ድምጽ እንስተኛ ስለነበረ በቀላሉ ሌላ ምክንያት መፍጠር እያቅተን ” ። ” ሲል አረጋጋው ።

ጃክሊን ግን “አምላኬ ! ምነው ለእኔ ባደረግከው ? ምንስ በድዬ ይሆን ? የፈጠርከኝ ሌላ ሰው ገድዬ የራ ሴንም ሕይወት በእጄ እንዳጠፋት ነበረን ? ” እያለች ታነባው ነበረ ። እርግናኗም ኮርኔሊያ እቅፍ አድርጋ ይዛት “ አይዞሽ የእኔ እመቤት ! አይዞሽ !” እያለች እር ቧም እንባዋን በማፍሰስ ልታጽናናት ሞከረች ።

ሳይመን ግንባሩ በላብ ተጥለቅልቆ ከተኛበት ወንበር ላይ እንዳለ ፡ “ እባካችሁ እርሷን ውሰዱልኝ ! ከዚህ ክፍል ውስጥ አስወጧት ! ” እያለ ሁለቱ ንም ይለማመጥ ጀመረ ። “ ወደ መኝታ ክፍሏ ውሰዱልኝ ! ብቻዋን ግን እንዳትተዋት ! ለእኔም የተቻለውን የሕክምና እርዳታ እንዲያደርግልኝ ዶክተር ቤስነርን ጥሩልኝ ። ወሬውን ግን ሊኔትም ቢሆን በዛሬው ቀን እንዳትሰማ ። ድካምና ንዴት



t.me/OLDBOOKSPDF

ሲፈራረቁባት ስለከረመ ፡ ሌላ ተጨማሪ ዜና አይድረሳት።
ዛሬ እንኳን የሰላም እንቅልፍ ወስዷት ባይሆን ሲነጋ ታረ
ዷታላችሁ። አደራችሁን!” በማለት ቁርጥ ቁርጥ በሚለው
ትንፋሹ በመናገሩ ዓይኖቹ ተከደኑ ።

የሳይመን ጭንቀት የገባቸው ፋንትሮፕና ኮርኔሊያ
ጃኩሊንን ደጋግፈዋት ወደ መኝታ ክፍሏ ወሰዷት ። ለቅ
ሶዋ ግን አላቋረጠም ነበረ ። እርሷም ፡ “ ምነው ለእኔ
ባደረገው ? በሞትኩኝ ! ያለሳይመን ለመኖር ስለማል
ችል እራሴን ከዓባይ ወንዝ ውስጥ ልወርውረው !
ልቀቁኝ ! የአዞዎች እራት ሆኜ ልቅር ! ” እያለች
ትታገላቸው ነበረ ።

ፋንትሮፕ ፡ የዶክተር ቤስነር ረዳት የሆነችውን አስ
ታማሚ እንድትጠራለት ኮርኔሊያን ልኮ ፡ እርሱ ግን
ጃኩሊን እራሷን አደጋ ላይ እንዳትጥል መጠባበቅ
ጀመረ ። ጃኩሊን ከእጁ ለማምለጥ ብዙ ጊዜ ብትሞክ
ርም ፋንትሮፕ እንደምንም ሊያሸንፋትና በምክርም ሊያ
በርዳት ቻለ ። አስታማሚዋም ሚስ ባወርስ እንደደረሰ
ችለት ፡ ፋንትሮፕ ፡ ዶክተር ቤስነርን ለመቀስቀስ እየተቻ
ኮለ ሄደ ።

ሳይመን የተመታው ከጉልበቱ ላይ ነበር ። ብዙ
ደም ፈሶታል ። አጥንቱም ተሰብሯል ። ስለዚህም ዶክተር
ቤስነርና ፋንትሮፕ ጥቂት ከተመካከሩ በኋላ ፡ ምሥጢ
ሩን ለመሸፈንም ሆነ ፡ ሆስፒታል ከሚገኝበት ከተማ
ደርሰው የተሻለ የሕክምና እርዳታ እስኪሰጠው ፡ ሳይ
መንን በዶክተሩ መኝታ ክፍል ውስጥ ለማቆየት ተስ
ማሙ ። ለሁለትም ተሸክመው ወስደው ከዶክተር ቤስ
ነር አልጋ ላይ አስተኙት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከአሥር ደቂቃ በላይ ካልፈጀ ቀዶ ጥገና በኋላ ከሳይመን ጉልበት ውስጥ ተሸንቅራ የነበረችው ጥይት ወጣችለት። እንቅልፍም እንዲያሸልበው የእንቅልፍ መርፌ ሊወጋ ሲል ሳይመን አንድ ነገር ትዝ አለው ። ይኸውም የቆሰለባት ሽጉጥ ከሳሎኑ ውስጥ እንደቀልድ ከሶፋ ስር መወርወሯ ነበረ ። ስለዚህም ፋንትሮፕ ሽጉጧን ፈልጐ ለዶክተር ቤስነር እንዲሰጠው ልመና ካቀረበ በኋላ አንቀላፋ ። ለጃክሊንም ቢሆን ተመሳሳይ የእንቅልፍ መርፌ በሚስ ባወርስ አማካይነት ተሰጥቷት ኖሮ እርሷም ለብዙ ጊዜ ተለይቷት በነበረው ጤናማ እንቅልፍ ተውጣ ነበረ።

ፋንትሮፕ ሽጉጧን ለማምጣት ወደ ሳሎኑ ከሄደ ከአምስት ደቂቃዎች በኋላ ተመልሶ መጥቶ ፡

" ሽጉጧን ላገኛት አልቻልኩም ፡ ዶክተር ! " ሲል ለቤስነር ነገረው ።

" እንዴት ? " ሲል ፡ ዶክተሩ ጠየቀ ።

" ከጃክሊን እጅ ላይ እንደወደቀች በሚማዋ መታ ከሶፋ ሥር ከታው ነበረ ። አሁን ብፈልግ አጣሁት " አለ ፋንትሮፕ ፡

'ማንወስዶት ሊሆን ይችላል?' ብለው ሁለቱም ግራ ቢጋቡም ለነገሩ እስከዚህም ክብደት ስላልሰጡት ወደ የመኝታቸው አመሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ሰባት

ሄርኩል ፑዋሮ ጢሙን ተላጭቶ በፊቱ ላይ የነበረውን የሳሙና አረፋ በፎጣ እያደራረቀ እንዳለ የመኝታ ክፍሉ በር በኃይል ተደጋግሞ ተንኳኳ ።

ፑዋሮም ያልታሰበ ችግር እንደተፈጠረ ተረድቶ በሩን በመቻኮል እንደከፈተ ኰሎኔል ሬስ መልኩ በድንጋጤ ተለዋውጦ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ገባ ። በሚርገበገብም ድምፅ ፡

“ የፈራኸው ደረሰ ፑዋሮ ! እንዳሠጋኸው ገደሏትና አረፉ ! ” ሲል መርዶ ሊያረዳው ጀመረ ።

“ ማንን ነው የገደሉት ? ማን ናት የሞተችው ? ” አለ ፑዋሮ ትክክለኛውን ዜና ለመስማት እየተጣደፈ ።

“ አንተስ በደመንፍስህ አውቀኸው ኖሯል ። ሌሊቱን መሆን አለበት ፡ ሊኔትን በሽጉጥ ገደሏት ! ” ሲለው ፑዋሮ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ምድርና ሰማዩ ዞረበት ፡ የሰማውንም ፈጽሞ ማመን አልቻለም ። አንድ ነገር ብቻ ትዝ አለው ። ወደመኝታ ክፍሉ ሊሄድ ሲል ጃኩሊን ተናግራው የነበረው በሕሊናው ውስጥ ደግሞ ደጋግሞ ደወለ ። “ እውነትም የቀፈፈና የተረገመ ቀን ! መኖርን የሚያስጠላ ፡ ሕይወትን ለማጥፋት የሚገፋፋ ... ” ብላ የተናገረችውና ፡ ዓይኖቿም በዓይኖቹ ላይ ሲያርፉ ከሆነ አደጋ እንዲያስጥላት የምትለማመጠው የመሰለው ትውስ አለው ። “ ወይ እኔ ፑዋሮ ! ትንንትና



t.me/OLDBOOKSPDF

ማታ ደንቁሬም ታውሬም ነበረ ለማለት ይቻላል!” ሲል ሐዘንና ቁጭት አንጀቱ ውስጥ ገብቶ አብሰለሰለው ።

ከኰሎኔል ሬስም ጋር ተያይዘው ወደ ሲኔት መኝታ ክፍል እየተጣደፉ ሲገቡ ፡ ቀደም ብሎ ደርሶ የነበረው ዶክተር ቤስነር አሟሟቷን የሚመለከት አንዳንድ የሕክምና ምርመራዎችን ያካሂድ ነበር ። እንፑዋሮንም እንዳየ ፡ ወደ ሲኔት እራስ በማመልከት “ ጥይቱ የገባው ከዚህ ከጆሮዋ በላይ ነው ። እንደምታዩት በቀዳዳው ዙሪያ ያለው ቆዳዋ ተለብልቧል ። ይህም የሚያመለክተው የገደላት ሰው በጣም ተጠግቶ መተኮሱን ነው ” አለና “ የሞተችው በእንቅልፍ ላይ እንዳለች ነው ። ለመታገልም ለመንፈራገጥም ምንም ሙከራ አላደረገችም ። ገዳዩዋ በጨለማ ውስጥ አድፍጦ መተኛቷን ካረጋገጠ በኋላ ነው የገደላት ” ሲል ማብራሪያውን ቀጠለ ።

ፑዋሮ ሲኔትን ጐንበስ አለና ተመለከታት ። በሰላም እንቅልፍ ላይ ያለች እንጂ የሞተ ሰው ገጽታ አይታይባትም ። ሲኔት ከፈራችው የሞት አደጋ እንዲያስጥላት ስትለማመጠው ፡ እርሱ ግን አትካራ የገጠማት ትዝ አለውና በሐዘን እንዳቀረቀረ ቆየ ። ከዚያም ቀና ሲል ነጭ ቀለም በተቀባው ግርግዳ ላይ ጀ የሚል ፊደል በደም ተጽፎ አየ ። ፑዋሮም እንደገና ጐንበስ ብሎ የሲኔትን ቀኝ እጅ ሲመለከት አንዱ ጣቷ በደም መለወሱን ተገነዘበ ።

“ ምን ሊሆን ይችላል ? ” ሲል ኰሎኔል ሬስ ጠየቀ ።

“ ነገሩ እንኳን ቀላል ነው ። ሲኔት በሞት ጣር ላይ እንዳለች የገዳይዋን ማንነት ለማሳወቅ ስትል ፡ ጣቷን በደሟ ውስጥ ነክራ የሰውየውን ስም የመጀመሪያ ፊደል ጻፈች ብሎ ለማስመሰል ነው ። ያረጀ የማታለያ ዘዴ !” አለ ፑዋሮ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶክተር ቤስነርም ለፑዋሮ አስተሳሰብ ያለውን ድጋፍ ለመግለጽ እየተጣደፈ "ሊሆን አይችልም እንጂ! አሳዛኟ ሊኔት የሞተችው ከመቅጽበት ነው ። እንኳንስ ጣቷን በደሟ ውስጥ ነክራ ወደ ግርግዳው ለመድረስ ልት ንጠራራና ልትጽፍ ቀርቶ ከተኛችበት ጎኗ በፍጹም አል ተላወሰችም ። ይህ የማይመስል እርካሽ ማወናበጃ ነው!" አለ ።

" ስለዚህ ሆን ተብሎ ለተንኮል የተደረገ ነዋ ? " ሲል ሬስ ፡ ፑዋሮ " አዎን ! በግልፅም ለማየት የሚ ቻል ነው ። ጃ ተብሎ የተጻፈው ገዳይዋ ጃኪሊን ናት ብሎ ለመጠቆም የተደረገ ሙከራ ነው።" አለና ወደ ዶክተሩ ዞሮ " ለመሆኑ ከሞተች ስንት ሰዓት ሊሆን ይችላል ? " ሲል ጠየቀው ።

" ትክክኛለውን ሰዓት እርግጠኛ ሆኜ ለመናገር ባልችልም ከሌሊቱ ስድስትና ስምንት ሰዓት መሀል ባለው ጊዜ ውስጥ ነው " አለ ዶክተር ቤስነር ።

" ባኗ ግን የት ሄዶ ነበር ማለት ነው ? " ሲል ሬስ አሁንም ተቸገረና ጠየቀ ።

" ሳይመን የተኛው በእኔ ክፍል ውስጥ ነበረ " ብሎ ቤስነር ሲመልስ ፡ ሁለቱም ተደናግጠው በመገረም ያዩት ጀመረ ።

" ለምን የገባንበት ችግር ያንሰን ይመስል ፡ የማይ መስል ወሬ ታወራለህ ? " አለና ሬስ ጮኸበት ።

ዶክተር ቤስነር ግን ለማስረዳት በመሞከር " ሌሊ ቱን ያሳለፍነው በጭንቀት ነበረ ። ሁለታችሁም በከባድ እንቅልፍ ላይ ሆናችሁ ባለመስማታችሁ እንጂ ጃኪሊን በተኮሰችው ጥይት ሳይመን ከጉልበቱ ላይ ቆስሎ የሕክ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምና እርዳታ ከአደረግኩለት በኋላ ያደረው በእኔ መኝታ ላይ ነው ። የቅልጥሙም አጥንት ተሰብሯል ። ስለዚህ ህም በእስቸኳይ ሆስፒታል መግባትና መታከም ይኖርበታል።” እያለ ሴሲቱን የደረሰውን ታሪክ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ ዘርዝሮ ሲያጫውታቸው ፣ በዝምታ ተውጠው አዳመጡት ። ዶክተሩም የሰማውንና ያየውን ሁሉ ተናግሮ እንደጨረሰ ፡

“እንደዚህማ ከሆነ ፡ ሁሉም ነገር ግልጽ ነው !” አለ ሬስ ፡“ ጃኩሊን በስካር መንፈስ ተገፋፍታ በመጀመሪያ ሳይመንን ካቆሰለችው በኋላ ፡ ቀጥላ ደግሞ ሊኔትን ገድላታለች ማለት ነው !” ሲል ዶክተር ቤስነር በተቃውሞ እራሱን እየወዘወዘ ፡

“ ኮሎኔል ሬስ ያሉት ልክ አይደለም ! ሊሆንም የማይችል ነገር ነው ። ገዳይዋ ጃኩሊን ከሆነች እንዴት የራሷን ስም መነሻ ፊደል ልትጽፍ ትችላለች?” በማለቱ፡ፑዋሮም ይህንኑ ሐሳብ በማጠናከር “ ጃኩሊን እስከዚህ ደረጃ እራሷን ዝቅ በማድረግ የምታታልል ሴት አይደለችም! የእንሳስሳነት ባሕርይም የለባትም !” በማለት ተናገረ ።

“ እንግዲያውስ በወንጀሉ ቀጥታ ተጠርጣሪዋ ጃኩሊን እንድትሆን የፈለገ ሌላ ሰው አለ ማለት ነው ? ” አለ ሬስ ።

ቤስነር ቀበል አለና “ አዎን ! ሆኖም የሊኔት ገዳይ እስከዚህም ዕድለኛ ነው ለማለት አልችልም ። ጃኩሊን ሊኔትን ከለመግደሏም በላይ ለጥርጣሬም የምትበቃ አይደለችም ። ሳይመንን ካቆሰለችው በኋላ የቀረውን የሌሊቱን ጊዜ ያሳለፈችው የእንቅልፍ መርፌ ተወግታ ነው ። አስታማሚዋም ሚስ ባወርስ ከአጠገቧ አልተለየችም ነበረ ” ሲል አስረዳ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ የሊኔትን መሞት በቅድሚያ ያየው ማን ነው ? ” አለና ፑዋሮ ጥያቄ አቀረበ ።

“ የቤት ሠራተኛዋ ሉዊ ቡርጂ ናት ። የቁርስ ሰዓት ከመድረሱ በፊት እንደልማዷ እመቤቷን ለመቀስቀስ ስትሄድ ሞታ አገኘቻት ። ከመኝታ ክፍሉም ውስጥ በድንጋጤ እየጮኸች እሮጣ ስትወጣ ከእኔ ጋር ተገናኘን ” ሲል ሬስ ተናገረ ።

ዶክተር ቤስነር ደቅርታ ጠያፊ ወደ ሕመምተኛው ሳይመን ተመልሶ በሄደም ፑዋሮና ሬስ አሁንም ውይይታቸውን እንደቀጠሉ ነበሩ ።

“ በቅድሚያ ሌሊት ስለተፈጸመው ድርጊት ዶክተር ቤስነር የነገረን ሁሉ ትክክለኛ ስለመሆኑ የዓይን ምስክር የነበሩትን ኮርኔሊያንና ፋንተርፕን ጠይቀን ማረጋገጥ ይኖርብናል ። ከነርሱ የተሻለ መረጃ የሚሰጠን ሰው የለም ። የሽጉጧም መጥፋት እንደሚቀላል ነገር የሚታለፍ አይደለም ። ጃክሊን በጣም የምታሳዝነኝ ልጅ ስለሆነች ከዚህ ወንጀል ውስጥ ነጻ እንድትሆን ያለኝ ምኞት ከፍተኛ ነው ፦ ” አለ ፑዋሮ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ኮርኔሊያና ፋንተርፕ እነ ፑዋሮ ወደነበሩበት ክፍል ተጠርተው ገቡ ። የኮርኔሊያ እንባ አሁንም አላቋረጠም ነበረ ። የሊኔት ሞት እጅግ አድርጎ አንገብግቧታል ። ለሳይመንም እጥብቃ አዝናለች ። መቁሰሉ እንሶት አሁን ደግሞ ስለሚያፈቅራት ሚስቱ ሞት ሲሰማ ፈጽሞ ያብዳል የሚል ሥጋት አድሮባታል ። ኮርኔሊያም ዓይኖቿን በመሐረቧ እያደራረቀች ያየችውን ሁሉ ለፑዋሮ መተረክ ጀመረች ።

“ ጃክሊን ወደ ሳሎኑ ገብታ ጥቂት እንደቆየች ፣ ከርታ ይጫወቱ ከነበሩት መካከል ሊኔት ኮሎኔል ሬስና



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስተር ፔኒንግተን ወደ የመኝታ ክፍላቸው ሄዱ ። በሳሎኑ ውስጥ የቀረነው እኔ ፤ ፋንትሮፕ ፤ ጃክሊን ፤ ሳይመን ፤ አራት ሰዎች ብቻ ነበርን ። ጃክሊን በመደጋገም ጂን በመጠጣቷ ሰክራ ነበረ ። ያለፈውን ታሪኳን አንድ በአንድ አጫወታኛለች ። የምታነሳቸው ነጥቦች ሁሉ ሳይመንን ቅስ በቅስ እያናደዱት በሄዱም በትዕግሥት ለማሳለፍ ሞክሯል ። ቢሆንም ጃክሊን በመጨረሻ ላይ ‘ እንደውሻ እገልሃለሁ !’ ብላ ሽጉጧን ስታወጣ ሳይመን ዘሎ እጅዋን ለመያዝ ሞክሮ ነበረ ። ግን ሳይደርስባት በፊት በመተኮሷ ከጉልበቱ ላይ አቆሰለችው ። ወዲያውኑ ማልቀስ ጀመረች ። እኔም ከሳሎኑ እሮጬ እንደወጣሁ ፋንትሮፕን አበራፏ ላይ ስላገኘሁት አብረን ተመለስን ። ሳይመንም ወሬውን ማንም ሰው እንዳይሰማ አጥብቆ ለመነን ። ጃክሊንም ይዛት የነበረችውን ሽጉጥ በሜማዋ መታ ከሶፋ ሥር ከተተቻት ። ከዚያም ይዘናት ወደ መኝታ ክፍሏ ወሰድናት ። እራሷን አደጋ ላይ እንዳትጥል ፋንትሮፕ ሲጠባበቃት እኔ አስታማሚዋን ሚስ ባወርስን ጠርቼአት መጣሁ ” ስትል ተናግራ ጨረሰች ።

“ በዚያን ጊዜ ሰዓቱ ስንት እንደሆነ ታስታውሻለሽ?” ሲል ሬስ ጠየቃት ።

ኮርኔሊያ እራሷን በማወዛወዝ ስትገልጽ ፋንትሮፕ ግን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ አካባቢ መሆኑን አስረዳ ።

“ ሲኔት ፤ ኮሎኔል ሬስና ፤ ፔኒንግተን ከሳሎኑ ወጥተው ወደ መኝታቸው የሄዱት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ተኩል ላይ ለመሆኑ ኮሎኔል ሬስ ራሱ አረጋግጦልኛል ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሳሎኑ ውስጥ ከቀራችሁት ከአራታችሁ መካከል ወደ ውጭ የወጣ ሰው ነበረ ? ” አለ ፑዋሮ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ማንኛችንም ወጥተናል ለማለት አልደፍርም ። እኔም ብሆን የጃኮሊንና የሳይመን ጭቅጭቅ ለጆሮዬ ስለቀፈፈኝ ፤ ከሳሎኑ ወጥቼ ከበራፉ ፊት ለፊት ነበር የቆምኩት ።” ሲል ፋንትሮፕ መለሰ ።

“ ስለዚህ ! ” አለ ፑዋሮ ጸጉሩን እያሻሸ እረጋ ብሎ በመናገር “ ስለዚህ ! ሊኔት ወደ መኝታ ክፍሏ ከሄደችበት ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ተኩል ጀምሮ ሳይመን እስከቆሰለበት እስከ ስድስት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ድረስ ጃኮሊን ከሳሎኑ አለመንቀሳቀሷን አውቀናል ማለት ነው ። ከዚያም በኋላ ቢሆን ወደ መኝታ ክፍሏ እንደ ወሰዷትና ሚስ ባወርስ እንድትረዳቸው ማድረጋቸውን ከኮርኔሊያ ገለጻ ተረድተናል ። የቀሩትንም የሌሊቱን ሰዓታት ጃኮሊን እንዴት እንዳሳለፈችው ልትነግረን የምትችለው አስታማሚዋ ስለሆነች እርሷን ማነጋገር አለብን ማለት ነው” አለና ፑዋሮ ቀጠል በማድረግ “ ሆኖም እርሷን ከማስጠራቴ በፊት ግልጽ ባልሆኑ አንዳንድ አንስተኛ ነጥቦች ላይ ያላችሁን አስተያየት እንድትሰጡኝ እፈልጋለሁ ። ምንም እንኳን ጃኮሊን ሳይመንን ብታቆስለውም ‘ብቻዋን እንዳትተዋት ’ እያለ ሰምቻችሁ ነበረ ። ይህንን የተናገረው ምናልባት ሌላም አደጋ ትፈጥራለች የሚል ሥጋት አድሮባት ይሆን ? ” ሲል ፑዋሮ ጠየቃቸው ።

“ ይመስለኛል ! ” አለና ፋንትሮፕ መለሰ ።

“ ሊኔትንም ልትገድላት ትችላለች ብሎ ስለፈራ ይሆን ? ” ሲል ፑዋሮ ደግመና ጠየቀ ።

“ አይደለም ሙሴ ፑዋሮ ! ” ብሎ ፋንትሮፕ መልሱን ለማብራራት ሞከረ ።“ የፈራው ለሊኔት ሕይወት አልነበረም ። ጃኮሊን ሳይመንን በማቁሰሏ ከመጠን በላይ የሆነ ጸጸት ተሰምቷት ነበረ ። ተንሰቅስቃ ታለቅስ ነበረ ። በተለይም ጥቷን ደጋግማ ትመኝ ነበረ ። ስለዚህም



t.me/OLDBOOKSPDF

በኋኔ አስተሳሰብ የሳይመን ሥጋት እራሷን ትገድላለች ብሎ በመፍራት ይመስለኛል” አለ ።

“ ጥሩ ! ” አሉና ፑዋሮ “ ያቺስ የጃኩሊን ሽጉጥ የት ደረሰች ለማለት ይቻላል ? ከእጆዋ ላይ አሽቀንጥራ መወርወሯንና በሚጣዋም ሙትታ ከሶፋ ሥር እንደ ኩተተችው ነግራችሁኛል ። ግን ጃኩሊን ከሳሎኑ ከመውጣቷ በፊት ከወደቀበት አንስታ መልሳ ላለመውሰዷ እርግጠኞች ናችሁ ? ” ሲል ጠየቀ ።

ሁለቱም በአንድ ጊዜ “ በፍጹም አልወሰደችም ! ” አሉና መለሱ ።

“ እንደዚህ ያለ ጥያቄ የምጠይቃችሁ በተቻለ መጠን የበኩሉን ትክክለኛ አስተያየት ለመስጠት እንዲረዳኝ ነው ። ስለዚህም እንበላችና ፡ ጃኩሊን ከሳሎኑ ስትወጣ ሽጉጧን አለመውሰዷን ካወቅን ፡ በኋላም ቢሆን ከሁለታችሁና ከአስታማሚዋ ከሚስ ባውርስ አለመለየቷን ካረጋገጥን ፡ ያችን ሽጉጥ የምታገኝበት ምንም ዕድል የላትም ማለት ነው” ብሎ ፑዋሮ ጥቂት አሰብ አደረገና “ ከማጠቃለላችን በፊት ለፋንትሮፕ የማቀርበው ሌላ ጥያቄ አለኝ ። አንተና ዶክተር ቤስነር ሳይመንን ከሳሎኑ ተሸከማችሁት የሄዳችሁት በስንት ሰዓት ይመስልሃል ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ከሃያ አምስት ደቂቃ ”

“ ሽጉጧን ለማምጣት ወደ ሳሎኑስ የተመለስከው ከስንት ደቂቃዎች በኋላ ይሆናል ብለህ ትገምታለህ ? ”

“ ከአሥር እስከ አስራ አምስት ደቂቃዎች ”

“ እንግዲያውስ በእነኝህ ደቂቃዎች ውስጥ አንድ የሆነ ሰው ያቺን ሽጉጥ አንስቷታል ማለት ነው ። ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህንን ያደረገችው ጃኪሊን ልትሆን አትችልም ። በሳሎኑ ውስጥ የተደበቀ ሌላ ሰው መኖር አለበት ። ሽጉጧ ከሶፋ ሥር መውደቋን በሚገባ ተመልክቷል ። ስለዚህም በዚያች ሽጉጥ ሊኔትን ከገደለ በኋላ እንዳይነቃበትና ገዳይዋ ጃኪሊን እንደሆነች ለማስመሰል ጃ የምትለዋን ፊደል ጻፈ ። ” አለና ፑዋሮ አንዳንድ የግል ጥያቄዎች እያቀረበላቸው ማስታወሻ መያዝ ጀመረ ። በቅድሚያም የጠየቀው ፋንትሮፕን ነበረ ።

“ ሙሉ ስምህ ? ”
“ ጀምስ ሌክደል ፋንትሮፕ ”
“ አድራሻህ ? ”
“ ዶራንግማተን ፣ ኖርዝሃምፕተን ፣ ሻየር ፣ ኢንግላንድ”
“ ሥራ ? ”
“ ጠበቃ ። ”
“ ወደ ግብጽ የመጣህበት ምክንያት ? ”
“ አገር ለመጎብኘት ። ”
“ ዕረፍት ላይ ነህ ማለት ነው ? ”
“ አዎን ! ”
“ ሊኔትን ከአሁን በፊት ታውቃታለህ ? ”
“ ስሟን እንጂ በመልክ አላውቃትም ነበረ ። ”
“ ቀደም ሲል ከነገርከኝ ሌላ የምታውቀው ነገር ቢኖር ? ”

“ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት አካባቢ ከመርከቧ ላይ የሆነ ነገር ወደ ወንዙ ውስጥ በመወርወሩ ቦርጨቅ የሚል የውሀ ድምጽ ሰምቻለሁ ። ከዚህ በኋላ ግን እንቅልፍ ወሰደኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

“አመሰግናለሁ!” ብሎ አሰናበተውና ፒዋሮ ጥያቄውን ወደ ኮርኔሊያ መለሰ ።

“ ሙሉ ስምሽ ? ”

“ ኮርኔሊያ ሩገ ”

“ አድራሻሽ ”

“ ሬድ ሃውስ ፡ ቤሊፊልድ ፡ ኮኔክቲከት ዩ ኤስ ኤ፡”

“ ወደ ግብጽ የመጣሽበት ምክንያት ? ”

“ ከአክስቴ ከሚስ ቫን ሻይለር ጋር ለሽርሽር ነው የመጣነው ። ”

“ ከሊኔትም ሆነ ከቤተሰቧ ጋር ትውውቅ አላችሁ?

“ የለንም ! ”

“ ቀደም ሲል ከነገርሽን ሌላ ያየሽው ወይንም የሰማሽው ነገር ቢኖር ? ”

“ በከባድ እንቅልፍ ላይ ስለነበርኩ ምንም የተለየ ነገር አላየሁም ፡ አልሰማሁምም ! ”

ኮርኔሊያንም ፡ ፒዋሮ አመስግኖ ካሰናበታት በኋላ አስታማሚዋን ሚስ ባወርስን አስጠራት ። ወዲያውንም ወደ ጥያቄው አምርቶ ፡

“ እኩለ ሌሊት አካባቢ ኮርኔሊያ የቀሰቀሰችሽ ለምን ነበረ ? ” ሲል ጀመረ ።

“ የደረሰውን አደጋ ስትነግረኝ ተከትያት ወደ ጃኩሊን መኝታ ክፍል ሄድን። ጃኩሊን እራሷን መቆጣጠር አቅቷት ነበረ ። በተለይም መጠጥ ወሳስዳ ስለነበረ በቀላሉ ከአደጋ ላይ ልትወድቅ እንደምትችል በመረዳቴ ብቻዋን



t.me/OLDBOOKSPDF

ትቶት ለመሔድ አልፈለግኩኝም ። ስለዚህም የእንቅልፍ መርፌ ከወጋኋት በኋላ እኔም ሲሊቱን በዛው ክፍል ውስጥ አሳለፍኩ ። ”

“ በሊኔትስ ላይ ስትገዠት ሰምተሽ ይሆን ? ”

“ አልሰማሁም ! ”

“ ከመኝታ ክፍሏ በፍጹም አልወጣችም ነበረ ? ”

“ አዎን ! ጭራሽ አልወጣችም ። ”

“ አንቺስ ? ”

“ እኔም ብሆን ጃኩሊን በእስጊ ሁኔታ ላይ ስለነበረች ፣ እስከሚነጋና ከእንቅልፏ እስከምትነቃ ድረስ ከአጠገቧ አልተለየሁም ። ”

“ እርግጠኛ ነሽ ? ”

“ ሊያምኑኝ ይገባል ። የተናገርኩት እውነት ነው!” አለችው ። እርሷንም እንደሌሎቹ አመስግኖ ካሰናበተ በኋላ ከሬስ ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች በዝምታ ሲተያዩ ቆዩ። በእርግጥም ሊኔትን የገደለችው ጃኩሊን አለመሆኗን ሁለቱም ያለ አንዳች ጥርጣሬ አመኑ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሰባት

ፒዋሮ በአእምሮው ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በማመላለስ በሐሳብ ተውጦ እንዳለ በሩ ተከፍቶ ጃኩሊን ገባች ። መልኳ በጣም ገርጥቷል ፤ ሰውነቷ ይንቀጣቀጣል ፤ መራመድ ተስኗት እግሮቿን የምታነሳቸው በግድ ነበረ ። ከአገኘችውም ወንበር ላይ አረፍ ከማለቷ ፍርሃት እንደገባው ሕጻን ባልተረጋጋ ድምጽ ፤

" እኔ አላደረግሁትም ሙሴ ፒዋሮ ! ጨክኜም አላደርገውም ነበረ ! ሁሉም የሚጠረጥሩት እኔን ነው ። እርስዎ እንኳን ይመኑኝ ! ማታ መጠጡም ጭምር እንደ ዕብድ ስላደረገኝ ሳይመንን ላቆስለው ቻልኩ ። ግን ሌላውን . . . . " ብላ የጀመረችውን ሳትጨርስ እየተንሰቀሰቀሰች ታላቅስ ጀመረ ። ፒዋሮም ከተቀመጠበት ተነስቶ ትከሻዋን እየደባበሰ ፤

" አይዞሽ የእኔ ልጅ ! ለምንስ ታለቅሻለሽ ? ሊኔትን አንቺ እንዳልገደልሻት ደርሰንበታል ። አይዞሽ ! የአንቺ ንጽሕና ተረጋግጧል " እያለ ያጽናናት ጀመረ ። እርሷም በለቅሶ የነፈረፉትን ዓይኖቿን ከጠራረገችና ትንፋሿ መለስ ካለላት በኋላ ፤ "ታዲያስ ማነው የገደላት ሙሴ ፒዋሮ?" ስትል በለዘበ ድምፅ ጠየቀችው ።

" አእምሮአችንን የበጠበጠው ጥያቄ የቱ ሆነና !" ብሎ " አንቺስ የሊኔትን ገዳይ ለማግኘት በምን መንገድ ልትተባበሪንና ልትረጂን ትችያለሽ ? " አላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጃክሊን እራሷን በማወዛወዝ “ በምን መንገድ ልረዳችሁ እንደምችል አላውቅም ። የሆነ ፍንጭ እንኳን ልሰጣችሁ የምችል አይመስለኝም ” ብላ ግንባሯን በመቋጠር ለጥቂት ጊዜ ከቆየች በኋላ “ የሊኔትን ሞት የሚፈልግ ማንም ሰው ያለ አይመስለኝም ነበር ። እኔ ብቻ ነበረ ይህንን የምመኝላት ” አለች ፡ እሁንም ባልተረጋጋው ድምጿ ። እራሷንም ዘንበል አድርጋ የእንዱን እጅ ጣቶቹን በሌላው እጅ ጣቶቿ እያቆላለፈች “ ሞት ጨካኝ ነው ! ሞት አስከፊ ነው ! ሞት የሚዘገንን ነው ! ስለ ሊኔት ሞት ሳስብ ከባድ ፍርሃት ይወድቅብኛል !” አለች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

“ እውነት ነው የእኔ ልጅ ። ሞት ደስታን የሚያሳድር ስሜት ሊኖረው አይችልም ። ሆኖም በዛሬዋ ቀን በዚች ሰዓትና ደቂቃ ሊኔትን የገደላት ሰው በፈጸመው አስከፊ ተግባር ይኩራራ ይሆን ይሆናል !” አለ ፑዋሮ እንደ ተከዘ ።

“ በሊኔት ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንደነበረኝ የሚያውቁት ነው ። ሆኖም ስለአሟሟት ሁኔታ ስሰማ እጅግ አድርጎ አሳዘነኝ ። በተለይም አገዳደሉ እኔ እንደተነበይኩት መሆኑ ” አለች ጃክሊን እንባዋ እንደገና በዓይኖቿ ግጥም እያለ ።

“ አዎን ጃክሊን ! አንቺ እንደዛትሽባት ሁሉ የተመታችው ከጆሮዋ ላይ ነበረ ። ” ሲላት ፡

“ ይልቅስ አንድ ነገር ትዝ አለኝ ” አለች ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ፑዋሮን እያየች ፡ “ ያን ቀን በካታራክት ሆቴል ውስጥ ከዓባይ ወንዝ ዳር እኔና እርስዎ ተቀምጠን በምን ነጋገርበት ሰዓት አንድ ነገር እንደጥላ ውልብ ሲል ታይቶኝ ነበረ ። እኛ እንነጋገር የነበረውን ተደብቆ ለመስማት



t.me/OLDBOOKSPDF

የፈለገ ሰው ሳይሆን አይቀርም ” ስትል ፑዋሮ ስለዚሁ በይበልጥ ለማወቅ ፈልጎ ፡

“ ሰውዬውን ልታስታውሽው ትችያለሽ ? ” አላት፡

“ ወንድ መሆኑን ለመገመት እችላለሁ ። ከዓይኔ ላይ ከመቅጽበት ተሰውሮ ስለጠፋብኝ ፍጹም እርግጠኛ ለመሆን ያዳግተኛል ” በማለት ላይ እንዳለች ዶክተር ቤስነር በራፉን ከፍቶ በመግባት ፤

“ ሳይመን በጥብቅ ሊያነጋግርዎት ስለሚፈልግ አብረን ብንሄድ ” ሲል ፑዋሮን ለመነው ።

ጃክሊን ከተቀመጠችበት ዘላ በመነሳት የቤስነርን ክንዶች ጨብጣ ይዛ ፡

“ ሳይመን ምን ሆነ ? ዶክተር ! ደህና አይደለም እንዴ? ሕመሙ እየጸናበት ሄደ ማለት ነው ? ” ስትል ትወተውት ጀመረ ።

“ አይዞሽ አትደንግጪ ! የደረሰበት የአጥንት ስብራት ብቻ ነው ” አላት ቤስነር ፡

“ አይሞትም ማለት ነው ? አይደለም ዶክተር ? ” ስትል አሁንም ወጉቱት ጠየቀችው ።

“ ሞት እንዲህ ቀላል ነገር መሰለሽ ። በእርግጥ ከሆስፒታል ገብቶ በሕክምና ላይ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት ይኖርበታል ” ” ሲላት እስከአሁን እንደያዘችው የቆየችውን ክንዶቹን ለቃ “ እፎይ ! ” ብላ በመተንፈስ ከወንበር ላይ አረፍ አለች ።

ሙሴ ፑዋሮ ፣ ኰሎኔል ሬስና ዶክተር ቤስነር ተያይዘው ሳይመን ከነበረበት ክፍል ሲገቡ ሳይመን ከጉል



t.me/OLDBOOKSPDF

በቱ ሥር ትራሶች ተደርድረውለት በጀርባው እንደተኛ ነበረ ። የፊቱ ቆዳ ወይቦ ሌላ ሰው መስሏል ። ከቁስሉም ሥቃይ ይልቅ የደረሰው አስደንጋጭ ዜና መልኩን ለዋ ውጦታል ። ግራም ተጋብቶ ፊቱ ነበረ ። እነ ሙሴ ፑዋሮ ወደ መኝታ ክፍሉ እንደገቡ ፡

“ እውነት ነው ሙሴ ፑዋሮ ? ሲኔትን በእርግጥ ጨክነው ገደሏት ? እባክዎን ኮሎኔል ሬስ ፡ እውነት ይክ ተሩ እንደነገሩኝ የእኔ ሲኔት ሞተች ? . . . ” እያለ ሲቃ እየተናነቀው ሲናገር ፡

“ የተደራረበ አደጋ ደረሰብህ ፡ ሲኔትን የመሰለች ሚስት ማጣት በጣም የሚያሳዝንና የሚዘገንን ነው ” ሲል ኰሎኔል ሬስ ሊያጽናናው ሞከረ ።

ሳይመን ግን ለብዙ ጊዜ ሲያለቅስ እንደቆየ ሰው ድምጹ ቢጐረንንም “ የሐዘኔ ተካፋዩነትዎን ስለገለ ጹልኝ አመሰግናለሁ ” ብሎ ወደ ፑዋሮ መለስ አለና “ መቼም እንዲህ ዓይነቱን አረመኔያዊ ተግባር ጃኩሊን ጨክና ትፈጽማለች ብዬ አልገምትም ። ሆኖም እርሷን ወንጀለኛ ለማድረግ የሁሉም ጣት ወደ እርሷ እንደሚያ መለክት እርግጠኛ ነኝ ። ማታም ቢሆን በመጠጥ ተገ ፋፍታ በእኔ ላይ አደጋ ብታደርስም ፡ ነፍስ ላጥፋ ብላ ሆን ብላ ተነሳስታ ሲኔትን እስከመግደል የምትደርስ አይ መስለኝም ። ” አለ ።

ፑዋሮም አረጋ ብሎ “ በሕክምና እርዳታ ላይ ያለህ ሰው ሆነህ እራስህን ብዙ ማስጨነቅ የለብህም ። የሚስ ትህን ገዳይ ግን እንደሆነ ለጊዜው ባናውቀውም ፡ ጃኩሊን አለመሆኗን ግን አረጋግጠናል ” ሲለው ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይመን የሰማውን በመጠራጠርና ጆሮውን ባለማመን "የነገሩኝ እውነት ነው ? ሙሴ ፑዋሮ !" ሲል ጠየቀ።

" ጃክሊን እንዳልገደለቻት ደግሜ አረጋግጥልሃለሁ። ሆኖም የገዳዩን ማንነት በተለይም አንተ በምታደርግልን ትብብር እንደርስበታለን ብለን እንገልምታለን " አለው ።

ሳይመን አሁንም ግራ በመጋባት " ከጃክሊን በስተቀር የሊኔትን ሞት የሚፈልግ አንድም ሰው ያለ አይመስለኝም " ሲል መለሰ ።

" እረጋ ብለህ ለማስታወስ ሞክር እስቲ ሳይመን ? ለመሆኑ ሊኔት ሌላ ጠላት የላትም ነበር ? በሆነ ነገር የተነሳ ቂም የያዘባት ሰው ሊኖር አያችልም ? " አለው ፑዋሮ ።

ሳይመን የረሳው ነገር ቢኖር ለማስታወስ አእምሮውን ማሠራት ጀመረ።ሊኔት ያወራችለትን ስለ ሊኔት የሰማውን ሁሉ ለማሰባሰል ሞከረ ። ለጥቂት ደቂቃዎች ዝምታ ከሰፈነ በኋላ ፡

" ያስታወስኩትን ለመናገሩ የሚጠብና የሚጨንቅ ነገር ሆኖ ይሰማኛል ። ቢሆንም አንዳንድ ሰው ትንሽም በደል ቢደርስበት እጅግ አድርጐ አጉልቶ ስለሚያየው በዚያኑ መጠን ለመበቀልም አይመለስ ይሆናል" አለና አሁንም ለደቂቃዎች ያህል ካሰበ በኋላ ፡"ዊንድልሃም የተባለው ሰው ከእንግሊዝ መሳፍንት ቤተሰብ የተወለደ ነው ። ሊኔትን ለማግባት ፈልጐ ብዙ አማላጅ ልኮባታል ። ለብዙም ጊዜ ልቡ እንደተሰቀለ በተስፋ ሲጠባበቅ ቆይቷል ። የሊኔት ምርጫ ግን እኔ ሆኜ ተገኘሁ ። ሰር ውድ የሚባል ሌላም ከበርቴ እንደዊንድልሃም ሊኔትን አስቸግሯት ነበረ ። ጉር ሱንም ፊት ነስታቸለች ። ግን እነኝህ ሰዎች ያሉት ከግብጽ ምድር በሺህ በሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች እርቀው በለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንደ፡ን ኩተማ ነው ። የፈለገውን በዶል ብታደርልባቸውና የጠነከረም ቂም ቢይዙባትም እዚህ ድረስ ተከታትለው ሊያስገድሏት የሚሞክሩ አይመስለኝም።”አለና በረጅሙ ተነፈሰ ።

የፒዋሮ ጥያቄ አቅጣጫ ግን ሳይመን ባወራው ታሪክ ላይ ያተኩረ አልነበረም። ስለዚህም ማብራሪያ መስጠት ማስፈለጉን አውቆ ፤

“ በዚች መርከብ ላይ እንደተሳፈርን ሊኔት የተና ገረችው አንድ ነገር ነበረ ። በሆነ ምክንያት ንዴትና ብስ ጭት ገብቷት ስለነበረ ሳጽናናት በሞከርኩበት ወቅት ‘ሰዎችን ሁሉም ሰው ጠላኝ ። የተከበብኩት በማይወዱኝ ሰዎች ስለሆነ ፍርሃት ተሰምቶኛል’ ብላኝ ነበረ ” ሲል ፒዋሮ ፣ ሳይመን ፈጠን አለና “ ያሚጠተችዎት ይህንን ከሆነ፡ ጃኪሊንን በመርከቢቱ ላይ ስለአየቻት በመናደዷ ይሆናል ። እኔም ብሆን በዚያን አጋጣሚ ጨኸ አርሬ ነበረ ” አለው ።

“ ያልከውም ትክክል ሊሆን ይችላል ። ግን ልብ ብለህ ብታዳምጠኝ ፤ ሊኔት ‘የተከበብኩት በማይወዱኝ ሰዎች ነው’ ብላ ነው ተናግራለች ያልኩት ። ስለዚህ ጃኪሊንን ብቻ ማለቷ ሳይሆን ቢያንስ ሌላም ተጨ ማሪ ሰው ለመኖሩ በግልጽ የሚጠቁም ነው ።” አለው ፒዋሮ ። ሳይመንም መለስ አደረገና ፤

“ አባባልዎ አሁን ግልጽ እየሆነልኝ ሄዷል ። አቀ ራረብዎንና የሒሳብ ትንታኔዎም ትክክል ነው ። አሁን እንዳታወሰኝ የሊኔት ደም የተለዋወጠው በመርከቢቱ ላይ አብረውን የሚጓዙትን ሰዎች ስም ዝርዝር ካየች በኋላ ነበር ” ሲል ፒዋሮ ያለልማዱ ተሽቀዳድሞ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

“ በተለይ የትኛው ስም ነው ፡ እንደዚያ ለመግረርና ተስፋ ለመቁረጥ ያበቃት ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ የሰውየውን ስም ስላልነገረችኝ ላውቀው አል ችልም ። ቢሆንም ነገሮችን በሕሊናዬ በማዛመድ ከአንድ ፍንጭ ላይ የደረስኩ ይመስለኛል ። ሊኔት ያደገችውና የምትኖረው በእንግሊዝ አገር ቢሆንም ቤተሰቦቿ ግን ዕድሜአቸውን ያሳለፉት በአሜሪካ ነው ። ታዲያ ብዙ ሀብት ለማካበት የቻሉትንም ያህል በዛው መጠን ብዙም ጠላት አፍርተው ነበረ ። በተለይም አባትየው ሚሊየነር ለመሆን የበቁት ለአነስተኛ ነጋዴዎች በከፍተኛ ወለድ ገንዘብ በማበደር መልሰው የሚከፍሉትም ሲያጡ ንብረ ታቸውን እያስገመቱ በመውረስ ነበረ ይባላል ። እንደ አጋጣሚም በዚች መርከብ ላይ አብረውን ከሚጓዙት ሰዎች ውስጥ የአንደኛው አባት ከሊኔት አባት ጋር የከ ረረ ግጭት ሳይፈጥሩ አልቀሩም ። ምን ብላ ብትነግረኝ ነበር መሰለዎት ? ‘ ሰዎች የአንድን ግለሰብ አመለካከት ሳይ ረዱ ፡ በደፈናው የእገሌ ልጅ ነው ብለው የሚጠሉት ከሆነ ምንኛ ያሳዝናል ? ’ ብላኝ ነበረ ” አለና ሳይመን አቆመ።

“ አዎን ለእኔም ቢሆን ያለችኝ ከዚህ እምብዛም የሚለይ አይደለም ። የወረሰችው ሀብት ችግር እንዳስከ ተለባት የተረዳችው በዚህ ጊዜ ነበረ ለማለት ይቻላል። አንተ ግን የሰውየውን ስም ለማወቅ እንዴት ሳትሞክር ቀረህ ? ” የሚል ጥያቄ አሁንም ጥዋሮ አቀረበለት ።

“ እስከዚህም ክብደት የሰጠሁት ነገር አልነበረም ። ለጊዜው ትካዜዋን ለማዘናጋት ስል ‘ በአባቶቹ ላይ ለተ ፈጸመው በደል የዘመኑ ትውልድ ክብደት አይሰጠውም ። የምንኖርበትም ጊዜ እጅግ ፈጣን ስለሆነ ሁሉም የሚረባ ረበው በዕለት ተግባሩ ላይ ነው ’ በሚል አነጋገር የደ



t.me/OLDBOOKSPDF

ለልኳት መስለኝ ነበረ ” አለ ሳይመን በትዝታ ተውጦ ጣሪያ ጣሪያውን እያየና በዓይኖቹ ጢም ያለውን እንባ ውን እየተቆጣጠረ ።

ዶክተር ቤስኔር ከንፈሩን በሐዘን እየመጠጠ “ እንድ ፈርግስን የሚሉት ጋጠ ወጥ የሆነ ጉረምሣ በዚች መር ከብ ላይ አለ ። ምናልባትም የሲኔት ጠላት እርሱ ሊሆን ይችላል ብዬ ጠርጥሬአለሁ ” ሲል ፣ ፑዋሮ ትዕግሥት በሞ ላበት አንደበት ፣

“ እያንዳንዱን መንገደኛ ተራ በተራ እየጠራን በመ ላና በዘዴ በማነጋገር ወንጀለኛውን ለማጋለጥ እንሞክ ራለን ። በቅድሚያ ግን ያቺን የሲኔት ሠራተኛ እዚሁ ጠር ተን አንዳንድ ጥያቄ ብናቀርብላት ይሻል ይመስለኛል ። እውነት ከመናገር በስተቀር ለመዘላበድ ብትሞክር እን ኳን ሳይመን ባለበት ብዙ ዕድል አይኖራትም ” አለ ፑዋሮ

“ ግሩም ሐሳብ ነው ” ሲል ሳይመን ደገፈ ።
“ ለመሆኑ ከተቀጠረች ስንት ጊዜ ይሆናት ይሆን?”
አለና ፑዋሮ ጠየቀው ፤
“ ከሁለት ወር ሳይበልጥ ይችላል ”

“ ሁለት ወር ብቻ ! ሲኔት ውድ የሆኑ ጌጣ ጌጦች ነበሯት አይደል ? ”

“ አዎን አሏት ! በተለይም የአንገት ድሪዋ በልዩ ልዩ የከበሩ ዕንቁዎች ያሸበረቀ ስለነበረ እስከ መቶ ሺህ ፓውንድ ሊያወጣ እንደሚችል ይገመታል ። ግን ስለ ጌጦች ለምን ጠየቅኸኝ ? ለሞቷ ምክንያት የሆነው ይኸው መዘዘኛ ድሪ ይሆን እንዴ ” ሲል ዓይኖቹን ገርበብ እንዳ ደረገ ተናገረ ።


t.me/OLDBOOKSPDF

“ አዎን ! ምክንያት ሊሆን የማይችልበት መንገድ የለም ። ለማንኛውም እስቲ ያቺን ሠራተኛዋን እናነጋግራት ” ብሎ እንድትጠራ አደረገ ። ቡርጂም ወደ ክፍሉ ውስጥ ስትገባ ጉንጮቿና ዓይኖቹ ቀልተው ነበረ ። ምንም እንኳን በእመቤቷ ሞት የተነካ ስታለቅስ ለመቆየቷ ምልክት ቢሆንም ያንን ብልጣ ብልጥ አመለካከቷን ሊሸፍንላት አልቻለም ።

“ ሊኔትን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሻት መቼ ነው ? ” አላት ፑዋሮ ጥያቄውን በመጀመር ፤

“ ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ላይ ነበረ ። ልብሷን አወላልቃ እንደተኛች መብራቱን አጥፍቼ ወደ መኝታ ክፍሌ ሄድኩ ” ስትል በዛ በተሞላሞለ አፏ መለሰች ።

“ ከዚያስ ያየሽው ወይንም የሰማሽው ምንም ነገር አልነበረም ? ”

“ እንዲያውም ብዬ ! ”

“ ይህን የምታውቂው አንቺ ብቻ ነሽ ” ሲላት ፑዋሮ ወደ ጐን ሰረቅ አድርጋ እየተመለከተች ፤

“ እኔ እኮ በአካባቢው አልነበርኩም ለማለት ነው ። ምንስ ለማየትም ሆነ ለመስማት እችላለሁ ። የእኔ መኝታ ክፍል በመርከቢቱ ምድር ቤት ክፍል ውስጥ ነው ። ስለዚህም ምንም ነገር ለመስማት አልችልም። ምናልባት እንቅልፍ አልወሰደኝ ቢለኝና ወደዚህ አካባቢ መጥቼ ቢሆን ይህን አውሬ ነፍስ ገዳይ ወደ እመቤቴ መኝታ ቤት ሲገባ ወይንም ሲወጣ ላየው እችል ነበረ ።” ብላ እጆቿን ወደ ላይ ሠማይ እንዲያማልዳት እየዘረጋች ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

" ከዚህ የተሻለ ምንም መልስ ለመስጠት ስለማ ልችል ፣ ጌታዬ እባክዎን ይርዱኝ " በማለት ትለምነው ጀመረ ።

ሳይመን ግን እንደመቅሰብትም ብሎ ፡ "ለምን እራ ስሺን ቂል ታደርጊዋለሽ ። ማንም ቢሆን ያላየሽውን ወይንም ያልሰማሽውን ትናዘዥ ብሎ የተጫነሽና ልዩ ተጽዕኖ ያሳደረብሽ የለም ። ስለዚህ ምንም ነገር መፍራት የለብሽም ። በተጨማሪም ደግሞ እኔም ስላለሁልሽ አይ ዞሽ ! ምንም አትሆኝም ። እንቺንም የወነጀለሽ ማንም ሰው የለም ! " አላት ።

ቡርጂም በተድፎነፎን ድምጽ፡ "ጌታዬን ያኑርልኝ!" ብላ አንገቷን ወደ መሬት አቀረቀረች ።

" ስለዚህ ምንም ነገር እንዳላየሽ ወይንም እን ዳልሰማሽ አድርገን ቃልሽን እናስፍረዋ !" አለ ፊስ የማ ስታወሻ ደብተሩንና እርሳሱን ለመጻፍ እያመቻቸ ።

" አዎን ! የተናገርኩትም ይህንኑ ነው ጌታዬ " አለች እንዳቀረቀረች ፤

" በእመቤትሽ ላይ ቂም ይኖረዋል ብለሽ የምት ጠረጥሪው ሰው የለም ? " አለና ፑዋሮ እንደቀልድ ጠየቃት ።

የሚያዳምጧት ሁሉ በሁኔታዋ እስኪገረሙ ድረስ ፈገግ አለችና ፡ " የምጠረጥረው አለኝ ። ፍጹም እር ግጠኛ ሆኜ ለእናንተ ለማሳወቅ እችላለሁ።" ስትል ፡

" ምን ? " አለና ሳይመን ከተኛበት ቀና ብሎ ተመ ለከታት ።

ፑዋሮ ግን ቀስ ብሎ " ድንገት ጃክሊን ናት እን ዳትይን " አለ ።" ሲጠላትንትማ ጃክሊንም ጠላቷ ናት



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ግን ስለእርሷ ልናገር አልነበረም ። በእመቤቴ ላይ ከፍተኛ ቂም የያዘ ሌላ ሰው በዚች በርከብ ውስጥ አለ” አለች አሁንም ዓይኖቿን በማቁለጭለጭ ።

“ የአምላክ ያለህ ! ” አለ ባይመን የሰማውን ማመን አቅቶት ፣ ቀጠልም አያፈገና “ ቤትዬዋ ምን ማለቷ ይሆን ? ጤነኛ አይደለችም መሰለኝ ? ” ሲል ተናገረ ። ሆኖም ቦርኚ ንግግሯን ከመቀጠል አላቋረጠችም ነበረ ። ከንፈሯንም በምላሷ ካራረሰች በኋላ ፣ “ ነገሩ የተያያ ዘው ከቀድሞዋ የእመቤት ወራተኛ ጋር ነው ። ስሟ ማሪ ይባላል ። እንግሊዛዊ ከሆነው ፍሊትውድ ከሚሉት ሰው ጋር ተዋደው ለመጋባት ጨርሰው ነበረ ። ሆኖም እመቤት ሊኔት ስለዚህ ሰው ቅድመ ታሪክ ለማወቅ ክት ትሉ አድርገው ኖሮ ቀደም ሲል ሥራ ይዞ በሚኖርበት በግብጽ ሀገር ሚስት እንዳለውና የአራት ልጆችም አባት እንደሆነ ይደርሱበታል ። በዚህም ምክንያት መገለጽ የተ ነሣ የታቀደው ጋብቻ ሳይፈጸም ይቀራል ። ፍሊትውድም ተስፋ በመቁረጥ ወደ ትድም ሚስቱና ወደ ልጆቹ ይሰመ ለሳሉ ። ” አለችና ቆም ስትል ከአሁን አሁን ምን ታመራ ይሆን ብለው እንፑዋሮ በችኮላ ይጠባበቋት ጀመረ ። እርሷም ባላደረጉው ልዩ ስሜት እየተኩራራች ንግግሯን በመቀጠል “ ታዲያ ያ ፍሊትውድ የተባለውን ሰውዬ የት አገኝሁት መሰላችሁ ? ” አለችና ተራ በተራ ስት መለከታቸው ፑዋሮ እንድትቀጥል እራሱን በመነቅ ነቅ አበረታታት ። “ ፍሊትውድ በዚች መርከብ ላይ በሞተር ክፍል ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራል ” ብላ አሁንም ቆም ስትል ፣ ሬስ ለሚቀጥለው ዜና እየቋመጠ ምራቁን ዋጠ ። “ እመቤት ሊኔት የፈጸሙብትን በደል ያጫወተኝ እራሱ ፍሊት ውድ ነው ። ቁጭቱንም የምወጣበት ጊዜ ሕጋጠመኝ ብሎ ሲዝት ነበረ ” ብላ ጨረሰች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፑዋሮ ወዲያውኑ ወደ ሳይመን በመዞር “ ስለዚህ ጉዳይ የምታውቀው ነገር አለ ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ በፍጹም ” አለ ሳይመን እየተገረመ “ ሊኔትም ብትሆን ስለሰውየው በዚች መርከብ ላይ መኖር የምታውቀው አይመስለኝም ። ታሪኩን ከነአካቴው ሳትረሳው አትቀርም ” ሲል ፑዋሮ ቦርጂን ትኩር ብሎ ለጥቂት ጊዜ ሲመለከታት ቆየ ።

“ ለሊኔትስ ስለሁኔታው ገልጸሽላት ነበር ? ” ሲልም ጠየቃት ፡

“ የለም ፡ አልገለጽኩላትም ? ”

“ ለምን ? ”

“ አሉባልታና ተራ ወሬ ይገኙ ለመቅረብ ባለመፈለጌ ”

ፑዋሮ የጥያቄውን አቅጣጫ ቀየረና ፡ “ ስለእመቤትሽ የአንገት ጌጥ የምታውቂው አለ ? ” ሲል ጠየቃት።

“ የአንገት ድሪያቸውን ነው ? ” አለች እንደመደናገጥ ብላ፡ ዓይኖቿንም እያሰበረች “ትናንትና አድርገውት ነበረ ” ስትል ጨምራ ተናገረች ።

“ ልትተኛ ስትል ነበረ ማለት ነው ? ”

“ አዎን ጌታዬ ”

“ ከአንገቷ አውልቃ የት አስቀመጠችው ? ”

“ እንደልማዳቸው ከትራስጌአቸው ካለው ኮመዲኖ ላይ ነበረ ። ”

“ ዛሬስ ጠዋት በኮመዲኖው ላይ አይተሽዋል ? ”

ደነገጠች ፡ ከፍተኛም ፍርሃት እንደወረራት ከፊቷ ላይ በግልጽ ይነበብ ነበረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ዛሬስ መኖር አለመኖሩን አላየሁትም ። ወደ እመቤቴ መኝታ ቤት ገብቼ የተፈጠረውን አደጋ በማየቴ ተደናግጬ በሩጫ ከመኝታ ቤቱ ውስጥ ወጣሁ እንጂ ፣ ወደ ኮመዲኖው አቅጣጫ አልተመለከትኩም ነበረ ። ደንግጬ እየሮጥኩ ለመውጣቴም ኮሎኔል ሬስም ቢሆኑ ይመሰክሩልኛል ።” ስትል ፑዋሮ እራሱን እየነቀነቀ ፣ “ አለመመልከትሽ ይገርማል ። በእርግጥም ደንግጠሽ ነበረ ። እኔ ግን በኮመዲኖው ላይ ምንም ነገር እንደሌለ ለመገንዘብ ችያለሁ ።” አላት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስምንት

ፑዋሮና ኮሎኔል ሬስ ሳይመን ከተኛበት ክፍል ወጥተው ቁርሳቸውን ለመብላት ወደ ምግብ ቤቱ አመሩ። በመንገዳቸውም ላይ እንዳሉ ፑዋሮ ሬስን አየት አደረገና :

“ ምን እያሰብክ ነው ፡ ሬስ ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ ቅድም ፋንቶርፕን ስናነጋግረው ከሰጠው መልስ ውስጥ አንድ ነገር እየከነከነኝ ነው። ወደ ውሃ ውስጥ የተወረወረ ነገር እንዳለ ጠቅሶልን ነበረ ። እኔም እርሱ በተናገረው ሰዓት አካባቢ ተመሳሳይ ድምጽ መስማቴን አስታውስኩ ። ምናልባት የሊኔት ገዳይ ሽጉጧን ወደ ወንዙ ውስጥ ወርውሯት ይሆን ? ” ሲል ሬስ ተናገረ ።

“ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ” ብሎ ፑዋሮ ሲመልስላት ሬስ ራሱን እንደ ማጨማደድ ብሎ :

“ በአንተስ በኩል ያለው ግምት ምንድን ነው ? ” ሲል ጠየቀው :

“ እኔ የምጠረጥረው ሽጉጧ በጃኪሊን ክፍል ውስጥ ልትገኝ እንደምትችል ነው ” አለና ፑዋሮ መለሰለት።

“ ለምን አሁኑኑ ክፍሉን እንፈትሸም ? ” አለ ሬስ ፣

“ መቻኩል ይሆናል ። ወንጀለኛውን ማንቃትና ማስበርገግ የለብንም ። ያለንበት ሁኔታ እንደልባችን የሚያዝናናን አይደለም ። ለማንኛውም ቁርሳችንን እየበላን ብንወያይ ” ብሎ ወደ ምግብ ቤቱ ገቡ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬስ ለሁለቱም ቡና እየቀዳ “ ስለ ቡርጂ ምን አስተያየት አለህ ? እኔ እንደመሰለኝ ለመሸሸግ የምትፈልገው ምሥጢር እንዳለ ነው ። ” አለ ፤

“ አንተም እንደኔ ጠርጥረሃታል ?”

“ ጥሩ ሰው አለመሆኗ በግልጽ የሚታይ ነው ።”

“ እምነት የሚጣልበት ዓይነት አይደለችም ፤”

“ በማድያው ውስጥ እጅዋን አስገብታ ይሆን ? ”

“ አይመስለኝም ”

“ በድረውስ ስርቆት ? ”

“ ለዚህ እንኳን ወደ ኋላ የምትል አይመስለኝም ።

የተቀጠረችው በቅርቡ ነው ። ምናልባትም የአንድ የተደራጀ የሌባ ቡድን አባል ልትሆን ትችላለች ። መልካም ሠራተኛ መሆኗን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት በቀላሉ አቅርባ ተቀጥራ ይሆናል።” አለና ፑዋሮ ሲያቆም፣

“ያስ ፍሊትውድ የተባለው ሰው?”አለና ሬስ ጠየቀ።

“ እርሱን አስጠርተን መጠየቅ ይኖርብናል ። ቀላልም መፍትሔ እናገኝ ይሆናል ። ቡርጂ የነገረችን እውነት ከሆነ በሊኔት ላይ ቂም የማይዝበት ምክንያት አይኖርም ። ምናልባትም በጃኪሊንና በሳይመን መካከል የተፈጠረውን ግጭት ከአንድ ቦታ ተሸሽጎ አይቶ ይሆናል። ሳሎኑም ባዶ እንደሆነለት ሽጉጧን ከሶፋው ሥር አንስቶ ሊኔትን ገድሏት ሊሆን ይችላል ። በተለይም ጂ የሚለውን ፊደል የጻፈው እርሱ መሆኑን ወደ ማመኑ እየተጠጋሁ ነው ።” ሲል ፑዋሮ ፤

“ እንዳልከውም ፤ የምንፈልገው ሰው እርሱ መሆን አለበት ” አለ ሬስ



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አዎን ! ብቻ ” አለና ጆዋሮ አፍንጫውን እያሻሸ ፤

“ ወንጀለኛውን እንዲህ በቀላሉ ልናገኘው እንችላለን ወይ የሚል ትንሽ ጥርጣሬ አለኝ ። ” ሲል ተናገረ ።

“ ሰማንኛውም አስጠርተን ማነጋገሩ ስለሚሻል ወደ አንተ ክፍል ብንሄድ ” አለና ሬስ ተያይዘው ወጡ ። ሬስ ንግግሩን በመቀጠል “ ሌላስ የምትጠረጥረው ሰው አለ ? ” አለና ጆዋሮን ጠየቀው ።

“ ይኖራል ! በተለይም ያ የሊኔት ሞግዚት ነው የተባለውን አሜሪካዊ ፤፣ ፔኒንግተን ”

“ ፔኒንግተን ? ”

“ አዎን እርሱን ነው በሁለተኛ ደረጃ የምጠረጥረው። ሊኔት በጣም ብልህ ልጅ ናት ። እንዳየሁት ሰነዶችን በጥልቀት ሳትመረምር ፊርማዋን አታስፍርም ። ሳይመን ግን የዋህና ቂላቂል ብጤ ፍጥረት ነው ”

“ ታዲያ ይህ ከወንጀሉ ጋር ምን ዝምድና ሊኖረው ይችላል ? ”

“ ሳይመን የሚቀርቡለትን ሰነዶች ለመመርመር ዕውቀትም ትዕግሥት የለውም ። ሲፈርማ የቀረበለትን ሁሉ ሳያነብ የሚፈርም ችኩል ባህርይ ያለው ነው ። ዝምድናው አሁን ግልጽ ሆነልህ?። ፔኒንግተን ለሳይመን የተለየ ፍቅር እያሳየ በጣም እያቀረበው ነው ። ሌላም ማስታወስ የሚኖርብህ ነገር ደግሞ ምን መሰለህ ? ፔኒንግተን በሞግዚትነት የሚያስተዳድረው ሀብት ሁሉቱ መሳፍርት የለውም ። በዚህም አጋጣሚ በሊኔት ሐብት ሲንበሸበሽ ዓመታት አልፈው ይሆናል ። እንደዚህ ስለመሳሰለው ድርጊት በመጽሐፍም በጋዜጣም ላይ የምናነበው ነው ”

“ ይህ አጠያያቂ አይደለም ” አለ ሬስ ፡ ጆዋሮ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ፔኒንግርን አርቆ በማሰብ ላይ እንዳለ ዕድሉ ፀአጭሩ ተቀጨበት ። ሲኔት ባል አገባች ። ከምግዚትነት ሥልጣኑ ባላሰበው ሰዓት ወረደ ። ከትልቅ አደጋ ላይ ወደቀ ። ስለዚህም እጁን አጣጥፎ የሚቀመጥ ሰው አይደም ሰልህ ። ሲኔት በአሁኑ ጊዜ በአፍላ ፍቅር ላይ ናት ። ስለዚህም በግዴለሽነት አንዳንድ የተሳሳቱ ሰነዶችን እንድትፈርምለት ሞከረ ። ሆኖም ሲኔት እንደታሰበው ሳይሆን ንቃትና ጥንቃቄዋ አልተጓደለም ። ፔኒንግተን ሳይመንን መወዳጀቱን መረጠ ። ለምን ? ምና ልባት ሲኔት ብትሞት ሀብቱ የሚተላለፈው ለየዋሁ ሳይመን ይሆናል ። ተዘጋጅቶ በሚቀርብለት ጽሑፍ ላይ በጭፍን ለሚፈርመው ሳይመን ! " አለ ።

" እንዳልከውም ሊሆን ይችላል ። ግን ምንም ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም "

" የሚያሳዝነው የቱ ሆነና ! "

" ያስ ፈርግሰን የሚባል ጉረምሳ ? እርሱም ቢሆን በሐብታሞች ላይ ያለው ጥላቻ ይህ ነው አይባልም ። ሳይመን እንደነገረን ከሆነ የሲኔት መልክ መለዋወጥና መበሳጨት የጀመረችው በመርከቧ ላይ የተሳፈሩትን ሰዎች ስም ዝርዝር ስታይ ነው ። ድንገትም የሲኔት አባት ካከሰራቸውና ሐብታቸውን ከወረሳቸው ሰዎች መካከል አንዱ የፈርግሰን አባት የሆነስ እንደሆነ ?" አለና ለደቂቃ ሀል ከአሰበ በኋላ " ያም እኔ የምፈልገው ነፍሰ ገዳ እኮ በተጨማሪ አለ " ብሎ ሬስ ሲያቆም ፡

" አዎን ያንተም ሰውዬ መረሳት የለበትም " አለ ፓዋሮ።በዚህም ጊዜ ፍሊት ውድ እንደተጠራ በመ ጣቱ ቀያይዘው ወደ ፓዋሮ ክፍል ገቡ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍሊ.ትውድ ግዙፍና ሲያዩት የሚፈራ ሰው ነበረ ። ፑዋሮንና ሬስን ተራ በተራ በሚቃኘው ዓይኑ ይመለከታቸው ጀመረ ። "ለምን ፈለጋችሁኝ ? " ሲልም በጥርጣሬ ጠየቀ ።

" በትናንትናው ሌሊት በዚች መርከብ ውስጥ ስለተፈጸመው ወንጀል የሰማህ ይመስለኛል ? " አለ ሬስ።

ፍሊ.ት ውድ እራሱን በማኅንበስ መስማቱን አረጋገጠ ።

"በማጇ ላይ የተለየ ጥላቻ እንደነበረህ የታወቀ ነው።" ዓይኖቹ በድንጋጤ እንዳፈጠጡ " ማን ነው ይህንን የነገራችሁ ? " ሲል ፍሊ.ት ውድ ጠየቀ ።

" አንተና ማሪ እንዳትጋቡ ያደረገችው ሊኔት እንደሆነች ደርሰንበታል "

" ማን እንደነገራችሁ አሁን ገባኝ ። ያቺ ሾካካ ገረድ ናት ፤ ቆይ ! ይቺን ውሽታም ባላደርጋላት !"

" ስለዚህ ቂም መያዝህ እውነት ነዋ ?"

" ፍጹም ፤ የማይመስል እውሸት !"

" ቀደም ሲል ካገባሃት ሚስት አራት ልጆች ያሉህ መሆኑስ እውሽት ነው ? "

" ቢሆንስ፡ ሊኔትን በእኔና በማሪ መካከል ምን ጥልቅ አደረጋት ? "

" በሕግ ያገባሃት ሚስት እያለች ፤ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ለመፈጸም ቆርጠህ ነበራ ?"

" አዎን ! ግን ያቺ እርጉም ሴት ዕቅዴን አጨናገፈችው ። በአንድ ሰው የግል ኑሮ ውስጥ ገብታ የምትበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠብጥበት ምን ምክንያት ነበራት ? ይህን ጊዜ የሞቀ ትዳር ይገጥ በአገሬ ላዩ እቀመጥ ነበረ ። ስለዚህም የም ፈራበት ምንም ምክንያት የለም ። አዎን ! በሊጹ ላይ ቂም ይገባት ነበረ ። እንደፀሐይ አንፀባርቃ በዚች መር ከብ ላይ በመሳፈር ላይ እንዳለች ሳይ ደሜ ተለዋወጠ ። ያለፈውም ትዝታዬ ተቀስቅሶ ነበረ ። ቢሆንም ፍሊት ውድ ልክስክስ ነፍስ ጉዳይ ነው ብላችሁ የምትጠረጥሩ ከሆነ ተሳስታችኋል ። ጨክኜ የሰውን ሕይወት የማጠፋ ሰው አይደለሁም ። አጠገቧም አልደረስሁ ። ይህንንም ብትፈልጉ በመሐላ አረጋግጥላችኋለሁ ” አለና እቆመ። ፊቱም በላብ ተጥለቅልቆ ነበረ ።

“ በሌሊቱ ስድስት ሰዓትና ስምንት ሰዓት መካከል የት ነበርክ ? ” አለና ሬስ አሁንም ጠየቀው ።

“ ተኝቼ ነበረ ። ከተጠራጠራችሁም መኝታ ክፍ ሌን የሚጋራኝን ሰው ልትጠይቁት ትችላላችሁ ”

“ ሁሉንም ወደፊት እናያለን ። ለጊዜው ማን ልት ሄድ ትችላለህ ” አለና ሬስ አሰናበተው ። ፍሊት ውድም እንደወጣ ፤

“ ታዲያስ ? ” ሲል ፑዋሮ ጠየቀ ።

“ እነጋገሩ እንኳን የሚያሳምን ይ ሥስላል ። በእ ርግጥ ፍርሃትና ድንጋጤ ይታይበት ነበረ ። ለማንኛውም አብሮት የሚተኛውን ሰው እናነጋግረዋለን ። ብቻ እር ሱንም ቢሆን በዛን ወቅት እንቅልፍ ወስዶት ሲሆን ስለ ሚችልፍሊት ውድ ሳይሰማበት ወጥቶ ለመመለስ ይች ላል ። ስለዚህ ሌላ ያየው ሰው ከሌለ ምንም ማድረግ አይ ቻልም ”

“ አዎን ! በዚህም አቅጣጫ ላይ ማተኮር ይኖርብ ናል ” አለ ፑዋሮ ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

" የሚቀጥለው ተግባራችን ከመንገደኞቹ መካከል የተኩስ ድምጽ የሰማ ሰው መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ይሆናል ። ዶክተር ቤስነር እንዳለው ሊኔት የተገደለችው ከሌሊቱ ስድስትና ስምንት ሰዓት መካከል ነው ። አንተስ ምንም አልሰማህም ? " ሲል ፑዋሮን ጠየቀው ።

" እንደ ግንድ ተጋድሜ ነበረ ለማለት እችላለሁ ። የእንቅልፍ ክኒን እንደወሰደ ሰው ነበረ ሳልላወስ ያደርኩት " አለ ፑዋሮ ።

" እስቲ ለማንኛውም ሚስስ አለርተንና ልጅዎን ተራ በተራ በቅድሚያ ጠርተን እናነጋግራቸው ። ከሌሎቹ የተሻለ ትብብር ያደርጉልን ይሆናል " አለና ሬስ ደወል ደወለ ። የመርከቧም ተላላኪ እንደገባ ሁለቱን ሰዎች እንዲጠራቸው ነገረው ።

ሚስስ አለርተን ከቀረበላት ወንበር ላይ እንደተቀመጠች " እንዴት የሚዘገንን ነገር ነው! ያቺን ቆንጆና ሐብታም ልጅ የገደላት ምን ዓይነት ጨካኝ አንጀት ያለው ይሆን?። የሊኔትን መሞት እስከአሁን ለማመን ተቸግሬ አለሁ " አለች ።

" የጠለቀ ሐዘን እንደተሰማሽ ይገባኛል " አለ ፑዋሮ እየተከዘ ።

" ሆኖም እርስዎ በዚች መርከብ ላይ በመገኘትዎ ተደስቻለሁ " አለች የልቧን እውነታ በመናገር " ይህንን ጉዳይ አረመኔ ፍጥረት እንደሚደርሱበት እርግጠኛ ነኝ ። እንኳን ያቺ አሳዛኝ ጃኪሊን ያልሆነች ብቻ " አለችና " ወደተፈለግሁበት ቁም ነገር ብንመለስ " ስትል አሳሰበች ።

" ወደ መኝታሽ የሄድሽው በስንት ሰዓት እንደ ሆነ ብትነግሪኚልኝ" ?



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ”

“ ወዲያውኑ እንቅልፍ ወሰደሽ ”

“ አዎን ! በጣም ተዳክሜ ነበረ ”

“ መላውን ሌሊት ምንም የሰማሽው ነገር የለማ ?”

ሚስስ አለርተን ማንባሯን ቋጥራ ለጥቂት ጊዜ ለማ

ሲታወስ ሞከረች :“ አዎን ! ውሀ ሲንቦራጨቅ የሰማሁ ይመስለኛል ። በተጨማሪም የሩጫ ድምጽ ሰምቻለሁ ። ቅደም ተከተሉ ግን ተደናግሮኛል ። ”

“ በስንት ሰዓት ላይ እንደሆነ ታስታውሻለሽ?”

“ አላስታውስም ። ”

“ ዕድለኞች አይደለንም ማለት ነው ”

“ አዝናለሁ ። በጣምትም መናገሩ ጥሩ አይመስለኝም”

“ ሌላ የምትነግሪን የለማ ? ”

“ አዎን ! የለም ”

“ ከሊኔት ጋር ከአሁን በፊት ትተዋወቁ ነበረ ? ”

“ አንተዋወቅም ”

“ አመሰግናለሁ ። እግረ መንገድሽን ቲምን እንዲገባ ብትነግሪልን ? ” አላት ።

ቲም ከበራፉ ላይ ሆኖ ተራውን ይጠባበቅ ነበረ ። እናቱም እንደወጣች :

“ አንቺስ በቀላሉ ተገላገልሽ ፤ ለመሆኑ ምን ምን ዓይነት ጥያቄዎች አቀረቡልሽ? ” አላት ።

“ ትናንትና ማታ የሰማሁት ነገር ቢኖር እንድነግራቸው ነው የጠየቁኝ ። ምንም ነገር ባለመስማቴ አዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ናሉብ ። የሲኔትና የእኔ መኝታ ክፍል ጎን ለጎን ስለነበረ ቢያንስ የተኩሱን ጩኸት መስማት ነበረብኝ ። ግባላቸው ቲም ! እየጠበቁህ ነው! ” ብላ ሔደች ።

ጭዋሮ ለቲምም ያቀረበለት ጥያቄ ከበፊቱ ጋር ተመሳሳይ ነበረ ። ቲም “ የተኛሁት ቀደም ብዬ ነው ። ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል ይሆናል ። ለጥቂት ጊዜ መጽሐፍ እንብቤ መብራቱን እንዳጠፋሁ እንቅልፍ ወሰደኝ ” ሲል መለሰ ።

“ ከዚያ በኋላ ምንም የሰማኸው ነገር የለም ? ”

“ አንድ ሰው ፡ ኮሪደሩ ላይ ቆሞ ደህና እደሪ ብሎ ሲናገር ሰምቻለሁ ። ”

“ እርሱ እንኳን እኔ ነኝ ። የካርታ ጨዋታችንን ጨር ሰን ከሳሎኑ ከወጣን በኋላ ሲኔትን መኝታ ክፍሏ እድር ሼአት በደህና እደሪ ብዬ ተሰናብቻት የነበርኩት ” አለ ሬስ ።

“ ሊሆን ይችላል ። ከዚያ በኋላ እንቅልፍ ወሰደኝ። ቀጥሎም ድም ድም የሚል የሩጫ ድምጽ ሰማሁ ፡ ተከ ታትሎም ወደ ወንዙ ውስጥ የሆነ ነገር ስለተወረወረ ውሀው ተንቦጫረቀ ። የዶክተር ቤስነርንም ድምጽ በተ ጨማሪ የሰማሁ ይመስለኛል ። ”

“ ከዚያስ ? ”

ቲም ለጥቂት ጊዜ አሰበና “ የፋንትሮፒ መኝታ ክፍል በር ሲከፈትና ሲዘጋ ሰምቻለሁ ። እኔም ሰውየው እንቅልፍም አያወስደው ስል ተገርሜ ነበረ ”

“ ይኸው ብቻ ነው ? ”

“ አዎን ። ከዚያ እንቅልፍ ወሰደኝ ”



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ዘጠኝ

ኮሎኔል ሬስ ፣ ከሊቤት መኝታ ክፍል ፊት ለፊት ያለውን ሴላ መኝታ ቤት ይዛ የነበረችው ሚስ ቫን ሻይለር እንድትጠራ አደረገ ። ከአዘቦቱ ቀን ይልቅ ዛሬ ቫን ሻይለር ፊቷ ተጨመዳዶ የዕድሜዋን መግፋት በግልጽ ያሳያል ። እንደ እባብ ዓይን የሚቁለጨለጩት ትንንሽ የሆኑት ጥቁር ዓይኖቿ በክፋት የተበከለ መንፈሷን ያንጸባርቃሉ ። ሬስ ብድግ ብሎ ሰላምታ ከሰጣት በኋላ ወንበር እያቀረበላት " ስላስቸገርንሽ ይቅርታ እጠይቃለሁ " ሲል ፤

ሚስስ ቫን ሻይለር በዚያ በሰላላ ድምጿ " እኔን በዚህ ጉዳይ ውስጥ መደባለቃችሁ ተገቢ አይደለም ! ። የተሰማኝ ቅሬታ ከፍተኛ ነው ! በቅድሚያ የሰውን ልክ ማወቅ አለባችሁ !" አለች ።

" እውነት ነው እመቤት ቫን ሻይለር ። ስህተት እንደሆነ ገብቶናል ። ለፑዋሮም ቢሆን ይህንኑ ሳጫወተው ነበረ ለማንኛውም ጊዜሽን ሳናባክን ለይስሙላ ያህል አንዳንድ ጥያቄዎች አቅርበንልሽ በቶሎ እንድትሄጂ ቢሆን ? " አለ አሁንም ሬስ ።

ሚስስ ቫን ሻይለር ከበፊቱ ሻል ብላ ወደ ፑዋሮ እያየች " የስሜቴን መጎዳት ሁለታችሁም ያወቃችሁ ልኝ መሆኑ ጥሩ ነው ። እንደዚህ ያለ ነገር በሕይወቴ ውስጥ ሲገጥመኝ የመጀመሪያ ጊዜ ነው " አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፒዋሮ በማገባበል ጭምር " እኛም ይገባናል ። ስለ ዚህም በአጭሩ እንድትገላገይ ወደ ጥያቄው ብናመራ" አለና ሳታቋርጠው ፤ " በስንት ሰዓት ነበረ ትናንት ማታ ወደ መኝታ ቤትሽ የሄድሺው ? " አለ ።

" እንደልማዴ ከምሽቱ በአራት ሰዓት ። ግን ኮርኔ ሊያን ስጠብቅ እንቅልፍ አልወሰደኝም ነበረ ። "

" ዕድለኞች ነን ማለት ነው ። ታዲያ ከተኛሽ በኋላ የሰማሽው ነገር ነበር ? "

" የመንኮሻኮሽ ድምጽ ስሰማ ወደ እኔ ክፍል የገባ ሌባ አለ ብዬ ተነስቼ ነበረ ። ሆኖም ድምጹ የመ ጣው ከእኔ ፊት ለፊት ካለው ክፍል ውስጥ ኖሯል ። "

" ከማን ? ከሊኔት ክፍል ?"

" አዎን ! ከዚያም በኮሪደሩ ላይ የሰው እንቅስቃሴ ነበረ ። ቀጥሎም ወደ ወንዙ ውስጥ የተወረወረ ነገር ስለነበረ ውሀው ሲንቦጫረቅ ሰምቻለሁ ። "

" በስንት ሰዓት ላይ እንደነበረ አታውቂውም ? "

" ለምን ? ሰዓቱን በትክክል ለመናገር እችላለሁ ። ከምሽቱ ስባት ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ነበረ ። "

" እርግጠኛ ነሽ ? "

" አዎን ፤ የጠረጴዛ ሰዓቱን ተመልክቼ ነበረ "

" የተኩስስ ድምጽ አልሰማሽም "

" አልሰማሁም "

" ምናልባት በዚያን ጊዜ እንቅልፍ አሸልቦሽ ይሆናል ለመሆኑ ስለውሃውስ መንቦጫረቅ የምታውቂው ነገር ይኖር ? "

" በሚገባ እንጂ ፤ በትክክል ነው የማውቀው "



t.me/OLDBOOKSPDF

ኮሎኔል ሬስ ከተቀመጠበት ተነስቶ “ እውነትሽን ነው ? ” አለና ጠየቀ ።

“ እርግጠኛ ሆኜ ነው የምናገረው ! ሰው ከተኛ በኋላ ጸጥታ መስፈን አለበት ። ታዲያ ቀደም ሲል እንደ ነገርኳችሁ የእንቅስቃሴ ድምጽ በመስማቴ በራፌን ከፍቼ ተመለከትሁ ነበረ ። በዚያንም ወቅት የዶራሲዋ የሚስስ ፀተርበርን ልጅ የሆነችው ሮዛሊ አንድ የተጠቀለለ ነገር ወደ ወንዙ ውስጥ ስትወረውር አይቻታለሁ ።። ”

“ ሮዛሊ መሆኗን በምን አወቅሽ ? ” አለ ፑዋሮ ፡

“ መልኳን አስተካክዬ ለይቻዋለሁ ”

“ እርሷስ አላየችሽም ? ”

“ ያየችኝ አይመስለኝም ”

ፑዋሮ በሆዱ “ ጉድ ፈላ!” አለና ወንበሩን ወደ እርሷ ቀረብ በማድረግ ፡

“ የፊቷ ሁኔታ እንዴት ነበረ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ ለመግለጽ የሚያስቸግረኝ ስሜት ይነበብበት ነበር”

ሬስና ፑዋሮ ተሰራርቀው ተያዩ ።

“ ከዚያስ ? ”

“ ወደ መኝታ ክፍሏ መግባቷን እንዳየሁ ፡ በራፌን ዘግቼ ወደ አልጋዬ አመራሁ ። ”

በዚህን ጊዜ የፑዋሮ ክፍል በር ተንኳኩቶ የመርከቧ ካፒቴን ገባ ። በእጁም ከያዘው አንድ ጥቅል ጨርቅ ውስጥ ውሀ ይንጠባጠብ ነበረ ። እርሱም “ ይኸውና ተገኘቷል! ኮሎኔል !” አለና ለሬስ ሰጠው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬሏ እየተጣደፈ እንደ ነገሩ ታጥሮ የነበረውን ሻርፕ ፈታቶ ሲዘረጋው አንድ በቀይ ቀለም በበለዘ መሐረብ የተጠቀለለች ትንሽ ሽጉጥ ብቅ አለች ። ሬስ ሽጉጧን በመዳፉ መሐል እያገላበጠ ፤

" አየህ ! የእኔ ግምት ልክ ነው ማለት ነው ። ወደ ወንዙ ውስጥ ተወርውራ ሊሆን ይችላል ብዬ ነበረ " አለና ለፑዋሮ ቀረብ አድርጎ እያሳየው ፤ " ምን ታስባለህ ፑዋሮ ? ጃኩሊንን በካታራክት ሆቴል ውስጥ ስታነጋግራት ያሳየችህ ይቺን ሽጉጥ ነበረ ? " ሲል ጠየቀው ።

ፑዋሮ ሽጉጧን ተቀብሎ በጥንቃቄ ከተመለከተ በኋላ " አዎን !! ሽጉጧ ይችው ነበረች ። በእጀታዋም ላይ ጄ-ቢ የሚል ምህጻረ ቃል ተጽፎበታል ። ይኸውም ጃኩሊን ቤልፎርት ማለት ነው " አለና ጥይቶቹን ሲያፈናጥር ሁለት ባዶ ቀበሆች ለብቻቸው ወደቁ ።

ሳይታሰብም "ሻርፑን?" አለችና ሚስስ ቫን ሻይለር ጠየቀች ፡

" የምን ሻርፕ!" አለ ሬስ እፍጦ እየተመለከታት

" ሽጉጧ የተጠቀለለችበት ሻርፕ ማለቴ ነው "

" ይሄ የአንቺ ሻርፕ ነው ? "

" አዎን ! "

እውነትም ያሻርፕ ከሚስስ ቫን ሻይለር ትከሻ ላይ የማይወርደው ያ ሰማያዊ ሻርፕ ነበረ ። ፑዋሮ ወደ ሬስ ተመለከተ ። ሬስም አንገቱን ጐንበስ በማድረግ ስለነገሩ ትክክለኛነት አረጋገጠ ።

" የት ነበረ ያስቀመጥሽው ? " አለና ፑዋሮ ጠየቃት፣
" ከሳሎኑ ውስጥ ነበረ ። "



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬስ ሻርፑን እየዘረጋና በጣቱ እያመለከተ “ ሻርፑ ለምን ጥቅም ውሎ እንደነበረ ተረድተሻል ! እነኝህ የሚታዩት ቀዳዳዎች ሁሉ ምን ይመስሉሻል ? የተኩሱን ጩኸት ለመቀነስ ሲባል በሽጉጡ አፈሙዝ ላይ ተደርጎ ነበረ ” ሲል ፤

“ ድፍረትም ! ብልግናም ነው ! ” አለች ሻን ሻይ ለር ፊጠን ብላ ።

“ ለመሆኑ ከዚህ ቀደም ሲል ከሲኔት ጋር ትተዋወቂ ነበር ? ” አለና ሬስ በጥርጣሬ እየተመለከታት ጠየቀ።

“ በመልክ ከሆነ አላውቃትም ነበረ ! ”

“ በምን መንገድ ነበር የምታውቂያት ? ”

“ የማን ልጅ እንደነበረች !”

“ በቤተሰብ ደረጃ ትተዋወቁ ነበራ ? ”

“ በሩቅ የምንተዋወቅ ይመስለኛል ። ጊዜ ካንሳቸው ግለሰቦች ጋር በቅርብ መወዳጀቱን ወላጆቼ አያምኑበትም ነበረ ። እርሷን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት በዚች መርከብ ላይ ነው ” ብላ ከተቀመጠችበት ተንሥታ በሩፋን ከፍታ ወጣች ።

ፑዋሮና ሬስ ለጥቂት ጊዜ ያህል ሳይነጋገሩ ፈዘው ቆሩ ።

“ ይቺ አደገኛ አሮጊት በቀላሉ የምትበገር ሰው አይደለችም ። ከአሁን ወዲያም ብናነጋግራት ልትተባበረን ፈቃደኛ የምትሆን አይመስለኝም ። ይልቁኑ ፤ ሮዛሊን ጠርተን ሌሊት ወደ ወንዙ ውስጥ የሆነ ነገር ወርውራ ሰች ስለተባለው ጉዳይ ብንጠይቃት ” ሲል ሬስ አስተያየት አቀረበ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ፑዋሮ ግን በሌላ ሐሳብ ተውጦ ነበረ ። ቆይቶ ቆይቶም ቀና አለና “ እንደ ዛሬ ነገሩ ሁሉ ተምታቶብኝ አያውቅም ” ሲል ፡

ሬስ “ ለምን ? ” አለው ።

“ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የወንጀሉ ቅንብር ግልጽና ቀላል ነው ። ሊኔትን ለመግደል የሚፈልግ ሰው ነበረ ። በትናንትናው ምሽት በሳሎኑ ውስጥ ተደብቆ በሳይመንና በጃክሊን መካከል የተፈጠረውን ግጭት ተመለከተ ፡ ከሶፋው ሥር የተወረወረችውን ሽጉጥ ወስዶ ፡ ሊኔትን ገደለና ገዳይዋ ጃክሊን እንደሆነች ለማስመሰል ጄ የምትለዋን ፊደል በግርግዳው ላይ ጻፈ ። እስከዚህ ደረጃ ድረስ ያለው ወለል ብሎ የሚታይ ነው ። ወንጀለኛዋ ጃክሊን መሆኗን ለመጠቆም የተደረገ ሙከራ ነው ። ግን ” አለና ፑዋሮ ለጥቂት ጊዜ ከተከዘ በኋላ “ ግን ፡ ገዳይዋ ጃክሊን ናት ብሎ ጥርጣሬ ሊያሳድር የሚችለውን መረጃ ለማጥፋት ለምን ሙከራ ተደረገ ። ሽጉጧ ለምን ወደ ወንዙ ውስጥ ተወረወረች ። ለምን ይመስልሃል ሬስ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ እውነትም ግራ የሚያጋባ ነው ” አለ ሬስ የፑዋሮ ትንታኔ ገብቶት ፡

“ ግራ የሚያጋባ ብቻ ሳይሆን ፡ መሆንም የማይችል ነገር ነው ፡ ”

“ መሆንማ ሆኗል ፑዋሮ ! ” አለው ሬስ ።

“ ወንጀሉ አልተፈጸመም ማለቴ አይደለም ። የሁኔታዎችን ቅደም ተከተል ስመለከተው በዚህ መንገድ ሊፈፀም እንደማይችል በማመኔ ነው ። ገና ብዙ ልፋት ይጠብቀናል ” አለ ፑዋሮ አሁንም እንደተከዘ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥር

ኰሎኔል ሬስ ፑዋሮን በአድናቆት ይመለከተው ነበረ። ለፑዋሮ አእምሮ ብሩህነት የነበረው አክብሮት እየጨመረ ሄዷል ። ፑዋሮ የተወሳሰቡ ችግሮችን ለመፍታት የማይዳሰሰው ማዕዘን የማያስሰው ነገር አልነበረም ። ስለ ዚህም ሬስ ብዙውን ጊዜ የፑሮን አስተያየቶች መጠበቅ ነበረበት ። በመሆኑም ። “ ቀጥሎስ የምናደርገው ምንድን ነው ። ሮዛሊን ማነጋገር ያለብን ይመስለኛል ” ሲል ለፑዋሮ የበኩሉን ሐሳብ አቀረበ ።

“ አዎን ፡ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ሊወስደን ይችላል ” አለ ፑዋሮ ።

ሮዛሊ ተጠርታ ስትገባ ፡ ያዘኔች ብትመ ስልም የፍርሃትና የድንጋጤ መልክ አይታይባትም ነበረ ።

“ የተፈለግሁት ለምን ነበረ ” ስትልም ጠየቀች ።

“ ስለ ሊኔት ሞት ምርመራ በማካሄድ ላይ ነው ያለነው ። ስለዚህ በትናንትናው ሌሊት ምን እንዳደረግሽ ብትነግሪን ?” አሏት ሬስ ።

ሮዛሊ ለጥቂት ጊዜ አሰላሰለች ፡ ከዚያም “ እኔና እናቴ ወደመኝታ ቤታችን የሄድነው ከምሽቱ አምስት ሰዓት በፊት ነው ። ወዲያውም እንቅልፍ ስለወሰደኝ ምንም የሰማሁት ነገር የለም ። ግን ዶክተር ቤስነር ክፍል



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ሰዎች ይንሾካሾኩ ነበር መሰለኝ ። ሌሊት የተ ፈጸመውን ጉድ የሰማሁት ዛሬ ጠዋት ነው ” አለች ።

“ ተኩስ አልሰማሽም ? ”

“ አልሰማሁም ”

“ ሌሊቱን ከመኝታ ቤትሽ አልወጣሽም ነበረ ? ”

“ አልወጣሁም ”

“ እርግጠኛ ሆነሽ ነው የምትናገሪው ? ”

“ ምን ማለትም ነው ? የተናገርኩት እውነቱን ነው!”

“ ለምሳሌ ከመኝታ ክፍልሽ ወጥተሽ ወደ ወንዙ ውስጥ ምንም ነገር አልወረወርሽም ?”

ፊቷ እየቀላ “ ወደ ወንዙ ውስጥ ምንም ነገር እንዳትወረውሩ የሚል ደንብ አለ እንዴ ? ” አለች ።

“ ደንብ ስለሌለ ወርውረሻል ማለት ነዋ ? ”

“ አልወረወርኩም ። ከመኝታ ክፍሌም አልወጣ ሁም ብየ አንድ ጊዜ ተናግሬአለሁ !”

“ ያየሽስ ሰው ቢኖር ? ”

“ ማን ነው አይቻትአለሁ ያለው ? ”

“ ሚስ ቫን ቫይለር ”

“ ሚስ ቫን ቫይለር ? ” አለች በፊቷ ላይ የጥርጣሬ መንፈስ እየታየ ።

“ አዎን ! ሚስ ቫን ቫይለር በራፏን ከፊት አድርጋ ስትመለከት የትጠቀለለ ነገር ወደ ወንዙ ውስጥ ስት ወረውሪ አይታሻለች ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮዛሊ እንደመደናገጥ ብላ “ ፍጹም እውሸት ነው ። ኧረ ለመሆኑ አይቻታለሁ ያልከው በስንት ሰዓት ላይ ነበረ ? ” አለች ።

“ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከአሥር ደቂቃ ሲሆን ነው ” አለና ፑዋሮ መለሰላት ። አንገቷን እንደማቅርቀር ብላ “ ሌላስ ያየኸው ነገር ነበረ ? ” ብላ አሁንም ጠየቀች፣

ፑዋሮ ሁኔታዋን እያጠና “ ሌላ ያየሁት የለም ። ግን የሰማሁት ነበራት ” አላት ፡

“ ምን ሰማህ አልክ ? ”

“ በሊኔት ክፍል ውስጥ የሌላ ሰው እንቅስቃሴ እንደ ነበር ”

“ እህ ! ” አለች ሮዛሊ ሰውነቷ እየተሸማቀቀ ፡

“ አሁንም ወደ ወንዙ ውስጥ ምንም ነገር አልወረ ወርኩም ስትዬ ትክጃለሽ ? ”

“ በእኩሉ ሌሊት ላይ እየቀሰቀሰ ወደ ወንዝ ውስጥ ዕቃ የሚያስወረውር በሽታ አልተጤናወተኝም ”

“ በሽታ ማለት ሳይሆን ፡ የተለየ ምክንያት ሊኖርሽ ይችላል ” አለና ፑዋሮ ቫርፑን በመግለጥ ያቺን ትንሽ ሽጉጥ አሳያት ። ሮዛሊ ድንግጥ አለችና ወደ ኋላዋ በማፈግፈግ ፡

“ ሊኔት የተገደለችው በዚህ ነበረ ? ” አለችና ጠየቀች

“ አዎን ! ሮዛሊ ” አለ ፑዋሮ በለዘብታ ።

“ እና ፡ እኔ እንዳደረግኩት የተጠራጠራችሁ ይመስለኛል ። ጊዜአችሁን በከንቱ ባታጠፉ ይሻላል ። ሊኔትን የምገድልበት ምንም ምክንያት የለም ። ከአሁን



t.me/OLDBOOKSPDF

በፊትም ቢሆን ትውውቅ የለንም ። ስለዚህ አጉል አት ልፉ ! ” ብላ ከመቀመጫዋ ተነሳች ።

“ ማስታወስ የሚኖርብኝ ስለሚስ ቫን ሻይለር ቃል ነው ። ፍርድ ቤት ቀርባ በመሐላ አረጋግጣ እንደምትቀመ ስክርብኝ ማወቅ ይገባኛል ። ”

ሮዛሊ ሳቅ አለችና “ ይቺ ያረጀች ድመት ! ስመሆኑ ዓይኗስ አስተካክላ ያይላታልና ነው ። እኔን አላየችኝም ! ስለዚህም እንድሄድ ፍቀዱልኝ ” ብላ ክፍሉን ለቃ ወጣች።

ሬስ ሲጋራውን እያቀጣጠለ “ ሁለት ተቃራኒ አን ጋገሮች ! የማንኛቸው ይሆን የሚታመነው ? የቫን ሻይለር ወይንስ የሮዛሊ ? ” ሲል ፑዋሮ ፡

“ ሁለቱም ቢሆን ለመሸፋፈን የሚፈልጉት ነገር እንዳለ ገምቻለሁ ” አለ ።

“ በወንጀል ምርመራ ወቅት ብዙ ጊዜ የሚያስቸግ ረን ይህን የመሳሰለው ጉዳይ ነው ። ሰዎች እንድን ወን ጀል ባይፈጽሙም በተለያዩ ምክንያቶች የቱንም እውነቱን ለመናገር የማይፈልጉበት ጊዜ አለ ። ቀጥሎ ምን እና ድርግ? እንደጀመርነው ተራ በተራ ማነጋገሩን እንቀጥል ?” ሲል ሬስ ጠየቀ ።

“ ይመስለኛል ። ምርመራችን ፈር እንዲይዝና በዘዴ እንዲመራ ያስፈልጋል ” ሲል ፑዋሮ ፡ ሬስ የመጥሪያውን ደወል ደውሎ ዶራሲዋ ሚስስ ዑተርቦርን እንድትጠራ አደረገ ።

ሚስስ ዑተርቦርን ሴሊቱን ሙሉ በከባድ እንቅልፍ ላይ ስለነበረች እንዳችም ነገር አለማየቷንም ሆነ አለመ ስማቷን ብትገልጽም ፡ ስለወንጀሉ አፈጻጸም በበኩሏ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለአባት ጥርጣሬ አስተያየት ለመስጠት ፈልጋ ነበረ ።
"የወንጀሉ መንስኤ ቅናት ነው ፤" ስትል ጀምራ "በተለይም ሴቶችን በቀላሉ የሚያጠቃቸው ስሜት ቅናት ስለሆነ ፤ ያቺ ጃክሊን የሚሏት በሌሊት ከመኝታ ቤቷ ተነስታ ፤ ሽጉጧን በእጅዋ እንደያዘች . . ." ስትል ጥዋር እጇን ብድግ በማድረግ አስቆማትና ፤

'ሊኔትን የገደለችው ጃክሊን አለመሆኗን አውቀናል ። አረጋግጠንማል ! " ሲል ገለጸላት ።

"እንግዲያውስ ባሏ ሳይመን መሆን አለበት ።" አለች ቶሎ ብላ ባለመሸነፍ "መንስኤውም በወሲብ ግንኙነት አለመጣጣም ነው ። አንደኛው ወገን ቀዝቃዛ ሆኖ ሲገኝ ማስወገጃው ዘዴ መግደል ለመሆኑ ተጨባጭ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ለማስረዳት እችላለሁ " ብላ ለመ ቀጠል ስትል ሬስ በትራው አቋርጧት ፤

"ሳይመን ክጉልበቱ ላይ በጥይት ቆስሎ ሌሊቱን ያሳለፈው ከዶክተር ቤስነር ጋር ነው " አለና አስረዳት ። የሚስስ ዑተርበርን ፊት ቅጭም አለ ። ተስፋ ወደመቁ ረጡ ብትቃረብም የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ አእም ሮዋን በፍጥንት አሠራች ፤

"እሁን ደረስኩበት! እስከአሁን ደድቤ ኖሯል ! ሚስ ባወርስ መሆን አለባት ! " ስትል ሬስ ፤

"ሚስ ባወርስ ? " አለና ጠየቃት ፤

"አዎን ! ያለአንድ ጥርጥር እርሷ ናት ! የሚጠይ ቀው ጥቂት ሥነ ልቦናዊ ጥናት ብቻ ነው ። የወሲብ ስሜቷን ለማርካት ያልቻለች ፤ በወንዶች የተናቀች ድንግል ፤ በመ ልክ ቀናው ሳይመንና በውቧ ሊኔት መካከል ያለውን የጋለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍቅር ሲታይ በቅናት ታራለች፣ ትኰማተራለች ። ክትት ላችሁን በርሷ ላይ አጠናክሩ፣ ወንድን ለመግረክ የማት ችል፣ሳታገባ ያረጀች ልጃገረድ!'የደረቀው ወይን' በሚል አርዕስት የደረስኩትን መጽሐፍ ብታነቡት . . . " ብላ ገለጣዋን ከመቀጠሏ በፊት ኰሎኔል ሬስ በዘዴ፣

" በሰጡን ትምህርት ተመርተን የምርመራችንን አቅጣጫ በአስቸኳይ እናስተካክላለን ። በጣምም እናመ ሰግንዎታለን " ብሎ አሰናበታት ። እንደወጣችም፣

" ምን መርዘኛ ሴት ነች ። ስንቱን ለማነካከት ሞከ ረች ። መግደል እንደዚች ዓይነቷን ነበረ " አለና እስተ ያየቱን ፈሰጥ ፣

" ማን ያውቃል ? " ሲል ፑዋሮ ተናገረ ።

" ከእንግዲህ የቀሩን ሶስት ሰዎች ብቻ ናቸው ። ሲኞር ሪቼቲ፣ ኰረምጣው ፈርግሰንና፣ የሲኔት ሞግዚት አሜሪካዊው ፔኒንግተን ናቸው " አለ ሬስ ወደ ፑዋሮ እያየ ፣

" ፔንግተንን የምናነጋግረው በመጨረሻ ይሆናል። በቅድሚያ ሪቼቲና ፈርግሰንን አስጠራቸው"አለው ፑዋሮ፣ ሺኞር ሪቼቲ በጣም ተናዷል ። እራሱን መቆጣጠር አቅ ቶት እጆቹን እያወናጨፈ ፣ ጉላ ባለ ድምጽ " ምን ዓይነት አረመኔነት ? ምን ዓይነት አውሬነት ነው ? በዚያች ወጣትና ውብ ልጅ ላይ የጨከነ ልብ ምን ዓይ ነት ልብ ይሆን ? የሰውን ዘር የሚያስጠላ ኢሰብአዊ ድር ጊት ! . . . " እያለ ስሜቱን ገላልጾ እንዳቆመ ለቀረቡ ለት ጥያቄዎች ሁሉ እጥር ምጥን ያለ መልስ ሰጠ ። እራትም እንደበላ ወደ መኝታ ክፍሉ እንደሄደና በቅርቡ የመጣለትን የታሪክ መጽሔት ሲያነብ ቆይቶ ከምሽቱ አም



t.me/OLDBOOKSPDF

ስቶ ሰዓት በፊት እንቅልፍ እንደወሰደው ተናገረ ። የተኩስም ሆነ ሌላ ድምጽ እንዳልሰማ አረጋግጠ ፣ በሊጀት ሞት የተሰማውን ሐዘን በድጋሚ ከገለጸ በኋላ እንጂስ ናበት ተደረገ ።

ለፑዋሮም ሆነ ለሬስ ወጣቷን ፈርግሰንን በቀላሉ ለማግባባት ተስኗቸው ነበረ ። ወደ ክፍሉም እንደገባ እግሮቹን ማዶና ማዶ በንቀት አወናክሮ ከተቀመጠ በኋላ፣

" ይህ ሁሉ ሽብ እረብ ምንድን ነው ? " ሲል ንግ ግሩን በፌዝ ጀምሮ " አንድ ሴት የሞተች እንደሆን እስከ ዚህ የሚያስጠብብ የሚያስጨንቅ ነው ? ዓለም እንደ ርሷ ባሉ አልፍ አእላፍ ዋጋ ቢስ ሴቶች የተጥለቀለቀች መሆኗ ተረሳችሁ ? " አለ ።

በዚህ ባልታሰበ ምልቃቃ እንጋገርኩሎኔል ሬስ በን ዴት ቢያርም እራሱን እንደምንም እየተቆጣጠረ " የጠ ራንህ የትናንትናውን ምሽት እንዴት እንዳሳለፍከው እን ድትነግረን ብቻ ነው " ሲል ሊያርመው ሞከረ ።

" ብፈልግ ላቀረብክልኝ ጥያቄ መልስ ባለመስጠት እችላለሁ ። ሆኖም የሚጎዳኝ ነገር ስለሌለ " አለና ወደ ኋላው በመለጠጥ ከኪሱ ሲጋራ አውጥቶ ካያያዘ በኋላ፡ "ቀኑን ያሳለፍነው ከኮርኔሊያ ጋር የአቡ ሲምበልን መቅ ደስ ስንጎበኝ ነው ። አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ኮርኔሊያ ወደ መርከቧ ተመለሰች ፣ እኔ ግን የማካሂዳቸው ተጨማሪ ጥናቶች ስለነበሩኝ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ በዛው ቆየሁኝ ። በኋላም ትንሽ ጀልባ ተከራይቼ መጣሁ " አለ ከአፉ የሚወጣውን ጢስ ቀለበት በመሥራት እያቦለቀ ።

" መኝታ ክፍልህ ከምድር ቤቱ ውስጥ ይመስለ ኛል ? " አለው አሁንም ሬስ



t.me/OLDBOOKSPDF

" አዎ ! ከደደቦችና ሳይሠሩ ከከበሩ ሐብታሞች ጋር ለመደባለቅ ስለማፈልግ " ሲል እየሳቀ መለሰ ።

ፑዋሮ ፡ ሁለቱ ሰዎች ከመካረራቸው በፊት ጣልቃ ገብቶ " ሚስተር ፈርግሰን ! ድንገት ከእኩለ ሌሊት በኋላ የተኩስ ድምጽ ሰምተህ እንደሆነ ብትነግረን ? " ሲል በትህትና ጠየቀው ።

ፈርግሰን ለጥቂት ጊዜ ከአሰበ በኋላ " በትክክል የተኩስ ድምጽ ነው ለማለት ባልችልም ፡ የሻምፓኝ ጠርሙስ ቡሽ ሲከፈት እንደሚሰጠው ዓይነት ድምጽ የሰማሁ ይመስለኛል ። ከበላይም ባሉት ክፍሎች ሰዎች ሲራመዱና ሲሮጡ ጫጫታው ያስተጋባ ስለነበረ ሰምቻለሁ " አለና መለሰ ።

"ሌላስ የሰማኸው ድምጽ የለም ? "
"የለም ! "

" ሌሊቱን ከመኝታ ቤትህ ወጥተህ ነበረ ? "
ፈርግሰን ፈገግ አለና " አልወጣሁም ። የዚያም መልካም ተግባር ተባባሪ ሳልሆን በመቅረቴ ዕድለኛ አይደለሁም ለማለት እችላለሁ " ሲል ፡

" ሚስተር ፈርግሰን ! " አለ ፑዋሮ ጮክ አለና " እንደ ሕፃን ልጅ ልትባልግ አይገባም ። የሰው ሕይወት መጥፋቱን ታውቃለህ ። ስለዚህ ጊዜያችንን በቀልድና በቧልት ልናሳልፈው አንፈልግም ። አንተም ለምና ቀርብልህ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ብቻ ልትሰጠን ይገባል !" ሲለው ፡ ፈርግሰን በተራው በንዴት ተግ ብሮ " የመሰለኝን የመናገር መብት የለኝም ማለት ነው? ሰው ጠላቱን ማጥፋት ይኖርበታል !" አለና ዓይኑን ያጉረጠርጥ ጀመረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥዋሮ ነገሩን ወደ ያውኑ ለማብረድ በመሞከር "እንደ ማይሆ ከሆነ ግን የምትናገረውን ሁሉ ጨክነህ የምትፈፅመው አይመስለኝም" አለና "ምናልባት ሲኔትን የጠላሃት ሐብታም በመሆኗ ይሆናል ። የሆነም ታሪክ ፍሊትውድ አሜውቶሃል ብዬ እጠራጠራለሁ" ሲለው ፈርግሰን ንዴቱ እየጋለ "ፍሊትውድን ደግሞ በዚህ ጉዳይ ውስጥ የሚያገባው ምን ነገር አለ ? ለመሆንስ ለምን ታነሱታላችሁ ? " አለ ።

" ፍሊትውድ ሲኔትን ለመግደል የቆየ ፍርሽ ነበረው ። ቁጭቱን ለመወጣት ያሁኑ አጋጣሚ ጊዜ በዚች መርከብ ላይ አገኘ ብለን በበኩላችን ገምተናል " አለ ሬስ በተራው ።

ፈርግሰን ከመቀመጫው ብድግ ብሎ "ለካስ በር ዘግታችሁ ስታውጠነጥኑት የነበረው ይህንን ተንኮል ኖሯል?" አለና የሬስ ጣቱን ቀስሮ በማወዛወዝ "ዋ ! እዚያ እድሃ ሰው ላይ እጃችሁን ለማሳረፍ ብትሞክሩ የምንተያየው ከእኔ ጋር ይሆናል ! ፍሊትውድ ገንዘብ የለውም ! ፊሊትውድ የሚከራከርለት ጠበቃ ለመግዛት አይችልም ! ብላችሁ እንደሆነ ከአሁኑ እንድታውቁት ያስፈልጋል ። ክርክራችሁ ከእኔ ነው !" ሲል ዛተ ፡

" ምናልባት ማንነትህን በትክክል ብታስተዋውቀን ? " አለው ጥዋሮ እረጋ እንዳለ ።

ፈርግሰን በዚህ ጥያቄ መነሳት ፊቱ ሲቀላ ይታያል። ሆኖም "ወዳጆቼን በክፉ ቀን የማልክዳ ሰው መሆኔን ብታውቁት ይበቃል " የምትለዋን መልስ ብቻ ሰጠ ።

ውይይቱም በዚሁ ላይ እንትቶ ፈርግሰን እጆቹን እሡሪ ኪሱ ውስጥ እንደከተተ ሲወጣ ጥዋሮና ሬስ ክጓ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላው በኩል ትኩር ብለው ተመለከቱት ። ሁለቱም በግል የተለያዩ ሐሳቦችን ሲያወጡና ሲያወርዱ ቆዩ ። በመጨረሻም ላይ ሬስ “ እንጋገሩ ጋጠ ወጥ ቢሆንም እስከዚህ ሙጥጮ ልጅ አይመስለኝም ” ሲል ያልተጠበቀ አስተያየት ሰጠ ።

“ እንግዲያውስ ከለንደን ድረስ ልትፈልገው የመጣኸው ነፍስ ገዳይ ይህ ጕረምሣ አይደለማ ? ” አለና ፓዋሮ ጠየቀው ።

“ አይመስለኝም ። የእኔ ሰው ያልኩት ወንጀለኛ በዚች መርከብ ላይ ለመኖሩ የማልጠራጠር ብሆንም ፈርማሰን እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ ። ስለዚህም የእኔ ክትትል ቀስ ብሎ ይደርሳል ። ለአሁኑ ግን የጀመርነውን አጣዳፊ ተግባር ብንገፋበት ” አለ ሬስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ አንድ

የሲሴት ሞግዚት ፔኒንግተን በደረሰው አደጋ የተነሣ እጅግ ያዘኑ የደነገጠም መሰሏል ። እንደልማዱ ጢሙን በጥንቃቄ ቢላጭም የሚያብረቀርቀው ፊቱ ወዘና ጠው ልጎል ። ሽክ ብሎ በለበሰው ግራጫ ሱፍና ነጭ ሸሚዝ ላይ የሐዘን ምልክት የሆነውን ጥቁር ክራባት አስሯል። ከቸቸሮ ፊት ለፊት የነበረውን ወንበር ይዞ እንደተቀመጠ፤

" ጌቶቹ!" ሲል መናገር ጀምሮ " የሲሴት ሞት የጠለቀ ሐዘን አሳድሮብኛል ። ቅስሜንም ሰባብሮታል ። ሲሴት እንዴት ያለች ብልህ ልጅ ነበረች መሰላችሁ ? አባቷ የሚኮራባት የሚመካባት ወጣት ነበረች ። አሁን ባስታ ውስጡ ምን ያደርጋል ? ምንም ጠቀሜታ ስለማይኖ ረው ይልቅስ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ብትነግሩኝ ? የም ትጠይቁኝም ካለ ብትገልፁልኝ " አለ ።

በቅድሚያ ጥያቄ ያቀረበው ሬስ ነው ። " ሚስተር ፔኒንግተን በትናንትናው ሌሊት የሰማኸው ነገር አለ?' አለው ።

" የሰማሁት ነገር አለ ለማለት አልችልም ። ብቻ እኩለ ሌሊት ላይ በዶክተር ቤስነር ክፍል ውስጥ የሆነ የሰዎች እንቅስቃሴና የንግግር ድምጽ የሰማሁ ይመስ ለኛል ። የሲሲቱን ጉዳ ያወቅኩት ሲነጋ ነው "

" ሌላ ምንም አልሰማህም?ለምሳሌ የተኩስ ድምጽ!"
" የለም ! አልሰማሁም "



t.me/OLDBOOKSPDF

" የተኛኸው በስንት ሰዓት ላይ ነበረ ? "

" ከካርታ ጨዋታ እንደተመለስን ወዲያውኑ ተኛሁ። ይሉቻስ " አለና ፔኒንግተን ወደ ጥዋሮ አንገቱን አስግጎ ድምፁን ዝቅ በማድረግ ፡ " እናንተ ከኑጋ ጀምሮ ከዚች ክፍል ውስጥ አልወጣችሁም ። በተቀሩት መንገደኞች መካከል አንድ ወሬ እየነፈሰ ነው ። ሊኔት ምሥጢሩን ባትነግረኝም በእርሷና በጃኩሊን መካከል ቅራኔ ነበረ። ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ ሳይመን ነው ። ሴትዮዋ ላይ አተኩሩ እላችኋለሁ ። ክትትላችሁን በእርሷ ላይ ካጠናከራችሁም ብዙም እንደማትለፉ እመክራችኋለሁ ! " ሲል ፡

" ሊኔትን የገደለችው ጃኩሊን ናት ማለትህ ነው?" አለው ጥዋሮ ፡

" ለእኔ እንደታየኝ ከሆነ ፡ አዎ ! እርግጠኛ ሆኖ ሊያውቅ ማን . . . " ሲል

" አንተ ባታውቅም እኛ የምናውቀው ነገር አለ " አለው ጥዋሮ አቋርጦት ፡

" ምን ነበረ ?" አለ ፔኒንግተን በድንጋጤ አስተያየት " እስከአሁን ድረስ ያወቅነው ነገር ቢኖር የሊኔት

ገዳይ ጃኩሊን አለመሆኗን ነው ። ስለዚህ ለሎች አካባቢዎችን መዳሰስ ተገደናል ። አንተም በተጨማሪ ለምናካሂደው ምርመራ የሚረዱ አንዳንድ ፍንጮችን ልትጠቁመን ትችላለህ ብለን የጠነከረ እምነት አለን " አለው።

" እኔ ? " አለ ፔኒንግተን ስውነቱ አሁንም ስቅጥጥ እያለ ፡

"አዎን!ስሊኔት ከአንተ የሚቀርባት ሰው አልነበረም። ስለሕይወት ታሪኳ" ቢሆን ከሳይመን ይበልጥ ማወቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ትችላለህ ። ሳይመን ባዷ ቢሆንም ከተገናኙ ሁለት ወራቸው ነው ። ስለዚህ በሊኔት ላይ ቂም ያለው ሰው መኖር አለ ዞሮራንና በተለይም ሲዝትባት ወይንም ሞቷን ሲመኝ የሰማኸው ሰው ቢኖር ብትገልጽልን ? ” አለው ፑዋሮ ፡

ፔኒንግተን የደረቁ ከንፈሮቹን በምላሱ እያራራሰ “ ሊኔት ያደገችው እንግሊዝ አገር ስለሆነ ይህን ስለመሳሰሉ የግል ጉዳዮቿ አንድም ነገር አላውቅም ። ምንም ሐሳብ ሊኖረኝ እንደማይችል ሊታምኑኝ ይገባል ። ከን ማን ጋር እንደተወዳጀች፣ ምን ምን ሥፍራዎችን እንደ ምታዘወትር ስለማላውቅ ለመናገር ያዳግተኛል ”

ፑዋሮ ጥቂት አሰበና “ የሊኔትን ሞት የሚፈልግ ሰው በዚች መርከብ ላይ መኖሩ የማያጠያይቅ ነው ። በመ ጀመሪያ የእቡ ሲምበልን መቅደስ ጉብኝትን ስንወጣ ድንገት ተንከባሎ የወረደ ናዳ በማስመሰል ሊኔትን በድ ንጋይ ጨፍልቆ ሊገድላት ሙከራ ያደረገ ሰው ነበረ ። እርስ ግን ለጥቂት አመለጠች ። ምናልባት በዚያን ጊዜ በአካባቢው ላትኖር ትችላለህ ?” ሲለው ።

“ አዎን ! አልነበርኩኝም ። ወሬውን ስሰማ ግን በጣም አዘንኩ። ሆኖም በዕቅድ የተደረገ ሳይሆን አጋ ጣሚ ሊሆን ይችላል ” አለና ፔኒንግተን አስተያየቱን ጭምር ሰጠ ።

ፑዋሮ ማንባሩን በመቋጠር “ እንዳልከውም፣ በፊት ለእኔም እንዳንተው መስሎኝ ነበረ ። አሁን ግን በጥብቅ እያሰብኩበት ነው ” ሲለው ፔኒንግተን ላብ ስላሰጠመው ፊቱን ከሐር በተሠራው መሐረቡ እየጠራረገ ፡ “ የሚያሳስብ ሊሆን ይችላል ” አለና ፀጥ አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ሲኔት በዚች መርከብ ውስጥ ከተሳፈሩት ሰዎች መካከል ቂም የያዘባት እንዳለ ተናግራ ነበረ ። ቂም በቀሉንምየ ተረፈችው በአራሷ በዳይነት ሳይሆን ከቤተሰብ ተጠራርሶ በመጣ ምክንያት ነው ። ስለዚህ በዚህ ነጥብ ላይ የምታውቀውን ብትነግረን ? " አለና ሬስ ጠየቀው ፡

" ምንም ነገር አላውቅም " ሲል መልሱን ዘጋ ፡
" ሲኔት ስለዚህ ጉዳይ እንስታብህ አታውቅም ነበረ?"
" በፍፁም !"

" አባቷ በንግድ ዓለም ላይ ተሰማርቶ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ከእርሱ አልተለየህም ። ስለዚህ ኪሣራ ደርሶበት ቤት ንብረቱን የሲኔት አባት ያሸጠጠበት ሰው ካለ ብት ነግረን ? "

ፔኒንግተን ተስፋ እንደቆረጠ ሰው አንገቱን እያወዛወዘ ፡

" በንግድ ዓለም ውስጥ መክሰርና መክበር ተቆራኝ ተው የሚጓዙ መንገደኞች ናቸው ። ይህንን ሐቅ ማንም ስለሚረዳው ፣ ከስሬአለሁ ብሎ አንድም ሰው ሲዝት አል ሰማሁም ።"

" በአጭሩ የምትረዳን ነገር የለም ብለን ሐሳባችንን እንደምድማ ? "

" መሆኑ ነው መሰለኝ እንደጠበቃችሁት ሆኜ ባለ መገኘቴ አዝናለሁ።" ሬስና ፕዋሮ ተሰራረርቀው ተያዩ። ከዚያም ሬስ " እኛም አዝነናል ። ፍንጭ እናገኛለን ብለን ተስፋ አድርገን ነበረ " አለውና አቆመ ። ፔኒንግተን ውይይቱ እንዳበቃ ቢረዳም ሌላ ያሳሰበው ነገር ስለነበረ ፡

" የሲኔት ሞግዚት ሆኜ ንብረቷን ሳስተዳድር እንደ መቆየቴ መጠን ፣ አሁን ደግሞ የሕግ ወራሿ የሆነው ላይ



t.me/OLDBOOKSPDF

መን አንዳንድ መመሪያዎችን እንዲሰጠኝ እንዳነጋግረው ቢፈቀድልኝ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ ነገ ሆስፒታል ካለበት ከተማ ከደረሰንና ፡ ለባይ መን በቂ የሕክምና እርዳታ ከተደረገለት በኋላ ፡ እንደ ጥያቄህ ሁሉ ልታነጋግረው ትችላለህ ” አለው ፑዋሮ ፡

“ የሊኔትስ አስከሬን ? ” አለና አሁንም ፔኒንግ ተን ጥያቄ አቀረበ ፡

“ ምርመራው እስከሚጠናቀቅ በማቀዝቀዣ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል ” ሲል መለሰለት ።

ፔኒንግተን ቆም ብሎ የታችኛውን ከንፈሩን ደጋግሞ ከነከሰ በኋላ ሌላ ነገር ሳይናገር ተሰናበቷቸውና ወጣ ።

“ ፔኒንግተን የተጨነቀበት ነገር ለመኖሩ ግልጽ ነው ” አለ ሬስ ። ፑዋሮ እራሱን ገንበስ ቀና በማ ድረግ ለሬስ አነጋገር ድጋፉን ከገለጸ በኋላ ‘ ፔኒንግተን አንተ እንዳልከው ተደናግጧል ። ግን ምክንያቱ ምን መሰ ለህ ? እውሸት በመናገሩ ነው ። በአቡ ሲምበል መቅደስ ገብኝት ወቅት በሲኦት ላይ የተጣለውን ናዳ ማን ገፍ ትሮ እንዳንከባለለው ያላወቅን መስሎታል ። ተወው ! ምንም አይደለም !። ጊዜው እስኪያመቻችን ድረስ ፔኒን ግተንን በጥንቃቄ ልንይዘው የሚገባ ሰው ነው ። አሁን ግን ጥናታችንን ብናጠቃልል ” አለ ። ሁለቱም እንገ ታቸውን አቀርቅረው ለጥቂት ደቂቃዎች ማስታወሻ እየ ተለዋወጡ ከጻጻፉ በኋላ ምርመራቸውን የሚያጠናቅር መግለጫ አዘጋጁ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## የሊኔት አሟሟት

— ሊኔትን ለመጨረሻ ጊዜ በሕይወት ያየቻት የቤት ሠራተኛዋ ሉዊ ቡርጂ ናት ፡ ሰዓቱም ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ተኩል ላይ ነው ። ( በግምት )

— ከዚህ ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ድረስ የሚከተሉት አራት ሰዎች ማለትም ፡ ጃክሊን ፡ ኮርኔሊያ፡ ሳይመን ፡ ፋንትሮፕ በሳሎኑ ውስጥ ነበሩ ። ስለዚህ ሊኔት የተገደለችው በጃክሊን ሽጉጥ ከሆነ እነዚህ አራት ሰዎች ለጊዜው በወንጀሉ ተጠራጣሪ ከመሆን ነፃ ናቸው።

— አስታማሚዋ ሚስ ባወርስና ዶክተር ቤስነር የሕክምና እርዳታ ሲሰጡ ሌሊቱን በማሳለፋቸው እነርሱንም ማንባር ቀደም ተጠርጣሪ አላደረግ ናቸውም ።

ማሳሰቢያ ፡ ምናልባት ሳይመንን ወደ ዶክተር ቤስ ነር መኝታ ክፍል ከወሰዱት በኋላ ፡ ፋንትሮፕ ሽጉጧን ለማምጣት ወደ ሳሎኑ በተመለሰበት ወቅት እንስቷት ከደበቀ በኋላ ፡ ለዶክተር ቤስነር አጣኋት የሚል መልስ ሰጥቶት ይሆን ?

### ሊኔትን ለመግደል ሊገፋፉ የሚችሉ ምክንያቶች

— እንድሪው ፔኒንግተን ፡ የሊኔትን ሐብት በሞግዚትነት ሲያስተዳድር ለዓመታት የቆየ ሰው ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህም መሐል ሊኔት በማታውቀው ዘዴ ብዙ ንብረት በዝብዞ ሊሆን ይችላል ። አሁን ግን ባል ካገባች ምግዚትነቱ ስለሚቀርና የሠራውም ተንኰል ሊጋለጥበት ስለሚችል ፤ ሊኔትን ተሸቀዳደሞ ለመግደል ፈለገ ። በአቡ ሲምበል መቅደስ ሊኔትን በናዳ ጨፍልቆ ሊገድል የመጀመሪያውን ሙከራ አደርጓል ። ስለዚህ በትናንትናው ምሽት በጃኩሊንና በሳይመን መካከል በተፈጠረው ግጭት ሳቢያ ባገኘው አመቺ ዕድል ተጠቅሞ ሊኔትን ገድሏታል ። ሆኖም ፤ የዚያች ሽጉጥ መገኘት ጃኩሊንን ወንጀለኛ ለማድረግ አሳማኝ መረጃ መሆኑን እያወቀ ለምን ወደ ወንዝ ውስጥ ወረወራት ?

— ፍሊትውድ ፤ በሊኔት ላይ ውሎ ያደረ ቂም በቀል አለው ። ሊያገባት ከነበረችው ሴት ጋር ያለያየችው እርሷ ናት ። ስለዚህም ሊኔትን ለመግደል ጥሩ አገጣጣሚ ሆነለት ። የሳይመንና የጃኩሊንን ጥል ተደብቆ ሲመለከት ቆይቶ ሳሎኑ ባዶ መሆኑን ሲያረጋግጥ ከሶፋ ሥር የተወረወረችውን ሽጉጥ በመውሰድ ሊኔትን ገደለ ። ሽጉጧንም ወዲያውኑ ወደ ወንዝ ውስጥ ወረወረ ። ለመጠቅለያም የተጠቀመበት ያቺ መሐረብ የእርሱ ልትሆን ትችላለች ። ጃ የሚለውንም ፊደል የጻፈው እርሱ መሆን አለበት ።

ሆኖም ጃ የምትለው ፊደል ጃኩሊንን እንድታመለክት ከጻፈ ለምን የጃኩሊንን ሽጉጥ ወደ ወንዙ ውስጥ

በተገደለችበት ሰዓት አካባቢ ከመኝታ ክፍሏ ወጥታ ፡ የተጠቀለለ ነገር ወደ ወንዙ ውስጥ ስትወረውር ታይታለች ። ጥቅሉም የሲኔት ሕይወት ያለፈችባትን ያቺን ሸጉጥ የያዘው የሚስ ሻይለር ሰማያዊ ሻርፕ ሊሆን ይችላል ።

ሆኖም ሮዛሊና ሲኔት ከዚህ ቀደም አይተዋወቁም ። ስለዚህም ለግድያ የሚያደርሰው ምክንያት ግልጽ አልሆነልንም ። በውበቷና በሐብቷ ቀንታ ይሆን ? ሮዛሊን ስናያት ጨዋና ልዝብ ልጅ ናት ። መልክና ቁመናዋም ጥሩ ነው ።

— ሚስ ቫን ሻይለር፣ ሽጉጧ ተጠቅልላ ወደ ወንዙ የተወረወረችበት ሻርፕ የእራሷ መሆኑን አምናለች ። ግድያውም በተፈጸመበት ሰዓት አካባቢ በራፏን ከፍታው እንደነበረ ተናግራለች ። የሲኔት አባት ንብረታቸውን ከወረሰባቸው አሜሪካዊያን አንዷም ልትሆን ትችላለች ።

ሆኖም ምንም እንኳን ሻርፑ የእራሷ ቢሆንም እራት በሚበላበት ጊዜ የጠፋባት መሆኑን አረጋግጠናል። ይህም ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ነው ማለት ነው ። ደብቃው ነበረ ብሎ ለመጠራጠርም አጥጋቢ ምክንያት አላገኘንም ። ሳይመንና ጃክሊን በዚያን ምሽት ግጭት ይፈጥራሉ ብላ አስቀድማ ለመተንበይ እንደማትችል ተረድተናል ።

— ያልታወቀው ነፍስ ገዳይ ፡ የብዙ ሰዎች ሕይወት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖም ፡ ከሌኔት ጋር የሚያገናኘውን ምክንያት በቅድሚያ መልስ ልንሰጥበት ይገባል ።

## መደምደሚያ

በመርከቢቱ ላይ ያሉትን መንገደኞች ለጊዜው በሁለት ምድብ ከፍለናቸዋል ።

ሊኔትን ለመግደል ምክንያት ሊኖራቸው በሚችልና በወንጀሉ ለመጠርጠር በማይችሉ ፡

| ምድብ 1 | ምድብ 2 |
|---|---|
| ፔኒንግተን | ሚስስ አለርተን |
| ፍሊትውድ | ቲም |
| ሮዛሊ | ኮርኔሊያ |
| ሚስ ቫን ሻይለር | ሚስ ባወርስ |
| ሉዊ ቡርጂ (ለድሪ ስርቆት?) | ዶክተር ቤስነር |
| ፈርግሰን (በፖለቲካ ምክንያት) | ሲኞር ሪቼቲ |
| ያልታወቀው ነፍስ ገዳይ ፡ | ፋንትሮፕ ፡ |

ፑዋሮ የተዘጋጀውን ማስታወሻ ደጋግሞ ከተመለከተ በኋላ ከጠረጴዛው ላይ ወደ ዳር ገፋ አደረገና ፡

" ይህም ጥናት ከምንፈልገው ፍንጭ የሚያደርሰን ስለመሆኑ እጠራጠራለሁ ። እራሴን ደጋግሜ የምጠይቀው አንድ ጥያቄ አለ ። ያቺ ሽጉጥ ለምን ወደ ወንዝ ውስጥ ተወረወረች ሬስ ? " አለ አንገቱን አቀርቅሮ በሐሳብ እንደተዋጠ ።

" ለማወቅ የምትፈልገው ይህንን ብቻ ነው ? " አለው ሬስ በመገረም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አዎን ፡ የምሥጢሩን መክፈቻ ቁልፍ የምናገኘው ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ስንችል ነው ”

“ ምናልባት በድንጋጤ የተደረገ ሊሆን አይችልም

ጆዋር እራሱን በመደጋገም በማወዛወዝ፤ እስመ ማማቱን ገልጾ ያቺ ሽጉጥ ተጠቅልላ የነበረችበትን ቀላ ያለች መሐረብ በማንሳት ፡ “ ይቺስ ቀይ ቀለም የነካት መሐረብ የማን ልትሆን ትችላለች ? ” አለ ።

“ የጥኔንግተን መሐረቦች ሁሉም ከሐር የተሠሩ ናቸው ። ባልሳሳት እንደዚህ ያለው እርካሽ ዕቃ የፍሊት ውድ ወይንም የፈርግሰን መሆን አለበት ” ሲል ሬስ መለሰ ።

ጆዋር ግን አሁንም በሐዘን አንገቱን እንዳቀረቀረ ቆይቶ ፡ “ ምስኪኗ ሊኔት ! በሰላም አንቀላፍታለች ። ሁኔታዋን እንደእኔ ልብ ብለህ ተመልክተኸው ነበረ ? ” አለና ሬስን ጠየቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

ፒዮትርና ሬስ ብቻቻቸውን ተቀምጠው እንዳሉ በሩ ተንኳኳ ። ከዚያም የመርከቧ ተላላኪ ይቅርታ ጠይቆ ፡

" ሚስተር ሳይመን ልከውኝ ነበረ ጌታዬ ፡ አንድ ጊዜ እንዲያነጋግሯቸው ይፈልጋሉ " አለ ። ፒዮትርም ወዲያውኑ ተነስቶ ሳይመን ወደተኛበት ክፍል አመራ ። ሳይመን ትኩሳቱ እያየለ በመሔዱ ፊቱ ቀልቷል ። ከአንገቱ ሥር ፡ ከጀርባው በኩል በተደራረቡት ትራሶች ተደግፎ ቀና ብሎ ለመቀመጥ ሞክሯል ። ፒዮትርንም እንዳየው አፈር እያለ ፡

"እንደላኩብዎት በመምጣትዎ በጣም አመሰግናለሁ ። አንድ ነገር ልጠይቅዎት ስለፈለግሁ ነው ያስቸገርኩዎት " አለ ።

" ጥሩ ነው ። ልትነግረኝ ትችላለህ " ሲል ፒዮትር መለሰለት ፡ የሳይመን ፊት ይብሱን እየቀላ ሄደ ። " ስለ ጃክሊን ነው ሙሴ ፒዮትር ፡ ላያት እፈልጋለሁኝ ። ግን በቀላሉ እሺ የምትል አይመስለኝም ። ስለዚህ ደፈረኝ አይበሉኝና እርስዎ ቢጠሩልኝ ። እንቢ እንደማትልዎት አውቃለሁ ። ብቸኛ ፍጥረት ናት ። የዋልኩባትንም ግፍ ተኝቼ ሳሰላስለው አሳዘነችኝ " አለ ሳይመን ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ።

ፒዮትር በሰማው ጥያቄ ተገርሞ ሳይመንን ለጥቂት ጊዜ አየት አደረገውና " ፍላጎትህ ከሆነ እጠራልሃለሁ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብሎ ሊወጣ ሲል “ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ። በጣም ደግ ሰው ነዎት ” አለ ሳይመን ።

ፑዋሮ ጃኪሊንን መፈለግ ጀመረ ። በመጨረሻም ከሳሎኑ ውስጥ እራሷን እማልላ ጥግ ላይ ካለው ሶፋ ተጨብጣ እንደተቀመጠች አገኛት ። ባታነበውም ከጭኗ ላይ ገጾቹ የተከፈቱ መጽሐፍ ነበረ ። ፑዋሮም ቀስ ብሎ ቀረብ አለና ፤ “ ሳይመን ሊያይሽ ስለሚፈልግ እንድነግርሽ ልኮኛል ” ሲላት ፊዛ ትመለከተው ጀመረ ። እንደ መጨነቅም እንደመጠበብም እያላት ፤

“ ሳይመን እኔን ለማየት ይፈልጋል ? እውነት እኔ ለማነጋገር ፈለገ ? ” አለች ። ፑዋሮም በሁኔታዋና በጥርጣሬዋ አዝኖላት ፤

“ ነይ ተነሺ ! ከእኔ ጋር አብረን እንሄዳለን ” ብሎ እጅዋን እንደሕጻን ልጅ ይዞ እየመራት ሄደ ። ሳይመ ንም የነበረበት ክፍል በር ሲከፈት፣ ለመግባት አቅማማች፣ በእራሷም እልተማመን ብላ ቆመች ። ፑዋሮ አሁንም እጅዋን ይዞ ቀስ ብሎ ሲያስገባት ዓይኖቿ በሳይመን ላይ ተተክለው መናገርም መጋገርም አቅቷት ቆማ ቀረች ።

ሳይመን ፣ ‘ጃኪ’ በሚለው የቀድሞው የማቆላመጫ ስሟ በመጥራት “ ጃኪ ደህና ነሽ ? ” ሲል እያፈረ መና ገር ጀመረ ። እንደምንም እየተጣጣረም “ ሊታዩኝ በመ ምጣትሽ አመሰግናለሁኝ ። ብታምኚም ባታምኚም ለማ ለት የምፈልገው . . . እንድታውቂልኝ የምፈልገው . . . ” አለና የጀመረውን መጨረስ አቃተው ። ጃኪሊን ከድን ጋጤና ከፍርሃት የተነሣ ትንፋሽ እያጠራት ፤

“ ሳይመን ! ሊኔትን እንዳልገደልኳት እንድታው ቀው እፈልጋለሁ ። አላደረግኩትም ። ትናንት ማታ እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

አብድ፡ አድርጎኝ ነበረ ። ግን ለፈጸምኩብህ በደል እስከ ዘለዓለሙስ ይቅርታ ታደርግልኝ ይሆን ? ” ስትል በሳ ይመን ፊት ላይ ያንገዋብብ የነበረው የሥቃይ ስሜት እየተገፈፈ ሄደ ።

“ የምትዪው ይገባኛል ። አታስቢ ! መጨነቅም አይኖርብሽም ። ብቸኝነትም አያጥቃሽ ። ያስጠራሁሽም ይህንን ልነግርሽ ነው ” ብሎ ሲመልስላት እንባዋ እየተ ናነቃት ፤

“ ሐሳብ ይነሰኝ ? መጨነቅ ይብዛብኝ ሳይመን ? ” አለችው ።

“ በበኩሌ ቂም ያልያዝኩብሽ መሆኑን ላረጋግጥልሽ እፈልጋለሁ ። የትናንትናው እድራጎትሽ ያለፈ ስለሆነ የሞተ የተቀበረ ነው ። ምክንያቱም በትክክል ስለሚገባኝ እኔ እረስቼዋለሁ ፤ አንቺም እንደእኔ ልትረሺው ይገባል ” አለ ፈገግ እያለ ። ጃኪሊን እንባዋን መቆጣጠር አቅቷት በጉንጮቿ ላይ እየወረደ ፤

“ ገድዬህስ ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ምን ይውጠኝ ነበረ ? የትስ እገባ የትስ እደርስ ነበር ” ? እያለች ተንሰቅ ስቃ አለቀሰች ።

“ እንደማትገድይኝ አውቀው ነበረ ። ያውም ደግሞ በዚያች አሻንጉሊት ሽጉጥ ነው ሳይመን የሚሞተው ?” ብሎ ትንሽም ቢሆን ሊያዝናናት ሞከረ ።

“ የቆሰለው ጉልበትህስ ሳይመን ? ሽባስ ሆነህ የቀ ረህ እንደሆነ?” ስትል ወደተለመደው የትካዜ ዓለሟ ውስጥ ገባች ።

“ አንቺ ደግሞ ሲበዛ የዋህ መሆን የለብሽም ጃኪ ! አስዋን ከተማ ስንደርስ ሆስፒታል እገባለሁ ። ኤክስ ሬይ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንሳለሁ ፣ የተሻለም የሕክምና እንክብካቤ ይደረግልኛል።
ከዚያም የዱሮው ሳይመን እንደምሆን አትጠራጠሪ ”
ሲላት ጃክሊን ያተናነቃት ከነበረው ሲቃ ተላቃ ተንደ
ርድራ በመሔድ ከአልጋው ሥር ተንበረከከች ። ፊቷንም
በአልጋው ልብስ ውስጥ ቀብራ ከደስታ ስሜት ፈልቆ
በሚመነጨው እንባዋ አራሰችው ። ሳይመን ጸጉሯን በእ
ጆቹ እያሻሸ ቁልቁል ሲመለከታት ቆይቶ ቀና ሲል ዓይ
ኖቹ በሚያየው ትዕይንት ተደንቆ ባልተንቀሳቀሰው በጥ
ዋሮ ዓይኖች ላይ አረፉ ። አፈር እንዳለም ፑዋሮ ለስገ
ባው በራፉን በዝግታ ከፍቶ ወጣ ።

በመናፈሻ ሥፍራውም ላይ ብቻውን በሐሳብ እንደ
ተዋጠ አንድ ሁለት ጊዜ ከተመላለሰ በኋላ “ ፀሐይ እስካ
ለች ጊዜ . . . . አዎን ! ፀሐይ እስከጠለቀች ድረስ . . .
. . . አዎን ! ከዚያም በኋላ ግን ” ሲል ፣ ቃላቱ በጉሮሮ ቃል
ጥ ከነበረው ኮርኔሊያ ጋር ውስጥ ጥልቅ አሉ ። እርሷም
ጠጋ አለችና ፡

“ ሙሴ ፑዋሮ!ምን ዓይነት ንግግር እየተናገሩ ነው? ”
ስትል በየዋሕነቷ ጠየቀችው ። ፑዋሮም ያነጋገረችው ኮር
ኔሊያ መሆኗን እንዳየ የረሳውን ነገር እንዳስታወሰ ሰው
ነቃና ፈገግ ብሎ ፡

“ ፀሐይ እስካለች ድረስ ጨረቃ አትታይም ። ፀሐይ
ስትጠልቅ ግን ጨረቃ ደምቃ ተውባ ትታያለች ማለቴ
ይመስለኛል ። ሆኖም የቂሎች ንግግር ስለሆነ ዋጋ አትስ
ጭው ” ብሏት አፏን ከፍታ በማዳመጥ ላይ እንዳለች
ጥሏት ሄደ ።

በኖርዝሊም መኝታ ክፍል በኩል ሲያልፍ አንዳንድ
የጭቅጭቅ ቃላት በእናቲቱና በልጂቱ መካከል ሲወረ
ወር ሰምቶ ለደቂቃ ያህል ጆሮውን ወደ በሩ አስጠግቶ



t.me/OLDBOOKSPDF

አዳመጠ ። በኃይለ ቃል ትናገር የነበረች እናትዬዋ ሚስስ ዐተርበርን ነበረች ።

" ውለታ ቢስ ነሽ ! ለአንቺ ስል ብዙ እድል አም ልጦኛል ። ባል ሳላገባ ፡ ወይንም ፍቅረኛ ሳይኖረኝ ዕድሜዬን የገፋሁት አንቺን ለማስደሰት ስል ነበረ ። እኔን እራሀሩኳን እናትሽን እስከዚህ ትበድይኛለሽ! . . . ለምን የእኔ ስቃይ አይሰማሽም ? " ስትል ሰማ ።

ቱዋሮ እራሱን በማደፋፈር ጥርሱን ነክሶ በሩፉን ሲያንኳኳ " ማነው ? " አለች ሚስስ ዐተርበርን በዛጡ በከረረ ድምጿ ።

" ሮዛሊንን ለማነጋገር ፈልጌ ነበር " አለ ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሮዛሊ ቀስ ብላ በሩፉን በርገግ አድርጋ ስታይ ያንኳኳው ሙሴ ቱዋሮ መሆኑን ተመለከተች ። ቱዋሮ በመልኳ መለዋወጥ ተደናገጠ ። ዓይኖቿ በእንባ እንደራሱ ነበረ ። በጉንጮቿ ላይ ያስማቋረጥ የፈሰሰበት መሥመር እንደበይ ጉዳና አውጥቶ ፡ ከንፈሮቿ ክችች ብለው ደር ቀው አየ ።

" ምን ፈልገው ነበር ? " አለች ሮዛሊ እንደተናደደች " አሁን ደግሞ ምን ቀረዎት ? " ስትል ግልምጫም ጨመረችበት ።

" ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ባነጋግርሽ ደስ ይለኛል። ስለዚህ ለብቻችን ልንወያይ ወደምንችልበት ሥፍራ ፈቃድሽ ሆኖ ብንሄድ ?" አለ በመለማመጥ ጭምር ፣

" ለምን ? " አለች እየተጠራጠረች ።

" ያቀረብኩልሽ ጥያቄ ልመናም ጭምር ነው ። ስለ ሆነም እንቢ ልትይኝ አይገባም ሮዛሊ !" አለ ዓይኖቿን በሐዘን እያየ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሮዛሊ ለጥቂት ጊዜ በአእምሮዋ ውስጥ የሆን ሐሳብ ካመላለሰች በኋላ “ እስቲ ይሁና ! ” ብላ በራፉን ዘግታ ተከተለችው ። ከመናፈሻ ሥፍራውም ጥግ በኩል ያለ ውን ብቸኛ ቤት መርጠው ብረቱን ተደግፈው የዓባይን ወንዝ ዙሪያ በዝምታ ሲመለከቱ ቆዩ ። ከዚያም “ ለምን ነበረ የፈለግኸኝ ? ” ስትል ሮዛሊ በቅድሚያ ጠየቀች ።

ፒዮር የሚናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ እየመረጠ ቀስ ሲል መናገር ጀምሮ “ አንዳንድ የምጠይቅሽ ጥያ ቄዎች ነበሩ ። ሆኖም መልስ ልትሰጪባቸው እንደማት ፈልጊ በቅድሚያ አውቀዋለሁ ” አላት ፤

“ እያወቁት ፤ እዚህ ድረስ ያለፉኝ በከንቱ ነዋ ! ” አለች ጋል ብላ ፤

“ የገጠሙሽን ችግሮች ብቻሽን ልትቋቋሚያቸው ጥረት አድርገሻል ። በኃይል አምቆሽ የያዘሽው ብስጭት ውስጥ ሲያድር አደገኛ የሆን የመንፈስ ጭንቀት እንደሚያ ስከትልብሽ ታውቂያለሽ ?” አለ ፤ በተለመደው አመለካ ከቱ እያያት ።

እርሷ ግን ፤ “ስለምን እንደሚናገሩ ግልጽ አላሆነል ኝም ” ስትል መለሰችለት።ፒዮር ኮስተር አለና “ የም ናገረው ስለዶሬ ስኩብት ሐቅ ነው ። ሮዛሊ ! ሐቁ ግን ስትሰሚው የማያስደስትሽ ሊሆን ይችላል ። ሆኖም መጥፎን ነገር መጥፎ ነው ብለን ለመጥራት መቁረጥም መድፈርም ይኖርብናል ። አንቺ ብትደብቂላትም እናትሽ በመጠጥ ሱስ የተመረዘች መሆኗን ልደርስበት ችያለሁ !” ሲል ሮዛሊ ክው አለችና ቀረች ። ለመከላከል፡ለመካድ አልቻለችም ። ለመናገር እንደፈለገ ሰው አፏን ከፈትና ዚጋ ብታደርገ ውም አንዲት ቃል ሊወጣት አልቻለም ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አንቺ እንድትናገሪ አያስፈልግም ሮዛሊ ” አለና ትክሻዋን በአባትነት ፍቅር መታ መታ ካደረጋትና እንድ ምትሰማው ካረጋገጠ በኋላ “የዛሬውን ንግግር ለእኔ ተዪልኝ” ሲል ቀጠለ ። “ በአንቺና በእናትሽ መካከል ስለአለው ።ሁኔታ አስዋን ከተማ ላይ ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ በመጠኑም ቢሆን ስከታተል ነበረ ። እናትሽ ከአይጋ ላይ እንዳትወድቅ እንደምትጠባበቂና እንደምትከላከይም ተረድቼው ነበረ ። ሆኖም እናትሽ በመጠጥ ተገፋፍታ የምታደርገውን ንግግር ስሰማ ጭንቀትሽንና ጥበትሽ ለምን እንደ ነበረ ግልጽ ሆኖ ታየኝ ። ከመጠጥ ሱሰኞች አደገኛው ተደብቆ የሚጠጣው ጠጪ ነው ። በቅሊሉ ለመምከር ፡ ለማረምና ለመከታተል ያስቸግራል ። የቻልሺውን ያህል ብትሞክሪም የእናትሽን ብልሃትና አዘንጊነት ልትቋቋሚው አልቻልሽም ። የተሰያዩ መጠጦችን ከነማንና እንዴት እንደ ምታገኛቸው ፡ የምትደብቅበምትን አሳቻ በታዎች ሁል ጊዜ አስሰሽ ለማግኘት አዳግቶሻል ። በትናንትናው ምሽት ግን እንደአጋጣሚ ቀናሽና የመደበቂያዋን ሥፍራ ደረስሽበት ። የእናትሽንም ሙተኛት ከአረጋገጥሽ በኋላ ጠርሙሶቹን ሰብስበሽ በጨርቅ በመቋጠር ወደ ወንዙ ውስጥ ወረወርሽው ” አለና ንግግሩን አቁሞ ያያት ጀመረ ። ሮዛሊ ግን እንደበፊቱ ምንም ለመናገር ባለመቻሏ ፡

“ የተናገርኩት ልክ ነው ወይንስ ተሳስቻለሁ ? ” አለና ጠየቃት ። ይህን ጊዜ “ አዎን ! ልክ ነዎት ” አለች ። ቃላቶቹን እየተቸገረች አምጣ በማውጣትም “ የእናቴ ስም እንዲጎድፍ አልፈልግም ። በጊዜዋ ደራሲ ነበረች ። ስለዚህ “ ያቺ ሰካራም ” እየተባለ ጣት እንዲቀሰርባት ፡ ማፋቂያ መሳለቂያ እንድትሆን አልፈልግም ። የእርሷን ክብር ለመጠበቅ ስል አውሸት በመናገሬ ጥፋተኛ ነኝ ” አለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ቀላል ጥፋተኛ አይደለሽም ! ወደ ወንዙ ውስጥ የጨረወርሽው ሲኔት የተገደለችበት ሽጉጥ ነው በማለት በወንጀል እስከመጠርጠር የደረስሽ ከባድ ጥፋተኛ ነሽ።" ሲሏት ሮዛሊ አባባሉ ገብቷት እራሷን አቀርቅራ ቆየችም። ከዚያም :

" እናቴ የመጠጥ ሱሰኛ ለመሆን የበቃችው በእራሷ ፍላጎት ብቻ አልነበረም ። ዝናዋ በገነነበት ወቅት በዙሪያዋ ከበው የሚያሽቃብጡ በሰሰሰ እንደብታቸው የሚያታልሉ ብዙ ብዙ ጓደኞች ነበሯት ። አንዱ ከአንዱ ጋር በሌላ ጊዜ ከሌላው ጋር ስትወዳጅ ፡ የሚጐበኙን እንግዶች ለማስደሰት ከመጣው ጋር አንዳንድ መለኪያ ውስኪ ስትጐነጭ እየተለማመደች ሄደች ። በመጨረሻም ሱሰኛ ሆና በየሆቴሉ እየዞረች እስከመሳደብና መደባደብ ደረሰች ። ሥራዋን እየዘነጋችው ተሰጥኦዋም እየተገፈፈ ሄደ። በዚህ መካከል የደረሰብኝ ሥቃይ ይህ ነው አይባልም ሙሴ ፑዋሮ!" ብላ ከንፈሯን በምሬት እየነከሰች " ይህም አነሰኝና እናቴ ሲሄይፏ ጠላችኝ ። ጠላቷ መስዬ እታያታለሁ " ስትል ፡

" የምታሳዝኝ ልጅ ! " አሉ ፑዋሮ ፡

" ለእኔ እንዲያዝኑልኝ አልፈልግም ። ደግም እንዲሆኑልኝ አልሻም ። እንደተሰቃየሁ ብኖርም ሞት በቅርቡ ይገላግለኝ ይሆናል " አለች ።

" የምትይው ሁሉ ይገባኛል " አሏት አሁንም ፑዋሮ።

" ከሰው ጋር መግባባት የማልችል ፡ ቁጡና አኩራፊ መስዬ እታያለሁ ። ግን ምን ላድርግ ? ደስታዬ ፡ ሳቄና ፍልቅልቅነቴ ከአባቴ ጋር አብሮ ሞቷል ። አብሮት ተቀብሯል" ስትለው :



t.me/OLDBOOKSPDF

ጁዋሮ ከመጠን በላይ ሐዘን እሆዱ ውስጥ ገብቶ “ እኔ ንም እንዳነጋግርሽ የገፋፋኝ በየዕለቱ ከፊትሽ ላይ የማነበው ጭንቀትሽ ነው ። በወጣትነት ዕድሜሽ ይህን ያህል ትዕግሥት በማሳየትሽ አደንቅሻለሁ ” አላት ።

“ ስለተናገሩት ሁሉ አመሰግናለሁ ሙሴ ጁዋሮ ! እኔም የልቤን አውጥቼ ከእርስዎ ጋር በመነጋገሬ ጭንቀቴን ለጊዜውም ቢሆን እንድረሳው አድርጎኛል ። እርስዎ ጥሩ ሰው ሆነው ሳለ ስለባለማከብዎ ይቅርታ ያድርጉልኝ ” አለችው የተሰማትን ውስጣዊ ደስታ ከዓይኖቿ በሚንጸባረቀው ብርሃንና በጥርሶቿ ፈገግታ በማሳየት ፡

“ ወዳጆች በልብ ስለሚገናኙ የቃላት ይቅርታ አያስፈልጋቸውም ” አለና ጁዋሮ እጅዋን ይዞ ወደ መኝታ ክፍሏ ሸኛት ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ ሦስት

የምግብ ቤቱ አዳራሽ የሐዘን ቤት መስሏል ። የምግቡን ሰዓት ደርሶ ቀስ በቀስ የሚገቡት የመርከቧ ተጓዦችም ሁሉ አንገታቸውን እንዳቀረቀሩ ነው ። የልማድ ጉዳይ ስለሆነ እንጂ አንድም ሰው ቢሆን የቀረበለትን ምግብ ሆዱ ከፈት ብሎለት የሚመገብ አልነበረም ።

ቲምና እናቱ ሚስስ አስርተን የቀረበላቸውን ምግብ ነካ ነካ አያደረጉ ትንሽ እንደቆዩ ፤ ቲም በቻይና ግሂን ተርቦለት የነበረውን ሾርባ በትካዜ በማንኪያ እያንላበጠ፤

" ይሄ የአገር ጉብኝት አይባልም ፤ ወይ ሲያልቅ ጉዞ እንጂ !" ሲል በማማረር ተናገረ ። እናቱም ድምጿን ዝቅ ለማድረግ ፤

" እውነትክን ነው ልጄ ! ያቺን የመሰለች ልጅ ከመካከላችን ስትለይ ፤ ያቺን የመሰለች ለማሳጋ እንቡጥ ሳይታሰብ ስትቀጭ ማየቱ የሚዘገንን ነው ። ለዚች መርከብ ብርሃኗ ፤ ሙቀቷ ውበቷ ሊኔት ነበረች ። የእርሷ ሞት ሳያንስ ደግሞ የባሷም መቁሰል ! ጃኩሊንም ብትሆን አንደት የምትባላ አሳዛኝ ፍጥረት ናት " አለችው ።

" ጃኩሊን ? " ሲል ቲም ከቀረቀረበት ቀና አለ ።

" አዎን ! ልቤ ለጃኩሊን እንዳለቀሰላት ነው ። ባየኋት ቁጥር ብቻዋን እንደተከራመተች ነው ፣ የማደርግላት ጠፍቶኝ ነው እንጂ . . . " ስትል ቲም ለመናገር የፈለገችውን ሳያስጨርሳት ፤



t.me/OLDBOOKSPDF

«የምታደርጊላት ነገር ምን እንደሆነ ልንገርሽ እማማ? » አለ ፣ ወደ አፉ ያደረሰውን ምግብ ሳይጉርሰው በአየር ላይ እንደያዘ። " ሽጉጥን ያህል አደገኛ መሣሪያ አሻንጉሊት ይመስል የትም የሚወረውር መሚወቻ አለመሆኑን ምከሪያት !" አላት ።

" ምናልባት ከአስተዳደግ አንዳንድ ጉድለቶች ሊኖሩ ይችላሉ " ስትል ጃኪሊንን ለመደገፍ ሞከረች ።

" እንቺም ልጅ ስላለሽ ፣ አመለካከትሽ ሁሉ በርኅራኄ የተሞላ ቢሆን አያስደንቅም " አለ እየተቁነጠነጠ ።

" ቲም ! ያልጠበቅኩት የብስጭትና የመቅበጥበጥ ባህርይ አይብሃለሁ ። ምን ነካህ ? " አለችው ትኩር ብላ እየተመለከተችው ።

" እኔ ብቻ አይደለሁም ። የሁሉም ሰው መንፈስ ተረብሿል ። "

" አዎን ! ሁላችንንም ሐዘን ተሰምቶናል ። ሆኖም ደም የሚያፈላና የሚያበሳጭ ነገር ለእኔ አልታየኝም።"

ቲም በትራው እናቱን በመኰሳተር እያየ " የአሁኑም አስተያየትሽ ቢሆን የጳታሽ ንጸብራቅ ከመሆን አልፎ በአጓማኝነቱ ሁለንተናዊነት ሊኖረው አይችልም ። በንፍስ ግድያ ወንጀል መጠርጠር ከባድ ነገር መሆኑን አታውቂም " አላት ።

ሚስስ ሐሮቶን በልጅዋ አነጋገር እንደመደናገጥ ብላ " ሊሆን ይችላል " ስትል መለሰችለት ።

" ሐቅ ነው ፣ እውነት ነው ፣ ብለን ቁርጥ አድርገን መናገር አለብን እንጂ ' ሊሆን ይችላል ' ብለን እንደቀላል ነገር የምናልፈው ጉዳይ አይደለም ። በዚህች መርከብ



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ያለነው መንገደኞች ፡ አንቺም ሳትቀሪ ተጠርጣሪ መሆንሽን መገንዘብ አለብሽ ” አላት ።

“ በመደዳው ተጠርጣሪ ልንሆን እንችላለን ። ግን መጠርጠራችን ደግሞ ሊያወራጨን አይገባም !”

“ መጠርጠራችን አያበሳጭም ማለትሽ ነው ? ይህ ከሆነ ወደ መጣንበት አስዋን ከተማ ተመልሰን ስንደርስ እንጋገሬ ይገባሽ ይሆናል ። የኅሊናሽን ንጽሕና ብትተማመኚበትም የሠለጠኑ የፖሊስ መርማሪዎች ይጠብቁሻል። ስለራስሽ ማንነት ከፍተኛ ግምት በ.ኖርሽና እራስሽን ከወንጀሉ ነጻ እንደሆንሽ አድርገሽ ብትቆጥሪው ፡ ሌላ ወገን ግን ላያምንበት ይችላል ። ስለዚህም ለደቂቃ በማያቋርጥ የጥያቄ ጋጋታ በሚያጣድፉሽ ወቅት ቲም የተናገረው ሁሉ ትዝ ይልሻል ” ሲል ሚስስ አለርተን ፊቷን አለችና ፡

“ ወንጀለኛው ከዚያ በፊት ከተገኘስ?” አለች ።

“ እንዴት ሆኖ ? ” አለና ቲም ጠየቃት ፡

“ ሙሴ ፑዋሮን የመሰለ ብልህ ሰው በመካከላችን አለ ” አለችው ።

“ አሁን ይሄ ጉረኛ ሽማግሌ ምን ፋይዳ ይሠራል ብለሽ ነው ? በእርግጥ በንግግር ለመራቀቅ ወሬ ለመሰለቅና ጢሙን ለማሳመር የሚስተካከለው የለም ” አለ የእናቱን አስተያየት በማኳሰስ ።

“ ያልከው ሁሉ ትክክል ቢሆንም የመጣው እስኪመጣ ድረስ እራሳችንን ተቆጣጥረን ከብራችንን መጠበቅ ይኖርብናል ” ስትለው ቲም አሁንም በዚያው በብስጭት አነጋገር ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

" የሲኔት ሞት እንኳ ፡ ይግም የድረዋ መሠረቅ "
አለ ጆየተገረመ ።

" የሠረቀው የገደላት ሰው ይሆናል ! " ስትል ሙሴ ፑዋሮ ወደ ምግብ ቤቱ ገብቶ አጠገባቸው ካለው ወንበር ላይ ተቀመጠ ። ቲም ዓይኖቹን በማንረጥረጥ ሲመለከተውም ሚሴስ አለርተን ገና አረፍ ከማለቱ የንጽሕናዋ መንፈስ አላስችል ብሏት ፡

" ሳይመን በጣም ተጐድቶ ይሆን ? " ስትል ፑዋሮን ጠየቀችው ።

" ቁስሉ ከባድ ይመስላል ። ዕድሜ ልኩን ሽባ አድርጐ ሊያስቀረው ይችል ይሆናልም ብሎ ዶክተር ቤስነር ፈርቷል ። ምናልባት ኤስዋን ደርሰን ኤክስሬይ ከተነሣ በኋላ ስለወደፊት ዕድሉ ለማወቅ እንችላለን " አላት ።

" አይ ሳይመን ! " አለች አንገቷን ቀና ደፋ እያደረገች " ትናንትና በዚህን ሰዓት ዓለምን በእጁ ውስጥ የጨበጠ ፡ በደስታ የታጠረ ወጣት ነበረ ። ዛሬ ቁስለኛ ሆኖ ከመኝታው መንቀሳቀስ አይችልም ፡ ሊኔትን የመሰለች ውድ ሚስቱን አጥቷል ። ማንስ ከደረሰበት ድርብ ድብ ሐዘን ሊያጽናናው ይችል ይሆን ? እኔ የምመኘው . በ.ኖር . . . " አለችና ፉም አለች ። ፑዋሮም ፡

"ጨርሸው እንጂ ፡ ምኞትሽ ምን ነበረ?" ሲል ጠየቃት "በዚያች በድሃ ልጅ ላይ እንዳከረፈ እንዳይቀር ነው" አለች ።

" ስለ ጃክሊን ከሆነ አታስቢ ። ማኩረፉ ቀርቶ የሳይመን ጭንቀት ስለእርሷ ደህንነት ማሰብ ሆኗል " አለና ወደ ቲም ዞር በማለት " አንተ ጐበዝ ! የሳይመን የአሁኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

አድራጎት በሥነ ልቦናዊ ጥበብ በኩል የሚያስተላልፈው ትምህርት ግልጽ ሆኖ ይታይሃል ? ጃኩሊን ከአገር አገር ከከተማ ከተማ ስትከታተላቸው ሳይመን በንዴት ይጨሰና ያር ነበረ ። ግን ሽጉጥ ተኩሳ ስታቆስለው ፤ ምናልባትም የሰድሚ ልክ ሽባ ስታደርገው ንዴቱ ሁሉ በንን ፡ ጠፋ ። አባ ባሌ ገባህ ? ” ሲል በቲም ፊት ላይ የነበረው የጥላቻ አመለካከት እየተገፈፈ ሄዶ ፡

“አዎን ! ” አለ ። ነገሮችንም በህሊናው ውስጥ እያብላላ ቆይቶ “ተሞኝቶ እንደነበረ የተገለጸለት ይመስለኛል፡” ሲል ፡ ጨመረ ። ፑዋሮም ፡ “ ትክክል ነህ ፡ ሲኔትን ለሐብቷ ሲል በማግባቱ የወንድነቱን ክብር ሽጦት እንደነበረ ቆስሎ በተኛበት አልጋ ላይ ተገለጸለት ፡ ውሎም ሳያድር ጃኩሊንን አስጠርቶ ይቅርታ ጠይቶ ታረቀ ። ሆኖም ጃኩሊን ለጥቂት ጊዜ እንኳን ሳትግደረደር ዛሬውኑ በመታረቋ ለወደፊት መሳቂያና መሳለቂያ እየሆነች እንደምትሔድ አልጠራጠርም ። ስለዚህ . . . ” ብሎ ንግግሩን ሳይጨርስ ፡ ሚስስ አለርተን ጣልቃ ገባች፡

“ ይልቁንስ ፡ ሳይመን እንደዒት ሲሲቱን በጥይት ያቆሰለችውን ሴት በማግባቱ ይቅርታ ጠይቆ ይታረቃል ። ወንዶች ስትባሉ ምን ጊዜም ሕፃን ናችሁ ልበል ? ” ስትል ለጺታዋ ያላትን ድጋፍ በመግለጺ ፑዋሮና ቲም እየተያዩ ቀስ ብለው ተሳሳቁ ። በዚህንም ጊዜ ጃኩሊን ከምግብ ቤቱ ደረሰች ። በአጠገቡም ሊታለፍ ስትል ፑዋሮ ከመቀመጫው ተነስቶ ሰላምታ ሰጣት ። የጃኩሊን ጉንጮች ቀላልተዋል ፡ ዓይኖቿም ያለወትሮው ያበራሉ ፡ በአጭር በአጭሩም ትተነፍስ ነበረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከፒዋሮ ጠረጴዛ ማዶ ላይ ተቀምጦ የነበረው ኮሎኔል ሬስና ፒዋሮ ዓይኖቻቸው ተገጣጠሙ ። የሆነም መልእክት ተለዋወጡ ። ፒዋሮ እንሚስስ አለርተንን ይቅርታ ጠይቆ ቆሞ ይጠባበቀው ወደ ነበረው ሬስ ዘንድ አመራ ። ሬስ እጁን በማንጨብጨብ የምግብ ቤቱን ጸጥታ ካስከበረ በኋላ ፡

“ ዛሬ በዚች መርከብ ላይ ሁለት ዓይነት ወንጀሎች ተፈጽመዋል ። አንደኛው ግድያ ሲሆን ሌላኛውም ስርቆት ነው ። ስለዚህ እኔና ሙሴ ፒዋሮ በእያንዳንዳችሁ መኝታ ቤት በመዘዋወር የምናካሂደውን ምርመራና ፍተሻ እስከምንጨርስ ድረስ ማንም ሰው ከዚህ አዳራሽ ውስጥ መንቀሳቀስ አይፈቀድለትም ” ሲል በመጠኑም ቢሆን የማጉረምረም ድምጽ ከየአቅጣጫው ተነሳ ። በተለይም ፈርግሰን ፣ ፔኒንግተንና ሚስስ ቫን ሻይለር ግልጽ ተቃውሞ በማሳየት ከየመቀመጫቸው “ ብልግና ነው ! ድፍረት ነው !” እያሉ ብድግ ብድግ በሉ ፣ ሬስና ፒዋሮ የምግብ ቤቱን በሩን አስቆልፈው በመርከቧ ዘበኛ እንዲጠበቅ ካደረጉ በኋላ አሰሳቸውን ጀመሩ ።

በቅድሚያም የገቡት ከምድር ቤት ውስጥ ከሚገኘው ከሲኞር ሪቼቲ ክፍል ውስጥ ነበረ ። እረጋም ብለው መመልከት ጀመሩ ። አንዳንድ የታሪክ ቅርሶች ፣ መጻሕፍትና መጽሔቶች በያለበት ተዝረክርከዋል ። ሁለት የግሪ ደብዳቤዎች እንደ ተከፈቱ በጠረጴዛው ላይ ተቀምጠዋል ። አንደኛው ከሶርያ ፣ አንደኛው ከሮም የተላኩ ነበሩ ። የጠረጴዛውን ኪስ ፣ ቁምሳጥኑን እየከፈቱ በጥንቃቄ ተመለከቱ ። ምንም የረባ ነገር እንዳላገኙ ሲረዱ ሁሉቱም እራሳቸውን እንዳቀረቀሩ ወጡ ።

ቀጥለውም የገቡት ከፈርግሰን መኝታ ክፍል ነበረ። ቤቱ በልዩ ልዩ መጻሕፍት ተሞልቷል ። በአልጋውና በየ


t.me/OLDBOOKSPDF

ወንበሮቹ ላይ የተቀዳደዱና የቆሸሹ ልብሶች ተወርውረዋል ። በሌላ በኩል ግን ከውስጥ የሚለብሳቸው ካኒቴራና ሙታንታዎቹ ፣ መሐረቦቹ በውድ ዋጋ የተገዙ ከሐር የተሠሩ ነበሩ ።

“ በእንጋገሩ ብቻ ሳይሆን በአለባበሱም ቅራኔዎችን የሚያንጸባርቅ ጉረምሳ ! ” አለና ፑዋሮ ተቸ ። ከዚያም የተጻጻፉቸው ደብዳቤዎች ቢኖሩ በማለት የኮመዲኖውን መሳቢያ ሲከፍተው ከአንዲት በአልማዝ ካጌጠች የወርቅ ቀለበት በስተቀር ባዶ ነበረ ። ቀለበቷንም እያገላበጠ ከተመለከተ በኋላ እራሱን እንቃነቀና ካነሳበት ቦታ መልሰ አስቀመጠ ።

በኮሪደሩ ላይ ያገኙት የሚቀጥለው የመኝታ ክፍል የሊኔት ሠራተኛ የሉዊ ቡርጌ ነበረ ። ቡርጌ በምሣ ሰዓት ላይ በምግብ አዳራሹ ውስጥ አልነበረችም ። የእነሬስም ግምት በእመቤቷ ሞት የተነሣ ከመኝታ ክፍሏ ውስጥ ስታለቅስ እንደሚያገኟት ነበረ ። ክፍሏ ግን ባዶ ነው ። ስለዚህም ወደ ተከታዩ ወደ ፋንትሮፕ መኝታ ቤት አመሩ።

ሁሉም ነገር በንጽሕና የተጠበቀ ነው ። ጥቂት ጥሩ ጥሩ ልብሶችና ጫማዎች ብቻ ነበሩት ።

“ ደብዳቤም አይጻጻፍ ማለት ነው ? ወይንስ እንደ ደረሰው ካነበበ በኋላ እያቃጠላቸው ? ፋንትሮፕ ሊበዛ ጥንቁቅ ሰው መሆን አለበት ” አለ ሬስ ።

ከፋንትሮፕ መኝታ ክፍል ቀጥሎ ያለው የቲም ነበረ። የቲም ክፍል ግርግዳ የካቶሊክ ሃይማኖቱን በሚያንጸባርቁ የመላእክትና የሰማዕታት ምስሎች አልፎ አልፎ ተሸፍኗል ። ከመኝታው በላይ እጅግ ያማረ መቁጠሪያና ከከበረ ድንጋይ የተቀረጸ መስቀል ተሰቅሏል ። በተረፈ ግን ክፍሉን ያጣበቡት ወቅታዊ የሆኑ አያሌ መጽሔቶች ነበሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በጠረጴዛቸውም ላይ ተከምረው የነበሩትን የግል ደብዳ
ቤዎች ፑዋሮ እያገላበጠ ተመለከተ ። ምንም ነገር ስላላ
ገኘ ወደ ሚስስ አለርተን መኝታ ቤት ሄደ ። እምብዛም
ሳይጨነቁ አሰፍ አሰፍ ብለው እየት እየት ከአደረጉ በኋላ
ሊወጡ ሲሉ ፡

"ክብሯን የምትጠብቅ ጥሩ ሴት ናት!" ሲል ፑዋሮ
ተናገረ ።

ብዙ ጊዜ የፈጀባቸው የሳይመን መኝታ ክፍል ነበረ።
ሳይመን ከቆሰለበት ሰዓት ጀምሮ ያረፈው በዶክተር ቤስ
ነር ክፍል በመሆኑ በተለይ የሊኔት ድሪ በዚያ ተደብቆ
ይገኛል የሚል እምነት ነበራቸው ። ፑዋሮም " ባለቤት
የሌለው ክፍል ይህ ብቻ ነው ። ድሪውን የሠረቀው ሌባ
ፍተሻ እንደሚካሄድ ከጠረጠረ ከዚህ የተሻለ መደበ
ቂያ ሥፍራ አያገኝም ። እንደደበቀው ሳይገኝ ከቀረለት
ሌባው በመልክም ዕድሉ ይኩራራል ። ቢገኝ ግን ማን
እንደደበቀው ስለማይታወቅ ባይኩራራም የመንፈስ ጭን
ቀት ስለማያድርበት ይዝናናል " ሲል ተናግሮ ነበረ ።
እረጅም ጊዜ የፈጀ በጥንቃቄ የተሞላ ፍተሻ ቢያካሂዱም
በመጨረሻ ላይ የወጡት ባዶ እጃቸውን ነበረ ።

የሊኔት መኝታ ክፍል ቁልፍ በኰሎኔል ሬስ እጅ ስለ
ነበረ በራፉን ከፍተው እንደገቡ ፡

" ፑዋሮ ! " አለና ሬስ መናገር ጀመረ " ምንም
ዓይነት ፍንጭ ይሁን የሚገኘው ከዚህ ክፍል ውስጥ ስለመ
ሆኑ እርግጠኛ ነኝ ። ስለዚህም እባክህን አእምሮህን እንደ
ዱሮው አሠራውና አንድ ነገር ፈልፍለህ ለማውጣት ሞክር"
ሲል ተማጠነው ።

" ስለድሪው መጥፋት የሚጠቁም ፍንጭ ማለትህ
ነው ? " አለው ፑዋሮ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አይደለም ! እንገብጋቢው የግድያው ጉዳይ ነው ” ሲል ሬስ መለሰ ።

ፑዋሮ በዝግታ በየእቅጣጫው ማማተር ጀመረ ። በጉልበቱ ተንበርክኮ ወለሉን አሰሰ ። አልጋውን ብድር ሉብሱንና ፍራሹን ምልክት አገኛለሁ ሲል መረመረ ። ቁምሣጥኑንና ሻንጣዎችን ተራ በተራ እየከፈተ ፈለገ ። መጽሐፎችንና ፡ መጽሔቶችን ፡ ደብዳቤ ዎችን አገላበጠ ። ምንም ነገር ለማግኘት አልቻለም ። ወደመታጠቢያው ክፍል ገብቶ የተደረደሩትን ልዩ ልዩ ዥቶዎችንና ቅባቶች አንድ በአንድ እያነሳ የተሠሩበት ፋብሪካ ስም ሳይቀር እያነበበ አስቀመጠ ። የፑዋሮን ትኩረት በመጠኑም ቢሆን የሳቡት ጐን ለጐን የተቀመጡ ሁለት የጥፍር ቀለም ብልቃጦች ነበሩ ። ፑዋሮ የመጀመሪያውን ብልቃጥ ከፍቶ ከአሸተተ በኋላ በውስጡ ከነበረው እንጥፍጣፊ ፈሰስ አደረገና ተመለከተ ። ቀይ ቀለም ነው ። ሁለተኛውን ብልቃጥ አሁንም ከፍቶ ካሸተተ በኋላ እንደ ሁለት ጠብታ አፈሰሰ ፡ ቀለሙም ቡናማ ቀይ ነበረ። እራሱን እያወዛወዘ ለብዙ ጊዜ እንደተከዘ ቆየ ። ፑዋሮ የሚያደርገውን ሁሉ በጥንቃቄ ይከታተል የነበረው ሬስ ፡

“የሆነ ፍንጭ አገኘህ መሰለኝ?” ሲል በጉጉት ጠየቀ።

“ ዕድለኞች አይደለንም ሬስ ! ያጋጠመን ነፍሰ ገዳይ ቀላል ሰው አይደለም ። ሆኖም ” አለና ሁለቱን የጥፍር ቀለም ቢልቃጦች እያነሳ “ ስለነዚህ ቢልቃጦች ቀለም ያቺን የሊኔትን ሠራተኛ ለማነጋገር እፈልጋለሁ ። የፔኒንግተንን ክፍል ካየን በኋላ ፍተሻውን አንተ ትቀጥላለህ። በተለይም የሁለታችንን ክፍል በጥንቃቄ እንድትመረምርልኝ ? ” አለና ጥቂት እንደማሰብ ብሎ “ ብዙ ዓመታት ያለፉት ቢሆንም አንድ ጊዜ የሆንኩትን ጉድ ላጫ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውትህ ። በባቡር ላይ በመጓዝ እንዳለን ከፍተኛ የምሥጢር ሰነድ የያዘ አንድ ብጫ የእጅ ቦርሳ ይሠረቃል ። ያንን ቦርሳ ለማግኘት ያላሰስነው ክፍል ያላገላበጥነው ዕቃ አልነበረም ። እኔም ወይምሔድበት ከተማ ደርሼ ከማር ፍበት ሆቴል መኝታ ያዝኩ ። አንድ ቀን መጽሐፍ ለማንበብ ፊልጌ መጽሐፎቼን የማንገዝበትን ሻንጣ ስከፍተው ያንን ቦርሳ ተጋድሞ አገኘሁት ። ሰነዶቹ ከውስጡ ተወስደው ባዶ ነበረ ። የተፈፀሙብኝ ድፍረት ድፍረት አያሀልም ” እያሉ ሲያጫውቱኝ ፔኒንግተን ክፍል ውስጥ ገብተው ነበረ ።

የሊኔትን ሐብትና ንብረት የሚመለከቱ አንዳንድ ሰነዶች አግኝተው እንብበዋል ። ሁሉም ግልጽና ሕጋዊ ጽሑፎች ነበሩ ። ግማሾቹ ላይ የሊኔት ፊርማ ያረፈባቸው ሲሆን የተቀሩትም አመቺ ሁኔታ የሚጠባበቁ ነበሩ ።

“ ሰውየው ቂላ ቂል አይምሰልህ ፖዋሮ ! ተንኮል ያዘሉ ጽሑፎችን እንደተማላ የትም የሚጥላቸው ዓይነት አይደለም ። የተለየ መደበቂያ ቦታ ሊያዘጋጅላቸው ይችላል ” አለ ሬስ ፤

ፖዋሮ አገኙንበሶ ይበረብር ከነበረው የቁምሣጥን መሳቢያ ውስጥ ያገኘውን አንድ ኩልት ሽጉጥ አንስቶ ለሬስ እያሳየ ፤

“ ወረቀቶችን መደበቂያ ሥውር ሥፍራ ሲያገኝላቸው ፤ ይዞት የሚዞረውን ሽጉጥ የሚያስቀምጥበት ከዚህ የተሻለ ቦታ እንዴት አጣ ? ” አለና ሽጉጡን ከእንሳበት ቦታ መልሶ አስቀመጠ ።

ከዚያም ተያይዘው እንደወጡ ፖዋሮ ከሊኔት መኝታ ክፍል ስላገኛቸው የጥፍር ቀለም ቢልቃጦች ሁርጅን ለማ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንጋገር ሲሔድ ራስ ፍቅተኛውን ቀጠለ ። የመርከቧም ሠራተኞች ቡርጂን ቢያፈላልጓት ለማግኘት አልቻሉም ። በሁሉም ዘንድ የሰፈነ ተመሳሳይ ጥርጣሬ ነበረ ። ቡርጂ የሲኒትን ድሪ ለመስረቋ ያላመነበት የለም ። ፍትሻ ከተደረገ እንደሚደረስባት በማወቅ ከመርከቧ ላይ ሳትታይ ዘላ በውሃው ውስጥ ለወቲጥ በመዋኘት እንዳመለጠች በየሕሊናቸው ሲብሰላ ቆይቷል ።

የመርከቧም አዛዥ ወደ ፑዋሮ በመቅረብ “ ቡርጂን ማፈላለግ ከጀመርን አንድ ሰዓት ሊሆነን ነው ። የት እንደ ገባች ምን እንደዋጣት ልንደርስበት አልቻልንም ። ስለ ዚህ በቅርብ ላለው የፖሊስ ኃይል ቴሌግራም ብናስታውቅ ሳሎናና ፍሊጋው በእነርሱ በኩል እንዲጠናከር ብናደርግ ” አለው ።

“ እስቲ በቅድሚያ የመኝታ ክፍሏን አንድ በአንድ እንፈትሽው ። እንደ ተባለውም አምልጣ ከወንዙ ዳር ብትደርስም በዚህ በረሃ ውስጥ በእግሯ ተጉዛ እርቃ ለመሔድ አትችልም ። ደግሞም የዓባይ አዞዎች ከወዲሁ አግኝተዋት ሊሆን ይችላል ” አለና ከመርከቧ አዛዥ ጋር ወደ ቡርጂ ክፍል ገቡ ።

ቡርጂ ይመገዝ የሚከፈላት የእመቤቷን ዕቃዎች በንጽሕናና በሥን ሥርዓት ለመያዝ ቢሆንም ለራሷ ንብረት ግን ጥንቃቄ የምታደርግ አልነበረችም ። ቁምጣ ጥንና ሻንጣዎቿ በተዝረከረኩ ልብሶች ታጭቀዋል ። የውስጥ ልብሶቿ በየወንበሩ ላይ ተንጠልጥለዋል ። የእግር ጮራ፡ፀቿ በያለበት ወዳድቀዋል ። አልጋዋም ተነጥፎ የሚያውቅ አይመስልም ። ለየት ያለ ነገር ቢኖር የጫማዎቿ ስመሥመር ተስተካክለው መደራደራቸው ነበረ ። ፑዋሮ ወደ አልጋው ሥር ጐንበስ ብሎ ሲመለከት ከመሥመሩ



t.me/OLDBOOKSPDF

አፈንግጦ በአየር ላይ የተንጠለጠለ አንድ ጥቁር ጫማ አየ። ያም ጫማ የጥዋሮን አትኩሮት ሳበ ። ወለሉም ላይ በሆዱ ተኝቶ ወደ አልጋው ሥር ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተ በኋላ ቀስ ብሎ ተነሣ ። ወደ መርከቧ አዛዥ ዞር ብሎ “ በርጂ አላጠፋችም ! ” ሲል አስታወቀው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ አራት

የሉዊ ቡርጂ አስከሬን ከአልጋዋ ሥር እንደወደቀ ነው ። ዶክተር ቤስነር ተጠርቶ ምርመራ ካደረገ በኋላ የሞተችው ከአንድ ሰዓት በፊት እንደነበረ አረጋገጠ ። በጣም ቀጭንና አረጅም በሆነ ስለት ከልቧ ላይ ስለተወጋች አማሟቷ ፈጣንና ጣር ያልበዛበት ነበረ ። የፊቷ ቆዳ ሳይታሰብ በደረሰባት የድንጋጤ ስሜት ተሸብሽቧል ። ጥርሶቿ ከንፈሯን ዘልቀው ወደ ውጭ ወጥተዋል ። ዓይኖቿም እንዳፈጠጡ ነበሩ ።

ቡርጂ በቀኝ እጇዋ ጨብጣ የያዘችው ነገር እንዳለ ፑዋሮ ተመለከተ።ጉንበስም አለና እጇዋን ቀስ ብሎ በመፈ ልቀቅ እንዷት በልዩ ልዩ ሕብረ ቀለማት የተሸለመች የወረቀት ቁራጭ አንስቶ ለሬስ አያሳየ ፡

" ይቺ ወረቀት የምን ብጣቂ እንደሆነች አወቅ ከው ? " ሲል ፡

" ያገንዘብ አለና ! " ሬስ መለሰለት ።

" አዎን! የአንድ ሺህ የፈረንሣይ ፍራንክ ኖት ቁራጭ ኖት "

" ይህ ከሆን ነገሮች እየቀለሉልን በመሔድ ላይ ናቸው ለማለት ይቻላል ። ቡርጂ ስለሲኔት ሞት የምታው ቀው ምሥጢር ነበረ ማለት ነው ። ስለዚህም ገዳዩን እንዳላጋልጥህ ብላ በማስፈራራት ገንዘብ ልትቀበለው



t.me/OLDBOOKSPDF

ስትል እርሷንም ደገመችው ፤ ለእኛም ልትነግረን ባለመፈለጓ በእራሷ ጥፋት ሕይወቷን ልታጣ ቻለች ” አለ ሬስ ።

ፑዋሮ ግን የመቆርቆር ስሜት እየተሰማው “ የተጎዳው ሰላማው እኛ ነን እንጂ ፤ ጠዋት አስጠርተን ስናነጋግራት የሰጠችን ፍንጭ ነበረ ። ትዝ ይልሃል ሬስ ! ‘ በእርግጥ እንቅልፍ አልወሰደኝ ቢለኝና ወደዚህ አካባቢ ክመጣሁ ፤ ይህን አውሬ ነፍሰ ገዳይ ወደ እመቤቴ መኝታ ክፍል ሲገባ ወይንም ሲወጣ አየው ነበር ’ ስትል ተናግራ ነበረ ። መለኛም ሴት ስለነበረች ያየችው ነገር እንደነበረ በንግግር ዘይቤ በመሸፋፈን ለመጠቀም ሞክራለች ። ስለዚህም አንተ እንዳልከው ምሥጢሩን ላለማውጣት እያስፈራራች በየጊዜው መደለያ ገንዘብ ለመቀበል የአሩቅ ጊዜ ዕቅድ ነበራት ። ሆኖም ሳታስበው በአጭሩ ተቀጭታ ቀረች ።” አለ በወለሉ ላይ የተዘረጋውን አስከሬኗን ቁልቁል እየተመለከተ ።

“ እውነትም ዘሬውኑ ገንዘብ መጠየቅ ጀምራ ነበር ማለት ነው ። ስውየው ያስ የሰጠውን አሟጦ ቢሰጣትም በቃኝ ባለማለቷ ለመጠባበቂያ ብሎ የያዘውን የፈረንሣይ ገንዘብ ሳይቀር እስከመስጠት ድረስ ተገዷል ማለት ነው” አለ ሬስ የፑዋሮን ሐሳብ እየደገፈ ።

ፑዋሮም “ አዎን ! ነገሬው እንዳህ ካደረገች ውሎ ካደረም ገደብ የሌለው ገንዘብ እንዲሰጣት ማስፈራራቷን ትቀጥል ነበረ ። ስለዚህ ሰስውየው የታየው አማራጭ እጅዋ ውስጥ የገባላትን ገንዘብ ተንገብግባ በመቁጠር ላይ እንዳለች በስለት ወግቶ ማሳረፍ ነበረ ” ሲል ፤ ሬስ ያቺን የፈረንሣይ ገንዘብ ኖት ብጣቂ በእጁ እያገላበጠ ፤

“ ይቺስ ቁራጭ ወረቀት የሆነ ፍንጭ ልትሰጠን አትችልም ? ” አለና ጠየቀ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" አይመስለኝም ። ይልቅስ ሌላ የደረስኩበት ፍንጭ አለ ። የሲኔትም ሆነ የቡርጂ ገዳይ የተለየ ተሰጥዖ ያለው ሰው መሆኑን አሁን በሚገባ ተረድቻለሁ ። ጎበዝ ፡ ብልህ፥ ደፋርና እንደመብረቅ ፈጣን ስለሆነ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አሁንም ቢሆን ሌላ ወንጀል ለመፈጸም እንደማያመነታ ለማመን ችያለሁ ። ስለዚህም ቀራጣ የሆነ የአንድ ሺህ የፈረንሣይ ፍራንክ ኖት በኪሱ ይዞ የሚዞር የዋሕና ቂላ ቂል ፍጥረት እንዳይመስልህ " ብሎት ተከታትለው ወደ ምግብ ቤቱ አመሩ ። እንደገቡም እስከአሁን በራፉ ተቆልፎባቸው የቆዩት መንገደኞች በተለያዩ መንገድ አፎይታቸውን አሰሙ ። ሮዛሊንና ጃኩሊንም እየተጣደፉ ወደ ጥዋሮ በመጠጋት ፡

" የከፍለኞ ፍተሻችሁ ውጤታማ ሆነ ? " ሲሉ እንደተማከረ ሰው ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረቡ ።

"አልቀናንም" አለ ጥዋሮ እየተኩሳተረ ። የፊቱንም መለዋወጥ ከመቅጽበት የተረዳችው ጃኩሊን ፡

" መልክዎ ተለዋወጠብኝ ። ምነው አዲስ ነገር ተፈጠረ እንዴ ? " ስትል ጠየቀችው ።

" ሌላ ግድያ ተፈጸመ " አለ ጥዋሮ እንደተኩሳተረ።

" የሲኔትን ሠራተኛ ገደሏት " ሲል ሬስ አብራራ ።

"ገደሏት ? " አለች ጃኩሊን እራሷን በሁለት እጆቿ ይዛ " እውነት ቡርጂንም ገደሏት ? " ስትል ጮኸች ።

ዜናውን የሰሙት መንገደኞች የቅሬታ ጉምጉምታ አሰሙ። ቀጥሎም ጫጫታና ሁከታው ደራ ። ከዚያም ከምግብ ቤቱ ውስጥ ተራ በተራ እየተቆናጠሩና አንዳንድ ሐሜቶች እየ ጠረወሩ ወጡ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጃክሊን ግን ብቻዋን ከበራፉ አጠገብ እንደቆመች ቀረች ። ዶክተር ቤስነር የቡርጇን አስከሬን ከመረመረ በኋላ ወደ ምግብ ቤቱ ውስጥ ተመልሶ ገባ ። ጃክሊንም እንዳየችው ፡

“ ሳይመንን ቀድሞ ሳየው በጣም አትኩሶት ነበረ ። በዚህም ሁኔታ ከቀጠለ ሲሕይወቱ ያሰጋዋል ብዬ ፈራሁ። እባክዎን ደጋግሜ ስለደህንነቱ የጠየቅኩዎት ከጭንቀቱ የተነሣ ስለሆነ አይሰልቹኝ ” ስትል እምባዋ እያቀረረ ተና ገረች ።

“ ለሕይወቱ የሚያሰጋ ነገር ስለሌለ ፍፁም እንዳ ታስቢ በፈጣሪ ስም እምልልሻለሁ ። ” አላት ትከሻዋን መታ መታ በማድረግ እያበረታታት ። ፑዋሮ በአጠገባቸው አልፎ ሲወጣ ተስፋ እንደቆረጠ ሰው አንገቱን በማቀ ርቀር ፡

“ ሕይወት ትርጉም የለሽ
እንደ ጥላ ጠፊ
ፍቅርና ጥላቻሽ

እንደጉም አላፊ ” የምትለዋን እንጉርጉሮ ያሰማ ነበረ ። ከኋላ ኋላውም ይከተለው የነበረው ሬስ ታክለውና ፡

“ ሳይመን ዛሬ ጠዋት ስለእንድ ቴሌግራም ያነ ሳው ወሬ ነበረ ። ለምን ለጥቂት ደቂቃዎች አናነጋግረው ም ? ” አለው ። ፑዋሮም “ ማን ያውቃል ? በተቻለ መጠን ሁሉንም አቅጣጫ መዳሰስ ስላለብን እንጠይቀዋ ” ብሎ ሳይመን ወደተኛበት ክፍል ገቡ ። ሳይመንም አንገቱን ከትራሱ ላይ ቀና አደረገና ዓይኖቹን በማንከዋለል ፑዋሮና ሬስን ተራ በተራ ተመለከታቸው ። በሕሊናውም ውስጥ የሚመላለስ ሐሳብ እንደነበረ በግልጽ ይነበባል ። ስለዚ ህም ሬስ ወደ ሳይመን ፊንግታ እያሳየ በመጠጋት ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ብዙ ጊዜ እንፈጅብህም ። ጠዋት ሳናጋግርህ ስለ አንድ ቴሌግራም ልታወራልኝ ጀምረህ ነበረ ። የቋስልህ ስሜት የማያሲቃይህ ከሆነ አሁን ብትነግረኝ ” ሲለው ትሉቅ ሽክም እንደወረደለት ሰው ሳይመን ተነፈሰ ። ከዚያም ሳቅ ኢያለ ፡

“ በጣም ቀላል ነገር ነው ። ከእሁ ሲምበል መቅደስ ጉብኝት እንደተመለስን ፡ አንድ ቴሌግራም ከሳሎኑ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጦ ነበረ ። የተላከው ለራቼል ቢሆንም የሲኔት የቀድሞው ሁለተኛ ስምዋ ራችዌ ስለነበረ ለእርሷ የተላከ መስሏት የቴሌግራሙን አሽግ በመቻኮል ከፍታ ታነብ ጀመረ ። ከዚያም ያለማቋረጥ እየተንከተከተች ስትስቅ በመስማቴ በሁኔታው ግራ በመጋባት ምክንያቱን ጠየቅኋት ። እርሷም ቴሌግራሙ ካዘላቸው ቃላት ውስጥ አንዳንዶቹን አነበበችልኝ ። እውነትም ያዘለው ጽሑፍ ያልተለመደ ስለነበረ ሁለታችንም እንደተቃቀፍን በመሳሳቅ ላይ እንዳለን ሲኖር ራቼል እንደተንደረደረ መጥቶ ቴሌግራሙን ከሲኔት እጅ ላይ መንጭቆ ወሰደ ። የሌላ ሰው ቴሌግራም በማንበቧም ማዘኗን ገልጻ ደጋግማ ይቅርታ ብትጠይቀውም ንዴቱ አልበረደለትም ነበረ ። ዓይኖቹን እንዳጉረጠረጠባት ወደ መኝታ ክፍሉ የሄደ ይመስለኛል ” ብሎ እንዳቆመ ፡

“ ቴሌግራሙ ያዘላቸው አስቂኝ ቃላት ትገዝ ይሉሃል ? ” አለው ሬስ አሁንም ፈገግታ እያሳየ ።

“ የረባ መልዕክት የለበትም ። የሚያወራው ስለ ዶንች ፡ ቲማቲም ፡ ጥቅል ፡ ጎመን ፡ ሠላጣ . . . ነበረ ” ሲል የሬስ ሰውነት ለሰከንድ ያህል ስቅጥጥ አለ ፡ ምራቁንም በኃይል ዋጠ ። ወዲያውንም ሬስ ሳይመንን



t.me/OLDBOOKSPDF

እየተመለከተ “ አይ ሲኞር ሬቼቲ ፣ በጣም ግልፍተኛ ሰው ካልሆን በስተቀር እንዴት የድንችና የሠላጣ ነገር እስከዚህ ያናድደዋል ። ዳሩ ምን ያድርግ ? ግሲ.ዮኖች ደስ የሚላቸው ለስስፖጌቲና ላዛኛ ሲወራ ነው ” ሲል ሳይመን ይስቅ ጀመረ ። ፑዋሮና ሬስም ተጠቃቀሱና አብረው በመሳቁ ላይ እንዳሉ ።

“ ሙሴ ፑዋሮ ! ሙሴ ፑዋሮ ! ” የሚል የሴት ድምጽ ከውጭ ሲጣራ ተሰማ ። ወዲያውኑም ደራሲዋ ሚስስ ዐተርበርን “ ሙሴ ፑዋሮ ! ሙሴ ፑዋሮ ! ” እያለች ከጥድፊያዋ ብዛት በሩቆን እንደከፈተችው ተንታ ከገባች በኋላ “ የምነግራችሁ ነገር አለኝ ! ታሪክ ነው ! ጉድ ነው ! ” ስትል መጮኋን ቀጠለች ። እንፑዋሮም መጠጥ መቅማመሏን ከትንፋሿ ጠረን ብቻ ሳይሆን ከፊቷም ቀዳ መከመታተር ተረድተውት ስለነበረ ከወንበር ላይ ደጋግፈው አስቀመጧት ። ትንፋሿም መለስ እስቲልላት ድረስ በትዕግሥት ይጠባበቋት ጀመረ ።

ሚስስ ዐተርበርን ወደ ሳይመን ዞር አለችና በንግግሯም እንደ ድርስቷ ሊመራቀቅ በመሞከር “ ደስ ሊልህ ይገባል ሳመይን ! የምሥራች ይገፎልህ መጥቻለሁ ! ። የሚስትህን የሊኔትን ገዳይ እኔ አግኝቼልሃለሁ ! ” አለችው ። ሳይመን በድንጋጤ ከተደገፈው ትራስ ላይ ቀና በማለት ፣

“ ምን ? ” ሲል አፈጠጠባት ። እነ ፑዋሮም እንደ ትንግርት ይመለከቷት ጀመረ ። ዐተርበርን ምስቱንም ሰዎች ተራ በተራ በኩራት ዓይን እያቃኘች ፡

“ እውነቴን ነው ። ለነሙሴ ፑዋሮም ቢሆን ወንጀለኛውን በማስመልከት ቀደም ሲል ስጥቼው የነበረው የዶራሲነት አስተያየቴ ትክክለኛ መሆኑ አሁን ተረጋገጠልኝ ። ያ ሰጊዜው የተቀበረና የተረሳ የሚመስለን ሆኖም



t.me/OLDBOOKSPDF

ክትውልዳችን ጀምሮ ፡ አብሮን በየጊዜው ያደገው የመዘቀል ስሜት ፡ ያ ቁጭታችንን እንድንወጣ የሚገፋፋን ከፍተኛ ኃይል . . . በጣም ይገርማል ። ” አለችና ንግግሯን አቋማ አሁንም እንፑዋሮን ተራ በተራ ስትመለከታቸው ፡ ሬስ ግልፍ እንደማለት አለውና “ ትምህርቱን ቀድም ሲል ሰጥተሽናል ። ይልቁኑ የሊኔትን ገዳይ አግኝቼዋለሁ ካልሽ ጥቆማውንና ማስረጃሽን ብትነግሪን ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ የማቀርበው ማስረጃ ሁኔታዎችን በማዛመድ ነው ። ስለዚህም ግልጽና ቀላል እንደሚሆንላችሁ አልጠራጠርም ። ሉዊ ቡርጂን የገደለው ወንጀለኛ ሊኔትንም የገደላት መሆን አለበት በሚለው መነሻ ነጥብ ላይ በቅድሚያ መተማመን ይኖርብናል ። ሁለቱም ወንጀሎች የተፈጸሙት በአንድ ግለሰብ ነው ” ስትል ፡

“እዎን ! ልክ ነሽ ” አለ ሳይመን ፈጠን አለና “ አቀራረብሽ አሳማኝ ይመስላል ” ቢላትም ዐተርበርን መልስ የምትጠብቀው ከንፑዋሮ ስለነበረ ወደ እርሱ ዞር አለችና፡

“ የሉዊ ቡርጂን ገዳይ ካወቅኩኝ ፡ የሊኔትንም ገዳይ አውቄአለሁ ማለት አይደለም ? ተማምነናል አልተማመንም ? ” ብላ በድጋሚ ጠየቀች ፡

“ የማያምት ወሬ ነው የምታወሪው ፡ ወይንስ ያየሽው ነገር አለ ? ” አለና አሁንም ሬስ ጠየቃት ። ሚስስ ዐተርበርን እንደ አራስ ነብር እፍጣበት ፡

“ ማያምት አይደለም ! የማወራው ትክክለኛ ሰው ቀት ስላሉኝ ነው ። የቡርጂን ገዳይ በዓይኔ በብሌኑ አይቼዋለሁ ” አለች ። ሳይመን መቁንቁጥንጥ አበዛ ፡ ሰውነቱም በትክሉላት እየጋለ ሄዶ ላብ አስጠመው ። ፑዋሮ ሽረፍ አድርጎ አየት እያደረገውና ወደሚስስ ዐተርበርን በመዞር



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ምን አለበት ያመጣሽውን ዜና በቀጥታ ብታብሥሪን ? ” ሲል አሳሰባት ፡

“ ያየሁትን ሁሉ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ደረጃ በደረጃ ላጫውታችሁ እወዳለሁ ” ብላ ለጥቂት ጊዜ ያህል ዝም አለች ። በደስታ ለመግምንሸንሿ የሚያጠራጥር ነገር የለም ። ያ ቀን እንደ ዳግም ልደቷ የሚቆጠር ቀን ሆነባት ። የደረሰቻቸውን መጽሐፎች ለማንበብ ንቆ የነበረው ሕዝብ አሁን በኑቡርጂና ሊኔት ሞት የተነካ በቴሌቪዥን ላይ የምትሰጠውን ገለጻና የምታቀርበውን ሐተታ ለማዳመጥ ሲያሰፈስፍና ሲረባረብ ታየት ። ለሳምንታትና ለወራት ስሟ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ በሬዲዮ እየተደጋገመ ሲጠራ ተሰማች ። በመቶ የሚቆጠሩ ጋዜጦች በመጀመሪያ ገጽ አምዶቻቸው ያቀረቡላትን ቃለ መጠይቅ አትመው ፎቶግራፏን አውጥተው በዓለም ዙሪያ እንደሚያሰራጩትም ታወቃት። ለምስክነርነት በምትቀርብበት በፍርድ ቤት አካባቢ ከሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች እስከ ታላላቅ ጠበቆችና ዓቃብያን ሕግ የሚያሳዩአት ፍቅር የሚያደርጉላት እክብሮት ሁሉ ከፊቷ ድቅን አለባት ። ከዚያም በእረጅሙ ከተነፈሰች በኋላ ፡

“ የምሣ ሰዓት ሊደርስ ሲል ነበረ ። በደረሰው ሐዘን የተነካ ወሰናቴ በመዘጋቱ ሮዛሊ ወደ ምግብ ቤት ስትሔድ እኔ ለሙቶኞች መረጥሁ ” ስትል ከችኮላዋ የተነሣ ክፍቱን በተወችው በር አካባቢ የሆነ እንቅስቃሴ ተካሂያደ ። ያንን እንቅስቃሴ ግን እኔ ጁዋሮም አልተገነዘቡትም ነበረ።

ሚስስ ዑተርበርግ “ ሆኖም ” ብላ መናገር ጀመረችና የፈራችው ነገር ያለ ይመስል ጭጭ አለች ። ጁዋሮም “ አደዘሽ ቀጥይ እንጂ ! ” ሲል አበረታታት ። እርሷም እንደ ምንም እያቅማማች ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ሆኖም እንቅልፍ ሸለብ ሊያደርገኝ ሲል እረስቼው የነበረው አንድ ነገር ትዝ አለኝ ። ለካስ በዚያኑ ዕለት በመርከቧ ላይ ከሚሠራ ሰው ጋር ቀጠሮ ኖሮኛል ። ስለ ቀጠሮው ማን ለሮዛሊያም አልነገርኳትም ። ሰውየው የሚያመጣልኝ ዕቃ ነበረ ” አለችና አሁንም ዝም አለች ። የምትናገረው ሁሉ የጠፋባትም መሰለ ። ምናልባትም የምስክርነት ቃሏን በምትሰጥበት ወቅት ቀጠሮሽ ከማንና ለምን ነበረ ተብላ ብትጠየቅ የምትሰጠው መልስ ከዕፍረት ላይ የሚጥላት መሆኑ ታይቷት ሊሆን ይችላል ። ፑዋሮ ወደ ሬስ እያየ “ መጠጥ ” የምትለዋን ቃል እንዳይሰማበት አፏን በማላወስ ተናገረ ። በበራፉ አካባቢ ግን አሁንም የበፊቱ ዓይነት እንቅስቃሴ ተካሂያደ ። አንድ ዓይነት ቅርፅ ያለው ብረት ሠልቶ ለለ ። ሆኖም አሁንም ቢሆን ማንም አላጤነውም ነበረ ። ሚስስ ዑተርበርንም ንግግሯን በመቀጠል ፡

“ ቀጠሮአችን ከምድር ቤት በምትገኘው አንዲት ድብቅ ክፍል ውስጥ ነበረ ። በኮሪደሩም ላይ ሳልፍ ሚቿ ቡርጂ በራፏን ከፍታ እያረጋ አየች ከአደረገችኝ በኋላ መልሳ ዘጋችው ። ቡርጂ ቀጠሮ ሰጥቷት በጉጉት የምትጠባበቀው ሰው እንደ ነበራት ገመትኩኝ ። እኔም የምፈልገውን ዕቃ አግኝቼ ስመለስ አንድ ሰው የቡርጂን በር ሲያንኳኳ አየሁኝ ። በራፏም እንደ ተከፈተለት ወደ ውስጥ ገባ ። ” ስትል ሬስ እየተጣደፈ ፡

“ ሰውየው ማን ነበረ ? ” ከማለቱ የጥይት ተኩስ ተሰማ ። ክፍሉ በድምፁ ጮኸችና በጭስ ተሞላ ። ሚስስ ዑተርበርን ከተቀመጠችበት አንገቷን ቀስ ብላ ወደ በራፉ በማዞር የተፈጠረውን ሁኔታ ለመመልከት ስትል ስሜቷ ከድቷት ኖሮ ከወንበሩ ላይ ተንሸራታ ወርዳ ከወለሉ ላይ ተዘረረች ። ጥይቱ ከገባበት ከማጅራቷም ላይ ደሟ ተሰል



t.me/OLDBOOKSPDF

እያለ ወረደ ። እንፔጥሮ ለጊዜውም ቢሆን እንደተደናገጡ ሬዘው ከቆዩ በኋላ እየሮጡ ወጡ ። ግራና ቀኛቸውን ቢያዩ አንድም ዝር የሚል ሰው የለም ።የተተኮሰው ሽጉጥ ግን ከበራፉ አጠገብ ተወርውሮ ነበረ ። ፔጥሮ ጉንበስ ብሎ ሽጉጡን በመሐረቡ እያገላበጠ በመመልከት ላይ እንዳለ የተኩሱን ጩኸት የሰሙት ሮዛሊ ፤ ጃኩሊንና ፤ ኮርኒሊያ ፡ከየመኝታ ክፍሎቻቸው እየተንጋጉ ወጡ።ፈርግሰን፤ ቲም ፤ ፋንትሮፕና ሚስስ አለርተን ከመናፈሻ ሥፍራው ላይ እየተንደረደሩ ወርደው እነ ፔጥሮን ከበው ቆመው በመደናገጥ ያዩአቸው ጀመረ ።

ሬስ " ሰውየው ወደ ላይ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ እንሚስስ አለርተን ያዩት ነበረ ። " አለና ሽጉጡን ከፔጥሮ ላይ ተቀብሎ ካየ በኋላ " ይህን ሽጉጥ በቅርቡ አይቼው ነበር መሰለኝ ። እስቲ ለማንኛውም " አለና ወደ ፔኒንግተን ክፍል እየተጣደፈ ሄደ ። በራፉን ደጋግሞ ቢያንኳኳም የሚመልስለት አጣ ። በራፉ አልተቆለፈ ኖሮ እጀታውን ነካ ሲያደርገው ወለል አለ ። ሬስ እንደተቻኮለ ሄዶ የቁምጣጥኑ መሳቢያ ሲከፍተው ያ የከሉት ሽጉጥ አልነበረም ። ተመልሶም እንደመጣ ፤

" ለመሆኑ የጣት አሻራ አግኝተህበታል ? " ሲል ፔጥሮን ጠየቀው ፤

" የለውም " አለው ፔጥሮ ፤

" እንግዲያውስ የሽጉጡን ባለቤት እንፈልግ !" አለ ሬስ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ አምስት

እነ ቱዋሮ ፔኒንግተንን ለማግኘት ጊዜ ፈጅቶባቸዋል ። ሳሎንና ምግብ ቤት ውስጥ የለም ። የመኝታ ቤቱ ባዶ ነው ። በመናፈሻውም ሥፍራ አካባቢ አልነበረም ። ስለዚህም ወደ ምድር ቤቱ በመውረድ በዚያ የሚገኙትን ባዶ ክፍሎች ተራ በተራ እየከፈቱ መመልከት ጀመሩ ። በመጨረሻም ላይ ፔኒንግተን ከአንዷት አነስተኛና በቂ ብርሃን ከሌላት ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ወረቀቶች ሲያገለባብጥ ደረሱበት ።

እርሱም ቀና ብሎ እንደተመለከታቸው ወረቀቶቹን በጥድፊያ እያጣጠፈ ወደ ኪሱ ከከተተ በኋላ ፡

" ምን አዲስ ነገር አለ ? " ሲል ጠየቀ ፡

" እሁንም ተኩስ አልሰማህም ? " አለው ሬስ ፡

" የሆነ ድምጽ ሰምቼ ነበረ ። ለካስ ተኩስ ኖሯል ማለት ነው ? " አለ ፡

" አዎን ! ሚስስ ዐተርቡርን የተገደለችበት ! "

" ሚስስ ዐተርቡርን ! " አለ ፔኒንግተን እየተደነቀ።

" እሁንስ የምሰማውን ሁሉ ከማላምንበት ደረጃ ልደርስ ነው ። ይህማ ከሆነ ተራ በተራ ከማለቃችን በፊት አንድ የመከላከያ ኃይል ማቋቋም ይኖርብናል ! " ሲል ሬስ ገሏመጥ አደረገው ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

" ለመሆኑ በዚህ ክፍል ውስጥ ለስንት ደቂቃዎች ነበርክ?" ሲል ጠየቀው ፡ ፔኒንግተን ሰዓቱን አየት አደረገና " ለሃምሣ ደቂቃዎች ' ' አለ ።

" ከዚህ አልተንቀሳቀስክም ?"

" በፍፁም ! "

ሁለቱም ትክ ብለው ያዩት ጀመረ ። እርሱም ተደናግጦ ከተቀመጠበት ከተነሣ በኋላ ፡ እንደመስማመጥ እያለ፣

" ጌቶቼ ! ይህ ጉዳይ እኮ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ በመሔድ ላይ መሰለኝ " ሲል ፡

" አዎን ! ግን አሳሳቢነቱ በይበልጥም ለአንተ እንደሚሆን አትጠራጠር !" አለው ሬስ ።

" ለምን ? " አለ ፊቱ እየተለዋወጠ ።

" ሚስስ ዐተርቦርን የተገደለችው በማን ሽጉጥ ይመስልሃል ? " ብሎ ሽጉጡን አሳየው ።

" በእኔ ሽጉጥ ነው ማለት ነው?" አለና ፔኒንግተን በቆመበት ቀረ ።

" አዎ ! ስለዚህስ የምትሰጠን ማብራሪያ ይኖርሃል ?" ሲል ፑዋሮ በተለመደ ዘዴው ጠየቀው ።

" በቅድሚያ ስህተተኛ መሆኔን ለማረጋገጥ እወዳለሁ ። ምክንያቱም ወደዚህ ለመምጣት ከመርከቢ ላይ እንደተሳፈርን በጉብኝታችን ወቅት ሊያጋጥሙን ስለሚችሉ አንዳንድ ጉዳዮች በሳሎኑ ውስጥ ተወያይተን ነበረ ። የቀማኞችና ወንበዴዎችን ወሬ አንስተናል ። እግረ መንገዳችንንም እራሳችንን ልንከላከልበት ስለምንችልበት መሣሪያ ስንጫወት እኔ ኰልት ሽጉጥ እንዳለኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተናግሬ ነበረ ። ይህንን የሰማ ሰው መሆን አለበት ዛሬ የእኔን ሽጉጥ ሠርቆ ሚሲስ ዑተርበርንን የገደላት ። ” ብሎ ፔኒንግተን አስረዳ ።

“ የነበሩትን ሰዎች ታስታውሳቸዋለህ ? ” አለና ጥዋሮ ጠየቀው ።

“ ብዙዎቹ መንገደኞች ነበሩ ። ስለዚህ ዕንግሊ ከዕንግሊ ብዬ ለመለየት የምችል አይመስለኝም ” አለ ። አራሱን እየወዘወዘም “ ጥሩ ተኛነቴን ግን ሙሉ በሙሉ ተቀብየዋለሁ ። የሚያሳዝነው ግን ወንጀለኛው መጀመሪያ ሲኔትን ፣ ቀጥሎ ሠራተኛዋን ገደለ ። አሁን ደግሞ አሮጊቷን ሚሲስ ዑተርበርንን ለመግደል ምን ምክንያት ይኖረው ይሆን ? ” ሲል ፔኒንግተን ፣

“ በቂ ምክንያት አለው ! ” አለና ሬስ መለሰለት ፣ “ በእርግጥ ? ”

“ አዎን ! ሚሲስ ዑተርበርን የተገደለችው የሲር ጂን ገዳይ ስም ልትነግረን ስትል ነው ” ሲለው ፣

“ የማይታመን ታሪክ ! ” አለ ፔኒንግተን ።

“ ለማመን ላለማመንም የምትችለው በኋላ ይሆናል ። ስለዚህም ደግሜ አነጋግርሃለሁ ” አለውና ጥዋሮ ከሬስ ጋር ተያይዘው ወጡ ። ወደ መናፈሻ ፕሮግራሙም እንደደረሱ ኮርኔሊያ አገኛቻቸውና ሙሴ ጥዋሮን አስቁማው ፣

“ በሕይወቴ እስካለሁ ድረስ የማይረሳኝ ነገር ! እንዴት በአንድ ቀን ጊዜ ውስጥ ሶስት ሰው ይገደላል ። የምንኖረው በቅዠት ዓለም ውስጥ ነው ለማለት አይቻልም ? ” አለች ። ነገር ግን ከኋላዋ የነበረው ፈርግሰን እንደ ልማዱ ጥልቅ አለና ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ሞት ብርቅ መስሎ የታየሽ ምናልባት ከሌላ ዓለም ስለመጣሽ ሳይሆን ይቀራል ። አለበለዚያ ግን ሞትን ዕለት በዕለት የምናየው ተራና ተደጋጋሚ ክስተት በመሆኑ ሊያ ስደንቅሽም ባልቻለ ! ” ብሎ ለከፋ ጀመራት ። ኮርኔሊ ያም የተናገራት ማን መሆኑን ዞር ብላ ከተመለከተች በኋላ ለውነቷ እንደመሸማቀቅ ቢልም ፡

“ ከሌላ ዓለም ስለመጣሽ ነው የምትለው አሜሪካዊ በመሆኔ ነው ? ” አለችው ።

“ አዎን ! አሜሪካኖች ውጥንቅጣችሁ የወጣ ፣ የት ምህርት አቅጣጫዎችሁ የተምታታ ፣ ባህል የለሽ ሕዝቦች ናችሁ ” አላት ፈርግሰን እየሳቀ ፡

“ ሚስተር ፈርግሰን ! የምትናገረው ሁሉ ትክክል አይደለም ” ስትል መለሰች ፣ ፊቷ መቅላት እየጀመረ ። “ ክጥንታዊ የግሪክ ሥልጣኔ ጀምሮ የሰው ልጅ ያሳየቻውን ዕድገቶች በየአቅጣጫው ትንትኜ ካስፈለገ ላስተምርህ እችላለሁ ። ደግሞም . . . ” ብላ ልትቀጥል ስትል ፣

“ አቤት ትምህርት ! እንዲህ አድርገውም ትምህርት የለም ! ያለፈው ታሪክ ከእድራጎቹ ጋር የሞተ የተቀበረ ነው ። እኛ ግን መጨረሻ መጠበቅ ያለብን ስለወደፊቱ የሰው ልጅ ብልጽግናና ዕድል መሆን አለበት ።ለም ባሌ ሶስት ሴቶች በዚች መርከብ ላይ ተገደሉ ። ግን ይህ ሊያስደንቅሽ አይገባም ። እስቲ የሚያስደንቀው ሲኔትና ክብረቷ ነው ? ቡርጂና ሥርቆቷ ነው ? ወይንስ ውተርሀ ርንና ወሬኛነቷ ? ምናቸው ነው ለዓለም የሚያጉድለው ? እነኝህ ሦስት የኅብረተሰብ ነቀርሳዎች ለሕይወት ከሚ ቆዩ ይልቅ ሞታቸው ይመረጣል ! ” አላት ፡

“ በጣም የምታሳዝን ፍጥረት ነህ ! ” ስትል ኮርኔሊያ አፈጠጠችበት ። “ ንግግርህ ድርቅ ያለ ለዛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቢስ ስለሆነ ለሰሚው የሚያቅለሸልሽ ነው ። የሆነው ይሁንና ሚስስ ዑተርቡንን እንኳን ብትጠላት ያቺ ቤሌዘን የተኰራመተችው ልጅዋ ሮዛሊ አታሳዝንህም ? እንተ ሴባ ብለህ የረገምካትን በርጂን ይህን ጊዜ የሚመርቋት ትና የሚጸልዩላት እናት አባት ይኖሯት ይሆናል ? ሲኔትስ ምን አደረገችህ ? የአንዲት ጀጌሬዳ አለምክንያት እንደሚያንገበግበን የአንዲትስ ውብ ልጅ መቀመቀጠፍ እንደሚያንገበግበን የአንዲትስ ውብ ልጅ መቀመቀጠፍ ለምኗውቃት እንደ እግር እሳት እንደሚለበልቤት ለእኛ ለምናውቃት እንደ እግር እሳት እንደሚለበልብን አታውቅም ? ” ስትል በዓይኗ ጭምር ከላይ እታች በመገላመጥ አፈር ድሜ አስበላቸው ።

ፈርግሰን ፀጉሩን እየነጨ ወደ ኋላው በማፈግፈግ፡ “ ከእንቺ ጋር መከራከሩ ቢቀርብኝ ይሻላል ። እንዳየሁት ባህርይሽ ከጾታ እምሳዮችሽ የተለየ ነው ” አለና ለመሔድ ዞር ሲል ፤ ንትርኳቸውን ከጀርባው ቆሞ ያዳምጥ ከነበረው ከዮዋሮ ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጠ ።

ፈርግሰን እንደማፈር አለና “ አዩት ጌታዬ ! ይቺ ልጅ የእንግሊዝ ሐብል የጀሮ ጉትቻ የላትም ። ከሐር የተሠራ ቀሚስ ከሱፍ የተሠራ ካባርት ለብሳ አታውቅም ። በስም ብቻ ለምትመጻደቀው እርግጊት አክስቷ እንደ ገረድ ታገለግላለች ። በሕላም በኩል እንደ ሲኔት ውብ እንደ ጃክሊን ቆንጆ አይደለችም ። የጾታ መሰሎቿ ባዩት ሁሉ የሚቀናኑ ናቸው ። እርሷ ግን . . . ” ብሎ ወደ ኰርኔሊያ ዞር አለና ፤ “ ለመሆኑ ባሳለፍሽው ሕይወትሽ ውስጥ አንድ ቀን እንኳን ቅር ብሎሽ ያውቃል ? ” ሲል ጠየቃት ።

“ስላለፈው ሳይሆን ማሰብ ያለብን ስለወደፊቱ ነው ኢያልኸ ከደቂቃዎች በፊት ታወራ አልነበረም እንዴ ? ጥያቄውን ለምን አሁን አነሣኸው?” አለች ሣቅ ሊያለችበት



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አሁን አሸነፍሺኝ ! ” አለና ፈርግሰን ፈገግ በማለት ሁለት እጆቹን ወደ እርሷ ዘርግቶ “ኮርኔሊያ!ኮርኔሊያ! እንደ አንቺ ያለ አንድም ቁም ነገረኛና ፍልትልት ልጅ በዕድሜዬ አጋጥሞኝ አያውቅም ። ስለዚህ ፈቃድሽ ሆኖ ብንጋባ ! ” አለና ያልታሰበ ዱብ ዕዳ አወረደባት።

ኮርኔሊያ ግን እረጋ ብላ “ እትባልግ ! ” የምትለውን ቃል ወረወረች ፡

“የቀልድ እንዳይመስልሽ ። ከልቤ የመነጨ ጥያቄ ነው ። ለዚህም ምስክሬ ሙሴ ፑዋሮ ናቸው ። የኮንትራት ውል ይመስል በሁለት ጾታዎች መካከል የሚመሠረተው ትዳር ሕጋዊ መሆን አለበት የሚለውን አስተሳሰብ ከማቃወሙት አንዱ ነበርኩኝ ። አንቺ ግን የእኔን አመለካከት የምትደግፊው ስለማይመስለኝ ለሁለተኛ ጊዜ በሙሴ ፑዋሮ ፊት በሕግ እንዳገባሽ ፈቃደኛነትሽን እጠይቃለሁ” አሳት ።

የኮርኔሊያ ፊት መለዋወጥ እየጀመረ “ አንተስ ጉደኛ ፍጥረት ነህ ! ” አለችው ።

“ እምቢ አልሺኝ ማለት ነው ? ” አለ እንደማስተዛዘን ብሎ ፡

“ ደህናም ቀልደኛ ኖረሃል ለካ ! ” አለችው ጨመረችና ፡

“ ቀልደኛ የምትይኝ ላግባሽ ስላልኩ ነው ? ወይንስ ባህሪዩን ለመግለጽ እየሞከርሽ ? ” አለ እንደመኰሳተር እያለ ።

“ ሁለቱንም ማለቴ ሲሆን በተለይ ባህሪህ የማያስተማምን ነው ። በማያሳቀው ትስቃለህ ! ከባዱን ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ታቃልላለህ ! በማይቀለደው ትቀልዳለህ ! ” አለችውና ወደ መኝታ ቤቷ ክፍሏ እየተጣደፈች ሄደች ።

ፈርግሰን ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ በዓይኖቹ ተከተላት ። ቆይቶ ቆይቶም “ ይቺ ሞጥማጣ ! እንዲህ እንደ ተጫወተች ብኝ የቀረ እንደሆነ?” አለና ቀኝ እጁን ቡጢ ጨብጦ የግራ እጁን ደጋግሞ ከመታታ በኋላ “ ግን እውነቷን ነው ። ያለ ችኝ አስተማማኝ ባህሪ የለህም ነው ” ብሎ ወደ ሙሴ ፑዋሮ ዞር አለ ። ሙሴ ፑዋሮ ግን የሁለቱን ወጣቶች ጭቅ ጭቅ እንዳላዳመጠ ለመምሰል በሐሳብ ባሕር ውስጥ እንደ ተጠመደ ሰው ፍዝዝ ብሎ ነበር ።

“ ምን ሆኑ ሙሴ ፑዋሮ? ” አለ ፈርግሰን ዓይን ዓይኑን እያየ ፤

“ አንዳንድ ነገር እያሰላሰልኩ ነበረ ” ሲል ፈገግ አለና መለሰለት ፤

“ እኔ ስለ ጋብቻ ሳወራ ! ምስክሬ ነዎት እያልኩ ስለ ፈልፍ ! ለካስ እርስዎ አሁንም ስለሞት ሲያስቡ ኖረዋል ። ለሞት ፤ የማያቋርጠው ነጠብጣብ የሚል ስያሜ የሰጡት እርስዎ አይደሉም እንዴ ሙሴ ፑዋሮ ? ” አለው ፤

“ እናስ ! ” አለው ፑዋሮ የመጣበትን ሣቅ እያፈነ ።

“ ነጠብጣቡ አንድ ጊዜ ፈቃድዎ ቢሆንና ተቋርጦ ስለኮርኔሊያና ስለእኔ ጋብቻ ብንነጋገር ? ”

ፑዋሮ አሁንም ፈገግ አለና “ ኮርኔሊያ በቀላሉ የም ትበገር ልጅ አይደለችም ። ሊያሸንፉትም የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ይመስለኛል ። ይኸውም መልካም ጠባይ ነው ” አለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እውነትዎን ነው ። የመጠቀ መንፈስ ያላት ልጅ ናት ። ትሁትና የዋሕ ናት ፤ የዚያኑም ያህል ደግሞ ልበ ሙሉና ደፋር ናት ። ይቺ ልጅ የመጣው ቢመጣ ልታ መልጠኝ አይገባም ። ምናልባትም ከዚያች አሮጊት መሰ የቱ ሊጨንቃት ይችላል ። ስለዚህ ” ብሎ ጉንጩን በጣቱ አስደግፎ ለጥቂት ጊዜ ካሰሰበ በኋላ “ ስለዚህ ! የሁ ለቱን ግንኙነት እንደመቀስ መበጣጠስ አለብኝ ” አለና እንደደነፋ ሚስስ ቫን ቫይለርን ፍለጋ ሄደ ።

ሚስስ ቫን ቫይለር ከውትሮዋም ይብስ ተኮፍሳ ከሳ ሎኑ በስተጥግ ፈንጠር ብላ በመቅመጥ ሹራብ ትሠራ ነበረ። ፈርግሰን እንደጎሰጎሰ ወደ እርሷ አቅጣጫ ሲሄድ ጥዋሮ ከኋላው ተሾልኩ ገባ ። እራቅ ብሎም በመቀመጥ እጁ ላይ የገባለትን መጽሔት አንስቶ ፊቱን ከጋረደ በኋላ ተመስጦ የሚያነብ ሰው መሰለ ።

ፈርግሰን ከሚስስ ቫን ቫይለር ፊት ለደቂቃዎች ያህል ተገትሮ ቢቆምም እርሷ ግን አንገቷን እንዳቀረቀረች የሹ ራብ ሥራዋን ቀጥላ ነበረ ። ስለዚህም “ እህህህ ! ” ሲል ትኩረቷን ለመሳብ ጉሮሮውን ጠራረገና ፤

“ እንደምን ውለዋል ሚስስ ቫን ቫይለር ! ” አላት ። ለሰከንድ ያህል ዓይኗን ቀና በማድረግ ማን መሆኑን እን ዳየች ወደ ሹራብ ሥራዋ ተመልሳ ድርቅ ባለ አነጋገር “ ደ-ህ-ና ! ” አለችው ።

ፈርግሰን እጆቹን እኪሱ ከቶ እግሩን አንፈራጦ ቆመና፣

“ እዩት ሚስስ ቫን ቫይለር ! እጅግ አስቸኳይና አን ገብጋቢ ለሆነ ጉዳይ ላነጋግርዎት ፈልጌ ነበረ ። በአጭሩ ኮርኔሊያን ላገባት መፈለጌን ላስታውቅዎት እወዳለሁ!” ሲል ከሚስስ ባን ቫይለር እጅ ላይ በድንገት የወደቀው



t.me/OLDBOOKSPDF

የሱፍ ክር ጥቅል በሳሎኑ ወለል ላይ እየተረተረ ይንከባ ለል ጀመረ ።

እንደ እባብ ምላስ የሚንቀለቀለውንም እንደቢቷን ከፍታ ፡ "ዕብደት እየጦካከረህ ነው ልበል ?" አለችው ቀና አለችና ፡

" ሲያልፍም አይነካካኝ ! ያቀረብኩት ጤናማ ጥያቄ ነው ። ኮርኔሊያን ለማግባት ወስኛለሁ ። እርሷንም እንድ ታገባኝ ጠይቁአታለሁ !" አላት ፡

ሚስስ ቫን ቫይለር ከበረዶ በቀዘቀዘ አመለካከት የፈ ርግሰንን ቁመና ከላይ እስከታች እየማተረች ፡

"እና ! ሥራ ባትፈታ ይሻላል ብላ መለሰችልህ አይ ደለም ? " አለች ።

" እምን እንቢ አለችኝ " ሲላት ፡

"በአግባቡ መልስ ሰጥታ አሰናብታሃለች!" አለችው የንቀት አመለካከቷን ሳትቀይር ።

" እሺ እስካላለችኝ ድረስ በአግባቡ አሰናብታኛለች ለማለት አይቻልም ። እኔም ደግሞ እንደሚያዩኝ በቀላሉ ተስፋ የምቆርጥ ሰው አይደለሁም ። " አላት ፡

" ጌታው ! አንድ ነገር የማረጋግጥልህ አለ ። እንደ አንተ ያለው ሰው ኮርኔሊያ በሆረችበት ዝር እንዳይል ማስ ደረጉ በጣም ቀላል ነው " አለች እንደሣማ በሚለበልብ አነጋገር ።

" በእኔ ላይ የሆነ ቅሬታ አለዎት ማለት ነው ? " አላት ፈርግሰን መለሰና። ሚስስ ባን ቫይለር ለሁለተኛ ጊዜ



t.me/OLDBOOKSPDF

በሙሉ ዓይኗ ልታየው አልፈለገችም ። ቅንድቧን ወደ ላይ ገርመም አድርጋ በማንቋሸሽና በጥላቻ ከተመለከተችው በኋላ የተንከባለለውን ክር በመሳብ ወደ ሹራብ ሥራዋ ተመለሰች ።

" ይንገሩኝ እንጂ እመቤቴ ! ኮርኔሊያን ባገባት ቅር የሚያሰኝዎት ምንድን ነው ? " ሲል አተካራውን ቀጠለ ።

" ቅሬታው እምን ላይ እንደሆን ለአንተም በግልጽ እንደሚሰማህ እርግጠኛ ነኝ ሚስተር . . . እ.እ. " ስትል ፈጠን አለና ።

" ፈርግሰን ! ፈርግሰን ! ነው ስሜ " አለ ።

" ሚስተር ፈ-ር-ግ-ሰ-ን- " አለች ያንን ስም በአፏ መጥራቱ እየቀፈፋት " ይህን አጉል ምኞትህን ከልብህ ውስጥ ብትፍቀው ይሻላል " ስትለው ፤

" እንደመሰለኝ የኮርኔሊያ ባል ለመሆን አትመጥና ትም ማለትዎ ነው ? "

" ለማለት የፈለግኩትን አንተ ተናገርከው !"

" የማልመጥንበትን ምክንያት ቢያስረዱኝ ? "

ሚስስ ቫን ሻይለር መልስ አልሰጠችውም ።

" እንደማንኛውም ሰው ሁለት እግር ሁለት እጅ አለኝ ። ጤነኛ ነኝ ። ደህናም አእምሮ ያለኝ ነኝ ። ቅሬታ ዎን ቢነግሩኝ ? "

" ለጋብቻ መመጠኛው ሚዛን አንተ የጠቀስከው ብቻ ኣይደለም ። የሰውየው የመደብ ጀርባ ፥ የኑሮ ደረጃና የመሳሰሉትም ተጓዳኝ ነጥቦች አሉ " አለችው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

" ጤና ካለ ከሁሉም ነጥብ ላይ ለመድረስ ይቻላል" ሲል በሳሎኑ ውስጥ ስለተጧጧፈው እንካ ስላንትያ ያል ተጠራጠረችው ኮርኔሊያ ዘው ብላ ገባች ፡፡ ፈርግሰንና እ ክስቷን እንደተፋጠጡም ስታይ በቆመችበት ቀረች ፡፡

ፈርግሰን ወደ ኮርኔሊያ በመዞር በፈገግታና በፍ ቅር ዓይን እያየ " ወደዚህ ቀረብ በይ ኮርኔሊያ ! እንደ ጥንቱ የሀገራችን ልማድ እጅሽን በጋብቻ ይሰጡኝ ዘንድ አክስትሽን በታላቅ ትህትና እየለመንኩ ነበር " አለ ፡፡

በንዴት የጋየችው ሚስስ ቫን ሻይለር ኮርኔሊያን በዛቻ አመለካከት እያየች " አንቺ ! ሂድና አክስቴን አተካራ ግጠማት ብለሽ ነው የላክሽብኝ ! " አለቻት ፡፡

" ማ ? እኔ ! በፍፁም . . . መቼ . . . የት ቦታ . . . አልወጣኝም " አለች ኮርኔሊያ መናገር እየተሳናት ፡፡

" ታዲያ ምን ያንተባትብሻል ! " ስትል አክስቷ ጮኸችባት ፡፡

ፈርግሰን ጣልቃ በመግባት " ፈቃደኛነቷን ብጠይ ቃት እንቢ ብላኛለች ስል ቅድም ነግሬዎት ነበረ ፡፡ ስለ ዚህ በሌላ በኩል ደግሞ እርስዎን እንዳነጋግርዎት እንዴት ልታበረታታኝ ትችላለች ? " አለና አሁንም የኮርኔሊያን ዓይኖች እያየ " እርሳቸውንም ብለምናቸው ለጋብቻ እት መጣጡንም በማለት ተቃውመዋል ፡፡ በመደብ ጀርባዬ አለመታወቅና በኑሮ ደረጃዬ ዝቅተኛነት የተነሣ አብረን ለመኖር እንደማንችል ገልጸውልኛል " ሲል ፤

" ይህንን ባትነግራትም ኮርኔሊያ በሚገባ ታውቀ ዋለች " አለችው ሚስ ቫን ሻይለር ፤

" ታውቂዋለሽ ? " " ለካስ የማታገቢኝ ድሃ ስለሆ ንኩ ነው " አላት ዓይን ዓይኗን እያየ ወደ ቆሸሹት ልብ ሶቹ መልከት አለና ያኰፈረውን ፂሙን በእጁ ደባበሰ ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

" አይደለም ! " አለች ኮርኔሊያ ፊቷ እየተለዋ ወጠ " ከወደድኩህ ጠባይህ የሚስማማኝ ከሆነ የማገባው አንተን እንጂ . . . "—ብላ ሳትጨርስ አቋረጣትና ፤

"አትወጂኝም ማለት ነዋ ? " አለና እየተጣደፈ ሲያ ፋጥጥ ጠየቃት ። የኮርኔሊያ ፊት ፍም መሰለ ። የልቧም ትርታ ይሰማ ነበረ ። ቁርጥ ቁርጥ በሚለው ትንፋሿም ፤

" ለምን ግልፍተኛ ትሆናለህ ? የምትናገረው ሁሉ እንደልብህ ነው ። ሰው ይታዘበኛል የሚል ይሉኝታ የለህም ። ቢሆንም በሕይወቴ እንዳንተ . . . " ስትል፤ ዓይኖቿ ያቀረሩትን እንባ መቆጣጠር አቅቷት ከሳሎኑ ውስጥ እየሮጠች ወጣች ።

ፈርግሰን ዓይኑ እስቲንቀል ድረስ ተመለከታት ። ቆይቶ ፤ ቆይቶም "ለመጀመሪያ ዙር ሙከራ ትስፋ የሚያ ስቆርጥ አይደለም !" ብሎ ተንፈስ አለ ።

" አንተ መናጢ ፍጥረት ! ሂድልኝ ! ጥፋ ከፊቴ ነው የምልህ!" እያለች ሚስ ሻን ሻይለር ትጮህበት ጀመረ። " ከዚህ ክፍል ውስጥ አሁኑኑ ባትወጣ . . . ልብ አድ ርግ!"እያለችም ስትገዛት ፈርግሰን ፈገግ ብሎ እጅ ነሳትና " በደህና ይዋሉ አክስቴ ! " ብሏት ወጣ ።

ንዴት ከጉሮሮዋ ተሰርንቆ ከተቀመጠችበት መነ ሳት አቅቷት ፤ በመንገዳገድ ላይ እንዳለች ጭዋሮ ፈጠን አለና ደገፍ አደረጋት ። ተረጋግታም እንደቆመች ከሳ ሎኑ ዳር እስከ ዳር ተንከባሎ የነበረውን የሱፍ ክር ሰብስቦ ከሰጣት በኋላ ፤

"ይሄ ጉረምሳ አናደደሽ መሰለኝ፤ግን አልፎ አልፎ በዘራቸው ተመሳሳይ ባህርይ ይታይባቸዋል ። በጠባያቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

አልክኞች በንግግራቸው ግልጽ ናቸው ።” አለና እንደ ቀልድም ጨመር በማድረግ ፣ “ ማን እንደሆነ አስታው ሰሺው የለም ? ” አላት ፤

“ ስሙን እረስቼዋለሁ ። ላስታውሰውም አልፈል ልግ ! ” አለች ።

“ እኔ እንኳን የማዕረግ ስሙን ማለቴ ነበረ ” አለ በሆዱ እየሣቀ ፤

“ ይሄ ጋጣ ወጥ ዱርዬ ! ከየት አባቱ ያመጣው የማ ዕረግ ስም ይኖረዋል ? ” ስትል

“ እርሱ እንኳን ዱርዬ አይደለም ። ብትረሺው ይሆ ናል እንጂ ፤ የእንግሊዛዊው የሎርድ ዴልዊሽ ብቸኛ ልጅና ወራሽ ነው። ታዲያ ሐብቱንም ማዕረጉንም አልፈልግም ብሎ እንደተራ ሰው መኖሩን መርጧል ” አላት ።

የሚስስ ቫን ሻይስር ፊት በተቃራኒ ስሜቶች ተወ ጣጠረ “ ለካስ እርሱ ኖሯል ፤ እንደዚሀ የሚያሾፍብኝ!” አለችና “ እረ ፎቶ ግራፉንም በጋዜጣ ላይ አይቸው ነበረ። መርሳቴ ግን ይገርማል ። ለማንኛውም እንዳውቀው ስላ ደረጉኝ ባለውለታዬ ነዎት ” ብላ ከሳሎን ስትወጣ ጭዋሮ ሳቅ እያለ ይመለከታት ነበረ ።

ከዚያም አጠገቡ ካገኘው ሶፋ ላይ አረፍ አለ ። ቀስ በቀስም የዓይኑ ሽፋሽፍቶች መከደን ጀመሩ ። በአእም ምሮው ውስጥ ተበታትነውበት የነበሩትን ሐሳቦች እንደ ሰንሰለት ማያያዙን ቀጠለ ። ቆይቶ ቆይቶም ከሰንሰለቱ ጫፍ ለመዳረስ ተቃረበ ። ያንጊዜም ከመቀመጫው ተነ ስቶ ፤

“ የተበታተነው መግጣጠሙ ተገባደደ !” አለ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

ፑዋሮ ፋንትሮፕን በድጋሚ ለማነጋገር የፈለገበት ምክንያት ነበረው ። እንደደረሰም ፡

“ ከጣትህ ቀለበት ለመረዳት እንደቻልኩት የኦክስፎርድ ዩንቨርስቲ ምሩቅ መሆን አለብህ ” ብሎ ፑዋሮ ሲናገረው ፡ ፋንትሮፕ ግራ ተጋብቶ ጣቶቹን አቀርቅሮ እየተመለከተ ፡

“ አዎን ! የኦክስፎርድ ምሩቅ ነኝ ” አለው ።

“ መደረግ የሚገባቸውንና መደረግ የማይገባቸውን ነገሮች ለይተህ እንደምታውቅ እርግጠኛ ነኝ!” አለው ፡ አሁንም ፑዋሮ ። ፋንትሮፕ ግን ግር እያለው ፡

“ ምን ለማለት እየሞከሩ ነው ? ” ሲል ጠየቀው ።

“ ሰዎች የራሳቸው የሆነ የግል ውይይት በሚያካሂዱበት ሰዓት ጆሮን ጣል አድርጎ የሚነጋገሩትን መስማትና ሳይጋበዙም ጣልቃ መግባት ከአንተ የማይጠበቅ ተግባር መሆኑን አታውቅም ? ” ሲለው ፋንትሮፕ በመገረም ዝም ብሎ ይመለከተው ጀመረ ። ፑዋሮ ግን ንግግሩን በመቀጠል ፡

“ በትናንትናው ዕለት ብቻ ይህንን ተግባር ሁለት ጊዜ ስትፈጽም ተመልክቻለሁ ። በቅድሚያ ወደ ቀኑ አካባቢ በሳሎኑ ውስጥ ሦስት ሰዎች የግል ውይይት በማድረግ ላይ እንዳሉ ሳያዩህ ከአጠገባቸው በመድረስ ንግግራቸውን ስታዳምጥ ቆየህ ። ከዚያም ማንም አስተያየ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቅህን ሳይጠይቅ ወደ ሲኔት ዞረህ ፔኒንግተን የሚያቀርብላትን ሰነዶች በጥንቃቄ እየመረመረች በመፈረሟ ለእርሷ ያለህን አድናቆት ጣልቃ በመግባት ገለጽህ ።

“ ይህ ሲደንቀኝ ማታ ደግሞ ፣ ሲኔት ሳይመን ፔኒንግተንንና ኰሎኔል ሬስ ካርታ በመጫወት ላይ እንዳሉ ፣ አሁንም ተመስጠህ መጽሐፍ የምታነብ በማስመሰል ጆሮህን አቅንተህ የሚነጋገሩትን ስታዳምጥ ነበረ ። በሳይመንም ላይ ለደረሰው አደጋ የዓይን ምስክር ለመሆንም የበቃኸው በዚሁ ሳቢያ ነው ።

“ ስለዚህም ነገሮችን ማዛመድ ስሞክር ፣ እንደነገርከን ሥራህ በአሁኑ ወቅት ብዙ ገቢ የማያስገኝው ቸብቅና ከሆን ፣ በእንጻሩም በወጣትነት ዕድሜህ ብዙ ገንዘብ አጠራቅመሃል ብሎ ለማመን ስለማይቻል ፣ በዚህ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቀው ጉዞ ላይ ለመካፈል የፈለግክበት ምክንያት ግልጽ ሆኖ አልታይም አለኝ ። ጤናህም የተሟላ ስለሆነ አየር ለመለወጥ ብቻ ከእንግሊዝ ግብጽ ድረስ እንደማያስመጣህ እርግጠኛ ነኝ ።

“ከነዚህም ነጥቦች በመነሳት በዚች መርከብ ላይ እንድትገኝ ያደረገህ ሌላ ምክንያት መኖር አለበት ። ስለዚህ ጊዜ ሳናባክንና ሳንደባበቅ ትክክለኛውን ምክንያትህን ብትገልጽልኝ ” አለና ፑዋሮ አቆመ ። ፋንትሮፕ በንዴት ፊቱ እየተለዋወጠ ፣

“ ለካስ ዕብድ ኖረዋል ሙሴ ፑዋሮ ! ከንደእርስዎ ዓይነት ሰው ጋር ምንም ለመነጋገር አልፈልግም!” አለው።

“ ዕብድ አይደለሁም ! ጤነኛ ሰው መሆኔንም በቅርቡ ትረዳዋለህ ። አድራሻህን ዛሬ ጠዋት ስጠይቅህ ኖርዝሃምፕተን ሻየር መሆኑን ነግረኸኛል ። ይህ ከተማ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደግሞ ከሊኔት መኖሪያ ቪላ ጋር የተቀራረበ ነው ። አን ዳንድ ወሬዎችን ጆሮህን እንደተሟላ ጣል እያደረግህ ስታ ዳምጥ ነበረ ። በተለይ ሊኔት ሰንዶችን በጥንቃቄ በመመ ርመሯ ያለህን አድናቆት ገለጸህላታል ። ይህንን ያደረግ ከው ያለምክንያት አልነበረም ” አለና ፑዋሮ ለጥቂት ጊዜ ትኩር ብሎ ከተመለከተው በኋላ ፤

“ በሙያህ ጠበቃ እንደመሆንህ የሕግ ሰው ነህ ብዬ አምናለሁ ። በዚች መርከብ ላይ በተከታታይ ሦስት ግድያዎች ተፈጽመዋል ። በተለይም ሚስስ ዐተርቦርን የተገደለችው በፔኒንግተን ሽጉጥ ነው ። ስለዚህ የምታ ውቀውን ሁሉ እንድትነግረን የሕሊና ግዴታ እንዳለብህ እንዳትረሳ !” ሲለው ፋንትሮፕ ለጥቂት ደቂቃዎች በዝ ምታ እንደተዋጠ ቆየ ። በመጨረሻም ላይ ፤

“ ነገሮችን ለማዛመድ የሚጠቀሙበት ዘዴ የሚያ ስደንቅ ነው ። አቀራረብዎም አሳማኝ ቢሆንም ተጨባጭ ነት ያለው ፍንጭ ልሰጥዎት አልችልም ” አለው ።

“ተጨባጭ ባይሆንም ጥርጣሬ አለህ ማለት ነው !” ሲል ፑዋሮ ጠየቀው ፤

“ አዎን ! ”

“ የጠላኸው ጥርጣሬህን መናገሩን መሆኑ ይገባ ኛል ። የሕግ ሰው ስለሆንክም አባባልህ ትክክል ነው ። ሆኖም አሁን ያለነው ፍርድ ቤት ውስጥ እንዳልሆነ ደግሞ ተረድተኸው ይህንን ወንጀለኛ ለመያዝ በምናደርገው ሙከራ ሊያግዘን የሚችል ማናቸውንም ግምትና ጥርጣሬ ህን ብትነግረን?” አለው ፑዋሮ በማግባባት ፤

ፋንትሮፕ አሁንም ነገሮችን በአእምሮው ውስጥ ለማመዛዘን ሞክሮ “ ጥሩ ! እስቲ ለማወቅ የሚፈልጉትን ነጥብ ይጠይቁኝ ” አለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"በዚች መርከብ ላይ የተገኘህበትን ምክንያት ብት ነግረኝ ? "

" ሚስተር ካርማይክል የሚባለው አጎቴ የሲኔት ዋና ነገረፈጅ ነው ። ስለዚህም ስለሲኔት አድራጎቶችና እንቅስቃሴዎች የተቻለውን ያህል ለማወቅ ይፈልጋል ። በተለይም ፔኒንግተንን በጥብቅ ይከታተለው ነበረ ። የሊኔትን ሐብት በመመዝበር ላይ እንደሆነም ይጠራጠረው ነበረ "

"በእጭሩ አጎትህ የፔኒንግተንን ሌብነት አውቆበት ነበር ማለት ነው?" ሲል ሬስ ጣልቃ ገብቶ ጠየቀው ።

" ግልፅ የሆነ ሌብነት አይደለም ። ስለገንዘብ አወጣጥ የሚሰጣቸው የማይመስሉ ምክንያቶችና የሚያቀር ባቸው ሰነዶች አጭበርባሪ መሆኑን ይጠቁሙ ነበረ።ሊኔት ባል በማግባቷ አጎቴ በጣም ተደስቶ ነበረ ። የግብፅም አገር ጉብኝቷን ፈፅማ እንደተመለሰች በሞግዚቷ ምትክ ንብረ ቷን እራስዋ ታስተዳድራለች የሚልም እምነት ነበረው ።

" ሆኖም ሊኔት ከካይሮ ከተማ ሆና የጻፈችለት ደብዳቤ ለአጎቴ ደርሶት ሲያነበው ከፔኒንግተን ጋር በድ ንገት መገናኘታቸውንም ገልጻላት ዋሮ እጅግ ደነገጠ ። የፔኒንግተን ዘዴ ወለል ብሎ ታየው ። ሊኔትን በዚህ አጋ ጣሚ ወቅት ተጠቅሞ የሐሰት ሰነዶች ለማስፈረም ከአሜ ሪካ ድረስ መምጣቱን ነቃበት ። ቢሆንም አጎቴ የፔኒንግተ ንን ሌብነት ለማሳመን ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅበት ያውቅ ስለነበረ ፡ በእርሱ ምትክ እኔን ወደ ግብፅ ላከኝ ። ዋናውም ዓላማ ፔኒንግተን ሊኔትን እንዳያታልላት ባለው ዕድል ሁሉ በመጠቀም ጥንቃቄ እንድታደርግ ለማሳወቅ ነበረ" እንዳለ ሬስ ከአፉ ላይ ቀበል ብሎ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ታዲያ ሲኔትን አንቅተሃት ነበረ ? ” ሲል ጠየቀው ”

“ነቅቶ ነበር ለማለት ባልችልም ፔኒንግተንን ግን ለማስደንገጥ ችያለሁ ። ትናንትና ቀን ፤ ሲኔትን ሰነዶችን ሳትመረምር ባስመፈረሟ ባመሰገንኩበት ጊዜ የፔኒንግተን ፊት ሲለዋወጥ ታይቶኛል ። ከንዴቱም የተነጣሉሎቹንም ሰነዶች ሳያስፈርማት ሰብስቦ ከቦርሣው ውስጥ ከቶ ነበር ፤ በመቆናጠር የወጣው ። ስለዚህ ድጋሚ ሙከራ ቢያደርግም ውሎ ከአደረ በኋላ ይሆናል ። እኔም እስከዛ ድረስ ሳይመንን በመቀራረብ ተዋውቄው ሲኔት ማድረግ ስለሚኖርባት ጥንቃቄ በተዘዋዋሪ እንዲነግራት ለማድረግ ዕቅድ ነበረኝ ። በትናንትናውም ምሽት በሳሎኑ ውስጥ አደጋ ባይፈጠር ኖሮ ሳይመንን ለማነጋገር አመቺ ሁኔታ እንደማገኝ አልጠራጠርም ነበረ” ሲለው ሬስ ነገሩን በትክክል ለመረዳት፡ እራሱን እያወዛወዘ አሳየ ።

ፖዋሮም “ ግልፅ ሆነህ የምትመልስልኝ ከሆነ ፤ አንተ በፔኒንግተን ቦታ ብትሆን ኖሮ ሲኔትን ነው ወይስ ሳይመንን ለማታለል ቀላል ሆኖ የምታገኘው ? ” ብሎ ጠየቀው ። ፋንትሮፕ ሳቅ እያለ ፡

“ ሁልጊዜም ሳይመንን ይሆናል ! ሲኔት ሞኝ ልጅ አልነበረችም ። ለሳይመንማን በተፈለገ መንገድ ሰነዶችን እያዘጋጁ ፤ የሚፈርምበትን መስመር ማሳየት ብቻ በቂ ነው ! ” ሲል ፡

“ እስማማለሁ ! ይህም ለግድያ በቂ ምክንያት ሊሆን ይችላል ” አለ ፖዋሮ በበኩሉ አስተያየቱን እየደመደመ ።

“ ችግሩ ማስረጃ ከማግኘቱ ላይ ነው ? ” አለው አሁንም ፋንትሮፕ ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አያስቸግርም ! ”

“ እንዴት አያስቸግርም ? ”

“ ከፔኒንግተን ከእራሱ ይገኝ ይሆናል!” አለና ጕዋይ ፋንትሮሜኖን አመስግኖ ከሸኘው በኋላ ፔኒንግተን እንዲጠራ አደረገ ። ፔኒንግተን እንደተጠበቀው ሳይሆን ፈገግታ እያሳየ ነበር የገባው ። በዓይኑ ዙሪያ ግን የድካም ምልክት ይታይበት ነበረ ። ብዙ ጥያቄዎችንም በአእምሮው ውስጥ ሲያመላልስ ለመቆየቱና የሚሰጠውንም መልስ ለማዘጋጀቱ ጥርጥር የለውም ። ስለዚህም ፡

“ ታዲያስ ጌቶቼ ! እንዳስጠራችሁኝ መጥቻለሁ፡” አለና ወንበር ስቦ ተቀመጠ

“እምን ! ያስጠራንህ ጉዳዩ ግልጽ እየሆነ በመሔዱና በተለይም ደግሞ አንተን በቀጥታ የሚመለከትህ በመሆኑ ነው ” ሲለው ጕዋይሮ ፡ ፔኒንግተን ከተዝናናበት ቀና እንደማለት ብሎ ፡

“ ለምን ! ” ሲል ጠየቀ ፡

“ መልሱን ታውቀዋለህ ብዬ ነበረ ። ለማንኛውም ሊኔትን ከህፃንነቷ ጀምሮ በሞግዚትነት አሳድገሃታል አይደለም ? ” እለና ጕዋይሮ እረጋ ብሎ ጠየቀው ።

“ እምን !” አለ የቀድሞው ፈገግታው እየተገፈፈ “ ሊኔትን የማውቃት ገና ትንሽ ልጅ ሆና ነው ”

“ ከአባቷ ጋር የቅርብ ጓደኞሞች ነበራችሁ ? ”

“ ነበርን ። በጣም ሲበዛ እንቀራረብ ነበረ ”

“ ስለዚህም ልጇን በሞግዚትነት እንድታሳድግ ለትና እጅግ ሰፊ የሆነውንም ሐብትና ንብረት እንድትቆጣጠርላት አደራ ሰጠህ !”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ቢሆንም ንብረቱን ለማስተዳደር ብቃቱን አልተወከልኩም ! ሁለት ሰዎች በተጨማሪ ነበሩ ”

“ ግን ሁለቱም አሁን ሞተዋል ! ”

“ አዎን ሞተዋል ! ”

“ ጥሩ ! ” አለና ፑዋሮ ትንሽ ተከዘ “ ሊመሆኑ እንደ ነገሬው የአንተ ሞግዚትነት የሚሻረው ሊኔት ስንት ዓመት ሲሞላት ነበረ ? ” ሲል ጠየቀው ፡

“ ሃያ አንድ ዓመት ”

“ እርሷ ግን በሃያ ዓመቷ ባል አገባች ”

“ አዎን !”

“ ስለዚህ ባል ካገባች በንብረቷ ቀጥታ ማዘዝ ትችል ምራለች ማለት ነው ? ”

ፔኒንግተን ከንፈሩን እየነከሰ “ይህን የመሳሰለ ጥያቄ የምትጠይቁበት ምክንያት ምንድን ነው ?” አለ በንዴት።

“ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት ካልፈለግህ ይቅር . . . ” ሲለው ፑዋሮ

“ የመፈለግና ያለመፈለግ ማይሆን ይህ ፡ ተፈጸመ ከተባለው ግድያ ጋር ምን ዝምድና አለው ?” ሲል ፔኒንግተን በመቆጣጠር ተናገረ ።

“ በበኩላችን ዝምድና ሊኖረው ይችላል ብለን እንገምታለን ” አለ ሬስ በተራው “ ግድያ ያለምክንያት አይፈጸምም ። ከምክንያቶቹ ውስጥ ደግሞ አንዱ ገንዘብ ሊሆን ይችላል ! ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ፔኒንግተን እየቀፈፈው " እሺ ! እንግዲያውስ ተነ ስቶ የነበረውን ጥያቄ ልመልስላችሁ ። እንደ አባቷ ኑዛዜ ሊኔት ሐብቷን በቀጥታ ማስተዳደር የምትችለው እድሜዋ ሀያ አንድ ዓመት ከሞላት ወይንም ባል ካገባችበት ጊዜ ጀምሮ ነው !" አለ ።

" ጠቅላላ ንብረቷ በስንት ይገመታል? "

" በብዙ ሚሊዮን ብር ፡"

" በጣም ከባድ ኃላፊነትና አሳሳቢ አደራ ነው የተ ጣለብህ ! "

" ለብዙ ዓመታት የተለማመድኩት ስለሆነ እያስ ጨነቀኝም "

" ይደንቃል ! " ብሎ ፑዋሮ ቆም ሲል ፔኒንግተን ብነገር ነካ እንዳደረገው ስለተሰማው ፡

" ምኑ ነው የሚደንቀው ? " ሲል ንዴቱ እየጨመረ ጠየቀው ። ፑዋሮ ግን ምንም ነገር ለመሸፋፈን ሳይሞ ክር " የሚያስደንቀው የሊኔት ያልታሰበ ጋብቻ በአንተ ዘንድ ጭንቀት አለማስከተሉ ? " ሲለው

" የምን ጭንቀት ? ለምን በግልጽ አንነጋገርም"አለ ፔኒንግተን ፡

" እውነትክን ነው ! ፡ ጥያቄዬን በቀላሉ ላስቀም ጠውና ለመሆኑ የሊኔት ሐብትና ንብረት ተመዝብሮም እያውቅ ?" ብሎ ፑዋሮ ንግግሩን ሳይጨርስ ፔኒንግተን ከተቀመጠበት ወንበር አፈፍ ብሎ በመነሣት ወደ በሩ



t.me/OLDBOOKSPDF

እየሔደ ፡ “ በጣም አበዛችሁት ! ልክ አይደላችሁም ! ” ሲል “ ከመሔድህ በፊት ጥያቄዬን መመለሱ ይሻል ይመስለኛል!” አለው ፑዋሮ በእርጋታ ። ፔኒንግተን የባሬ ፋን እጀታ ለመክፈት ከሞከረ በኋላ የሆነ ሐሣብ በአእምሮው ውስጥ መጣ ። እንደማመንታትም ካለ በኋላ “ ሐብቷም ንብረቷም የተያዘው በጥንቃቄ ነው ! ” አለ እዚያው እንደቆመ ።

“ ታዲያ ግብጽ ድረስ ምን ሲያርጥ አመጣህ ? ”

“ የመጣሁት ለሽርሽር ነው ። ሊኔት ባል ማግባቷንም የሰማሁት እዚሁ ነው ። ካይሮ ላይ እንደአጋጣሚ በአንድ ሆቴል መኝታ ይዘን ስለነበረ ተገጣጠምን ። ስለ ጋብቻዋ ገልጻ የጻፈችልኝ ደብዳቤ አሜሪካ ከመድረሱ በፊት እኔ ወደዚህ መጥቼ ነበረ ።”

“ የመጣኸው በየትኛዋ መርከብ ነበረ ? ”

“ ካርማኒያክ በምትባለው ! ”

“ ካርማኒያክ ? ” አለና ፑዋሮ ሠረቅ አድርጎ እየተ አደረገው ፡ “ የሊኔትን ጋብቻ የሚገልጸው ደብዳቤ ሣይደርስህ መጣህ ማለት ነው ?”

“ አንድ ጊዜ የተናገርኩትን ለምን እንድደጋግመው ታደርጉኛላችሁ ? ”

“ ለምን መሰለህ ? አንተ የመጣኸው በካርማኒያክ ሣይሆን ኖርማንዲ በምትባለዋ መርከብ ለመሆኑ ካይሮ ከሚገኘው የገዛ ወኪል ጽሕፈት ቤት በቴሌግራም ስለ አረጋገጥን ነው ። ”



t.me/OLDBOOKSPDF

ፒኒንግተን በቆመበት ፍዝዝ ብሎ ቀረ ። ምድርና ሰማዩ ብዥ አለበት ። በእጁም ዳብሶ ወንበር ፈልጎ ከተቀመጠ በኋላ ፡

“ እጅን አንስቻለሁ ጌቶቼ ! ከእናንተ ጋር መስተካከል የማይገባኝ ደካማ ፍጡር መሆኔን አሁን ነው የተረዳሁት ። ግን እንደዚህ ለማድረግ የተገደድኩበትን ምክንያት ባስረዳችሁ ? ” ሲል ጠየቀ ።

“ ሞክር ! ” አለው ሬስ ወደ ጐን እያየ ።

“ ግን ምሥጢር ስለሆነ በእናንተ ዘንድ ብቻ እንደታወቀ ቢቀርልኝ ? ”

“ ምሥጢር አባካኞች ባንሆንም የአንተን ምሥጢር እንደብቅልሀለን ብለን ቃል ከመግባታችን በፊት ስለምን እንደምታወራ ማወቅ አለብን ። ”

ፒኒንግተን ወንበሩን እያንፏቀቀ ወደ ፑዋሮ በጣም ከተጠጋ በኋላ ፡ “ የእኔን ንጽሕና እንደምትረዱልኝ አልጠራጠርም ። ምን መሰላችሁ ? በእንግሊዝ አገር ውስጥ የተፈጸመ የሚጭበረበር ተግባር ነበረ። ይህንን ደግሞ በደብዳቤ ለመግለጽ ስለተቸገርኩ እራሴ መጥቼ ማስረዳት ነበረብኝ።” ሲል

“ ማን ነው የተጭበረበረው ? ” አለው ፑዋሮ ።

“ ሊኔት ! ”

“ በማን ? ”

“ ካርማይክል በሚባለው ነገረ ፈጅ ። በጽሁፍ የሚገለጽ ስላልነበረ ሊኔትን በቅርብ አግኝቼ ላስጠንቅቃት ፈልግኩኝ ። ”

“ ነገሩስ ባልከፋ ነበረ ! ግን ደብዳቤዋ አልደረሰኝም ብለህ ለምን ለመዋሸት ፈለግህ ? ”



t.me/OLDBOOKSPDF

“ ለወሬ ስል ግብጽ አገር ድረስ ሲኔትን ተከታትዬ የመጣሁ መሆኑ እንዲታወቅብኝ አልፈልግሁም ነበረ ። ስለዚህ በድንገት እንደተገናኘን ማስመሉን መረጥሁ ። በተለይም ስላባሏም አንዳንድ ሁኔታዎች ለማጥናት በመፈለጌ ነው ።”

“ አድራጐትህ ሁሉ በንጹህ አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ ይመስላል !” አለው ሬስ በሽርደዳ አነጋገር ። ፔኒንግተን ግን በተቀመጠበት እየተቁነጠነጠ ፡

“ ልክ ነዎት ኰሎኔል ! በትክክል አስቀምጠውታል ! አለ ። ለጥቂት ጊዜም ጸጥታ ሰፈነ ። ፑዋሮ ፔኒንግተንን ሲያጠናው ቆይቶ ፡

“ ሚስተር ፔኒንግተን ! ከተናገርከው ውስጥ አንድም የሚታመን ቃል የለም !” አለው ።

“እንዴት ? እንዴት እታም ትኝም?” ሲል ፔኒንግተን ይጮህ ጀመረ ። ፑዋሮ ግን አነጋገሩን ሳይቀይር ፡

“ እኛ የምናምነው የሲኔት ያልታሰበ ጋብቻ ከትልቅ ጭንቀት ውስጥ እንደጣለህና ወደ ግብጽም በተቻለ ፍጥነት ሁሉ መምጣትህን ነው ። እኛ የምናምነው ሲኔትን በአፍላ ፍቅር ላይ እንዳለች አንዳንድ ሰነዶችን በማዘናጋት ልታስፈርማት አቅድ እንደነበረህ ነው ። ይህም አልሳካ ሲልህ የአቡ ሲምበልን መቅደስ ጉብኝታእንደወጣች ሊኔትን በናዳ ለመግደል ትልቅ ቋጥኝ ድንጋይ ከተራራው ላይ ለቀቅክ” ሲለው ፡ ፔኒንግተን በተቀመጠበት ላቡ እያስጠመጠ ፡

“ ፍፁም ሐሰት ! የማይታሠን ነው ! ” እያለ ይለፈልፍ ጀመረ ። ፑዋሮ ግን ንግግሩን በመቀጠል ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አንተ ባታምንበትም እኛ የምናምነው ፤ የመጀመሪያ የማይድያ መክራህ ማይሳካልህ ሲቀር ሌላ ዘዴ ማጠንጠንህን ነው ። ማመን ብቻ ማይሆን እንደምናውቀውም ሚስስ ዑተርበርን የተገያለችው በአንተ ሽጉጥ ሲሆን እርሷ ደግሞ ሊኔትንና በርጀን የገደለውን ሰው ስም ልትነግረን ስትል ነው . . . ” ሲል ፔኒንግተን አቋረጠት ፤

“ ለምን ሁሉንም ነገር በእኔ ላይ ትደፈድፉብኛላችሁ ? ምንስ ትጠቀማላችሁ ? ሊኔትን የምገድልበት ምን ምክንያት አለ ? የእርሷን ሐብት የምወርስ እኔ ነኝ ? አይደለሁም ። ወራሿ ባሏ ሳይመን ነው ! ለምን እርሱን አትጠይቁትም? የሚጠቀመው እርሱ እንጂ እኔ አይደለሁም!” እያለ ጮኸ ።

“ ሳይመንን ያልጠየቅነው አለመግደሉን በሚገባ ስለምናውቅ ነው ። ሳይመን ቆስሎ ነበረ ። መንቀሳቀስ አይችልም ። ይህ ደግሞ በዶክተር ቤስነር የተረጋገጠ ነው ። ሳይመን ከቆሰለበት ተነስቶ ሊኔትንና በርጀን ለመግደል አይችልም ። በተለይም ሚስስ ዑተርበርን ስትገደል እኔም ፑዋሮም በሳይመን ክፍል ውስጥ ነበርን ” እያለ ኮሎኔል ሬስ ሊያስረዳው ሞከረ ። ፔኒንግተንም ቀዝቀዝ እያለ ፤

“ ነገሩን ማለቴ ነው እንጂ እኔም ብሆን ሳይመንን ወንጀለኛ ማድረጌ አይደለም ” አለ ።

“ ስለዚህም ወደ ጀመርነው ቁም ነገር እንመለስና ” አለና ፑዋሮ“ሊኔት ባልታሰበ ጊዜ ማግባቷ ያሳሰበከውን ችግር እንደፈጠረብህ ቀደም ሲል ተናግሬዋለሁ ። ስለዚህም ሐብቷን መቆጣጠር ስትጀምር አደራህን ባለማክበር ብዙ ንብረት እንደበዘበዝካት ትደርስብሃለች ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ ሊኔት አስቀድሞ መገደል አለባት ። እንደተናገር ከሙም ሊኔት ከተወገደች የሐብቷ ወራሽ ሳይመን ይሆናል ማለት ነው ። ስለዚህም ሳይመንን በቀላሉ ማንቀሳቀስ እንደምትችል ስለምታውቀው . . . ” ብሎ ሳይጨርስ ፔኒንግተን እንደልማዱ ፡

“ ውሸት ! የማይመስል ታሪክ ! ” አያለ በመጮህ አቋረጠው ።

“ ወደ ፊት እናያ ይሆናል ! ” ሲለው ፑዋሮ

“ ምን ማለትዎ ነው ? ” አለ ፔኒንግተን ፡

“ ጊዜ ወደፊት ያሳየናል ያልኩት በዚች መርከብ ላይ፤ ሦስት ሰዎች ተገድለዋል ። ስለዚህ ለሁሉም ምንም ቢሆን የሊኔት ሐብት ስለሆነ ፡ ነካ ነካ ተደርጎ የሚታለፍ ምርመራ አለመሆኑን ሳስገነዝብህ ብዬ ነው ። ” ሲለው ፔኒንግተን ለሁለተኛ ጊዜ ተነስቶ ከነበረበት ወንበር ቀስ ብሎ አረፍ ካለ በኋላ ፡

“ ምን ሳድርግ ሙሴ ፑዋሮ ! ምን ሳድርግ ኩሎኔል ሬስ ! መስለኝና ጥፋት ሠርቻለሁ ። አክብራለሁ ስል በመከሰሬ የሊኔትን ሐብት ማባከኔ እርግጥ ነው!” አለና በሚንቀጠቀጡት እጆቹ ሲጋራ ፈልጎ አያያዘ ።

“ ሐብቷን ማባከንህን ካመንክ ፡ ሊኔትን ለመግደል ስለአደረግከው ሰ ሙከራ ! ” አለው ፑዋሮ ። ፔኒንግተን እንደምንም የሲጋራውን ጢስ አንድ ሁለት ጊዜ ስቦ

“ ሆን ብዬ ያንን ቋጥኝ ድንጋይ አላንከባለልኩትም። እርግጥ አያናቅሮኝ እላዩ ላይ መውደቁን አውቃለሁ ። ሌላ ወንጀል ግን አልፈጸምኩም ! ስለዚህም ጊዜያችሁን በእኔ ላይ አታባክኑ! ” ብሎ አንገቱን እንዳቀረቀረ ወጣ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥዋሮና ሬስም ለብዙ ጊዜ በዝምታ ሲተያዩ ቆዩ ። በመጨረሻም ጥዋሮ ፣ “ የተበታተነው ሰንሰለት ተገጣጥሞ አለቀ ! ” አለና ፈገግ ሲል፣

“ እውነትክን ነው ጥዋሮ ? ወንጀለኛውን ያረሰክበት ማለት ነው ? ” አለና ሬስ በጉጉት ጠየቀው ። ጥዋሮ ግን

“ እዎን ! ” የምትለዋን ቃል ብቻ መለሰ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

“ ያ ያንተስ ሰውዬ ? አገኘኸው አይደል ? ” አለና ጥዋርድ ሬበን ሲጠይቀው ፡ ሬስ ፊንግ እያለ ፡ “ እንደምን ወቅህ ? ” አለው

“ ሳይመን ሲኔት አንብባው ስለነበረው ቴሌግራም ይዘት ሲነግርህ ሰውነትህ ከመቅጽበት ሲለዋወጥ ተመ ክቼ ነበረ ። ለካ እን ድንችና ሰላጣም የተለየ ትርጉም ኖሯ ቸዋል ?” አለ በተራው ጥዋርድ ፊንግ እያለ ፡

“ሪቼቲንም ያናደደው ይህ ነበረ ። በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ተቀጣጥሎ በነበረው አመጽ በዱሮች ይጠቀሙበት የነበረ የምሥጢር መግናኛ ነው ። ድንች ጥይት ፡ ቲማ ቲሙ ቦንብ ፡ ሠላጣው ደግሞ ጠመንጃ . . . ማለት ነው ። ሲኔት እንደቀልድ በለዚያ ቴሌግራም እኔ ፊት ካወራች ሪቼቲ ያለቀለት መሆኑን ተረድቶ ነበረ ” አለና ሬስ ለጥ ቂት ጊዜ ጥዋርድን ትኩር ብሎ እየተመለከተ “ ስለሆነም ሲኔትንም የገደላት እርሱ ነው እንዳትለኝ ? ” ሲል በመ ገረም ጠየቀ ።

“ አይደለም! ” አለና ጥዋርድ መለሰ ። ለጥቂት ደቂ ቃዎችም ጸጥታ ሰፈነ ። ሬስ በታላቅ ጉጉት “ ታዲያ ገዳዩ ማን እንደሆነ ለምን አትነግረኝም ? ” አለው ።

“ የመጀመሪያ ዘር ግድያ የፈጸመውን ከደረስኩበት ቆየት ያለ ቢሆንም ፡ ሁለተኛውን ዘር የፈጸመውን ለማ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማኘት ጊዜ ፈጅቶብኛል ። አሁን ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኗል ። ሆኖም አንድ አስቸጋሪ ነገር አለ። መረጃ ልሰጥበትም አል ችልም ። ነገር ግን ስነግርህ እንደምትረዳው በአእምሮ ደረጃ ተቀባይነት አለው ። ስለዚህም የሚኖረን አንድ ዕድል ብቻ ነው ። ግዳዩን የፈጸመውን ሰው በረቀቀ የአ ቀራረብ ዘዴ ማሳመን አለብን ” አለ ፔዋሮ

ሬስ እራሱን በመነቅነቅ “ በተአምር ካልሆነ በስተቀር እድል ያለን አይመስለኝም! ” ሲል አስታያ የቱን ሰጠ ።

“ ወንጀለኛው እስከዚህም መንፈስ ጠንካራ ሰው ስላልሆነ ብዙም ሳንለፋ እናናዝዘዋለን ብዬ እገምታለሁ”። ብሎ ፔዋሮ ሲናገር ሬስ እየተቻኮለ ፡ “ እባክህ ስሙን ንገረ ኝና፡በጉጉት የታመቀው ልቢ ይተንፍስ!” ሲል አጣደፈው።

“ ትክክለኛውን ሁኔታ ለመረዳት እንድትችል ታሪ ኩን ከመጀመሪያው ጀምሬ እንዳጫውትህ ያስፈልጋል” አለና ፔዋሮ ወንበሩን ወደ ሬስ ጠጋ በማድረግ ንፈጅም ንግግሩን ጀመረ ።

“እንደምታስታውሰው እኔና አንተ ምርመራችንን የጀ መርነው ወንጀሉ ያለአንዳች ቅድመ ዝግጅት እንደተፈፀመ በመቁጠር ነበረ ። በእኛ አስተሳሰብ በትናንትናው ምሽት በጃኩሊንና በሳይመን መካከል በተፈጠረው ግጭት ተጠ ቅሞ ገዳዩ ሽጉጧን ከተወረወረች በት ከሶፋው ስር በማ ንሣት ሊኔትን እንደገደላት ነበረ ። በወንጀሉም ቀጥታ ተጠርጣሪ ጃኩሊን እንድትሆን ተሞክሮ ነበረ ። ሆኖም ይህ የእኛ ግምት በመጨረሻ ላይ ስህተት ሆኖ አገኘሁት።

“ወንጀሉ ቅጽበታዊ ሳይሆን ለእረጅም ጊዜ የታ ቀደ ነው ፡ የሚፈጸም በት ሥፍራና ሰዓት ሳይቀር በዝርዝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ርና በጥንቃቄ የተጠና ነበረ ። ሌላው ቀርቶ እኔን በትናን ትናው ሌሊት በክባድ እንቅልፍ እንድዋጥና እንዳችም ነገር እንዳልሰማ ለማድረግ እራት ከበላሁ በኋላ በጠጣሁት ወይን ውስጥ የእንቅልፍ ኪኒን እስከ መጨመር ድረስ ቀደም ሲል የተጠና ዘዴ ነበረ ። እኔም በወቅቱ ምንም አልተጠራጠርኩም ፤ እንደምታስታውሰው የትናንትናው እለት በጣም ይመብቅ ነበረ ። የአቡ ሲምበልን መቅደስ ለመጎብኘት በእግራችንም ተጉዘን ነበረ ። ስለዚህም እናንተ በሳሎኑ ውስጥ ካርታ ስትጫወቱ እኔን ያልተለመደ እንቅልፍ ተጫጫነኝ ። በጊዜ ለመተኛትም ተገደድኩ ። ከዚህም በመነሣት ወንጀሉ ቅድመ-ዝግጅት ተደርጎበት የተፈጸመ ለመሆኑ እንደ መተማመኛ አገኘሁ ። ”

“ ሌላው ፍንጭ ደግሞ የባች ሽጉጥ ከወንዙ ውስጥ መገኘት ነው። እንደ ቀድሞው አስተሳሰባችን ከሆነ ሽጉጧ በመጀመሪያ ደረጃ ወደ ወንዙ መወርወር የለባትም ነበረ። ወንጀሉን የፈጸመችው ጃኪሊን እንድትሆን ለማስመሰል እቅድ ካለ ያቺ ሽጉጥ በመርከቧ ላይ መገኘት ነበረባት ። ግን ወደ ወንዙ ውስጥ ተጣለች ! ለምን ይመስልሀል ሬስ?” አለና ፑዋሮ ለጥቂት ጊዜ በሐሳብ ተመስጦ ቆየ ። ሬስ ምንም አስተያየት ለመስጠት አልቻለም ነበረ ። ስለዚህም ፑዋሮ ማብራሪያውን በመቀጠል ፤

“ ታስታውስ እንደሆነ ሊኔት የተመታችው ከጆሮዋ በላይ ሲሆን በቁስሉ ዙሪያ ያለው ቆዳዋ ተለብልቦ ነበረ ። ይህም ማለት በተገደለችበት ጊዜ የሽጉጡ አፈሙዝ ወደ ሰውነቷ በጣም ተጠግቶ ነበር የተተኮሰው ማለት ነው ። ”

“ አዎን ! ልክ ነው ” አለ ሬስ ።

“ግን ሽጉጧ ወደ ወንዙ ውስጥ ተወርውራ የነበረው በሰማያዊ ሻርፕ ተጠቅልላ ነበረ ። ሻርፑም በተደጋ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተበሳጭቶ ነበረ ። ይህም የሚያሣየው የተኩሱን ጩኸት ለመቀነስ ሲባል ምንን ሻርፕ በማጣጠፍ ተተኩሶበት እንደ ነበረ ነው ። ሆኖም በሲኔት ቁስል ዙሪያ ያለው ቆዳ ተልብ ሉፏል ። ስለዚህ ሲኔት የተገደለችው በተጣጠፈው ሻርፕ ውስጥ በተተኮሰው ጥይት አይደለም ማለት ነው ። ጃኪ ሲንም በሳይሞን ላይ በተኮሰችው ጥይት ሲኔት ላለመ ገደሏ እርግጠኞች ነን ። ለዚህም በተኩሱ ጊዜ የነበሩት የዓይን ምሥክሮች አረጋግጠውልናል ። ሁኔታው ይህ ከሆነ ሌላ የተተኮሰ ጥይት ነበረ ማለት ነው ።

“ ከዚህ ሌላ ያለው ፍንጭ ደግሞ በሲኔት ክፍል ውስጥ የተገኙት ሁለት የጥፍር ቀለም ብልቃጦች ናቸው ። ሴቶች የጥፍር ቀለሞቻቸውን እንደሚቀያይሩ ማልጽ ነው ። ሆኖም ከአንደኛው ብልቃጥ ውስጥ ያፈሰሰኳቸው ጥቂት ጠብታዎች ቀይ የብእር ቀለም እንጂ የጥፍር ቀለም አልነበረም ። ይህንንም በሽታው ጭምር አረጋግ ጫለሁ ። ሲኔት በቀይ ቀለም ልትጽፍ ትችላለች ። ቀለሙ ግን በብእር ቀለም ብልቃጥ ውስጥ መገኘት ይኖርበታል እንጂ በጥፍር ቀለም ብልቃጥ ውስጥ የሚቀመጥበት ምክ ንያት የለም ። ነገሮችንም ማዛመድ ስሞክር ሽጉጡ ከበ ስተውስጥ በኩል ተጠቅልሎበት ከነበረችበት ከዛች በቀይ ቀለም ከራሰች መሐረብ ጋር ግንኙነት እንዳለው በቀላሉ ለመረዳት ቻልኩኝ ።

“ ጥቂት ጊዜ ቢፈጅብኝም ከነኝህ ፍንጮች በመ ነሣት ጉዳዩን ልደርስበት እንደምችል እርግጠኛ ነበርኩ ። ሆኖም ነገሮች ሁሉ እንዳይፋጠኑ አንድ ያልተጠበቀ ክስ ተት ተፈጠረ ። ይኸውም የሉዊ በርጂ መገደል ነበረ ። የተገደለችው ወንጀለኛውን ለማጋለጥ በማስፈራራት ገንዘብ በመቀበል ላይ እንደነበረች ለመሆን በእጅዋ ይዛው በነበረው የፈረንሣይ አንድ ሺህ ፍራንክ ኖት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁራጭ ግልጽ ማስረጃ ነው ። በተለይም ዛሬ ጠዋት ጠር ተን ስናነጋግራት ምን ተናግራ እንደነበረ ትዝ ይልሀል ? ልብ በልና አዳምጠኝ ። “ እንቅልፍ አልወስድ ሽም ቢለኝና ምናልባት ወደ እመቤቴ መኝታ ክፍል ብመጣ ኖሮ ያንን አረመኔ ነፍሰ ገዳይ ወደ መኝታ ክፍሏ ሲገባ ወይንም ሲወጣ ባየሁት ነበረ ’ ብላለች ። ምን ማለቷ ይመስልሀል ሬስ ? ” አለናፑዋሮ ሲጠይቀው ሬስ በፑ ዋሮ አስተሳሰብ ጥልቀት እየተገረመ ፡

“ ወደ እመቤቷ መኝታ ክፍል መምጣቷን የሚጠ ጠቁም ይመስለኛል!” አለው።ፑዋሮ ግን በተቃውሞ እራ ሱን በኃይል እያወዛወዘ ፡ “ ለመጠቆም የፈለገችው ይህ ንን ማይሆን ሌላ ነገር ነው ። ለወንጀለኛው የምታስተላ ልፈው መልእክት ነበራት ” ሲለው ፡

“ ምን ማለትህ ነው ፑዋሮ ? ጠዋት ስናነጋግራት በዚያ ክፍል ውስጥ የነበረነው ዶክተር ቤስነር ፥ ሳይመን ፥ አንተና እኔ ብቻ ነበርን ። እርግጥ አቅርበንላት ለነበረው ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ በመስጠት ‘ ማንንም አላየሁም ተኝቼ ነበረ ’ ወይንም ‘ ስላልተኛሁ ገዳዩን አይቼዋለሁ፡ እገሌ ነው ’ ማለት ነበረባት፡ አመላለሷ ግን አንድ ነገር ለመደበቅ እንደሚፈልግ ሰው የተሸፋፈነ ለመሆኑ አሁን ግልጽ ሆኖ ታይቶኛል ። ያልገባኝ ነገር ለወንጀለኛው የምታስተላልፈው መልእክት ነበራት ስትል ወንጀለኛው ከአራታችን መካከል አንደኛችን ነን ማለትህ ነው ? ” አለና ሬስ ግራ ተጋብቶ ጠየቀው ።

“አዎን !” አለ ፑዋሮ በተለመደ ትእግሥት በተሞላው አነጋገሩ፡ “ ስለዚህም ረጋ በልና አዳምጠኝ።በክፍሉ ውስጥ



t.me/OLDBOOKSPDF

የነበርነው እንደ ተናገርከው አራት ሰዎች ነን ። ቡርጂ ከአራታችን ውስጥ ለአንደኛችን መልእክት ለማስተላለፍ ሞክራለች።በቅድሚያ ዶክተር ቤስነርን እንውሰድ ። ወን ጀለኛው ቤስነር ሊሆን ይችላል ? አይመስለኝም ! ቤስነር ሲኔትን የሚገድልበት ምንም ምክንያት አይኖረውም ። ሌላስ አብሮን የነበረ ሰው ማነው ? ” አለና ፑዋሮ ሲጠ ይቅ :

“ ከእኔና ከአንተ በስተቀር ሳይመን ብቻ ነው ”ሲል ሬስ መለሰለት ፡

“ ታዲያ መልእክቱ እንዴት ለሳይመን የተቃጣ ሊሆን ይችላል ? ሳይመን ያመሸው በሳሎኑ ውስጥ ነው። በኋላም ከጃክሊን ጋር ቡተፈጠረው ግጭት የተነካ ቆስ ሏል ። ለዚህም በቂ ምስክሮች አሉት ። ቁስሉም ሊያንቀ ሳቅሰው የሚችል አልነበረም ። ይህንንም ቢሆን የሕ ክምና ባለሙያው ዶክተር ቤስነር አረጋግጦልናል ። ስለዚህ የሲኔት ገዳይ ሳይመን ሊሆን እንደማይችል ስለ ምናውቅ አሁንም ወደ ሌላው ተጠርጣሪ ዶክተር ቤስነር እንመለሳለን ። በተለይም ቡርጂ የተወጋችበት ስለት ሐኪ ሞች ለቀዶ ጥገና የሚጠቀሙበት ዓይነት መሣሪያ በመ ሆኑ ጥርጣሬአችንን እያጠናከረው ይሔዳል ።

“ ግን ” አለና ፑዋሮ የሬስን ዓይኖች እየተመለከተ “ ግን ቡርጂ የማስፈራሪያ መልእክቷን ለማስተላለፍ ያፈለገችው ለዶክተር ቤስነር ከሆነ ለምን ያንን አጋጣሚ ጠብቃ ጠበቀች ? ቤስነርን በማንኛውም ሰዓት ብቻውን አግኝታ ልታነጋግረው ትችላለች ። ስለዚህ አሁንም ልንጠረጥረው የምንችለው አንድ ሰው ብቻ ይኖራል። ሳይ መን ብቻ ነው ማለት ነው ። ሳይመን ቆስሎ ስለነበረ ቡርጂ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደልቧ አግኝታ ልታነጋግረው እድል የላትም ። ስለ ዚህም በእነኛ በተሸፋፈኑ ቃላት ማስጠንቀቂያዋን አስ ተላለፈችለት ” አለና አሁንም ለጥቂት ጊዜ እንዳቀረቀረ በሐሣብ ተውጦ ከቆየ በኋላ ቀና አለና ፤

“ ሬስ ! ዛሬ ጠዋት ሴላ በተጨማሪ ተናግራው የነበረውስ ትዝ ይልሀል?” ሲል ጠየቀው ።

ሬስ እራሱን በማወዛወዝ ብቻ የሚያስታውሰው ነገር እንደሌለ አሳየ ። ፑዋሮ ንግግሩን በመቀጠል ፤

“ ‘ጌታዬ እባክዎን ይርዱኝ ፤ ከዚህስለ ሌላ ምን ለመናገር እችላለሁ ” ብላ ወደ ሳይመን እየተመለከተች ስትናገረው ምን ብሎ መለሰላት ፤ ‘ አይዞሽ አትፍሪ ማንም የማታውቂውን እንድትናገሪ የሚያስገድድሽ የለም ። እኔ እያለሁልሽ ምንም አትሆኝም ! ማንንም መፍራት የለብሽም ! ’ በማለት መልሶላት ነበረ ” ሲል ሬስ አቋረጠውና ፤

“ ፑዋሮ ! እንዴት ሊሆን ይችላል ? ሳይመን እኮ ንቱ ተሰብሮ በሕክምና ላይ ይገኛል ። ዶክተር ቤስነር እንዳረጋገጠውም ቁስሉ ከባድ ነው ። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ላይ ያለ ሰው ሊኔትን በሽጉጥ በርጁን በጩቤ ወግቶ ለመግደል ይችላል ? በአንድ እግሩ እየዘለለ ነው እንዴት ለኝ ?” ሲል ጠየቀው ።

“ ሳይመን ቆስሎ ከተኛበት አልጋ ላይ መነሣት እንደ ማይችል እኔም ብሆን የማውቀው ነው ። መሆንም የማይ ችል ነገር ነው ። ግን በርጁ እነኛን ቃላት ለምን ተና ገረቻቸው ? ለዚህ መልስ ማግኘት ነበረብኝ ። ስለዚህም የማታውቀን ሁኔታ እንደገና ሀ ብዬ ማመዛዘን ጀመርኩ ።

“ ምናልባትም ሳይመን ከጃኩሊን ጋር ከመጋቡ በፊት ከሳሎኑ ወጥቶ ሊሆን ይችላል ወይ የሚለውን ጥያቄ



t.me/OLDBOOKSPDF

በቅድሚያ መመለስ ነበረብኝ ። አለመውጣቱን ኮርኔሊያና ፋንቅሮኘ አረጋግጠውልናል ። ቆስሎ ከተኛበት ከዶክተር ቤስነር ክፍል ውስጥ ወጥቶ ግድያ ለመፈጸም እንደማይችል የተረጋገጠ ነው።እንግዲያውስ የሊኔት ገዳይ ሳይመን ነው ለማለት እንዴት ይቻላል ? ሳይመን ብቻውን የነበረበት ጊዜ ቢኖር ጃኩሊን ካቆሰለችው በኋላ አንኮር ኔሊያ ጃኩሊንን ወደ መኝታ ክፍሏ ለማድረስና ለእርሱም የሕክምና እርዳታ እንዲያደርግለት ዶክተር ቤስነርን ሊጠሩለት በሔዱበት ወቅት ነው ። ከዚህ በመቀጠል ሳይመን በእርግጥ ቆስሎ ነበር ወይ ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞከርኩኝ ።

“ እንደ ኮርኔሊያ ቃል ከሆነ ጃኩሊን ሽጉጧን ከቦርሳዋ ውስጥ አውጥታ በሳይመን ላይ በመደገን ‘ እንደ ውሻ እገድልሀለሁ ! ’ ብላ መተኮሷን ከዚያም ሳይመን ተሸክርክሮ ከወንበር ላይ እንደወደቀና ፋንትሮፕን ጠርታው ስትመለስ ከጉልበቱ ላይ ቆስሎ ቁሬው ቀስ በቀስ በደም እየራሰ መሔዱን ገልጻልናለች ። ፋንትሮፕስ በበኩሉ ያየው ምን ነበረ ? የጃኩሊንንና የሳይመንን ጭቅጭቅ ላለመስማት ከሳሎኑ ወጣ ከማለቱ የጥይት ተኩስ ሰማ። ከኮርኔሊያም ጋር እየተሯሯጡ ሲገቡ ሳይመንን በወንበር ላይ ወድቆ ቁሬው በደም እየራሰ መሔዱን ተመልክቷል ። ከዚያስ በኋላ ምን ተፈጠረ ? ጃኩሊን ተፀጽታ ማልቀስ ስትጀምር ሳይመን ወደ መኝታ ክፍሏ እንዲወስዷትና ብቻዋን እንዳይተዋት ፤ ለእርሱም ዶክተር ቤስነርን እንዲጠሩለት አሳጠናቸው ።

“ ፋንትሮፕና ኮርኔሊያም እንደተለመነት ጃኩሊንን ወደ መኝታ ክፍሏ ከወሰዷት በኋላ ፤ ፋንትሮፕ ጃኩሊንን ሲጠባበቅ ኮርኔሊያ አስታማሚዋን ሚስስ ባወርስን ለመቀስቀስ ሔደች ። በመጨረሻም ፋንትሮፕና



t.me/OLDBOOKSPDF

ዶክተር ቢስነር ተያይዘው ለሳይመን እርዳታ ሊያደር ጉለት መጡ ። ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ሳይመን ብቻውን በሳሎኑ ውስጥ ነበረ ። ቢያንስ ቢያንስ ሳይመን ብቻውን ለአምስት ደቂቃዎች ያህል ነበረ ማለት ነው ።

“ ለሳይመን ግን የሚያስፈልገው ሁለት ደቂቃ ብቻ ነው ። ሽጉጧን ተፋጥኖ ከሶፋው ስር ካነሳ በኋላ ጫማውን አውልቆ እንዳይሰማበት በካሊሲው እየሮጠ ሊኔት ከተኛችበት ክፍል ገባ ። በእንቅልፍዋ ላይ እንዳ ለች ከገደላት በኋላ በጥፍር ቀለም ብልቃጥ ውስጥ ይዞት የነበረውንና ደም በማስመሰል የተጠቀመበትን ብልቃጥ ከሌላው የጥፍር ቀለም ብልቃጥ ጉን በመተው ወደ ሳሎኑ እየሮጠ ተመለሰ ። ከዚያም ከሳሎኑ ውስጥ ደብቆት የነበረውን የሚስስ ቫን ሻይለር ሰሚያዊ ሻርፕ አጣ ጥፎ ከጉልበቱ ላይ ከአደረገ በኋላ እራሱን ተኩሶ አቆ ሰለ ። አሁን ግን እርግጠኛ ስቃይ ቢደርስበትም፣በነኮር ኔሊያ ፊት ጃኪሊን እንዳቆሰለችው ለማስመሰል ጉልበቱን አስሮበትና በቀይ ቀለም እርሶ በነበረው መሐረብ ያቺን ሽጉጥ ከጠቀለለና በሰማያዊው ሻርፕ ከቋጠረ በኋላ እየ ተንፏቀቀ ወደ ወንዙ ውስጥ ወርውሮ ቀድሞ ወደ ወደ ቀበት ‹‹ፍራ ተመልሶ ተንጋለለ” ብሎ ፑዋሮ ሲያቆም ፣ ሬስ ከተቀመጠበት በመነሣት “ፍጹም የማይመስል ነው!” ሲል አስተያየቱን ሰጠ ።

ፑዋሮ ግን እረጋ እንዳለ “ ሬስ ! ” አለና ለጥ ቂት ጊዜ ከተመለከተው በኋላ “ ታስታውስ እንደሆን ብዙዎቹ ያነጋገርናቸው ሰዎች ሌሊቱ ላይ የፋጫና የው ሀው መንቦጫረቅ ድምጽ መስማታቸውን ገልጸውልናል ። የሮጠው ሰው ሳይመን ነው ። ውሀውንም ያንቦጫረቀው ወደ ወንዙ ውስጥ የወረወረው ሽጉጥ ነው ! ” አለው ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሬስ አሁንም እንደቆመ “ በፍጹም አላምንም ! ማንም ሰው ቢሆን በእነኝህ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ይህን ሁሉ ለማከናወን አይችልም ! በተለይም ሳይመን ደህና ቁመና ይኑረው እንጂ እስከዚህም የአእምሮ ብስለት የለውም ! ” አለ ።

“ ግን ፈጣንና ደፋር መሆኑን አትክደኝም ? ” ቢል ጥዋሮ ጠየቀው ።

“ አዎን ሰውነቱ ቀልጣፋና መንፈስ ደፋር መሆኑን አምንበታለሁ! ግን ይህን ሁሉ የእርሱ አእምሮ አመንጭቶ ለማለት አልችልም ። ”

“ ሐሣብ ማመንጨቱ የሌላ ሰው ሥራ ነበረ ። እን ተም እኔም ተሳስተን የነበረው እዚህ ላይ ነው ። ብሩህ አእምሮ ያቀነባበረው እቅድ እንጂ የሳይመን ጭንቅላት ውጤት አይደለም ። እኛ እንደገመትነው ወንጀሉ ቅጽበ ታዊ ሳይሆን በቂ ጥናትና ዝግጅት የተደረገበት ነበረ ። በዚያን እለት ሳይመን በጥፍር ቀለም ብልቃጥ ውስጥ ቀይ ቀለም መያዙ እንደነበረበት የእቅዱ አንዱ ክፍል ነበረ ። ጃኪሊን ያቺን ሽጉጥ ከሰፋው ሥር መወርወሯ የእ ቅዱ ሌላ ክፍል ነው ። ” ሲል ፡

“ ጃኪሊን ? ” አለና ሬስ በመገረም ፡ በመደናገጥም ጠየቀ ።

“ አዎን ! ሁለተኛውን ዘር ግድያ የፈጸሙት ሁሉቱም እንዳይጠረጠሩ በተራቀቁ ዘዴዎች በመጠቀም ነበረ ። ጃኪሊን ሳይመንን ያቆሰለችው አስመሰለች ። ስለ ዚህ ሊጠረጠር አይችልም ። እርሱ ደግሞ ጃኪሊንን ብቻ ዋን እንዳትተዋት እያለ አማጠነ ። ስለዚህ ከጃኪሊን ጉን ሰው ባለመለየቱ እርሷም ለመጠርጠር አልቻለችም ነበረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በእነኝህ በሁለቱ ሰዎች መካከል ጥበበኛ የሆነ ነፍስ ገዳይ ሊኖረው የሚገባውን ባሕርይ ሁሉ ተሟልቶ እናገኛለን ። የማይረበሽ ፡ መለኛና ሐሣብ የማፍለቅ ችሎታ ያለውን የጃኪሊንን አእምሮና ፈጣን ደፋርና ጨካኝ የሆነውን የሳይመንን ወንድነት የሚጠይቅ ግድያ ነበረ ።

“ ነገሮችን ሁሉ ከትክክለኛ አቅጣጫ ከተመለከትናቸው ምሥጢሩ ወለል ብሎ የሚታየን ይሆናል ። ጃኪሊንና ሳይመን የዱሮ ብቻ ሳይሆን አሁንም ፍቅረኞች ናቸው ። ሳይመን ሐብታሟን ሊኔትን በዘዴ ካስወገደ በኋላ ሐብቷን ይወርሳል። ውሎ ሲያድርና ሁሉም ነገር ሲረጋጋለት ጃኪሊንን ያገባል ። የጃኪሊን በሐዘን መቆራመድ እና ሊኔትን በሐፍረት መከታተሏም ፡ የሳይመን ቁጣና ንዴት ሁሉ የእቅዱ አካሎች ናቸው ። እኔን በትናንትናው ምሽት ያለወትሮዬ እንቅልፍ እንዲወስደኝ ከምጠጣው ወይን ውስጥ ክኒን መጨመሩ ፡ በሳሎኑ ውስጥ ለሚካሄደው ትርኢት ምስክር ስለሚያስፈልግ ኮርኔሊያን ወደ መኝታ ክፍሏ እንዳትሔድ ማድረጉ ሁሉ ለዘዴ ነበረ ። ኮርኔሊያም ፋንትሮፕም ሳይመን ከጉልበቱ ላይ መቁሰሉን አረጋገጡ ፡ ሲታይም ሳይመን ከጉልበቱ ላይ ቆስሏል ። ስለዚህም እንደተሸፋፈነ እንዲቀር የታሰበው እቅድ ለጊዜውም ቢሆን ሠራ ።

“ ማን ” አለና ፑዋሮ ራሱን ሲያወዛው የምከረውን ላብ በመሐረቡ እየጠራረገ “ ማን እቅዱን የሚያስናክል ያልታሰበ አጋጣሚ ተፈጠረ ። ሉዊ ቡርጂን እንቅልፍ አልወስድ ስላላት ወደ ሊኔት መኝታ ክፍል አካባቢ ስትመጣ ሳይመንን ከክፍሉ ውስጥ እየሮጠ ሲወጣ ተመለከተችው ። የሊኔትን ሞት እንዳወቀች ሳይመንን በማስፈራራት ወዲያውኑ መደለያ ገንዘብ ጠየቀች ። በሰላ አንጋገር ሞቷን ጋበዘች ! ” ሲል ፡



t.me/OLDBOOKSPDF

“ እርሷንም የገደለው ሳይመን ነው እንዳትለኝ ብቻ ! ” አለ ሬስ ፡ የሚሰማውን ማመን አቅቶት ።

“ እርሱ አይደለም ! ይህ የሁለተኛውን ዙር ግድያ ፈጻሚ የሆነው ሰው ተግባር ነበረ ። ሳይመን ጃኪሊንን እንድጠራለት ያደረገው ለምን መሰለህ ? በእስቸኳይ ሊነግራት የፈለገው ነገር ስለነበረ ነው ። ካላሰቡት አደጋ ላይ መውደቃቸውን ሊነግራት ስለተጣደፈ ነው ። ስለዚህ ያንን አደጋ ለማስወገድ ፈጣን እርምጃ መውሰድን ጠየቀ። ጃኪሊንም ቡርጂን ከገደለች በኋላ ምሳ ለመብላት ወደ ተሰበሰብንበት ክፍል ለመግባት የመጨረሻዋ ነበረች ።

“ ግን እሁንም ቢሆን እነ ጃኪሊን ከሌላ አቅጣጫ አደጋ መጣባቸው ። ሚስስ ዐተርቦርን ጃኪሊንን ወደ ቡርጂ መኝታ ክፍል ስትገባ አይታት ስለነበረ ልትነግረን እየተቻኮለች ስትመጣ በራፉን ከፍቷን በመቆዋ ከውጭ ሆና ወሬውን ሁሉ ታዳምጥ የነበረችው ጃኪሊን እንደ መብረቅ የፈጠነ እርምጃ ወሰደች ። ፔኒንግተን ኮልት ሽጉጥ እንዳለው ሲያወራ የሰማችው ትዝ አላት ። በዚያም ሽጉጥ ሚስስ ዐተርቦርን የቡርጂን ገዳይ ስም ልትነግረን ስትል ተገደለች ። ጃኪሊን አባቴ ከህጻንነቴ ጀምሮ የተኩስ ልምምድ ያስደርገኝ ነበር ብላ የነገረችኝ ትርጉሙ ሁሉ አሁን ገባኝ ” አለና እረፍ አለ ።

“ ግን ጃኪሊን በሳይመን ላይ የተኮሰችበትስ የመጀመሪያዋ ጥይት ? ” አለ ሬስ ፡

“ ለማስመሰል ያህል የተተኮሰ መሆኑን ነግሬሀለሁ። ስለዚህም ምናልባት ከሳሎኑ ወለል ውስጥ ገብቶ ሊሆን ስለሚችል እንፈልገዋለን ። ” አለና ፑዋሮ ሲመልስለት ሬስ በጣም እየተገረመ ፡ “ በሁሉም አቅጣጫ አስበ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውበት ነበር ማለት ነው ! ” ሲልፑዋሮ ፈገግ ብሎ የሬስን ትክሻ በፍቅር እየመታታ ።

“ ስለ ሄርኩል ፑዋሮ ማንነት ግን ያሰቡበት አይመስለኝም ። ተነስና ይልቁኑ ሳይመንን እናነጋግረው። ቀደም ሲል እንደነገርኩህ ምንም ተጨባጭ መረጃ ስለ ሌለን እድላችን ሁሉ እርሱን በማሳመን ላይ የተመሰነ ነው ” ብሎት ሳይመን ወደተኛበት ወደ ዶክተር ቤስነር ክፍል አመሩ ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

በዚያኑ እለት ወደ ማታ ላይ ፑዋሮ የአንድ መኝታ ክፍል በር አንኳኳ ።

" ይግቡ !" የሚል የሴት ድምፅ ተሰማ ። ፑዋሮ ወደ ክፍሉ ሲገባ ፣ ጃኩሊን ከግርግዳ አጠገብ ከነበረ አንድ ወንበር ላይ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና አቀርቅራ እንደተቀመጠች ተመለከተ ። ፑዋሮም ቢሆን በሁኔታዎች ስሜት ዘኑ ከመልኩ በቀላሉ መረዳት ይቻል ነበረ ። አጠገቧ የሚገኘውንም ወንበር ስቦ ተቀመጠ ። ለተወሰነም ጊዜ ሁለቱም በዝምታ ተሞልተው ነበረ ። ጃኩሊን ሐፍረት እየተሰማት ዓይኖቿን ሰበር እያደረገች ከተመለከተችው በኋላ ፣

" ሁሉም ነገር አለፈ ። እርስዎንም ማታለል እንደ ማይቻል በመጨረሻ አወቅኩት ። በጣም ጎበዝ ሰው ነዎት ሙሴ ፑዋሮ!" አለችው።እርሱ ግን ያ ወትሮው የሚሰጠው መልስ ጠፍቶበት እጆቹን እንደዘረጋ ቀረ ። ስለዚህም ጃኩሊን ቀጠል አደረገችና ፣

" በቂ መረጃ ሊያቀርቡበት የሚችሉበት ጉዳይ አልነበረም ። ፍርድ ቤትም በቀርብ አማማኝነት አይኖረውም ነበር ። ሆኖም እርስዎ መንፈስ ደካማውን ሳይመንን በዘዴ አማመኑት ። እኔ ብሆን ግን በቀላሉ የምረታልዎት አልነበርኩም ። " ስትለው ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

“ አውቃለሁ የአእምሮሽንም ብሩህነት አደንቀዋለሁ ። ስለዚህም በጣም አዝኛለሁ ” አላት ።

“ ካዘኑልኝ ምናልባት ድርጊቱን በመሸፋፈን ከወንጀሉ ነጻ ሊያደርጉኝ አስበዋል ? ” አለች ጃክሊን ዓይን ዓይኑን እያየች ፡

“ አላደርገውም ” አለ ፒዋሮ ቀስ ብሎ ።

“ ይገባኛል ! የዋሕነትም ሲበዛ መጥፎ ነው። አደገኛ ሰው ነኝ ። ማን ያውቃል አሁንም ሌላ ግድያ ለመፈጸም እችላለሁ ። ሰው መግደል ለካስ እንደዚህ ቀላል ኖሯል ? የሚታየኝ ሁሉ ስለ እራሴ ደህንነት እንጂ በሌሎች ላይ የሚደርሰውን ሥቃይ ከኢምንት አልቆጥረውም ። ሲበዛ አደገኛ ሰው ሆኛለሁ !”ብላ በፀፀት ከንፈሯን መላልሳ ከነከሰች በኋላ “ እርስዎ ግን በተቻለዎት መጠን ሁሉ ሊረዱኝ ሞክረዋል ። በአስዋን ሆቴል ውስጥ ከዓባይ ወንዝ ዳር ተቀምጠን በነበረበት ምሽት የለገሱኝ ምክር ትዝ ይለኛል ። ‘ ልብሽን ለኃጢዓትና ለክፋት ወለል አድርገሽ አትክፈችለት ብለውኝ ነበረ ’ ፡ በዚያን እለት ሐሣቤን ለመቀየር እችል ነበረ ። ለሳይመንም ልነግረውና ላሳምነው እችልነበረ ። ግን ሌላ ፍርሐት አደረብኝ ። ምናልባት ከመጀመሪያው ጀምሬ ባጫውትዎት ያዳምጡኛል?” ስትል ጠየቀችው ።

ፒዋሮም “ ፈቃድሽ ከሆነ!” ሲል መለሰላት ። ጃክሊንም በሚርገበገብ ድምጽ ታሪኩን ልታጫውተው ጀመረች ። “ እኔና ሳይመን በጣም እንደምንዋደድ ያውቃሉ ። ሆኖም ሳይመን ከፍቅር ሌላም ገንዘብ የሚወድ ፡ የሚያየውን ሁሉ የሚያምረው ሰው ነበረ ። በሮልስ ሮይስ መኪና ለመሽከርከር ፡ በትልቅ ቪላ ውስጥ ለመኖር ፡ በግል ሄሊኮፕ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሩ ለመብረር የሚፈልግ ዓይነት ፍጥረት ነበረ ። ምንጊዜም ሁሉ እንደ ሕፃን ልጅ ነበረ ። ጥሮ ግሮ ሠርቶ ላቡን አፍሶ ገንዘብን ከማግኘት ይልቅ ሁልጊዜ በአቋራጭ መንገድ የሚከበርበትን ዘዴ ይሻ ነበረ ። ስለዚህም ከሚሠራበት መሥሪያ ቤት በሰነድ ገንዘብ ሲያጭበረብር ስለተደረሰበት ከሥራው ያባርሩታል ። ከእኔም ጋር የተገናኘነው በዚህ ወቅት ነው ።

“ ሥራም አፈላልግለት ጀመረ ። እንደአጋጣሚም ሲኔት ለንብረቷ አስተዳዳሪ የሚሆን ሰው በጣም ለመቅጠር መፈለጓን በመስማቴ ይህን እድል ለሳይመን እንድ ትሰጠው በጓደኛነታችንና በፀናው ፍቅራችን አማጥኛት ፈቃደኛ ሆነች ። እንደሚያስታውሱትም በለንደን ከተማ ውስጥ በሚገኘው በሼ ማታንት ሆቴል እንድ ምሽት እኔና ሳይመንን ያገኘን ሥራ በሚጀምርበት ዋዜማ እለት በፈ ንጠገዷ ተሞልተን ነበረ ።

“ ሳይመንን በማግስቱ ወደ ሲኔት መኖሪያ ቤት ወሰድኩትና አስተዋወቅኳቸው።ከዚያችው ደቂቃ ጀምሮ ሳ ይመንን እንደአጣሁት አወቅኩኝ ። ገና እንዳየችው በቁ መናው ተማርካ በፍቅር መንደፏ ገባኝ ። የእኔን ጓደኝነት ሰርዛ ከሳይመን ጋር ትከንፍ ጀመረች ። ሁሉም ማያድርጋ ተጋቡ ። እኔም ለንደን ውስጥ በምትገኝ አነስተኛ መኝታ ክፍሌ ውስጥ ተቀብሬ ማለቅስ ከረምኩ ። ሥራዬን እርግፍ አድርጌ ተውኩት ። ምግብ መብላት አስጠልቶኝ ቆዳዬ መሸብሸብ ጀመረ ።

“ ባላሰብኩትና ባልጠረጠርኩበት ወቅት አንድ ቀን ሳይመን መጣ ። ሁኔታዬን አይቶ እጅግ አዘነ ። ደጋ ግሞም ሊያጽናናኝ ሞከረ ። በአእምሮውም ውስጥ ሲያ ብሰለ የነበረውን ምሥጢር ዳር ዳር እየነካካ ሊነግረኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጀመረ ። ሊኔትን ያገባት ለገንዘቧ ሲል እንጂ አፍቅሯትም
እንዳልሆነ ገለጸልኝ ። ሐብታም ለመሆን ከፍተኛ ጉጉት
ሲኖረው የሚፈልገው እራሱ እንደልቡ የሚያዝበትን
ገንዘብ እንጂ በሚስቱ ቁጥጥር ስር የሆነ ሐብት እንደማይ
ፈልግም ነገረኝ ። በተለይም አንድ ሌሳ ቀን እንደልማዱ
መጥቶ ስንጫወት እንደቀልድ የወረወረው አንድ ሀረ
ፍተ ነገር የሳይመንን እቅድ ወለል አድርጎ አሳየኝ ።
ምን አለ መሰለዎት ? “ዕድለኛ ከሆንኩ ሊኔት በአንድ
ዓመት ጊዜ ውስጥ ትሞት ይሆናል ! ከዚያም ሐብቷን
በሙሉ እወርሳለሁ ! ’ ሲል ተናግሮ ነበረ ። እኔም እን
ዲህ ዓይነቱን ክንቱ ምኞት አጥብቄ አወገዝኩበት ።

“ሆኖም በሌላ ቀን ስለ ልዩ ልዩ መርዞች የሚገልጽ
መጽሐፍ ሲያነብ አይቼ አሁንም እቅዱ ስለገባኝ አምርሬ
ተቃወምኩት።እርሱ ግን ‘ምንም ያልሞከረና ያልተፍጨረ
ጨረ ምንም ነገር አያገኝም ሃ ስለዚህ በሕይወቴ ሙሉ
ስመኘው የነበረውን ገንዘብ የማገኝበት ከዚህ የተሻለ
እድል ዳግመኛ አይገጥመኝም ’ ሲል ተናገረኝ ። ሣይ
መን ቆርጦ መነሳቱ ገባኝ ። የአእምሮም ብስለት በሰሌ
ሰው በቀላሉ እንደሚጋለጥ ስለተረዳሁ ጭንቀቴ እለት በእ
ለት እየተባባሰ ሔደ ። ሳይመን የነበረው እቅድ ጥልቀት
የገደለው እጅ ከፍንጅ የሚያሲዘው ነበረ ። ሊኔት
ምግብ ውስጥ መርዝ በመጨመር ሊገድላት ፈልጓል።
ግን በሕክምና ምርመራ ያለችግር ሊደረስበት እንደ
ሚችል ለማመን ተሳነው ።

“ ስለዚህ ሳይመንን ለማዳን ስል የእቅዱ ተባባሪ
ለመሆን ተገደድሁ ። አእምሮዬንም ያለእረፍት አሠራ
ሁት ። በቀድሚያም ሊኔትን ለመግደል ስለሚቻል
በት ዘዴ አሰብሁ ። ሆኖም ያ ዘዴ እኔንም ሆነ ሳይመ
ንን የማያስጠረጥረን መሆን እንዳለበት ዝርዝር ጥናቶ



t.me/OLDBOOKSPDF

ችን አካሄድህ ። ከዚያም ታሪኩን እንደሚያውቁት በሁለቱ ላይ ጥላቻ እንዳለኝ በማስመሰል በሔዱበት ሁሉ እከታተላቸው ጀመረ ። ሳይመንም ሳይነቃበት ሊኔትን የሚገድልበትን ሁኔታ አመቻቸሁለት ። በጥንቃቄ የተቀነባበረ እቅድ ነበረ !'' ብላ ቆም ስትል ፡

ጥዋሮ ሐሣቧን በመደገፍ "እዎን ! የሚደንቅ እቅድ ነው ! ሆኖም በዚያ ምሽት ሉዊ በርጄን እንቅልፍ ሳይ ወስዳት ቀረ '' ሲል አባባሉ ገብቷት ፡ " ሳስበው

እጅግ ይዘገንነኛል ። ጩኸቴም ሰው በስለት ወግቼ ለመግደል መቻሌ ያስገርመኛል ። ' ልብሽን ለክፋትና ለኃጢአት ክፍት አታድርጊው ' ያሉኝንም ምክር በይበልጥ ግልጽ ያደርግልኛል ። ሆኖም ይህንን ከመፈጸም ሌላ አማራጭ የለኝም ነበረ ። በርጄ ዛሬውኑ ሳይመንን ማስፈራራት ጀመረች ። ወዲያውኑም በእርስዎ በኩል እንድጠራለት አደረገ ። እርስዎ ከመኝታ ክፍሉ ውስጥ ሁለታችንን ጥለውን እንደወጡ ስለ በርጄ ነገረኝ ። ምን ማድረግም እንደሚገባን ተመካከርን ። የገኝሁትን ገንዘብ ሁሉ ሰብስቤ ወስጄ ሰጠኋት ። እርሷም ያንን ገንዘብ እየተስገበገበች በመቁጠር ላይ እንዳለች ከልቧ ላይ ወግቼ ዘረርኳት ። እርሷ ሳይመንን ባታየው ኖሮ ይህ ሁሉ ጉድ አይፈጠርም ነበረ ።እኔና ሳይመን እንደ እቅዳችን ብሩህ የሆነ ኑሮ ይጠብቀን ነበረ።'' አለች።

" ሚስስ ዐተርበርንስ ? '' ሲል ጥዋሮ ጠየቃት ።

"እርሷም ቢሆን ሞቷን የጋበዘችው በገዛ እጅዋ ነው። ወደ በርጄ ክፍል ስገባ አይታኝ ስለነበረ የበርጄ ገዳይ እኔ መሆኔን ልትነግራችሁ እየተጣደፈች ስትመጣ ተመለከትኩ ። ፊጥኜም የፔኒንግተንን ሽጉጥ ወስጄ ስሜን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከመናገሯ በፊት ገደልኳት ። ” ስትል ፑዋሮ ከተቀመጠበት እንደአቀረቀረ ተነሣ ። ጃክሊን ግን ያልተጠበቀ ፈገግታ አሣየችው ። “ የሚመራኝን ኮከብ መከተል አለብኝ ብዬ ስነግርዎት ሰጥተውኝ የነበረው መልስ ትዝ ይልዎ ታል ሙሴ ፑዋሮ ? ” አለችና ጠየቀችው ።

“ አዎን ! ሐሰተኛ ኮከብ እንዳይሆን ብዬሽ ነበረ ?”

“ ሐሰተኛ ብቻ ሣይሆን ወድቆ የተሳባበረ ደብዛው የጠፋ ኮከብ!” ስትል፡ፑዋሮ ወደ በራፉ በዝግታ ማዝገም ጀመረ ፤ ጃክሊን ግን ከመውጣቱ በፊት አስቆመችውና ከጡት መያዣዋ ውስጥ አንድ ነገር አውጥታ እጅዋን ወደ ፑዋሮ ዘረጋች ።

“ የሊኔት ድሪ ? ” አላት ፑዋሮ እምብዛም ሣይደነቅ

“ አዎን ! ሳይመን ሊኔትን ከገደላት በኋላ ወስዶት ነበረ ። እኔም በሊኔት ግድያ አለመጠርጠሬን እንዳረጋገጠ ያስጠራኝ ጊዜ ነበረ የሰጠኝ!” ስትለው ፑዋሮ ድሪውን ተቀብሏት እያገላበጠ እያየ በራፉን ከፍቶ ወጣ ። ጃክሊን ግን ያልተለመደ ጀሮ የሚሰረስር ልዩ ሳቅ ትስቅ ነበረ ።—



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ጉሕ ሲቀድ ሲል'ካርናክ'ወደ አስዋን ከተማ መቃረብ ጀመረች። በዓባይ ወንዝ ግራና ቀኝ የአፈጠጡት ቋጥኝ ድን ጋዮች አሁንም ልዩ ልዩ ዓይነት አውሬዎች መስለው ይታ ያሉ ። በመርከቧ መናፈሻ ላይ ፑዋሮና ሬስ ቆመው ነበረ ።

ፑዋሮ " ምን ዓይነት አሰቃቂ ገዛ! " አለና ተቻ ።

" ቢሆንም መጽናናት ይገባናል ። ከእኛ የሚጠበ ቀውን ሁሉ ፈጽመናል ። በተጨማሪም ሪቼቲን የመሰለ አደገኛ ነፍሰ ገዳይ ለመያዝ ችለናል ። መርከቧ ከምትቆ ምበት ሥፍራ ፖሊሶች እንዲጠብቁን ቴሌግራም አስተ ላልፌአለሁ ። እንደ ሳይመንና ሪቼቲ ያሉትን ወንጀለኞች በስቅላት መቅጣት ያስፈልጋል ። ጃክሊን ግን የምታሳ ዝን ልጅ ብትሆንም የምትረዳበት መንገድ ጨንቆኛል ።" አለ ሬስ ።

ፑዋሮ እራሱን አወዛወዘና " እንደ ጃክሊን ለወ ንድ ከመጠን በላይ የሚጨነቁ ሴቶች አደገኛዎች ናቸው ። ስለዚህ እርሷም ብትሆን በቁጥጥር ስር መቆየት የሚገባት ናት ። ቀጥሏም ምን እንደምታቅድና እንደምት ሠራ ለመተንበይ አይቻልም ! " አለው ።

'ካርናክ' ከአስዋን ወደብ ደርሳ መልሕቋን ጣለች ። በቀድሞውም ሪቼቲ እጁ በካቴና እንደታሰረ በሁለት ፖሊ ሶች ታጅቦ ወረደ ። ፀጉሩ ተመሰቃቅሎ ፊቱ ጠቁሮ ፣ ዓይኖቹ ቀልተው ነበረ ። ቀጥሎም ሳይመንን በቃሬዛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሸከመው አወረዱት ። ከጃክሊን ኋላ ኋላ ፈርግሰንና ኮርኔሊዮ እጅ ለእጅ ተያይዘው ተከትለዋት ነበረ ። ከመርከቧ መናፈሻ ላይ ቆማ የነበረችው ሚስስ ቫን ሻይለር የኮርኔሊያን አድራጎት እንደተመለከቱች ፤

" ኮርኔሊያ ! ኮርኔሊያ ! እንዴት ብትደፍሪኝ ነው እኔን ትተሽ ከዚያ ጉረምሳ ጋር የምትሔጅው?"፡ ስትል ጮኸችባት ። ኮርኔሊያ ግን መልስም ልትሰጣትም አልፈለገችም ነበረ ።

" ዛሬውኑ ወደ አገርሽ ባልክሽ ! " ስትል ሚስስ ቫን ሻይለር አሁንም ፎከረች ።

" ባል ላገባ ስለሆነ ከአሁን ወዲያ አገሬ የባሌ አገር ነው ! " አለችና ኮርኔሊያ ስትመልስላት ፤

" እንዲዚያስ ከሆነ ጥሩ ነው!" ብላ ሚስስ ቫን ሻይለር ሳቅ አለች ። ጃክሊን እዲሶቹን ፍቅረኞች ፈርግሰንንና ኮርኔሊያን እንደማበረታታት ፈገግ ብላ እየቻቸውና ሳይመንን ተኝቶበት ወደነበረበት ቃሬዛ ተጠግታ እንባ ባቀረሩት ዓይኖቿ ቁልቁል እየተመለከተችው ፤

" ሳይመን ! ደህና ነህ ? " ስትል ጠየቀችው ። ጥላሸት ለብሶ የነበረው የሳይመን ፊት ጥቁረቱ እየተገፈፈለት፡

" አዝናለሁ ጃክሊን ! ለዚህ ሁሉ ወድቀት አደረስኩሽ ! በጥያቄ ስላዋከቡኝ ሕሊናዬን እስከመሳት ደርሼ ምስጢራችንን ለማውጣት ተገደድኩ ! " ሲላት ሳቅ አለችና ፤

" አትጨነቅ ሳይመን ! ወንጀል ሠርቶ መ... በእኛ አልተጀመረም !" አለችው ። ሳይመን የተኛበ... ቃሬዛ ተሸካሚዎቹ ከመሬት ላይ ብድግ ሲያደ...



t.me/OLDBOOKSPDF

የጃኩሊን እጅ ተፋጥኖ ወደ ቦርሣዋ ውስጥ ገብቶ ወጣ ። ከመቅጽበቱም የተኩስ ድምጽ ተሰማ ። የሳይመን አካ-
ላት ሲታጠፍ ሲዘረጋ ይታያል ። ወዲያውኑ ጽ-
ብሎ ተዘረጋ ።

ጃኩሊን ሽጉጧን በእጅዋ እንደያዘች ፑዋሮን ፊትን፡ በሚያንጸባርቁ ዓይኖቿ ተሰናበተችው ። ሮጥ ብሎ ሊይ-
ዛት ሲል ያቺን ትንሽ ሽጉጥ በልቧ አኳያ ደግና ምላሱን ሳበች ።

ጃኩሊን እግሮቿ ቀስ በቀስ እየከዱ·ት ሔደው ተዝለፍልፋ ወደቀች ። ደሟ ተስል ብሎ እየወረደ ከወር-
ቃማዋ አሸዋ ጋር ተደባለቀ ። ሳይመን ሲኔትን የገደለባት ሽጉጥና ጃኩሊን ሳይመንንና እራሷን የገደለችበት ሽጉ ጥ ተመሳሳዮች ነበሩ ።

“ ከደቂቃዎች በፊት ጃኩሊን እደግና ልጅ እንደ ነበረች ነግሬህ አልነበረም ሬስ ? ” አለና ፑዋሮ በግብጽ በረሐ ላይ የወደቀውን የጃኩሊን አስከሬን እንባ በተሞሉ-
ት ዓይኖቹ እየተመለከተ “ አይ ጃኩሊን ! ” የምትለዋን የሀዘኑ ቃል ተናገረ ።



t.me/OLDBOOKSPDF